የቤተሰብ አልበም



Scanned with CamScanner

የቃተተች ነፍስ

(ልቦለድ)

ከአለማየሁ ታደሰ

1986 ዓ.ም
አንተየሁ ፀአለ



ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ



ሠ ሠሙን ሽታታለለሙ ግሀ ግመን ሰለባታ
ሽንተ ትዋሽ ዩሠሩለ፡ ሼክስፒር

Scanned with CamScanner

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
ALL RIGHTS RESERVED

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

112719 30933

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia

መጀመሪያ ሕትመት 1985

ሽፋን ስእል ብርሃነ ህይወት ጌታቸው

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

Scanned with CamScanner

ምእራፍ አንድ

ከራስጌው መብራት የሚሰራጨው ደብዛዛ ቀይ ብርሃን መኝታ ቤቱን ፍፁም ጨለማ እንዳይወርሰው አድርጐታል ። በብርሃናማ ፍንጣቂዎች እንዲያገጥ ያደረገው ይህ የራስጌ መብራት ፡ ጨረሩን የክፍሉ ቁሳቁስ ላይ እያሳረፈ ልዩ ውበትን ፈጥሯል ። ከባለቤቷ ጐን አልጋው ላይ ተጋድማ በሃሳብ በምትዋልለው እፀገነት አይኖችም ላይ በማንፀባረቅ የራሱን ህብረ ቀለማዊ ውበት ፈጥሯል ። ከሃሳቧ ርቀት ጋር እይታዋ እየሰፋ ፡ ከስበቱ ጋርም አብሮ እየተሰበሰበ ድንቅ ትዕይንትን ያሳያታል ፡ ለዕፀገነት ።

ባለቤቷ ክንፈ እንደልማዱ ፡ ከወገቡ በላይ ራቁቱን እንደሆነ ጀርባውን ሰጥቷት ያንኮራፋል—ቀናችበት ።

ሰላሙን በተጐናፀፈው ረጭ ባለ የሚያገሣ ሌሊት ፡ አልፎ አልፎ ከሚሰማው የመንደር ውሾች ጩኸት በተጨማሪ የሚደመጡት ፡ ሳሎን ውስጥ የሚገኘው የኤሌክትሪክ ማቀዝቀዣ ኩርርታና የክንፈ ኩርፊያ ናቸው ። ድምፁ ለጆሮ ይከብዳል ።

በዚህ ረጭ ብሎ በተደመመው ሌሊት ፡ ዘረ አዳም ከፊሉ ያልማል ፡ ከፊሉም የሰላም እንቅልፉን ይለጥጣል ፡ ጥቂቱም በየራሱ የሃሳብ ንጉዶት እየተንሳፈፈ ጭልጥ ይላል ። ሌሊቱ ተጋምሶ ሰባት ሰዓት ሲያልፍ ፡ የሠፈሩ አውራ ዶሮዎች እየተጠራሩ መጮሃቸውን አልጀመሩም ።

ክንፈ በረጅሙ ተንፍሶ ወደ ባለቤቱ ዞረና በእንቅልፍ የቀሉትን አይኖቹን ለመግለጥ እየሞከረ ፡—

“አሁንም አልተኛሽም—አንዴ?” አላት ፤ ሊያቅፋት እጆቹን ወደ ሆዷ እየሰደደ ።

ዕፀገነት አይኖቿን ኮርኒሱ ላይ እንደሰቀለች “እተኛለሁ ፡ ተኛ” አለችው ፡ ልቧን ሁለት ቦታ ከፍለው በያዟት ሃሳቦች ተወጥራ ።

ገና አልጋ ላይ እንደወጡ በፍቅር ጨዋታ ፡ ሊያቃብጣት ፈልጐ ሳለ፡ እንደወትሮው አልሞቅህ ብትለው ፡ እንደስሜቱ ግለት ባትጣመር ለት ፡ ያለወትሮዋ ስሜት አልባ ብትሆንበትም ፤ ስሜቱን አሸንፎ ሊቃለዳትና ሊቃበጣት ሞከረ ። አልሆን ሲለው ፡ ምን ሆነች? እያለ ለራሱ

Scanned with CamScanner

እያወጣ እያወረደ ላለ ነው ያ የሚወደው እንቅልፉ የረታው ።

እሁንም ከእንቅልፉ ሲባንን ተኝታ ያለማግኘቱ ፡ ነገሩን አቅልሎ አላስመለከተውም ። በቀስታ ሆዷን እየዳበሰ ፡-

“ምነ ሆነሻል ውዴ?” አላት በዘወትር ማቆላመጫው ።

“ምንም አልሆንኩ ፡ እርፈህ ተኛ” አለችው ፡ በቁጣ ።

ክንፈ ቁጣዋ አላናደደውም ። ይህን ታጋሽ አመሉን ጠትሞኛል ብሎ ለራሱ ባያስበውም ፡ በሚያውቁት ዘንድ ግን መከበርና መወደድን ፡ እንዲያም ሲል ፍቅራዊ ፍርሃትን አትርፎለታል ። እወነትንም ከሱ ያስተሳሰራት ዋናው ነገር ይህ አመሉ ነው ። ሆደ ሰፊ ነው ።

ከእንግዱ ቀና አለና “እንዲህ እንቅልፍ አጥተሽ ስትጨነቂ እያየሁ እንዴት የሰላም እንቅልፍ ይኖረኛል?” አላት ፡ እጆቹ ከሆዷ ወደ ደረቷና ጡቶቿ እየተዘዋወሩ ፡ አይኖቹ ደግሞ ከገጿ ላይ አንድን ነገር ለማንበብ እየሞከሩ ።

እሷም ተመለከተችው ። ፊቱ ወፈር ያለና ሰፊ ነው ። ሰፋ ብሎ ያፈጠጠው ግንባሩ ገራገርነቱን አጉልቶታል ። የሃዘን ስሜት ይፈጥራል– ፊቱ ። እንደ ወትሮው ሁሉ ዛሬም እንዳየችው ዘወትር ስትመለከተው የሚሰማት ጥልቅ ሀዘን ተሰማት ። የዚህ ሀዘን ምንጩ ገራገርነቱ ይመስላታል ። ወትሮም የምትሸሸው ጥያቄ አሁንም ተደቀነባት ። ፍቅሯ ከሃዘኔታ የመነጨ ነው ውይንስ ?… አታውቅም ።

ክንፈ በእወነት አእምሮ ከአቅሟ በላይ የሆነ ነገር ገብቶ አረፍት እንደነሳት ማወቅ አልተሳነውም – ግን ምንድነው?

“ከአለቃሽ ተጣላሽ እንዴ?” አላት ፡ ምክንያቱን ራሱ ለመገመት እየሞከረ ፡ አሁንም በአዘኔታ ተመለከተችው ። መላ ሰውነቷ በጭንቀትና ካልወጣሁ በሚል ውስጣዊ ውጥረት ታጭቋል ።

“ከዚህ ሁሉ ምነው በገላገለኝ!” አለች ለራሷ ። ዝም ብሎ በሚያስተውላት አላዛኝ ፍጥረት ልትጨክንበት እያቃታት ። አብራው መኖር ከጀመረች ሶስት ዓመት ሆኗታል ።

ክንፈ አሁንም ፊቷ ላይ የሚለዋወጠውን የተለያየ ስሜት ለማንበብ ሞከረ ፡ ግን ምንም!

“ለምንድነው እንዴት የምታይኝ ውዴ?” አላት በስስት ፡ የሌሊት ልብ፟ ያልሸፈነውን አንገቷን እየሳማት ። ከአስተያየቷ ለመሸሽ ሞከረ –

“እንዴት አየሁህ!” አለችው ። አስተያየቷ ግን አልተቀየረም ።

“እንጃ !” ፈራት ። “…አጠገቤ እያለሽ የሌለሽ ይመስለኛል ።”

ሃዘኗ ባሰባት ፡ በእጆቿ ወተሮቹን ዳበሰቻቸው ። ራሱን ደረቷ ላይ አሳረፈ ። ክብደቱ ያስጨንቃታል ። ጭንቅ ሲላት ደግሞ ደስ ይላታል – ውስጧን የመኮርኮር አይነት ስሜት ። ሰውነቷን ፎቀቅ አድርጋ ተመቻቸች ። ቀና ብሎ ተመለከታት ። እንደወትሮዋ መረታት ጀምራ ለች።

የባህሪዋ ለውጥ ፍጥነት ግራ አጋባው ።

ወትሮም ለፍቅር ጨዋታ ጉጉ ነች ። ፍቅርን ሰጥታ መቀበልን ታውቅበታለች ። ክንፈ በዚህ በኩል የሚወዳደራት የለም እስኪልላት ድረስ …. ። በወፋፍራም ክንፈሮቹ ስስ ክንፈሮቿን ሳማቸው ። እጆቿን ከውጉሩ ላይ አንስታ ወደትክሻና ማጅራቱ ሰደደቻቸው ። ስሜቷ ከውስጥ ቢታገላት ፡ መንፈሷ ደግሞ በመንታ መንገድ ተከፍሎ ሀሊናዋን ያሳቅላል። በመጨረሻ አንዱ ረታ ። በክንፈ ሰውነት ምትክ የሄኖክ ተተካ–በወፍራም አስጨናቂ ሰውነት ፋንታ ቀጭን የሚወራጭ ገላ ። ስጋ የሞላው ሰውነት ሳይሆን አጥንታም ። ሁሉም ነገር ከሄኖክ ጋር የተከወነ መሰላት ። የፈራችውና የሸሸችው ይህንን የሀሊናዋን ሽርሙጥና ነበር ።

ሁሉም ነገር ካለፈ በኋላ ፡ ሰውነቷን በእጆቿ እየዳበሰ እንደ ሕፃን ልጅ ሊያስተኟት ይሞክር ጀመር ። በጨለማው ጉንጯን ፡ አይኗን ፡ አገጯን ፡ ከንፈሯን እየሳመ በእጆቹም እየዳበሳት ፡ የተኛች መስሎት እሱም እንቅልፉ ረታው ።

እሷ ግን ብዙ አመታት ወደኋላ በሃሳቧ ነጉዳች ….

* * *

ከሰባት አመት በፊት ።

ሄኖክ ሻንጣውን ያዘገጃጀል ። ወደ ዩጐዝላቪያ ነፃ የትምህርት እድል አግኝቶ በማግስቱ ለመሄዱ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ መያዙን አረጋገጠ ፡ የቀረው መሄድ ብቻ ነው ። እወነት አልጋው ላይ ተቀምጣ በለቅሶዋ ወደበርበሬነት በተለወጡት አይኖቿ የሚሰራውን ሁሉ ትመለከታለች ።

ሄኖክ ሻንጣውን ቆላልፎ ቀና አለና በዛ ሴታሴት መስሎ ወደ ቅላት በሚያደላው ቀጭን ፊቱ ተመለከታት ። “ጐብዘሻል የኔ ቆንጆ!” አላት እንባዋን መግታቷን ተመልክቶ ።

Scanned with CamScanner

ምንም አልመለሰችለትም ።

ሰባት አመት ! እርዝማኔው ከእጥፍ እጥፍ ያህል ተንጣሎ ታያት ። ለሰባት አመታት ወደማታውቀው የብቸኝነት አለም ···ለሰባት አመታት የእንባዋ አባሽ የሌለበት ባዶ አለም… ለሰባት አመት ሄኖክ አልባ ህይወት… ሰባት– ሰባት– ሰባት አመታት ።

“ሂንዬ በጣም በዛ–ኮ!” አለችው ፣ አይኖቿ በድጋሚ እንባ እያቀረሩ።

“ምኑ?” አላት

“ሰባት አመት….”

“አንቺ ደግሞ” ….. አላት እንደመሰላቸት ብሎ ··· “ቅድም ስንቱ ነገርኩሽ ፣ በመሃሉ እረፍት ስላለ እመጣለሁ ። ይልቅ እስከዛው ቤት ይዘሺ ተደራጅተሽ ቆይኝ ። ስመጣ ቤት ነው ጥልቅ የምለው!” አላት ሊቃለዳት እየሞከረ ።

ፊቷን ይባስ አቀጨመችው ። አይኗን ስትጨምቀው ያቆረው እንባዋ ቅጠል ላይ እንደሚንከባለሉ ጤዛዎች ኮለል እያለ በጉንጯ ላይ ወረደ ። ሲያባብሏት ይሽው ነች ፣ ያመቀችውን ያፈነችውን ስሜቷን ታፈነዳዋለች ። ማባበሉ የብሶቷን ጫፍ እየነካካባት የባሰ እንድትንሰቀሰቅ ያደርጋታል ።

“እሺ! አንድ ነገር ልለምንሽ” አላት ሄኖክ ፣ አይኖቹ አይኖቿ ላይ በማረፋቸው ተሳቀው ወለል ወለሉን እየተመለከቱ ።

“ምንድነው?” አለች እየተነፋረቀች ።

“ዛሬ አብረን እንደር ።” አጠያየቁ የፍርሃትም የጉጉትም ስለነበር ፣ ሌላ ተጨማሪ ማግባቢያ ሊያክልበት ቢፈልግም አልቻለም ።

ቀና ብላ ተመለከተችው ። አስተያየቷ ግራ የመጋባት የመደነቅና ‘እንዴት ይህንን ጥያቄ ጠየቀኝ’ የሚል ይመስላል ። አብራው ማደሩን አልጠላችውም ። እንኳንስ ለአንድ ቀን ፣ ከሚሄድበትም ቀርቶ ዝንተ አለም ተቃቅፈው ቢያድሩ የምትረካ አይመስላትም ። ግን እንዴት አድርጋ ይህንን የከባድ ቀላል ጥያቄ ልትመልስለት ትችላለች? ከባድ ፈተና ሆነባት – የእህቱ ነገር ።

ሄኖክ የሚኖረው ከብቸኛዋ ታላቅ እህቱ ጋር ነው ። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሳይኮሎጂው የትምህርት ዘርፍ ከተመረቀች ስድስት አመታትን ያላለፈችው አዜብ ፣ ከአሳዳጊዎቿ ትከሻ ተላቅቃ ራሷን ችላ መኖር

ስትጀምር ፣ ወንድሟ ሄኖክንም ከዘመዶቿ እጅ አውጥታ ተከራይታ ወደምትኖርበት አነስተኛ ቤት ወሰደችው ።

ጐረቤትና ቤተዘመድም ስለ ሄኖክ እህት ያወራሉ ። ከሁሉ ተገልላ በብቸኝነቷ ተቆራምዳ የምትኖረውን አዜብ ፣ ግማሹ ‘መካሪ እናት አባት በማጣቷ ፣ ከሁሉም ጋር እንደተባለለች መኖር መርጣ ነው’ ሲል ፣ ሌላው ደግሞ ‘የተማረችው ትምህርት ሞንቅላቷን ነክቷት ነው’ ይላል ። ‘ከሰው የሚያርቅ መድሃኒት ቢጤ አጠጥተዋት ነው’ የሚልም አልጠፋም ። ‘በእናት አባቷ ሞት ሃዘን ሳቢያ ነው’ የሚሉም ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም ። ባጠቃላይ ስለሷ ከንፈሩን የማይመጥ ቤተዘመድ ነኝ ባይ የለም ።

‘ባጐረሰን ተነከስን’ የሚሉትንም አሳዳጊዎቿን ከዘነጋቻቸው ውላ ከርማለች ።

እንኳን ለውጭው ሰው አብሯት ለሚኖረውም ሄኖክ ባህሪዋ አይገባውም ። እስከዛሬ ሲኖሩ አንድም ቀን የወንድ ጓደኛዬ ፣ አልያም እፎኛዬ ነው ብላ የነገረችው ሆነ ያስተዋወቀችው ሰው የለም ። ደስ ካላት ወንድ ጋር አልጋዋን ስታጋራ ይመለከታታል ። ሆኖም አንድም ቀን ከልቧ ተደስታ የምታውቅ አይመስለውም ። ሁሌ ቀዝቃዛ ፣ ሁሌ ግድየለሽ የሚያስመስላት ገፅታዋ በፊት እሱንም ያስጨንቀው ነበር ። አሁን ግን በመጠኑም ቢሆን ተሳምዶታል ።

“ቤተሰቦችሽን ፈርተሽ ነው?” አላት ሄኖክ ለጥያቄው መልስ ለመስጠት የተጨነቀችውን እፀገነትን እየተመከተ ።

አልመለሰችለትም ።

“ለአስቴር ደውለሽ ንገሪያት!” አላት ፣ ለእፀገነት ታናሽ እህት ።

“ምን ብዬ ?”

“ነገ መሄዴን ታውቅ የለ?”

“እና እሱን ትንገራቸው?”

ሄኖክ እየሳቀ “የሆነ ምክንያት ፈጥራ ትንገራቸው ።” አለ ።

እፀገነት ቤተሰቦቿን ምን ያህል እንደምትፈራቸው ያውቃል ።

የጨነቃት የቤተሰቧ ጉዳይ አይደለም ። እሱን በቀላል ዘዴ እንደምትወጣው ታውቀዋለች ። ሰአቷን አየች ። አስራ ሁለት ሰአት ተኩል ሆኗል ። ይኼኔ ከመሥሪያ ቤት – ቤቷ ገብታ ፣ ልብሷን ቀያይራ ከቤተሰቦቿ ጋር ተሰይማለች ። ቡናም እየተፈላ ይሆናል ። ዛሬ ደግሞ/

Scanned with CamScanner

በማምሸቷ የቤተሰቧ የመወያያ ርዕስ ሆኖ ይሆናል ።

"እዜብ ምን ትላለች?" አለችው በፍርሃት አስተያየት እየተመለከተችው ።

ሄኖክ ተናደደ ። ፈፅሞ ያልጠበቀውና ያልጠረጠረው ጥያቄ በመሆኑና ለምክንያትነትም የማይቀርብ መስሎ ስለተሰማው ። ይኸው ነው ፤ ቶሎ ይቆጣል ፣ መቆጣት ብቻም አይደለም ፤ ሲቆጣ የመጣለትንም ይናገራል ። አሁን ግን ለመልስ አልተጣደፈም ። እንደ ምድጃ ውስጥ እሳት የሚንቀለቀለውን አይኑን እንዳታስተውልበት በእርግብግቢቱ እያጣደፈው በረጅሙ ተነፈሰና ፣

"እሺ!... መሄድ ከፈለግሽ ...." ንግግሩን ሳይጨርስ ተወው ።

"ላይሆን ሄኒ ፣ አዜብንኮ በጣም ነው የምፈራት ፣ ባድር ምንትለኛ ለች?" አለች ፤ ችግሯንና የውስጧን ስሜት እንዲረዳላት በአይኗ ጭምር እየተማጠነችው ።

"እ– አዜብን ምክንያት አታድርጊያት! ይልቅ ሌላ ዘዴ ብትፈል ጊስ!" አለና ከሚግጠነው አይኖቿ ላይ እይታውን አንስቶ "በፍፁም አዜብን ፈርተሽ አይደለም " አላት ።

"እሺ! እና ..ምንድነው?"

"እንጃ! እሱን የምታውቂው አንቺው ነሽ ።"

እፀገነት ውስጧ ተቃጠለ ። "ሄኖክ !"... ጮኽችበት... "ይግባህ እኔ ካንተ ጋር እንድሆን የሚያስገድደኝ ነገር የለም! ከፈለኩ እሆናለሁ! ካልፈለኩ አልሆንም! በቃ ! በል ንገረኝ ተገድጄ ነው?... ኸ ! በል እንጂ ፣ ወይንስ ካንተ ጋር ማደር ጠልቼ ነው?..." አፈጠጠችበት ። ሳግም ተናነቃት ። "....በ–በል ተናገራ ! ምን ይዘጋሃል?... ተናገር እንጂ ! እኔ ....እ–ኔ ..." ለቅሶዋ አቋረጣት ።

ሄኖክ ቁጣው በረድ አለለት ። "እና ታዲያ አዜብን አታውቂያት ምና ነው?"

እፀ ገነት እንባ ባራሰው አይኗ እየተመለከተችው "አውቃታለሁ ሄኒ! አውቃታለሁ ። ብቻ... ብቻ አንተ አይገባህም ፣ ሴት አይደለህማ! ተወው ከፈለክ ሌላ ቦታ እንደር! እባክህ ሄኖክ አታስጨንቀኝ !" ብላ ፊቷን በሁለት እጆቿ ሸፈነችው ።

ታያት ! የአዜብ ቀዝቃዛ ፊት ፣ ቀዝቃዛ ፈገግታ ፣ ለሷ የምታሳያት ግድ የለሽነት ። አዎ ስትናገርም ቀዝቃዛ ፣ ሌላው ቢቀር የተዋወቀቻትም

እለት ቀዝቃዛ ነበረች ። ታድያ ሄኖክ ስለ እህቱ ምንም ቢነግራት አይገባትም ። እንደዛ የምትሆነው እሷን ስታይ ይመስላታል–እናም ያስጨንቃታል ። ያናድዳታልም ። ካወቀቻት ሁለት አመት ቢያልፍም ፣ አንድ ቀን በቅጡ አናግራት አታውቅም ፤ እፀገነትም 'ለምንድነው የምትጠላኝ?' እያለች በተቻላት ስትሸሻት ኖራለች ።

እሷ ብቻ አይደለችም ፣ ብዙዎችም የአዜብ ቀዝቃዛ ስሜት ሲያኮማት ራቸው ይሸሿታል ። ሄኖክና እፀገነት ነገሩን ዳግም ሳያነሱ ለተወሰነ ጊዜ ተውት ።

ወደ አንድ ሰአት ተኩል ገደማ እፀገነት ለመሄድ እያሰበች ፤ ከመኝታ ቤቱ ውጭ ኮቴ ተሰማቸው ። ወዲያው መኝታ ቤቱ ብርግድ አለ– አዜብ ነች ።

"አው ሶሪ! ብቻህን መስለኸኝ ነበር" አለችና ለሁለቱም ቀዝቃዛ ፈገግታ አሳየቻቸው ።

"እንዴት ነው ተዘጋጀህ?" አለችው ሄኖክንና ሻንጣውን እያየች ።

"እዎ ጨርሻለሁ ።"

"እፀገነት እየረዳሺው ነው?" አለቻትና ከሷ መልስ ሳትጠብቅ ሰዓቷን እየተመለከተች "አልመሸበሽም?" አለቻት ስሜት በማይሰጥ አነጋገሯ ።

ሄኖክ ጣልቃ ገብቶ "አዳሪ ነች" አለ ። እፀገነት ከው ብላ አፍጥጣ ታየዋለች ። አዜብ ምንም አልተናገረችም ፣ በሩን ዘግታ ሄደች ።

እፀገነት የእልህ ሲቃና ንዴት እየተፈራረቁባት "አላድርም!" አለች ንግግሯን አጥብቃ ።

"ለምን እንዲህ ትሆኛለሽ እፀገነት ?" አላት ማባበልም መታዘብም እየቃጣው ።

"አይገባህም አልኩህ እኮ! ሴት እይደለህም ብዬሃለሁ ፤ ቤቱ ያንተ አይደለም ፣ የሷ ነው!" አለችው ለቅሶዋ እንደልማዱ እያገረሸባት ።

"ቢሆንስ?"

"የሚጠላኝ ሰው ቤት ማደር አልፈልግም!"

ከብዙ መግባባት በኋላ ቤቷ ደውላ እንድታስፈቅድ አደረጋት ። የመጨረሻቸው ሌሊት ፣ ፍቅራቸውን ያራገፉበት ሌሊት ። በአብዛኛው አልተኙም ። ለስንብቱ ባመጣችው ውስኪ 'ቼርስ!' ሲባባሉ ጥሩውን ፣ በጉውን ፣ ፍቅራቸውን ፣ ምኞታቸውን ሲገላለጡ ፍቅር ሲሰሩ ...ምሽቱ

Scanned with CamScanner

ለንጋት ስፍራውን ለቀቀ ።

አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ የተናገራት ቃል መቼም ቢሆን ከህሊናዋ አይጠፋም ። እንደሩቅ ሰመመናዊ ትእይንት እየተስለመለመ ይታያታል ። ድምፁም አድማሱን ተሻግሮ ፣ እንደሞገድ እየተስተጋባ ፣ የጊዜ ርዝመት ሳያግደው ፣ እንደ አዲስ ሁሌ በጆሮዋ ይስተጋባል ። “እፀገነት እስክ ህይወቴ መጨረሻ ድረስ አፈቅርሻለሁ ፣ ማንም ቢሆን ከኔ ሊለይሽ አይችልም ። እስክመለስ ብቻ በትእግሥት ጠብቂኝ” ድምፁ እየራቀ ሲሄድ ይሰማታል ። ጣዕሙና ለዛው ያው ነው ። ‘ጠብቂኝ… ጠብቂኝ…’

በሄደ በአመቱ ነው ፣ ‘ዘንድሮ ለእረፍት እትመጣም ወይ?’ ብላ የፃፈችለት ። ትምህርቱ እየከበደው እንደሄደና ለዘንድሮው ቢቀር ለከርሞው ለመምጣት እንደሚሞክር ፃፈላት ። አያይዞም ‘እፅሽ ቀናት ባለፈ ቁጥር ናፍቆቴ እየጨመረ ሄዶ ነው መሠለኝ ጭራሽ እንዳገና ላገኝሽ መቻሌ እንኳን እያጠራጠርኝ ሄደ –እፅሽ አንቺስ?’ ነበር ያላት ። ደብዳቤውን ስታነብ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። ሳይታወቃት ለካ ይህ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ተጋብቶባት ኖሯል ።

ሲል–ሲል በየጥናቱ በየምናምኑ እያማካኝ ፣ የሚፅፍላት ደብዳቤ መዘግየት ጀመረ ። የእሷም ምላሽ በፉከክር ከሱ ደብዳቤ ጋር መዛመድ ጀመረ ። እሱም እንደ ቃሉ ሳይሆን ለከርሞው ሳይመቸው ቀረ ····

ይህን ሁሉ ትውስታ ታጠነጥን የነበረው ከባሏ ከክንፈ ጋር ተኝታ እያለች ነበር– አውንም እንቅልፍ እምቢ እንዳላት ነው ።

ከሃሳቧ ጋር ይጫወት የነበረውን የራስጌ መብራት አጠፋችው – ከለሊቱ ዘጠኝ ሰአት ሆኗል ።

የመንደሩ አውራ ዶሮዎች ጮኽታቸውን መቀባበል ጀመሩ ።

* * *

ኔንደ ብቸኝነት የምትፈራው ነገር የለም ። የመለየቱ ጥላቻ ደግሞ ከሰው እንዳትቀርብ አድርጓታል ። በሀዘንና በብቸኝነት እንዲሁም በስነ ልቦና ትምህርት እውቀት የደነደነው ልቧ ከሚገባው በላይ ጠጥሯል ። ደካማነቱ የሚታወቃት መለየት ሲያገኛት ብቻ ነው ።

ስለብቸኝነቷና ከሰው መገናኘት ለምን እንደምትፈራ ያጫወተችው የስነልቦና መምህሯን ነበር ። የህይውት ታሪኳን ሲጠይቃት ፣ “ችግርሽ

ከምትወጂያት እናትሽና ወንድምሽ መለየት ይመስለኛል” ነበር ያላት ፣ በትክክል የልቧን ስብራት አግኝቶታል ። ተደነቀች ። በአእምሮዋ ጀርባ ተደብቆ እድሜ ልኳን ብቸኛ ያደረጋትን ስነልቦናዊ መንስኤ ስትረዳ ፣ ለትምህርቱ ጥልቅ ፍቅር እደረባት ። ከሚሰጣት ኮርስ ሌላ ብዙ መፅሀፎችን አነበበች ። ልታጠናቸውም ሞክረች ። በግሏ በተለይ በሰው ስነልቦናዊ ህይወት ላይ የምታደርገው ጥልቅ ትኩረትና ምርምር ከዩኒቨር ስቲው ትምህርቷም በኋላ አልተለያትም ።

ከጊዜ ብዛት ለያንዳንዱ ሰው ያላት አመለካከት እየተለወጠ መጣ ። ሰው ከጀርባው ብዙ የስነልቦና ውጥንቅጦች ያዘለ መሆኑን ተረዳች ። ራሱ ባለቤቱ ሊረዳው ያልቻለው ውስጣዊ ማንነት በህይወቷ ላይ ችግር እያመጣ ሄደ ። ሰውን ማወቅ አይቻልም ።

ይህ እምነቷ ሰዎችን እንድትሸሻቸው ጨርሶም እንድትርቃቸው አደረጋት ። “እኔ ነኝ” ብሎ እሱነቱን አውቆ ያለ ሰው እስከመኖሩ አጠራጠራት ። የህይወት ምስጢሯ ይሄ ይሆን? ትላለች ። የሚማርካት የአንድ ፈላስፋ ቃል አለ “አለምን ለማወቅ ከፈለክ ምድርን አትጫር ፣ ሰማይን አትቧጥጥ፣ አጠገብህ ስላለው ሰው ህይወት መርምር”

የተሰማራችበት የስራ መስክ ያበሳጫታል ። የአስተዳደር ስራ ከሰዎች ቢያገናኛትም ሙያዋን ያጫጫዋል ። በአስተዳደር የሰለጠኑ ባለሙያዎች አሉ ። በግል ከምታደርገው ጥረት ሌላ ሙያዋን በተመለከተ የምትሰራው የለም ። ብዙ እንድታስብ ግን ጊዜ ሰጥቷታል ።

ማንበብ ብርቅ የሆነባትን የልጅነት ጊዜዋን ስታስብ በውስጡ እርግዞ የሚመጣው የቤተሰብ ፍቅር ውል አለባት ። እናቷ ሞተው የሚረዳቸው ሰው ባለመኖሩ ፣ እሷን አንድ የእናቷ ወዳጅ ፡–ወንድሟን ደግሞ አክስቷ ሲወስዷቸው ፣ ያን ጊዜ ከናቷ መሪር ሀዘን በቀር ብዙም የተሰማት ነገር አልነበረም ። ገና የአስራ ሶስት አመት ልጅ ነበረች ፣ ሄኖክ ደግሞ የአምስት።

“አይዞሽ ፣ እንደናትሽ የሚያስፈልግሽን ሁሉ አደርግልሻለሁ ። ነፍሷን ይማርና እናትሽ እኮ እኛን ሁሉ ለዚህ ያበቃች የደግ መጨረሻ እህታችን ነበረች” ሲሏት ጥሩ ተስፋ ታይቷት ነበር ። በተለይ ሁለት ክፍል ከሆነችውና ጥቁርሻ ካበለዛት ከእናትዋ ቤት ፣ ላንቃው በሰም ወደተወለወለ ባለንጭ ኮርኒስ ትልቅ ቤት ሲወስዷት ፣ ከአጎዛ ድልዳል ወደ ሳር ፍራሽ ስትዘል ፣ ለትንሿ ልቧ የብርሃን ጭላንጭል ጭል ብላላት ነበር ።

Scanned with CamScanner

ከአመታት በኋላ ደረጃዋን ስትወጥነው ከልጆቻቸው በታች ከሰራ ተኞቻቸው በላይ መሆንዋ ቢሰማትም እንኳን ፣ በታጋሽነቷ ሁሉን ችላ በቤት ውስጥ አደገች ።

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እስከትጀምር ድረስ ፣ በትምህርቷ ደከማ ነበረች ። የኋላ የኋላ ከተጫናት ቀንበር ነፃ የሚያስወጣት ብቸኛ መንገድ ትምህርቷ መሆኑን ተረድታ ፣ ከትምህርት ቤቷና ከሰራ መልስ ደብተሯን የሙጥኝ እያለች እዚህ ደረሰች ። በልጅነቷ የተጠናወታት የብቸኝነት በሽታ ግን አለቀቃትም ።

ፍሮይድ ከፃፈው መፅሀፍ ውስጥ ራሷን አስምጣ እሷነቷን እየፈለገች ሌሎች ሰዎችን ለማየት ትሞክራለች –ወደ አመሻሹ ላይ ።

በጠባቧ የእንግዳ መቀበያ ውስጥ ተቀምጣ ፣ በመስኮት በሚገባው ብርሃን ታነባለች ። የብርሃኑ ኃይል ሲቀንስ መፅሀፉን ወደ አይኗ እያስጠጋች የአይኗን ቆብ እየበለጠጠች ፣ ፍውም ለማንበብ አስቸጋሪ ሲሆንባትንባቧን አጠረጠች ። ያነበበችው ሃሳብ ያብስለስላታል ። በንባቡ ውስጥ ያነበበቻቸውን ባህሪያት ከራሷና ከሰዎች ጋር ታመሳክራለች ። በድንገት ሰራተኛዋ ከሰጠመችበት ሃሳብ አባነንቻት ።

“ቡናው ደርሷል ላምጣው?”

“እምጪው! አለቻት ድምጿ እንደከረረ ። ተነስታ ማብሪያ ማጥፍያውን ተጫነች ። እምስቱ አምፑሎች ቦግ አሉ ። ቤቱ በብርሃን ተመላ ። የቤት ዕቃዎቿን ተመለከተቻቸው ። ቀዩ መለስተኛ ፎቴዋ መንተብ ጀምሯል ፣ ድሮም አሮጌውን ነው የገዛችው ። ከትንሿ ቴሌቪዥን እናት ላይ ትልቅ ራዲዮ ቴፕ አለ ። ድምውን ጮክ አድርጋ ከፈተችው ። እንዳንዴ ጮክ ያለ ሙዚቃ መስማት ትፈልጋለች ። ያላለፍት ቀን ደግሞ ማንኛውም ድምፅ ያስጠላታል ።

ቡናዋን አስቀምጣላት ሄደች ። ቀዝቀዝ ካላለ መጠጣት አትወድም። አሁንም ቤቱ የተንሰራፋበትን ድብርት ፣ መብራቶቹም የቴፑም ጩኸት ሊያባለቅቁት አልቻሉም ። አዜብ የሃሳብ ውጥረቷ ከአካባቢው ሕይወት ፍዘት ጋር ሲጻመርባት ነፍሷ ተጨንቃ ፣ የምትሆነውን ያሳጣታል። ይህ ስሜት እየባሰባት የመጣው ፣ ታናሽ ወንድሟ ሄኖክ ለትምህርት ወደውጭ ሄዶ ከተለያት ቀን ጀምሮ ነው ። እመታት ቢያልፉም በፍውም ልትለምደው አልቻለችም ። ሌላው ቢቀር ባያናግራትም ፣ ሲያንኳኳ ሲዘፍን ፣ በተለይ ደግሞ እሱን ፍለጋ የሚጮኸው ስልክ

ብዛት ባጠቃላይ በቤቱ ላይ ሕይወት ይዘራበት ነበር ። እናም ቤቷ እና እና አይልም –አይደብርም ።

እንደገና ቴፑን አጥፍታው ተመለሰችና በርዶ የቀዘቀዘውን ቡና በቁሟ ጨለጠችው ። መንፈሷ ለምን እንደሚጨነቅ አላወቀችውም ። የእጆቿን ጣቶች ወጉሯ ውስጥ እንደማበጠሪያ ሰገሰገቻቸውና ወደታች መሻርጣ ፣ –የተቆላለፉትን የሰውነቷን ጡንቻዎች ወጣጠረቻቸው ።

በረጅሙ ተነፈሰች ።

ውስጧ ያላዝናል –ህይወት ቅዝቃዜዋ ያስጠላል –ከበረዶ ይበልጥ ያኮማትራል ። ልቧ ይሸበር ጀመር ። መንፈሷ ጻምኖ ያው ስለብቸኝነቷ ሊያላዝንባት ነው ። ይህን አትወድም ።

“ሁላችንም የተወለድነው ፣ የምናልፈውም ብቻችንን ነው ። ለሰው የምናጋራው ምን ነገር አለን?” ትለዋለች ራሷን ።

ሞልቶ!

እጆቿን አወናጭፋ መኝታ ቤቷ ገባች ። እንደልማዱ ብቸኝነቷ መዝፈኑን ትቶ ሊያለቃቅስ ፣ የደስታ እንጉርጉሮውን ትቶ የሃዘን ማርሹን ሊጀምር ነው ። ይህን ሊያደርግ ሲል ነው ሁሌ ከራሱ ሙግት የሚጀምረው ።

መኝታ ቤቷ ገብታ በውስጡ ባለው የልብስ ቁምሳጥን መስታወት ጠቅላላ ቁመናዋን አየች ። ዳሌዋ እንደኮራ ነው ፣ ጡቷም መላላት እንጅ መውደቅ አልጀመረም ። በደንብ ተጠግታ ፊቷን ተመለከተች ። አውንም ተጠጋችው መስታወቱን … ጉንጯንና የአይኗን ስር በጣቶቿ እየደባበሰች እየቻቸው … ማዲያት ሊያወጡ ነው? ቆዳዋ ከወትሮ ቆጣ ብሏል ። እድሜዋን አሰበች ፣ ለሴት ልጅ ቀላል አይደለም –ሰላሳ መድፈኗን ካወቀች ከርማለች ።

በነጋህ አመታት ህይወት በሚሏት ስውር ምስጢር ውስጥ ብዙ ነገሮችን አሳልፋለች ። ለዛሬ የብቸኝነት ህይወት የጻረጓትን ሁኔታዎች ከሞላ ጎደል ለማሰብ ሞከረች ። የአፍታ ወዳጅ አጥታ አታውቅም ። ይሄ ግን እንደእንጦሮጦስ የጠለቀውን የብቸኝነት መንፈሷን ሊያወጻላት አልቻለም ። በቅርቡ በሰሞነኛው ወዳጅነቱ በሃሳቧ ብቅ ጥልቅ የሚለው ሲራክን እንኳን ፣ እንደሌሎች ከጊዜያዊ ወዳጅነቱ ፈቀቅ አድርጋ አይታው አታውቅም ።

ያለፈችበትን የህይወት ዘመን ስታስብ ፣ እንደወትሮው ሁሉ ዛሬም

Scanned with CamScanner

ሰውነቷን የነዘራት ትውስታ ውልብ አለባት –ክንፈ! አሁን እሱን ያሰበችው ከእጇ እንዳመለጠ ወርቅ ነው ። ስለሱ እያሰቡ ጊዜ ማጥፋት ከንቱ ነገር መሆኑን ከተረዳች ቆይታለች ። ግን ፍፁም ከጭንቅላቷ ልታወጣው አልቻለችም ። አሁንም ወዲያው ለመርሳት ሞከረች ።

ለማጣቷ ጥፋተኛ እሷም እሱም እንዳልሆኑ ተረድታለች ።

መስታወቱ ላይ እንዳፈጠጠች ነው ።

ሙሉ ጤነኛ ነች ። "ታዲያ በዚህ እድሜ ለሴት ልጅ ብቻዋን መሆን ደግ ነው?" መስታወቱ ውስጥ ያፋጠጣት ጥያቄ ነበር ። ጭንቅላቷን አወናጭፋ ጥያቄውን ከአእምሮዋ ለማስወጣት ሞከረች ። በምትኩ ቅድም በትውስታዋ የተነቃቃውን ሰውነቷን ፡···ጡቶቿን ነካካቸው ። ሰውነቷ አንድ ነገር ፈልጓል ፡ ደግሞ ብቻዋን ነች ። እንዲህ አይነት ሁኔታ አልፎ አልፎ አያጋጥማትም ···

ክንፈሯን በጥርሷ በኃይል ነከሰችው ። ጡቶቿን ከመነካካት አልፋ በመዳፏ አሸቻቸው ። አስጨናቂ ስሜት ። አሁንም በኃይል በኃይል ··· የጡቶቿን ጫፎች አሁንም በኃይል እየጨበጠች ጫፎቻቸውን አልመዘ መዘቻቸው ፡ ሲቃ··· ከባድ ትንፋሽ··· ልዩ የሆነ የሚያፍነከንክ ስሜት ፡ ያልበረደ ጣፋጭ ለስላሳ ስቃይ···የስሜት ጣር–ሁሉን በእጆቿ ከወነች ።

በረጅሙ ተነፈሰች ። ቢሆንም አሁንም ውስጧን አልደረሰችበ ትም። በመስታወት የምትመለከተው የሯሷ መልክና ቁመና አስጠላት ። ጥቂት ቆይታ ወደ አልጋዋ ስትዞር ትንፋሿም መቆራረጡን ፡ ልቧም የወትሮ ምቱን ቀጥሎ ነበር ።

ምእራፍ ሁለት

ክንፈ ባለፉት ሶስት ዓመታት እንደተገነዘበው ፡ ትዳር ቀድሞ እንደሚያስ በው ጭፍግግ ህይወት አልሆነበትም ። እንዲያውም የተረጋጋ፡ ጤናማና ሰፊ ጥልቅ ህይወት ነው የሆነበት ። ከማግባቱም ሆነ ዕፀገነትን ከማወቁ በፊት ስለ ትዳር አስቦ አያውቅም ። የትዳር ውጥን አልነበረውም ። እንዲያገባ ያስገደዱት ግን ህሊናዊ ጉዳዮች ነበሩ ።

የዛሬ ሰባት ዓመት ፡ ትዳሩን ሊመሠርት አካባቢ ፡ እፀገነት አንዳች የህይወት መርዶ አረዳችው ። እንዳረገዘች ስትነግረው ብዙ እንዲያስብ በት ጊዜ አልሰጠችውም ። እንባዋ አይኖቿን እያጠበ ፡ ስቅታው ደምስሯን ወጣጥሮ እያነፋረቃት ፡ እንዲሁም ቤተሰቧቿ ይህንን ጉድ ቢሰሙባት እነሱ ሰው ሆነው ሰው እንደማያደርጓት እየተንሰቀሰቀች ስትነግረው ምንም አልታየው ፡ ዘወትር ይፈራውና ይሸሸው ወደነበረው የትዳር ህይወት ሲወረወር ተሰማው ።

አላቅማማባትም ፡ ሁኔታዋም ለጥርጣሬ አልዳረገውም ። በቅርብ ቀን ጋብቻቸውን መፈፀም እንደሚችሉ ሲነግራት ፡ ውስጧ በሃሴት እየተወራጨ ፡

"ባፋጣኝ መሆን አለበት ክንፈ" አለችው ።

"ይሆናል አይዞሽ!"

"ቢበዛ ሁለት ወር!"

"ይህን ያህል?"

"አዎ ክንፈ ፡ አምስት ወሩን እኮ ይዟል!"

እስካሁን ለምን ዝም አልሽ?"

ዕፀገነት የታወቀባት መስሏት ልቧ ቀጥ አለ።

"ማለቴ ሳትነግሪኝ?"

"እኔማ ···እኔማ እንዳይሆን ብዙ ሞክሬ ነበር ፡ እምቢ አለኝ እንጂ ።"

ተንሰቀሰቀች ።

ክንፈ እያባበለ እንዴት እሱ ራሱ እንኳን ሊያውቅባት እንዳልቻለ ሲያሰላስል የሚያቅማማባት መስሏት ፡

Scanned with CamScanner

"አንድ ነገር ከንፈ ፣ አንድ ነገር እሺ በልኝ?"

"ምንድነው የኔ ውድ ንገሪኝ ።"

–"ሰርጉ ቶሎ ይውንና ከዛ ብትፈልግ ብ·ት·ፈ·ል·ግ …" መናገር አቃታት ።

"እባክሽ ዝም በይ እሂ ።"

"ብትፈልግ ፍታኝ ፣ ብቻ ከዚህ ውርደት አውጣኝ ።"

ከንፈ ተሳቀቀ ። በርግጥ በዕፀገነት ፍቅር ተጠምዶ ነፍሱ ባትሳቀልም፣ የምትጠላ አይነት አይደለችም ። አብሯት ቢኖር ሞቅታዋ የሚያሞቀው ፣ የስሜቷ ንቃት የሚያነቃው እንጂ የሚከፋባት አልመሰለውም ።

እናም በፍቅር ልውውጣቸው ወቅት የምትለግሰው የስሜት ሙቀት እንዳይርቃት አግዶታል ። ብቻ የዚህ ሁሉ መቋጫው ትዳር የሚሆንበት ምክንያት አይገባውም ። ለእርሱ የሚመስለው እርስ በርስ ለመጠላለፍ ፣ አንዱ የአንዱን ገበና ፀሀይ የሚያሞቅበት ፣ የጥላቻ ጦራቸውን የሚሰባበቁበት ሀይወት አድርጎ ይቆጥረዋል ። እናም ትዳር ማለት የገዛ ራስን ሰላምና ነፃነትን ለማስማማት የሚደረገ ሩጫ – ያስፈራዋል ።

አንድ ያልሆነ አካላትን ለማዛማድ የሚደረግ ፍልሚያ –ይመስለዋል። ሰዎች ትዳራቸውን ከመገንባት ይበልጥ ትዳራቸውን ለማፍረስ የሚጭሩት እሳት ፣ የሚሰሩትን ተንኮል ፣ በይበልጥ ደግሞ በጦሱ በተጠነሰሱት ነፍሶች ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጠባሳ –ይህንን ነው ከንፈ የሚፈራውና እድሜውንም ለብቻው እንዲገፋ የሚያስገድደው ።

ትዳራቸው በፈረሰባቸው ቤተሰቦቹ ውስጥ ማደጉ –ማስታወስ የማይፈልገው ዋነኛ ምክንያት ነው ።

"እፀገነት ፣ መጋባታችን በመሃከላችን ያለውን ፍቅር የማያደፈርስ ብን ከሆነ ፣ ጥሩ ሀይወት መምራት ከቻልን ፣ ለምን ዛሬ አንጋባም ። አይዞሽ አትጨነቂ" ብሎ ነው ጉንጯን ደባብሶ ፀጥ ያሰኛት ።

እንደገመተው ትዳራቸው አስፈሪ አልሆነባትም ። ከጋብቻው መጀመሪያ ላይ ግን ድሮም ለጋብቻው መሰረት የሆነው ፣ እንደራሱ ጨትካውም ያለ ቤተሰብ ብቻውን እንዳያድግ ሀሴናዊ የሞራል ግዴታ ውስጥ ያስገባው ፅንስ ከጋብቻው ጥቂት ሳምንታት በኋላ እፀገነት ባጋጠማት ድንገተኛ አደጋ ላቢያ ልሀደመቷ ዋልቅና ሲላል በሀኪሞች ጥረት ፅንሱ እንዲወጣ ሲጠየቅ እናቴ ልሁልት ተከፈለ ። አማራጭ አልነበረውም ፣ ተስማማ ። ከዚያን ወዲያ ያ የወደቀችበትን የመስሪያ ቤቷን ዶሪጃ እንደ ሲኦል በር መውጫ ጠልቶት ላለማየት ፣ ቢሮዋ መሄድ ትታል ።

ያም ሆኖ ፣ የእፀገነት ጤንነት ከተስተካከለ በኋላ ለሁለት ደፋ ቀና ሲሉባት ፣ ሲያቆላብጧት ፣ ሙቀቷ ውጭ ሳይቀር የሚሰማ ድንቅ ነጆ ሆኖላቸው ነበር ። ትዳራቸው የረጋ ፣ የሚያስደስት ፣ ድንቅ ሀይወት ነበር።

ታዲያ ከሶስት ዓመት በኋላ ያ ዋንት ይፈራው የነበረው አስፈሪ ሚአበል ለመምጣት ዳር – ዳር ማለት የጀመረ ስለመሰለው ተጨነቀ ። "ምን ሆንች·ብኝ?" የየደቂቃው ጥያቄ ሆነበት ። ፍፁም የቀድሞዋ ዕፀገነት አይደለችም ።

ይህን ሶስት ቀን ከስራዋ ዘግይታ ፣ ያለዚያም አምሽታ ነው የምትመጣው ። ሲናገራት ቁጣዋ ይቀድማል ። ልትደብቀው እምቢ ያላት ውስጧን አንዳች ነገር ይዞታል ። የዚህን የተጠነሰሰ ሽል ምንነት ባይረዳም ባጭሩ ሊቀጨው አስቧል ። ያለዛ ጊዜ የሰጠው እንደሆነ ጡንቻውን አፈርጥሞ የትአባክ! ሊለው ነው ።

ከስራው በኋላ ቤቱ ገብቶ ስላሳለፈው የትዳር ህይወቱ ፣ እያንዳንዱን ትዝታ ሲያወጣ ሲያወርድ ቆየና ፣ ከሳሎኑ በእንደኛው ጥግ የተቀመጠውን ፒያኖ መጫወት ጀመረ ። ከእፀገነት ቀጥሎ ቤቱን የሚያስናፍቀው ፒያኖው ነው ። ከብዙ ልፋት በኋላ እንደምንም ብሎ ወደሀገሩ ከሚመለስ የውጭ ቤጋ ላይ በመጠነኛ ዋጋ በገዛው ፒያኖው ሲጫወት አብሮ ማንጎራጎር ይወዳል ። በጣም ሲጨነቅ ፣ ያለዚያም ሲደሰት ፣ ካረገዘው ስሜት የሚገላገለው ጣቶቹን ፒያኖው ላይ ሲያሳርፍ ነው ። ኖታ አንብቦ የመጫወት ችሎታም አለው ።

እፀገነት ከምሽቱ ለሁለት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ቤት ደረሰች ። ከንፈ ከፒያኖ ጨዋታው አልተለየም ። መግባቷን እንዳየ ሰአቱን ሲመለከት ብታየውም ግድ አልሰጣትም ።

"በደህና ነው ውዴ?"

አጠያየቁ የጤና አልመሰላትም ። ቦርሳዋን ፊት ለፊቷ ካለው ሶፋ ላይ ወረወረችና "ምን ደህና ነገር አለ?" አለች መንጨቅ እያደረጋት ።

ከንፈ ተመለከታት ። በውስጡ በተሰማው ጥልቅ የሃዘን ስሜት … ፒያኖ መምታቱን ሰላቆመ ቤቱ የውስጡን ዝምታ አብሶታል ። እፀገነት ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደች ። በጣቶቹ የፒያኖውን ቁልፎች ተጫናቸው፣

Scanned with CamScanner

ድምፁ የሲአል ኡኡታ እንደሚሉት አይነት ሆነበት ። ተወው ። ከመታጠቢያው ቤት የሚሰማው የሀይለኛው የውሃ ድምጽ ለአንድ አፍታ በጆሮው ተተራመሰበት ። ከመታጠቢያ ቤቱ ስትወጣ በሩን በሀይል ዘግታ ወደ እንግዳ መቀበያ ቤቱ ተመለሰች ። ቦርሳዋን አንስታ ወደ መኝታ ቤት ስትገባ ተከተላት ።

"እባክህ ክንፈ! እባክህ ተወኝ! ትንሽ ጊዜ ስጠኝ!" አለችው ፍክ ብላ በተረበሸ ስሜት ።

"ንገሪኝ! ምንድነው የሆንሽው? ወይንስ ያስከፋሁሽ ነገር አለ? ለምን አትነግሪኝም? ብቻሽን አምቀሽ የምትብሰለሰይበት ምክንያት አልገባኝም ፡ ምንድነው ነገሩ ?" አላት አይኖቹን አጉረጥርጦ ።

እፀገነት ስሜቷን መቆጣጠር አቃታት "ተወኝ! ተወኝ ብያለሁ" ፍክችበት "ለምን እዚ? ...አይኖቹ እንባ አዘሉ ።

ክንፈ ከተቀመጠችበት አልጋ ላይ ሆኖ ሊያባብላት ቢሞክር አልፅናናልህ አለችው ። ከፊት ለፊቱ ተንበርክኮ ጉልበቷ ላይ የደፋችውን ራሷን እየደባበሰ ፡ "ለምን ታለቅሺያለሽ ውዴ? ለምንድነው እንዲህ የምትሆኚው? "አላት ።

ቀና ብላ በቀላው አይኗ እያየችው "ተወኝ ስልህ! ለምን አትተወኝም?" አለችው መለማመጥና ተስፋ መቁረጥ በዋጠው ድምጿ ።

"እዚ!..." ድምፁ ይነዝራል "...የኔነት ትርጓሜ እምኑ ላይ ነው ውዴ? ስትጨነቂ ጭንቀትሽን ካልተካፈልኩ ፡ ችግርሽን ፡ ብሶትሽን ካልተጋራሁ ምንሽ ነኝ? በትዳር ከለላ ስር ሆነን እንደሌሎቹ ባሻን መንገድ በየፈናችን እንሂድ? ይህንን የደባል አይነት ኑሮ ነው በፊትም ስሸሸው የኖርኩት ፡ እናም ልታገስሽ አቅም የለኝም ፡ ፈራሁ ።"

ተያዩ ።

ተጨንቃ ፊት ለፊቷ ተንበርክኮ ጭንቀቷን ሊጋራ ለሚማስነው ባሏም ተጨማሪ ጭንቀት መፍጠሯ ይበልጥ እረፍት ነሳት ። "ለምን? ለምን? " ለራሷ እንደምታወራ አይነት ፡ ጮሃ በእጆቿ መዳፎች ጉልበቶቿን ከደቃች በኋላ መንሰቅሰቋን ቀጠለች ።

ክንፈ አብሯት ተናጠ ። "በደሌ ይኼን ያህል ምንድነው?" እየወዘወዘ ጠየቃት ።

"እባክህ ክንፈ! አንተ ምንም አላደረከኝ ፡ የራሴ ጉዳይ... ብቻ! ትንሽ ጊዜ ፡ ስጠኝ —ግዴለም ።"

"እፀገነት...እኔ አይገባኝም ምንድነው ነገሩ? " ውስጡ ፍርሃት ሲሰራጭ ተሰማው ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ፡ እንባው ድቅን እያለ ይፈታተነው ጀመር ። ይኼን ያህል እዚ ፡ ይህን ያህል ተራርቀናል?"

እፀገነት ፍክችች "ክንፈ ተወኝ የምልህ ኮ ይህን ነው ፡ ለምን አይገባህም? ተ..ወ..ኝ" ራሷን አርገፈገፈችው ።

"በቃ ትቻለሁ!" አላት ክንፈ የገነፈለበትን ቁጣ ለማብረድ እየሞከረ ፡ አሁንም ፊቱን ተመለከተችው ። ሰፊው ግንባሩ ላይ ያፈጠጡት ደም ስሮቹ አባብጠዋል ። ከዚህ ቀደም እንደዛሬው ዓይነት ባህሪይ አይታበት አታውቅም ። ቀስ ብሎ ከተንበረከከበት ተነሳ ።

"እሺ" አላት እራሱን ለማረጋጋት "ምክንያትሽ እኔ እንዳልሆን ፈራሁ ። አንቺ ልትነግሪኝ ካልደፈርሽ በኔ በኩል ይቅርታዬን ይኸው !""ብሎ ግንባሯን ስሟት ወደ እንግዳ መቀበያ ቤቱ ሄደ ።

የእፀገነት መንፈስ ተናወጠ ።"ምን አይነት ሰው ነው? ምናለ መጥፎ ወይም ክፉ በሆነና ጥየው በበረርኩ ፡ ምናባቱ ልሁን!" በረጅሙ ተነፈሰች ። ስትታዋ ትንፋኟን ቆራረጠባት ። ከአፍንጫዋ የሚወጣው ቀጭን ፈሳሽ ፡ ከእንባዋ እየተቀላቀለ ፊቷን እንደህፃን አበላሽቶታል ። ከቦርሳዋ መሃረብ ስትፈልግ ፡ የአለማየሁ እሸቱ ዜማ ከእንግዳ መቀበያው ክፍል ይሰማት ጀመር ።

'ማ—ሪኝ ብዬሻለሁ

እሞት....ብሻለሁ

ማ—...ሪኝ ብዬሻለ—ሁ

እሞት....ብሻለሁ' እያለ ፡

የክንፈ ወፍራም ርግብግብና አሳዛኝ ድምፅ ፡ በዝግታ በክንፈሩ ታፍኖ ተሰማት ፡ የምትፈልገውን መሃረብ ትታ አልጋው ላይ በደረቷ ተደፍታ ትንፋሽ እስኪያጥራት ተስረቀረቀች ።

ክንፈ ከፒያኖው ጋር ያንጎራጉራል ። አእምሮው ደግሞ ከፍጡራን አለቃ ጋር ሙግት ገጥሟል — በዝምታ!

አለማችን የፍጡራንን እንባ አጠራቅማ ቢሆን ኖሮ ፡ ገና ድሮ ሰጥማ በነበር ። የነዋሪዎቿ ጣርና ሰቆቃ ከአድማስ አድማስ አስተጋብቶ ጆሮ ሲያደነቁር ፡ ከህይወት በላይ አንዳች ፍጡር መስማት ይችል ይሆን? አዎ! አንጀቱ የጠና ፡ ጆሮው በሰዎች ሰቆቃና ጦር የደነቆረ ፡ አይኑ የሰዎችን ችግር ማየት ታክቶት የታወረ ካልሆነ በቀር ። ከቶ አይን ያለው ፡ ጆሮው የሚሰማ ፡ አንጀቱ ያልጠና የፍጡራን አለቃ ይኖር ይሆን? መልስ የለም! ... ፒያኖው ብቻ አስተዛዛነው ።

Scanned with CamScanner

ምእራፍ ሦስት

የመጨረሻ ደብዳቤዋ ከሁለት አመት በፊት ደርሶታል። ሁለት አመት የደብዳቤዋ መቋረጥ ይኽን ያህል አላስጨነቀውም። አመታት በተገባደዱ ቁጥር ሀገሩ የመሄጃው ጊዜና የትምህርት መጠናቀቂያ ወቅት በመሆኑ የሚያስባቸው ብዙ ጉዳዮች ነበሩት — ሄኖክ።

ባዕድ ሀገር ሆኖ እሷን እያስታወሰ አንዳንድ ጊዜ ቢተክዝም፣ ስሜቱን እየተቆጣጠረ ወደ ትምህርቱ በማዘንበሉ እንዳውም በአሳቡ እየመጣች እንዳታስቸግረው በማለት እሷን ላለማሰብ ብዙ ጊዜውን በተለያየ ነገሮች ላይ በማጥፋት ሲመራ ቆይቶ፣ ትምህርት መገባደጃው ሰሞን ግን ናፍቆቱም ትዝታውም በጭንቅላቱ ውስጥ ቦታ በማግኘታቸው እወኩት። ከሀገሩ ቀጥሎ የናፈቀው እፀገነትን ነበር።

የግንቦት ወር ከሁሉም ወራት የበለጠ ሙቀት አለው። የአካባቢው እፅዋት አንገታቸውን ደፍተው ስሞታቸውን ለፈጣሪያቸው ያቀርባሉ። ፀሐይ ጨረሯን ያገኘችው ላይ ሁሉ ያለ ርህራሄ ትለቃለች። የዛጉ የቤት ቆርቆሮዎችን ይበልጥ ታጠቁራለች። አዳዲስ ቆርቆሮዎች ላይ ጨረሯ ሲያርፍ ደግሞ አይንን ይወጋል። ጠጠር በደንብ ያልጠገቡ የአስፋልት መንገዶች ሬንጀቸው በፀሐይ እያቀለጠ የጫማን ቅርፅ ያስቀራሉ። ርቆ ማየት ያስቸግራል። አይን እያጥበረበረ ያውካል።

ሄኖክ ይህ ሁሉ አላስከፋውም። ትምህርቱን ጨርሶ ከአንድ ቀን በፊት አዲስ አበባ ቢገባም፣ ከተማውን ካወከው ሙቀትና ከብርቅየው የሃገር አየር ጋር በመነፋፈቁ አልተከፋበትም። ቀጭን ሰውነት ቢኖረው ውም ጉንጮቹ አበጥ አበጥ ብለዋል። ቆዳውም ከበፊቱ ይበልጥ ጠርቶ ፈክቷል።

"አሁን ስታየኝ ምን ይሰማት ይሆናል?» አለ በመጣ በማግስቱ አራት ሰአት ገደማ ወደ ቢሮዋ እየገሰገሰ ። በድንገት ብቅ ስልላት «አሁን ስታየኝ ምን ይሰማት ይሆናል?» አለ በመጣ በማግስቱ አቤት! ይስታውንም አትችለውም ።" ያኔታ መላ ሰውነቱን ወረረው ።

" መሥሪያ ቤት ቀይራስ ቢሆን?" አለ ድንገት የመሥሪያ ቤቷ ሀንፃ አካባቢ እንደደረሰ። ከቤት ከመውጣቱ በፊት ስልክ ሊደውልላት ፈልጎ ነበር። ግን ከስልኩ ይልቅ ፊትለፊት ሊያገኛትና እንዴት እንደምትሆን ሊመለከት መረጠ። "አይ እፀገነት እንደድሮዋ እርብትብት ትሆን ?" የትዝታ ወላፈን ለበለበው። "ግዴለም ባላገኛትም የቀየረችበትን መስሪያ ቤት ጠይቄ እሄዳለሁ" አለ።

የመስሪያ ቤቷ አካባቢ ብዙም አልተለወጠም። ሌላው ቢቀር ዘበኛው እንኳን ድሮ የሚያውቃቸው ናቸው። ሲፈትሹት አስተዋላቸው። ሰላምታ ነበራቸው፣ አሁን ግን ዘንግተውታል። እርጅና ጎንተር አድርጓቸው ጠቆርና ከሳ ብለዋል— "የመጠጥ ሰው አይደሉ!" ብሏቸው በሃሳቡ ዘልቆ ገባ።

እፀገነት ገና አንደየችው "ውይ!" ብላ ከምትተይብበት የፅህፈት መኪና አጠገብ ተፈናጥራ ተነሳች። ሄኖክ ፈገግ እያለ አጠገቧ መጣ።

"..ሄኖክ ...ሄኢ" ቁና ቁና ተነፈሰች። ተወርውራ መጥታ ትጠመጠ ምብኛለች ብሎ ነበር ፣ ግን ብርክ ያዛት ።

"እፅዬ!..." አጠገቧ ደርሶ ትከሻዋን በእጆቹ ያዘ። ትመለከተዋ ለች። በውስጧ ተዳፍኖ የኖረው ስሜቷ ተፈንቅሎ ሲወጣ ተሰማት። በድንገት ጥምጥም አለችበት። ሊስማት ከንፈሯን ሲፈልግ ስትሸሸው፣ አንገቷን፣ ጉንጯን ይሰማት ጀመር።

"..ሄኢ መቼ መጣህ!.."

"..ትላንት ገባው "አላት በተራቡት አይኖቹ አይቶ አልጠግባት ብሎ። ለረጅም ሰዓታት ሲተያዩ ከቆዩ በኋላ፣ ያገረሸው ፍቅሯ ገደቡን አልፎ ወጣ። አስተያየቷ ተቀያየረ። ፊቷ ይበልጥ ፍም መሰለ። ከንፈሮቿ መንቀጥቀጥ እንደጀመሩ አራሷን ለመቆጣጠር ሞከረች፣ የባሰ ተርበተበ ተች። ሄኖክ እንደገና እጆቿን አጥብቆ ከያዛቸው በኋላ ወደራሱ አስጠ ጋት፣ ከንፈሮቿን ፈልጎ አገኘው ።

"..ሄኖክ በቃ! ቢሮ'ኮ ነው!" አለችው አይኑን ማየት እየፈራች ። ለቀቃትና ከጠረጴዛው ፊት ለፊት ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠ። የተራቡት አይኖቿ ሄኖክን አይተው አልጠገቡም።

Scanned with CamScanner

"..ተስማምቶሃል ሄኒ.."

"..አንቺም ወፍረሻል! "አላት ፊቷን በደንብ እያስተዋለ።

ዕወንት ልብ ውስጥ የሆነ ነገር ይተራመሳል። ሰውነቷ በጭንቀት ተወጥሮ ሊፈነዳ ነው። 'ማግባቱን ሰምቶ ይሆን? አለች ራሷ። በማንም በኩል ሊሰማ እንደማይችል ገመተች። ሄኖክ ከሄደ ወዲያ አንድ ቀን የገበያ አዳራሽ ውስጥ ተገናኝተው ነበር። እወንት አይታት ስትርበተበት አዜብ የወትሮውን ቀዝቃዛ ሰላምታ ሰጥታት ነበር የተለየቻት።

"..እንዴት ነው? ቤት ይዘሽ ቆየሺን ወይንስ ከቤተሰቦችሽ ጋ ነሽ?" ሄኖክ ፈገግ አለ።

ሰውነቷ ሲሸማቀቅ ታወቃት። 'ማግባቱን አልሰማም ማለት ነው?' እንዴት እንደምትነግረው ጨነቃት፣ መንገሩ ቢዘገይ መረጠች። የግዷን ፈገግ ብላ ዝም አለች።

ሄኖክ የሚያስጨንቃት ነገር እንዳለ ገመተ። 'በመምጣቱ ከፍቷት ይሆን? እንዴት ሊሆን ይችላል? ወይንስ ቤት ይዘሽ ቆይኝ ያልኳት ባለመሳካቱ ስታዩኝ ጨንቋት ይሆን? በመጨረሻው ግምቱ ወና።

በመጀመሪያም እንደገመተው አልሆነለትም። እርብትብትነቷ ስታ የው እንደሚያደርጋት አልነበረም። ሰባት ዓመት ቀላል ጊዜ አይደለም። በሰባት አመት ውስጥ አስተሳሰብም የዛን ያክል ልቆ ይገኛል። መስከንም ይመጣል—ሁሌም እንደቀድሞ አይኖር።

"አዜብን በደህና አገኘሃት?" አለችው ንግግራቸውን ለመቀየር ፈልጋ።

"አይተሻት አታውቂም! " አላት፣ መጥታ አንደማታውቅ ከአዜብ ቢሰማም፣ ጨዋታ ለማራዘም ፈለጎ።

እወንት አይታት እንደማታውቅ ለመግለጽ እንጂቷን ብቻ ነቅንቃ ዝም አለች። በሰባት አመታቸው ተገናኝተው ጨዋታው ሁሉ ለምን ጣእም እንዳጣ ሲያብሰለስል፣ በድንገት እጇ ላይ ያለውን የጣት ቀለበት አየ። ሰውነቱን አንዳች ነገር ከላይ እስከታች ነዘረው። የልቡ ምት ፍጥነት ጨመረ።

"እገባሽ እንዴ?" አፉ እየተርበተበተ ጠየቃት።

ደንግጣ አየችው። ከንፈሩ ደርቆና አይኑ ፈጥጦ ያያታል። መናገር አቅቷት እንባዋ ዱብዱብ ይል ጀመር።

"እገባሽ እሂ? እገባሽ ! ....እውነት ነው? ባክሽ እውነቱን ንገሪኝ ።" ሰውነቱ ይንቀጠቀጣል ፣ "..በኔ ጨክነሽ እገባሽ!"

"እንደሱ አትበለኝ ሄኒ ጨንቆኝ ነው፣ ጨንቆኝ...."

"ምኑ እዜ? ሰባት አመት መታገሱ....."

"አላውቅም! ....አይገባህም!" ፊቷን በእጆቿ ሸፈነች፣ የጣቷ ቀለበትም ቦግ ብሎ ታየው። ረዘም ላሉት ቀያዩ ጣቶቿ ላይ ተስማምታ የገጠመችው የጣቷ ወርቅ.... የቃልኪዳን ምልክት—የሌላንቷ አርማ። የሆነ ነገር ትገ አለው።

"ቃል ኪዳናችንስ እዜ፡ ቃል ኪዳናችን እንደሌላው በወርቅ ቀለበት ስላልሰፈረ ነው? ...ቃላችንስ?"

እወንት አንድ እጇን ወደ ፊት ዘርግታ አርገፈገፈችው "እንደዚህ አትበለኝ። አላውቅም....እንደሱ አትበለኝ" ድምጿ ቢሮዋ ውስጥ ያስተጋባል።

አእምሮዋ ውስጥ እንደሞገድ የሚስተጋባ ድምፅ ተሰማት። ሰውነቷ በድን ሆነ። ከፊት ለፊት የተቀመጠው ሄኖክ በትዝብት አይኑ ያያታል። የቢሮዋ ስፋት ከወትሮው ጨምሮ የተንጣለለ ሜዳ ሲመስላት፣ በሩቁ ከንፈ ሲንቀራደድበት ታያት። ፒያኖ ሲመታ ይመስላታል፣ ያንጎራጉራል፣ ያያታል። ሳምንሽ፣ ከስንት ጉድ አውጥቼሽ፣ ሃሳቤን ሰርገር ያለእቅዴ እንቺን አግብቼ በማላውቀው ....የዋህ ፊቱ ገዝፎ፣ ፈጣጣ ማንባሩ እየቀረበ ሲመጣ፡

"እባክህ ሄኖክ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ውጣልኝ ..ውጣልኝ ፡ አልቻልኩም" ብላ ጠረጴዛዋ ላይ በግንባሯ ተደፋች።

ሄኖክ ግራ ተጋብቶ ሰውነቱን እያወናጨፈ ሄዶ በሩን ከከፈተ በኋላ "እሺ መልካም ትዳር ይሁንልሽ፣ አስቀድመሽ ብትነግሪኝ ግን ጥሩ ነበር። ቃልኪዳናችን ዝንተአለም የሚዐና መስሎኝ ነበር። እግዚአብሔር ውስታ ሽን ይክፈልሽ አልልሺም። አሁንም እወድሻለሁ" አላትና በሩን በንዴል ዘግቶት ሄደ። የበሩ ጨኸት አስበርግጓት ከጠረጴዛው ቀና አለች። የተጠረቀመ በር! ተንስታ በሩን ከፍታ፡ ኮሪደሩን አየች፡ ሄኖክ የለም።

Scanned with CamScanner

በሩን ዘግታ አጠገቧ ያለውን ግድግዳ በእልህ — ሲቃ ትደበድበው ጀመር፡እንባዋ በጉንጯ ላይ እየወረደ የምተደበድብበት እጇን እስኪያ ማት ድረስ።

እፀገነት እንደወትሮ ምሳዋን ከበብ ሄዳ አልበላችም። አለቃዋ ለስድስት ሩብ ጉዳይ ላይ ወጥተዋል። በድንገት የቢሮዋ በር ተንኳኳ ። ከሰመጠችበት የሃሳብ ጎዳና ወጥታ "ይግቡ" አለች። በሩ ተከፍቶ የክንፈ ግዙፍ ሰውነት በሩን ሞላው።

"ስራ የለም እንዴ? "አለችው ላመል አይኖቿን እሱ ላይ አሳርፋ። ቢሮዋ ገብቶ ከጠረጴዛው ፊት ለፊት ወንበር ላይ ተቀመጠ፣ ከጥቂት ሰአት በፊት ሄኖክ ተቀምጦበት ነበር።

"ከበባችሁ ጎራ ብዬ ነበር፡ የለሽም " አላት ግዙፍ ሰውነቱን መቀመጫው አላገገና ብሎት እየተቁነጠነጠ።

"በደህናህ ነው? ማለቴ ምነው ሳትነግረኝ መጣህ? ..." አለች እፀገነት የመምጣቱ እንቆቅልሽ አልገባሽ ብሏት ፡ ከሄኖክ ድንገተኛ አመጣጥ ጋር፡ አነፃፅራው ይኼኛው እንኳን ያኔ አልመጣ' አለች በሃሳቧ።

"ለስራ በአጋጣሚ ወጥቼ ነው። እግረ መንገዴን ምሳሽን ስትበይ እደርስብሻለሁ ብዬ ነበር ፡ አልሆነም። ለመሆኑ ከመቼው ነው ምሳሽን የበላሽው? በላተኛው ገና እየተተራመሰ ነው " አላት።

"ከነጋ ከቢሮ አልወጣሁም" አለችው መከፋቷ ከፊቷ እንዳያስታ ውቅ እየጣረች።

"ምነው ደህና?"

"ምላ አላሰኘኝም ።"

ክንፈ ወዲያውኑ ከመቀመጫው ተነስቶ "በይ ተነሽ አብረን እንበላለን" አላት።

"አልወጣም ። ምንም መብላት አልፈልግም ።"

ክንፈ ተቆጥቶና አግባብቶ ምላ እንዲበሉ ይዟት ወጣ። ትንሽ እርፍዳ ወደ ቢሮዋ ተመለሰች። ጠዋት እንደባ ፍሃበት ከቢሮዋ ያስወጣችው ሄኖክ ፍውም እረፍት ነሳት። ስትጨነቅ ዋለች።

በማግስቱ ጠዋት ቢሮዋ እንደገባች ሄኖክ ጋ ስልክ ደወለች።

ሌሰቱን ሙሉ በአሳቧ ሲያስጨንቃትና ሲያሰቃያት ስላደረች፡ ዛሬ አግኝታው ነግራው ልትወጣው ቆርጣለች። እሱን ከተለየች ሰባት ዓመታት፡ እንዲሁም ፍቅሩን ካጻፈነች ሶስት ዓመታት አልፏታል፡ እንደ አዲስ እያስገመገመ መንፈሷን ሰላም ሲያሳጣት ያደረውን ፍቅሩን ገደብ አበጅታለት እንዴት ልታቆየው እንደምትችል ከሀሊናዋ ተሰሙሯል። ሄኖክን የማግኘቱ ፍላጎትም ሰላሚን ነስቶታል። ሄኖክን ትናንት ካየችው ጀምሮ እንደአዲስ ፍቅረኛ አቅበጠበጣት። ብዙ ጊዜ የሆነውን ፎቶውን ካስቀመጠችበት አውጥታ እንዳየችው ርግብግብ ፍቀሯን እናረው፡ በጥዋቱ ስልክ እንድትደውልም ተገደደች።

ትላንት ማታ ክንፈ "ምን ሆንሽብኝ ውዴ' ያላት በእንድ ወገን 'ታል ኪዳኔ! ታል ኪዳኔ!' ካላት የሄኖክ ድምፅ ጋር እየተነፃፀረ የሄኖክ ፍቅሩና ትዝታው እያየለባት አስታያት ።

ከሄኖክ ጋር በስልክ መነጋገር ሲጀምሩ ፡ የክንፈ ወገን ወዲያ ማዶ ሲፈናጠር የሄኖክ ፍቅር፡ ትዝታና እሱነቱ ቦታውን ሞሉት። የብዙ ዓመት እምቅ ፍቅር፡ በመላው ሰውነቷ ሲጥለቀለቅ ታወቃት። ጥንት አብራው ስትቦርቅ፡ ሲስቁ፡ ሲጣሉ፡ እጅ ለእጅ ተያይዘው ከተማን ሲያዳርሱ፡ ቡና ቤቶቹ፡ ሲኒማ ቤቱ፡ ትያትር ቤቱ፡ ያዩዋቸው ትያትሮች...ኸረ ስንቱ! በሕሊናዋ ውስጥ በአንዴ ተሰባስበው ትዝታዋን ቀሰቀሱት። ከጥቂት ዓመታት በፊት ሰውነቷ የረሳው ስሜት እንደ አዲስ አፍነከነካት።

በስልኩ ውስጥ እንባ ቀረሽ መቀሳ ሲያዘንብላት መቋቋም ከምትችለው በላይ ሆነባት። በመጨረሻ ከሰአት በኋላ አሱ ጋ እንደምትመጣ ነገረችው። የፈለገችውንና ያሰበችውን አደረገች። መላ ሰውነቷ በሃሴት ተወራጨ።

የገባ ስሜቷን ተጠየፈችው።

በቀጠሮ ተስማምተው ስልኩን ከዘጋች በኋላ ፈርጥጦ የነበረው ሃሳቧ እየቀረበ፡ እየተሰበሰበና እየጠራ መጣ። 'ከሶስት ዓመት የሰከነ ሕይወት በኋላ…ከችግርሽ ሳይሸሽ ጋሻ መከታ ከሆነልሽ በኋላ ...' በተለይ ይህን ሁለተኛ አሳቧን አትወደውም። ልታስበው የማትፈልገው ንና የምትጠላውን ነገር አስታወሳት ። ይኼኔ ደማሞ ትጨነቃለች። ሀሊናዋ ራሷኑ ይሞግታታል። 'ክንፈ'ኮ የዋሀና ምንም የጥርጣሬ እርቮ

Scanned with CamScanner

የሌለበት ሰው ነው' እያለ እራሷን ሲጠቀጥቃት ይውላል። ምክንያት አለው።

በህይወቷ ልትፈታው ያልቻለችው አንድ እንቆቅልሽ አለ። ከሄኖክ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ውጪ ሀገር በመሄዱ ሳቢያ ቢቋረጥም፣ በደብዳቤ መገናኘታቸው አልቀረም። ከሁለትና ሶስት አመታት በኋላ ግን በደብዳቤ ለመገናኘት የሚያደርጉት ጥረት ጊዜ እያደበዘዘው ሄደ፣ ኋላም ጨርሶ ጠፋ። ይህ እየሆነ በሄደ ቁጥር ብዙ ወንዶች አውቃለች። እፀጋነት ፍቅሯ እየሰከነና እየተደላደለ የሚሄደው እያደር እየለመዷቸውና እየቀረበችው በምትሄደው ሰው ላይ እንጂ ድንገተኛ ፍቅር ብሎ ነገር እያውቃትም። አብራ በቆየችውና ገላውን እየለመደች በሄደች መጠን ነው ፍቅሯ እየፈካ እያበበ የሚሄደው። ወንድ ልጅ በድንገት እድታ ይማርካት እንደሆነ እንጂ በፍቅር እይጥላትም።

በየእጋጣሚው ከሚያረኳት ወንዶች ጋር አካላዊ የወሲብ ውህደቷን ቋሚታ ከመለየት በቀር፣ በውስጧ ታምቆ በጊዜው መለየት አመድ ተጻፍኖ የተቀመጠው የሄኖክ ፍቅር የሌሎች ፍቅር ጠልቆ እንዳይንሰራፋ ተለላክሏል። ያሻት ቀን ከተለያዩ ወንዶች ጋር በስእታት ልዩነት የምትወጣበት ጊዜ አለ። ለግለት ስሜቷ ገደብ አበጅታ፣ ነፃነት ነፍጋና ታፍና መኖር አላስቻላትም። በፍቅሩ የማርካት ሄኖክን በልቧ አስተምጣ፣ በፍቅሩ ጥማት ውሃ እንዳጣ የበረሃ ተክል ጉዳቷ ሳያንሳት፣ በተፈጥሮአዊ ስሜት ሲቃ ራሷን ገምዳ መሰቃየት አልወደደችም። ከሄኖክ ፍቅር ባሻገር ያለው የፍቅር ስሜቷ ለዛእው መክኗል። ከሌሎች ወንዶች የምትሻው ነገር ቢኖር ፍቅር ሳይሆን ስሜትና ዋሩ እርካታ ብቻ ነው። በነኚህ ነገሮች ተጠምዶ መቅረት እንዳለ አልተገነዘበችውም። ያም ሆኖ በተፈጥሮዋ ለስሜቷ በራድ ባለመሆኗ ፣ በእድሜዋ ከሚከሰተው ነበልባላዊ ስሜት ባሻገር ግልፅነቷ ለወሲብ ያላትን ጉጉነት ያሳያል። ይህም ወንዶችን በቀላሉ እንድትቀርባቸው ያደርጋታል።

አሁን ድረስ ያልፈታችው እንቆቅልሽ ግን ይህ አይደለም። ክንፈ እስከዛሬ እንዳጋጠሟት ወንዶች ቢሆን ኖሮ፣ ሄኖክን ያገኘች ዕለት ጥላው በሄዶች ነበር። ነገር ግን አሁን ክንፈ ላይ ይህንን ማድረግ አልቻለችም ።

ያኔ ከጋብቻዋ በፊት እርግዝናዋን ስታወቅ ነው እስከዛሬ ድረስ መልስ ያላገኘችለት ጥያቄ የተፈጠረው። አባቱን እታውቅም።

አብዛኛውን ጊዜ አብራው ስትወጣለት ለነበረ፣ ስለመሰላት ብቻ ፅንሱ ሳይሆን አይቀርም ብላ ጠርጥራው ወደነበረው እስክንድር ሄዳ ማርገዟን ብትነግረው ፣ እንበላ ሆኖ "ከኔ ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለሽ? ወይንስ እስክንድር የማንንም ዲቃላ ያሳድጋል እሱሽ? " ብሎ ፊቱን ከስክሶባት ነበር የሄደው። ከሌሎችም የተሻለ መልስ አላገኘችም። የህይወትን የስቃይ ድፈድፍ መጋት ጀመረች።

ውርጃ እደገኛ እንደሚሆንባት ደግሞ ዶክተሩ እምቢ ብላ የአብሮ አደግ ጎረቤቷ ልጇ እጣ ፈንታ እንዲደርሳት አልፈለገችም ። ሞት አፍጥጦ የመጣባት መሰላት። ቸልተኛነቷን ረገመች።

በወቅቱ አልር አልር ብቻ አብራው ትወጣ የነበረውንና ብዙውን ጊዜ በምትሰግስሰው የስሜቷ እሳት ሲማረክላት የቆየው ክንፈ ፣ ዘወትር አብሯት እቸኳ ገዳሜ ብሎ እንዳያቃብጣት ተፈጥሮው አላመች እያለው ፣ እንዳይተኛት ስሜቷን በማጥመዱ፣ በሕይወቷ አልር አልር ብቅ ጥልቅ ይልባት ነበር።

ግዙፍ ቁመና ያደለውና በእድሜውም ቢሆን የአስር ዓመት ብልጫ ልዩነት በመያዛቸው ያለው ክንፈ፣ በሃያምቹ መጨረሻ የእድሜ ክልል ውስጥ ሆና አልር አልር የሚያጫውታት እወንነት፣ እሷ እንደምትሻው ወዲህ ወዲያ እያለ አይማልልላትም። ቆንጆም ባይሆን ገራገር ፊቱ እንዲውም ግርማ ሞገሱ ለስሞነኛ ፈትኗታል። ችግሯን የነገረችው ለሱ ነው። አልተጠራጠራትም፣ አብሯት መፍትሄውን አሰላላት።

ስላመናት እገባት። ከጋብቻው ሌላ ልጅ ተወልዶ ለማየት ናፈቀ። እሷ ግን ልቧ፣ ሀሊናዋ በበደሏ እየታነከ ተሰቃየች። እውታ ባታደርገውም ከደረጃ የወደቀችበትን እደጋ የተቀበለችው በታላቅ ወጋ ነው።

ልጁ ያልሆነውን 'ልጅህ ነው' ልትለው አልፈለገችም ።

እስከዛሬ ያላወቀችው እንቆቅልሽ ባልጠበቀችውና ባላሰበችው ሁኔታ ተፈታ። ክንፈ እንደአባቱ ገዳይ የጠመደውን ደረጃ እሷ እንደ አዳኟ ቆጠረችው። ከዛ ወዲህ ባሳለፉት የትዳር ህይወት ፍፁም መውደድ ግፍቀር ጀምራለች። ፍፁም ተለይቼው መኖር አልችልም ብላ ባትወስንም በተለይ ዘሬ ስለእርሱ ማሰብ ስትጀምር፣ የመለያየቱ ነገር ተራራ

Scanned with CamScanner

እክሎና ገዝፎ ታያት። ፍቅሩም ከዕለት ዕለት እየደበዘዘና እየጠፋ የሄደ የመሰላት የሄኖክ ፍቅር፣ የረጋውንና የሰከነውን ህይወቷን ሲበጠብጠው ታያት…ሁሉም ነገር ከቁጥጥሯ ውጭ ሆነ። ቀደም ብላ የደመሰችውን እንኳን ላለማሰብ በውስጧ ትግል ይካሄዳል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የኋላው ቀጠሮ ረዝሞባት ናፍቆትና ትዝታው ያብላላት ጀምሯል።

በሁለቱም አላቦጀ እንደተጠራሞተች፣ ልቧ የሃዘን ማርሽን ጎሰመ። ህይወት ትርጉሟን አጥታ ባዝና መርትዛባታለች፣ አስጠይፋታለች። ከፊት ለፊቷ የተቀመጠው የጽህፈት መኪናዋ እንዳች ሜሄና አለው። ቢሮ ስትገባ የመጀመሪያ ስራዋ የአለቃዋን ቢሮ ማስተካከል ሆነ፣ ይህንን አለማድረጓ ትዝ ብሏት ከመቀመጫዋ ስትነሳና አለቃዋ ቢሮውን ከፍተው ብቅ ሲሉ አንድ ሆነ።

* * *

ለክሰአት በኋላ ቀጠሮዋ ቢሮ እንደማትገባ ለአለቃዋ ከነገረች በኋላ የምላ ሰአት በመድረሱ ከመውጣቷ በፊት ትንሿን መስታወት ከቦርሳዋ አውጥታ ፊቷን አየች። የከንፈር ቀለሟን አውጥታ በውበት ላይ ውበት ጨምራለት ይበልጥ አምሮባቸው። የላይኛውን ከንፈሯን ከታችኛው ጋር አፋተገችው፣ ቀለሙ እንዲዳደረስ። ዘወትር የከንፈሯን ቀለም መጋራት የለመደውን ጉንጩን በትንሹ ነካ ነካ አድርጋው በመዳፍ ስታሻሸው ከቀዩ ፊቷ ላይ ደም የሚርመሰመስበት መሰለ። በመስታወት እየተመለከተች በሚገባ በስሱ ወለወልችው። ቀሚኑ ቀዩ መልኳ ከሰልካካ አፍንጫዋ ጋራ ተጣምሮ አርቲፊሻል መቆንጀጂያ አላሰፈለገውም። ከመስታወት ይበልጥ ጠርቶ ውበቱ እንዐባረቀ።

ካገባች ወዲህ፣ ለውበቷ እንደዚህ ስትጨነቅ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነው። በቀላሉ ተጋጊጣ የሚያምርላት ውበቷ ዛሬ በቂ አልመሰላትም። በጣም የምትወደውን ከአስራ አምስት ቀን በፊት ከንፈ ለልድቷ ስጦታ ያመጣላትን ኮ ኮ ሽቶ ከቦርሣዋ አውጥታ ፣ በጡቷ ስር በመጠኑ ረጨችበት። ከፍሱ በአንድ ጊዜ በሽቶ ታወደ። አለቃዋ እያሉ ተጣድፋ ወጣች።

የመስሪያ ቤቷን ኮሪደር አልፋ ደረጃውን ቁልቁል ስትወርድ እንዳንድ ሰራተኞች ከስራ እየወጡ ነበር። እየተጣደፈች ግቢውን ለቃ ወጣች። ታክሲ ይዛ ከብዙ አመታት በፊት ስትመላለስበት የነበረው ቤት በአይን ሀሊናዋ እየታያት የሚያጋጥማት ሁኔታ ተጋርዶ እያስፈራት ፣ በእንድ በኩል ሄኖክን የማግኘቱ ጉጉት እየናረባት ሲሄድ ፣

ያቺ ሰፈር! ሄኖክ ከሄደ በኋላ ዞር ብላ ማየቱ እንኳን ያስጠላቻት ሠፈር ናት ፣ ታኮ ጫማዋ እያወላከፋት ወደ መንደሩ ዘለቀች ። ችርችም ያለች ሠፈር ፣ ምንም የተለወጠ ነገር የለም ። የነሄኖክ ቤት እንዳለች ነች ። ያረጀው በሯ እንኳን ወይ አልተጠገነ ወይ ጨርሶ አልፈረሰ ። በሩን በቀስታ እንኳኳች ። አውንም ደገመችው ።

አንዲት አጠር ወፈር ያለች ልጅ እግር ቢጤ በሩን ከፈተችላት ።

"ሄኖክ አለ!" አለች መኖሩን ባትጠራጠርም ለይምሰል ።

"አለ ግቡ!" አለቻት በሩን በርገድ አድርጋ ።

ልቧ እየተጨነቀ ፣ እየተሸበረ ፣ በይበልጥ ደግሞ ሄኖክን ለማግኘት እየጓጓች ልጅቷን ተከትላት ወደ ቤት ገባች ። ህይወት ባለቤቱ ባቀዳት መስመር የምትጓዘው መቼ ይሆን? በውስጣችንስ ስንት ነፍስ አለ? ሁሏንም የምትገዛና የምታዝ ነፍስ የትኛዋ ትሆን? —እያለች የተከፋፈለው እይንቷ እያስጨነቃት ሳሎን ስትገባ ሄኖክ ቆሞ ተቀበላት ።

የተዘበራረቀ ስሜት በገፅታዋ ላይ ይንበባል ። የምታደርገው ጠፋት። ትሳመው! እጁን ትዘረጋለት? ወይንስ ዝም ብላ ትቀመጥ ። ወደሷ ሲራመድ ታያት ፣ በቀስታ ፣ ምንም ማሰብ አልፈለገችም ፣ ሁሉም ነገር ባንድአፍታ እንዲከናወን አሻች — ባለትዳር መሆኗን ለመርሳት ። እርምጃዎቹ በቀስታ ናቸው ። ፈዛ እንደቆመች ደርሶ እጁን ያዛት ። ጊዜ ሰጣት — እንድታስብ ፣ ሳትወድ በግድ እንድታስብ አደረጋት ። እጆቹን በቶሎ አስለቀቀችና ወደ ፎቱው ሄዳ ተቀመጠች ።

ሄኖክ ቆሞ እያያት ነው ። እልህ ፣ ፍቅርና በቀል በሞንቅላቱ ውስጥ ተቀያየጡበት ፣ ለማድረግ የወሰነው ነገር የለም ። ከቢሮዋ ውጣልኝ አለችው — ወጣ ። ቤትህ አመጣለሁ አለችው — መጣች ። እሱም ጠበቃት ፣ በቃ ፣ 'በቃ ይሄው ነው፣…' አለ በሃሳቡ ።

"እሺ እፅሽ ቤቱ አልጠፋሽም!" አላት ከቆመበት እየተንቀሳቀሰ ። ዝምታው የውስጡን ጭንቅት ያስተጋባ ይመስል ፣ እጅግ አድርጉ

Scanned with CamScanner

እያስፈራው ።

“ባክህ በሙሉ ስሜ ጥራኝ?” ንጭንጭ አደረጋት ፡ ሆድ ባሳት ። ‘ደግሞ ከመቼ ወዲህ ነው እፅሽ የሚለኝ? እፅዬ ነበር የቀድሞ ማቆላመጫው ። እፅሽ ሲላት የክንፈ ገፅታ ታያት ።

ሄኖክ ተናደደ ። “ደግሞ ባንቺ ብሶ እንዲህ ትሆኛለሽ?…እፀገነት ለምን የሆዴን ታናግሪኛለሽ? እንግዳዬ እንኳን መሆንሽ ይገርመኛል ። ድፍረትሽ ይደንቀኛል ። እኔነቴን በውስጥሽ አምክነሽ እኔ ጋ ስትመጪ ትገርሚኛለሽ ። ደግሞ ባንቺ ብሶ ቁጣሽ ። ሄኖክ ስሜት ፡ ፍላጐት ፡ ፍቅር የለውም አሉሽ? ሄኖክ ስሜቱ የማይደማ የማይቆስል ድንጋይ ነው አሉሽ?…” ድምፁ እየከረረና እየጐላ ከቁጥጥሩ ውጭ እየሆነበት ሄደ ።

“ንገሪኝ እንጂ እፅዬ! ይቅርታ ሙሉ ስምሽ ተዘንግቶኝ ሳይሆን አፌ ልማዱን አልተው ብሎ ነው!”

“በቃህ!…በቃህ!…” አለች ድምጿን እጅግ ድክም አድርጋ ። በነገር መትከኗ በንግግሯ ይታወቃል ።

“በቃህ ሄኖክ! አንዴ የፃፍክልኝን ታስታውሳለህ? አዎን መቼም ከሀሊናዬ አይጠፉም ። ጨካኙ ሄኖክ ሁለት አመት እንኳን አልሆነህም ነበር…” ከቦርሳዋ መሀረብ አውጥታ ተናፈጠች ። “…ስለሆነም…፡ እኔን ለሌላ አሳልፈህ ጥንካሬዬን ስታደፈርሰው ፡ እምነቴን ስትንደው ሁለት አመት እንኳን አልሆነህም ፡ ትዝ ይልሀል ሄኖክ! ደብዳቤ መፃፊያ ጊዜ አጣሁ አላልከም? ለኔ የሚሆን ጊዜ ጠፍቶህ…”

“እና በቀል ነው? በቀል…” አለ ሄኖክ ስሮቹ ተገታትረው አይኖቹ እየደፈረሱ ።

“…አስጨርሰኝ ሄኒ ፡ አስጨርሰኝ ፡ እንዴ ብቻ ላውራህ ። እናማ እኔን ገፍትረህ ለሌሎች አሳልፈህ ሰጠኸኝ ። በፍቅርህ ፍፁም ተስፋ እንድቆርጥ አደረግኸኝ ።

“…ሄኒ ብዙ ጊዜ ታገልኩኝ ። ብዙ ታገስኩኝ ፡ በመጨረሻም ከአቅሜ በላይ ሆኖብኝ እንጂ ባንተ ተስፋ ቆርጬ አይደለም ። እስከማገኝህ ጥንካሬ ነበረኝ ። እስካየሁህ ቀን ድረስ ልረሳህ የሞከርኩት የተሳካልኝ መስሎኝ ነበር ። …ሄኒ አቃተኝ ምን ልሁን? …” ማልቀስ ጀመረች ። እንባዋ በቀዩ ፊቷ ላይ ኮለል እያለ ይወርዳል ። በዝምታ አየችው ። እንባዋን ለመጥረግ አላሰበችም ፡ ቁልቁል በጉንጯ ይንከባለላል ። እንዲያዝንላት ብላ አይደለም — ፍፁም ራሷን ዘንግታ ነበር ። ከብዙ ዓመታት በኋላ ከፊቷ የተቀመጠውን ሄኖክ የምታይ ትመስላለች፡ አይኖቿ እሱን የተራቡ ይመስላሉ ፡ ግን አያዩትም ፡ ፅንባዋም መውረዱን አልተገነዘበችም …ከአድማስ ማዶ ታያት ከአድማስ ማዶ…ፅፀገነት ቃል ኪዳን ከቡር ነው ፡ እስከመጨረሻው በተስፋ እጠብቅሻለሁ ። ጠብቂኝ… ጠብቂኝ…ጠብቂኝ ።”

“ጠብቁህ ነበር ሄኖክ” አለችው በድንገት ከተጓዘችበት ተመልሳ ።

ከምንም ነገር በላይ መታለልን አይወድም ። ደረቅ እውነት ይመርጣል ። ታምና ለመቆየቷ እርግጠኛ አይደለም ። ባለመታመኑ ደግሞ ሊለያት አልፈለገም ። ‘እንዳሻት ትሁን ፡ ብቻ ሀገሬ ስገባ የኔ ትሁን የሚለው መንፈሱ አደላ የሄኖክ ።

* * *

ሊማር የሄደበት ሃገር የጠበቀውን ያክል አስደሳች አልሆነለትም ። ብቸኝነት ይሰማው ጀመር ። ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ነበሩ ። ነገር ግን አንዳቸውንም ሊተርባቸው አልፈለገም ። ምክንያቱ ባይገባውም ይሸሻቸዋል ። ጠዋት ማታ ትምህርቱን ብቻ ሲከታተል ይውላል ። በተረፈ ለእፀገነት ድብዳቤ መፃፍ ነበር ቋሚ ስራው ።

አንድ አመት አልፎ ሁለተኛው ተተካ ። ወደ ሀገሩ ለመምጣት የነበረው እቅድም በተለያዩ ምክንያቶች ተሰናከለ ፡ በቤልግሬድ አወራ ጐዳናዎች ላይ የእረፍት ጊዜውን አሳለፈ ። ይህ ብቻም አይደለም ። ብቸኝነቱን ማስታመም የቻለችው መቅደስ ነች ። በአንድ ዓመት የትምህርት ዘመን ትቀድመዋለች ። የሚማሩበት ዩኒቨርሲቲዎችም የተለያዩ ናቸው ። በቤልግሬድ የተገናኙት ከእያሉበት ለእረፍት ሄደው ነው ።

ትካዜው ይሰማታል ። ብቸኝነቱ ያሳዝናታል ። ወገናዊነቱ ደግሞ እንድትንከባከበው አድርጓታል ። ሄኖክም ብቸኝነቱ እንዲፈቅዳት አድርጐታል ። እንዲህ እንዲህ እያሉ ተላመዱ እስኪደንቃቸው ድረስ። አረፍት ሲያልቅም ፡ ወደ ትምህርት ቤታቸው ነጐዱ ። ልቡ ከሷ ፡ ልቧ ከሱ እንደሆነ ፡ በሚያጋጥሟቸው የዕረፍት ቀናት ሁሉ እንዳቸው ወደ ሌላኛው መንገድ ሆነ — በባቡር! እሱ ወደሷ እሷም ወደሱ ። አብረው የሚያሳልፉት አጭር ጊዜ ሰመመን እየሆነ አሰቃያቸው ። አጭር በመሆኑ የመቋጫ ውሉ ጠፋ ።

Scanned with CamScanner

እፅገነት ከአድማስ ማዶ ፥ ከወንዞች ፥ ከባህሮች ፥ ከተራሮች ጀርባ ሆና ትታየዋለች ። መቅደስ ደግሞ ከጉያው ሆና ብቸኝነቱን ታስታምማለች ። አንድ ነገር ማድረግ አለበት ። አንድ ነገር ።

ስለእፅገነት አንድ ሳይቀር ለመቅደስ አጫወቷታል ። መቅደስ ደሞ ልትርቀው አልቻለችም "እሷ ያገር ቤትህ ፥ እኔ ደግሞ የባዕድ ሀገር ጓደኛህ ፥ ምን ያገናኛናል?" አለችው ፍርጥም ብላ ። ሕሊናው አያርፍም ። ያስባል ፥ ይጨነቃል ፥ ያወጣል ፥ ያወርዳል ፥ ትምህርቱን እፅገነትን አገር ቤትን መቅደስን…ሁሉም ለሱ ጥሩዎች ናቸው ። ሁሉም ሀልውናው ሆነውበታል ። ሁልጊዜም ትታየዋለች ከአድማስ ማዶ እፅገነት ።

አንድ ቀን ግን ወሰነ ። ሊዋሻት አልፈለገም ። ሊነግራትም ጠላ ። 'ግን' አለ ፥ 'ጥፋቱ በጥፋቷ ይካካስ ፦' ሕሊናውን ሸነገለ ።

ከመቅደስ ፍቅር አልያዘውም ። ለብቸኝነቱ ግን መድሀኒት ሆናለታለች ። ዘወትር ባያጣት ይመርጣል ። የእረፍት ቀኑን ለሷ መደበ ። ወይ ትመጣለች ፥ ያለዛም ይሄዳል ። መክነፍ ፥ መብረር ሆነ ስራቸው — በባቡር!

ትምህርቱ እየተደራረበ መጣ ፥ ጥናቱም በዛ ። ሰአታት ክንፍ እያወጡ ሲበሩ ደብዳቤ መፃፊያ ጊዜ አጣ ። የመፃፊያውንም ጊዜ ሲያገኝም ወኔውን አጣ ። በደሉ እየታወቀው ፥ ላያስባት ይሞክራል ። ለተወሰኑ አመታት ምኞቱ ተሳካለት ።

ሶስተኛውን አመት አገባዶ አራተኛውን እንደያዘ መቅደስ እናት ሀገሬን — ኢትዮጵያን አለች ። የቀራት አንድ አመት ብቻ ነበር ። ይሄኛውን የእረፍት ጊዜዋን አብራው እንድታሳልፍና አንደኛውን በሚቀጥለው አመት አጠቃላ ወደ ሀገሯ እንድትሄድ ጠየቃት ። አስተላሰቧን ሊያስለውጣት አልቻለም ። የእረፍት ጊዜዬን ሀገሬ ሄጀ ማሳለፍ አለብኝ ብላ ለጉዞ ተነሳች ። የመሄዷን አጋጣሚ ለመጠቀም ብሎ በእህቱ በኩል እንዲደርሳት በማለት ደብዳቤዎች ሰጣት — ለእፅገነት የሚላክ ። በወሩ አንድ ደብዳቤ ደረሰው ። ከዚህ በፊት ከሚደርሱት ደብዳቤዎቿ አድራሻው የተለየ ነው ። ስሙ የሚያውቀው ነው — መቅደስ አብርሃ ። በመገረም አድራሻውን አየ ። 'አቴንስ ፥ ግሪክ' ይላል ። ልቡ አንዳች ነገር ጠረጠረ ። ከፍቶ አነበበው ።

የሰላምታውን ሀተታ እየጨረፈ አልፎ '…ሄኖክዬ ላንተ አላማከር ኩህም እንጂ ውጥኑ አስቀድሞም በልቤ አድሯል ። ባማክርህ-ኤንኳን ሃሳቤን መለወጥ የምትችል አልመሰለኝም ።

'…ያለህበትን አድራሻ ፖስታው ላይ ገልጨልህለሁ ። እንዴት እንደገባህ ዝብዝብ ታሪክ አላበዛም ። በርግጥ ለብዙ ጊዜ ያሰብኩት ተሳክቷል ። የሚያሳዝነው ግን የጠበቅኩትን አላገኘሁም…

'…ሄኔዬ እዚህ አቴንስ ውስጥ ከምትገምተው በላይ ኢትዮጵያው ያን አሉ ። ይደንቅሀል…ምን እየሰራሽ ነው አትበለኝ ። ግን እዚህ ያሉት ኢትዮጵያውያን የሚሰሩትን ላጫውትህ ። ይኸውልህ የእድል ነገር ሆኖ ከወንዶች የሴቶች ዕጣ ይሻላል ። በየሰው ቤት እየተቀጠሩ ሞግዚትም ገረድም እየሆኑ ይኖራሉ ። ነገሩን እንደ ደብዳቤዬ ቃላት አታቅልለው ። እጅግ በጣም ያሳዝናል ። ለዚህ ነው አንቺ ምን እየሰራሽ ነው እንዳትለኝ ያልኩህ ። የወንዶቹን ግን ባልነግርህ ይሻላል ። ባገር መሞት መታደል አይደል!…ለወደፊቱ ምን እንደማደርግ አላውቅም ። ወደትምህርቴ መመለስ ብችል ምንኛ በታደልኩ ፥ ግን አይመስለኝም ።

'ሄኒ ! ግን በምንም መንገድ የኔ አይነት ሃሳብ በሚንቀላቀላትህ እንዳያድር አደራ! እዚህ የምትሰማውም ሆነ የምታየው አንዳች ጥሩ ነገር የለም ። በነገ ተስፋ በዙ ዛሬዎች የሚባክኑበት ሀገር ነዉ ። ዛሬን በአግባቡ መኖር ያልቻለ ፥ ነገን መኖር እንዴት ሊያስብ ይችላል?

'ደብዳቤዎችህን በሙሉ በእህትህ አድራሻ ፖስታ ቤት ከትቻለሁ ። ሄኒ ያጭር ጊዜ ትውስታዬ ነህ ። አብረን ብንቆይ ወደፊት የሚሆነውን መገመት አልችልም ። እንደ ቀልድ ተጠግቼህ መለየቱ እየከበደኝ ሄዶ ነበር ። በልብህ ያለችውን ልጅ ስለረሳኋት አንተም የረሳሀት መስሎኝ ነበር። ነገር ግን ልሂድ ስል የሰጠሽኝን ደብዳቤ ስመለከት ልቤ ከፉኛ ሲቆስል ታወቀኝ ።

'አላስተዋልከልኝ እንደሆነ እንጂ በጣም ተረብሼ ነበር ። ግን በርግጥ ወድጄ የገባሁበት ነው ። ይሄን ጊዜም በተስፋ ስትጠብቀህ ይሆናል ። ድረስላት ። ልረሳህ እሞክራለሁ ፥ እንተም እንደዛው ። እኔ ግን የሚሳክልኝ አይመስለኝም ። ሄኒ አደራ የኔ አይነት ሃሳብ በፍፁም ከአምሮህ ውስጥ እንዳይገባ ። እሺ! በል ቻው ።

Scanned with CamScanner

ብዙ ጊዜ መልስ ሊፅፍላት እያሰበ ይተወዋል ። ያለፈን ትዝታ ማስታመም አልፈለገም ። እሷ እንዳለችው ሊረሳት ሞከረ ። ለእፀገነት ብእሩን ካነሳ በኋላ ድፍረት አጥቶ ይተወዋል ። አንዳንዱም ፅፎ የጨረሰውን ደብዳቤ ለመላክ ድፍረት የሚያጣበት ጊዜ አለ ። የኋላ ኋላ ትምህርቱን ሲጨርስ ሊያገኛት ቆረጠ ።

* * *

"...በቃሽ እፅሽ ፡ አታልቅሺ" አላት ሄኖክ ከሄደበት የሃሰብ ጐዳና ሲመለስ አትኩሮ እያያት ።

"እፅሽ አትበለኝ አልኩህ እኮ!" ብላ እንባ በሞጠሩ አይኖቿ ተመለከተችው ። ባልታወቀው ፍጥነት በጥፊ አጮላት ። ደነገጠች ። አይኖቿ እንደ ፈጠጡ ናቸው ። እሱም ደነገጠ ። "ይቅርታ..." አላት እየተርበተበተ የሚያደርገው ጠፍቶት ።

ወዲያው ፊቷን በእጆቿ ሸፍና ማልቀስ ጀመረች ። ተጠግቶ አባበላት ትከሻዋንና አንገቷን እየደባበሰ ። በአጋጣሚ በውስጣቸው የሚንቀለቀለው የከረመ ፍቅር ነዲድ እሳት እየተቆሰቆሰ በአካላቸው መቀራረብ እየተራገበ ተቀጣጠለ ። ፊቷን የሸፈነችበትን ሁለቱን እጆቿን አነሳው ።

ጉንጯ የጋለ ብረት መስሏል ። ጉንጯ ላይ ያረፉት የእጅ ጣቶች ምልክቶች አበጥ ብለው ያስታውቃሉ ። ቀስ አድርጐ ደባበሳቸው ። እሱም እፁም ፊታቸውን ሲያቀራርቡ አልታወቃቸውም ። ብቻ የሁለቱም የሞቀ ትንፋሽ በየገፃቸው ላይ ይሰማቸዋል...ለረጅም ጊዜ የተነፋፈቁ ከንፈሮቻቸው እየተርገበገቡ እየተንቀጠቀጡ ናፍቆታቸውን ተገላለፁ። ያገዳቸው ኃይል አልተገኘም ። ተገናኙ...

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ከፎቱው ላይ አስነስቷት ወደ መኝታ ክፍል ሲወስዳት ቢታወቃትም ሁሉም ነገር ታክቷት ነበር ። ልትታወመው አልፈለገችም ። ልብሷን ሲያወላልቅ አልረዳቸውም ። የቀድሞው እሱነቱን እያሰበች...ነጎደች ።

አሁንም እሱነቱን ሰጣት ። ማንም ሊያደርገው ያልቻለውን ፡ ከማንም ልታገኘው ያልቻለችን ፡ የስሜቷ እርካታ ጫፍ ደረሰላት ።

"...ሄኒ...ሄኒ...ዬ ልለይህ አልፈልግ...ም ..." ከሰባት አመት በፊት የቀረው የስሜቷ ዳርቻ ከዳር—እዳር አስጋለባት ። ልዩና ረቂቅ ምትሀት እንዳለው ሆኖ ተሰማት ። ቃላት ሊያውጇቸው ከሚችሉት በላይ ። ከፅ በቀር ሌላው ሊረዳው የማይቻል የእርካታ አጥናፍ...እኩል በረጅሙ ተነፈሱ ።

...ትንሽ ቆይታ ማሰብ ጀመረች ። ከሁለት ጊዜ በላይ ስሜቷን አንጠፍጥፋ ካወጣች በኋላ ፡ 'በርግጥ አፈቅረዋለሁ?' አለች — እርግጠኛ መልስ አለማግኘቷ ለራስዋም ደነቃት ።

ምእራፍ አራት

አስር ሰዓት ከአምስት ሆኗል። አዜብ፡ ወዳጇ ሲራክ መስሪያ ቤቷ ግቢ ገብቶ እንደሚጠብቃት አልተጠራጠረችም። ያቀረቀረችበትን ፋይል በፍጥነት ዘግታ ቦርሳዋን አንጠልጥላ ወጣች።

ፀሐይዋ ከመጠን በላይ ከራለች። መኪና ውስጥ ከሆኑ ሙቀቱ እጅግ ያስጨንቃል። ሲራክ ፔጀ መኪናው ውስጥ ተቀምጦ ነፋስ መስጫውን እስከመጨረሻው ከፈተው። ሊያቀዘቅዘው ግን አልቻለም። መዘግየቷ እያበሳጫው መኪናውን ከፍቶ ሲወጣ፡ የፀሐይዋ ግለት መላጣውን ብትወጋውም ውስጥ ካለው ሙቀት ውጭው ተሽሎታል።

ሰራተኞች ከቢሮ እየወጡ ናቸው። አምስተኛ ፎቅ ወርዳ እሱ ጋ ለመድረስ ሌላ ጊዜ ከአምስት ደቂቃ በላይ አይወስድባትም። አሁን ግን ሰአቱ አስር ከሩብ ሊሆን ነው። ከሩቅ ስትመጣ ተመለከታት። ረዘም በሚለው ቁመቷ ከለበሰችው ረጅም ቀሚስ ጋር ስትታይ መስህብ አላት። እንዳያት አንድ ጥያቄ አእምሮው ውስጥ ገባ። ጥያቄውም ውሳኔውን ወዲያው አስገኘለት። ዛሬ ቆርጦ ሊጠይቃት ወሰነ። እንድታገባው።

ቀድሟት ገብቶ ከውስጥ በሩን ከፈተላት ። ተዝናንታ ተቀምጣ "ሶሪ ፡ ዘገየሁ..." ስትለው "ሰላምታው አይቀድምም?" ብሎ ጉንጩን ሳማት። ቀዝቃዛ ፈገግታ አሳየችው።

ሲራክ መኪናውን አስነስቶ ጋለበ። ጥቂት እንደተጓዘ አቅጣጫቸውን ለማስመረጥ ወደሷ ሲዞር ታነባለች። ምኔ እንዳማደፋት እየተደነቀ "

Scanned with CamScanner

ወዴት እንሂድ?”ሲላት፣ የመጽሀፉን ገጽ በጣቷ ምልክት እየያዘች ‹
እ…ወጥ ያለ ቦታ ቢሆን እመርጣለሁ!” አለችው። ይህንን ምርጫዋን
ያውቃል። በሁኔታዋ አልተበሳጨም፣ ተላምዶታል። የራሱን አማራጭ
ወሰደ “እቤት እንሂድ” አላት፣ ምርጫም ትዕዛዝም በሚመስል ጥያቄ፣
“ሙዚቃ ልክፈት እያልክ የማትበጠብጠኝ ከሆነ ደስ ይለኛል።
ዛሬ ጀሮዬን ያስጠላው ነገር ቢኖር የመሣሪያዎች ኳኳታ ነው እ…? ብቻ
ሰላም ከሰጠኸኝ ” ብላው ወደመጽሀፍዋ ተመለሰች።

“ እንቺም ላንብብ እያልሽ ካላስቸገርሽኝ እኔም ሙዚቃ አልከፍ
ትም። ድምጽሽ ራሱ ለኔ ሙዚቃዬ ነው።”

ሃሳቧን ከመጽሀፏ ወደ ሲራክ አዞረችው። ስሜቷን፣ ፍላጐቷን
ሊረዳትና ሊገነዘብላት የሚችል ሰው ማን ይሆን? አብዛኞቹ ወንዶች
የተወሰነ ጊዜ ሁሉን ይቀበላሉ። ከዛ የራሳቸውን ፍላጐት በሷ ፍላጐት ላይ
ተፅእኖ ያሳድራሉ። እሷ ደግሞ ይህንን ማስታመም ያቅታታል። ስትርቃ
ቸው ይከተሏታል፣ ስትቀርባቸው ደግሞ ይጫኗታል። አሁንም ሲራክን
ይህና አድርጋ አስተዋለችው። ብልጣብልጥ አይን አለው። ከንፈሩ
ቀጭንና ስስ ነው። ሁልጊዜ በምላሱ ስለሚጠርገው እርጥበት አለው።
ፀጉሩ ወደኋላው እየሸሸ፣ ጨርሶ ባይመለጥም ከጥቂት ጊዜ በኋላ
በእብዛኛው ባዶ እንደሚሆን ያስታውቃል። ኃይለኛ ነው። በሷ ላይ
ጉልበቱን ፈትኖ አያውቅም። እርጋትዋና ቅዝቃዜዋ አደብ ያስገዙታል።
እልኸኛም ይመስላል። ማድረግ የሚፈልገውን ካላደረገ መንፈሱ ሰላም
አያገኝም። ያቅበጠብጠዋል፣ ያነጫንጨዋል። ከዚያም እንኛ ስስ ከንፈ
ሮቹ ያሞጠሙጣሉ።

“ እንግዲህ በቃሽ!… ” አላት ቤቱ ሊደርሱ ሲሉ የምታነበውን
መጽሀፍ ሊቀማት እየሞከረ። “ አጠገብሽ ሰው አለ ብለሽ እንኳን
አይከብድሽም? ” አላት እያኮረፈ።

“ የኔ ማንበብ ለምን ያበሳጭሃል? ” አለችው ግራ በተጋባ ስሜት
እያየችው።

“ እስከዚህ ይሉኝታ ቢስ መሆንም አያስፈልግም። ለፊስ ብቻ
ላይሆን ስለሰዎች ማሰብምኮ ያስፈልጋል” አላት እየተነጫነጨ።

መኪናውን አቁም ጡሩምባ ሲነፋ የመኖሪያ ቤቱ በር ተከፈተ። ወደ
ውስጥ አስገብቶ ካቆም በኋላ “ ምንድነው የምታስቢው?” አላት ፈዞ

በመኪናው የፊት መስታወት ወደፊት የተወረወረውን እይታዋን ተመል
ከቶ።

“ እ…ምንም፣ ግን የሚያስበው ጉዳይ ይለያይ እንጂ፣ የማያስብ
ጭንቅላት ይኖራል ብለህ ነው?”

“እኔም የጠየቅኩሽ ለዚህ ነው ። ለምን አስብሽ ላይሆን ፣
ምንድነው የምታስቢው ነው ጥያቄዬ” ፈገግ ብላ “ ጥያቄው መከተሉ
አይቀርም ብዬ ነዋ! ስላንበብኩት መጽሀፍ ነበር የማስበው “ እንዳለችው
በስጨት ብሎ ” ግን ለምን …” ንግግሩን ሳይጨርስ ደመቅ ያለ ፈገግታ
በፊቷ እየተረጨ ፣ “አላልኩህም!” ብላው ቀድማ ከመኪናው ወረደች።

ከአባቱ የወረሰው ትልቅ ቪላ አለው። የቤት እቃዎቹም የተሟሉ
ናቸው። ፍፁም ወንደላጤ አይመስልም። “ እንግዲህ ልንጣላ ነው” አላት
ወደ አዜብ እያየ፣ እይታዋን ከመጽሀፏ ላትነቅል“ ለምን? ” አለችው
በግዴለሽነት ስሜት። ቅዝቃዜዋ ያናድደዋል። የሚገርመው ደግሞ
የሳበው ቅዝቃዜዋ መሆኑ ነው። እልህ ያሲዘዋል። እያለች አለመኖሯ
ያስደንቀዋል። በውስጡ የሚላወሰው የፍቅሯ ሃይል ደግሞ …..

ለምንም ነገር ደንታ ያላት አትመስልም። ደግሞ እያንዳንዱን ነገር
በሚገባ ታጤናለች። “ ቆይ እሰቲ ግን…” አለች በድንገት ከምታነበው
መፅሐፍ ላይ ቀና ብላ ወደሱ እየተመለከተች። በአግዳሚው ሶፋ ወንበር
ላይ ከፊት ለፊቷ ተቀምጧል“ ….ምንድነው የሚያናድድህ” አለችው
አትኩራ እያየችው።

“ ነገርኩሽ፣ አይገባሽም። አጠገቤ እያለሽ የለሽም፣ ለኔ የምትሰ
ጪው ጊዜ ኖሮሽ እያውቅም። ዘወትር የራስሽን ፍላጐት ብቻ ትጠብቂያ
ለሽ። በዚህ አይነት…” የሷ ጉዳይ ሲያብሰለስለው ከርሟል። ይህም
ከመራራው ንግግሩ ያስታውቃል። “ እ…ብቻ መጨረሻሽን ለማወቅ
እጓጓለሁ። የተለየሽ ፍጥረት ትመስይኛለሽ” አላት እየተበሳጨ።

ቃላቱ በአእምሮዋ ውስጥ ቦታ አላጡም። ለሰው የማይመች ተፈጥሮ
እንዳላት አላጣችውም። ነገር ግን የምታውቀውን የሚነግራት ሳይሆን
አዲስ ነገር የሚያወራላት ነው የሚያስደስታት። በቀዝቃዛ ፈገግታዋ
“የወደድከኝም በዚሁ ተፈጥሮዬ መሰለኝ” አለችው። ሲራክ አቅማማና
“ይሆን ይሆናል” አላት በሚያዋጣት መንገድ ጥያቄዋ እንዳቀረበች
በመገመት።

Scanned with CamScanner

“ ታዲያ! … ” አውንም ፈገግ አያለች “… እንድትወደኝ የዳረገህን ተፈጥሮዬን እንድቀይር ለምን ትገፋፋኛለህ። አንድ ያልተረዳህልኝ ነገር አለ። ማንበብ ለኔ የትርፍ ጊዜ ስራ አይደለም። ይገርምሃል ደግሞ ባሻኝ ሰአት ወይም በቂ ጊዜ ሲኖረን አይደለም የማነበው። የማንበብ ስሜቱ የተጠናወተኝ እለት ብቻ ነው። ያለዛ ቃላት በነጭ ወረቀት ላይ ተለጥፈው ማየት እጅግ የሚያስጠላኝ ቀን አለ። ይገባኛል፣ ተፈጥሮዬ ግራ ነው። ግን ደግሞም ይህንን ያክል አስቸጋሪ የሆንኩ አይመስለኝም” ብላው መዕሀ ጁን አጥፋ ከጐኑ ተቀመጠች። ሲራክ በሁኔታዋ ተገርሞ “ ስራሽ ሁሉ እንደኪነጥበብ ነው። ለሰው የማትገቢ ግራ ፍጡር፣ ሲርቁሽ የምታስቸግሪ ፣ የምታጓጊ ፍጡም የኪነጥበብ አይነት ሰው ነሽ። ባህሪሽ ከደራሲ ህይወት ጋር ይመሳሰልብኛል። እንደነሱ ቀጥተኛና ዝግ ፍጥረት ነሽ። ፍፃሜያቸው አንድ ነው፣ ለራሳችሁ አትሆኑም።”

“ ታድዬ! …” አለች ቀዝቃዛ ፈገግታዋ እየጐላ እየሄደ ። “…የደራሲ ባህሪይ ነው ያልኝ? ደራሲ እመስላለሁ? ” አለችው በጉጉት እያየችው። “ግን ይገርምሃል፣ ያሳዝናል፣ ደራሲ አይደለሁም። ደራሲን እንዳደንቅ እንጂ ደራሲ እንድሆን ተፈጥሮ አልገሰችኝም። ለቃላት ትእግስት የሉኝም። በውስጤ መከነው የሚቀሩ እንጂ እራሳቸውን ችለው የሚወጡ ቃላት የሉኝም። ከምወደው የስነልቦና ጥናት ውስጥ የማገኛቸ ውን ሰዎች በጭንቅላቴ ውስጥ ተብላልተው እንዲቀመጡ እንጂ በቃላት ተጊጠው በወረቀት እንዲሰፍሩ የማድረጉ ሃይልና ጉልበት የለኝም። ይህም ሳይሆን አይቀርም ውስጤን እየበላ የጨረሰኝ፣ ግን የደራሲ ባህሪይ አለሽ አልከኝ? ታድዬ! ይገርምሃል ማንም ብሎኝ አያውቅም።”

ደስ አላት። መንፈሷ ተፍነከነከ። የውስጧን ድብቅ ፍላጐት ነበር የገለጸላት። ደራሲ መሆን አልችልም። ተሰጥኦ የለኝም’ ብላ ደባብሳ የቀበረችውን ልታስበው አትፈቅድም። ወኔው ያንሳታል፣ ድፍረቱ የላትም። ደስ አላትና አቀፈችው፣ ሳመችው፣ እየደጋገመች።

“ ለምን አንዳንድ ነገር ለመጻፍ አትሞክሪም? ” አላት በድንገት፣ በእንዲ መንፈሷን የለወጣትን ነገር እያሰበ።

“ታላት የሉኝም። የምፅፈው ነገር የለኝም” አለችው በድንገት ተቆጥታ።

“ ሳትሞክሪ?”

“ምን መሞከር ያስፈልጋል? የሌለን ነገር ተወለድ ቢሉት ከየት ይመጣል ። ፍላጐት ሌላ ፡ ተሰጥኦ ሌላ ።”

አስተውሎ ካያት በኋላ “ ተሰጥዎ የሚዳብረው ፍላጐት ሲኖር ነው። ያለዛ መክኖ ይቀራል። ፍላጐትሽ ንሮ ተሰጥዎሽን ካልኮረኮረው መኖሩ ሳይታወቅ ተዳፍኖ ሊቀር ይችላል።”

አትኩራ አየችው። ለኪነጥበብ ያለውን ስሜትም ሆነ ዝንባሌ እስከዛሬ አለማጤኗ ደነቃት። “ አነጋገርህ የኪነጥበብ ሰው ያስመስል ሃል” አለችው። ከግማሽ አመት በላይ የምታውቀውን ሲራክን እንደአዲስ እየተመለከተችው።

“ ሳይሆን ፡ ለሙያውና ሙያው ላፈራቻቸው ሰዎች አድናቆት አለኝ። በስሯ ለመሰለፍ ግን እኔ እንደሚሉት ደመበራድ አይነት ነኝ። ሙያዋ የምትጠይቀውን ሁሉ የማሟላት ሃይል እንደሌለኝ አውቃለሁ። ህመሟ ህመሟ፡ ስቃይዋ ስቃዬ እንዲሆን የምፈልግ፡ መክራዋ የሚሰማኝ ዓይነት አይደለሁም። ያም ቢሆን፡ ግን ለሙያው አድናቆት እንዳይኖረኝ አላደረገኝም ። ተግባባን?” አላትና ፈገግ አለ ። ጉንጩን ሳመችው….. ።

* * *

“ዛሬ እንዲሁ ደስ ደስ ይለኛል” አለችው አዙብ ከጎኑ በጀርባዋ ተኝታ ኮርኒስ ኮርኒስ እያየች።

“ጥሩ ስሜት ነው፡ ምክንያቱ ግን ምን ይሆን?” አላት ሲራክ ባንተራሳት ክንዱ እያቀፋት፡ ላሰናዳው ጥያቄ ደስተኛነቷ አመቺ ስለመሰ ለው የሚያነሳበትን አጋጣሚ እየፈለገ።

“እንጃ… ለኔም አልገባኝም። ብቻ ቅድም ያሳደርክብኝ ስሜት ሳይሆን አይቀርም። ባሳሰብነው አጋጣሚ የሕይወት ጥሪያችንን እናውቃ ለን። ያልጠረጠርነው ሰው የኔንታችንን አስኳል ቅርፊቱን ሰብሮ የሕይ ወት ጐዳናችንን ይፈጠርቅልናል። ታመምሽ ካሏልክኝ ቀለም ቀለም ይሸተኛል። ቃላት ግን አይታየኝም…ሲገርም” አለች በመነባነብ ንግ ግሯ።

በውስጧ የተቀጣጠለው ስሜት በአንድ በኩል ሲያስደስታት በሌላው ወገን ደግሞ ስሜት ብቻ ሆኖ እንዳይቀር እየሰጋች ቁጥብነቷን

Scanned with CamScanner

መረጠች። ስለ ስሜቷ ብዙ ብታወራ በወደደች ግን አስፈራት። እውነት ይሆን ወጥንስ በስሜት ብቻ ይቀራልን… 'እይታዋን ወደ ኮርኒሱ አደረገች፣ ጥንት ነው ይሏታል በታሪክ ስትማር፣ ድሮ ድሮ…ግሪክ የሥልጣኔ ቁንጮ በነበረችበት ዘመን። እነ ሆሜር የሰገዱላት ጣኦት፣ የኪነ ጥበብ ሰዎች የተማጠኗት አምላክ፣ ለነሱ ብቻ የተፈጠረች…ጥንት ነው፣ ዘመነ ግሪክ በታላቋ አቴና ምድር ኪነጥበባት ተዳምረው የሰገዱላት፣ ሰዓሊያን በብሩሻቸው ያመለኩባት፣ ደራሲያን በብዕራቸው የተማለዷት፣ ከያኔው ያዜመባት ያቺ ጣኦት… አሪስቶፋኔስን ያማለደች፣ ….ፒን ዳርን ያዕናናች፣ የኪነጥበባት ጣኦት አምላክ… ኢፖሎን ፍለጋ ወደ ጣራው አቀናች… ቢሳካላት ብላ… ምንም የለም፣ የኦሊምፖስን ተራራ በአይነ ህሊናዋ ቃኘች— የጣኦት አምላኮችን ማደሪያ…በኮርኒሱ ላይ ብዙ ሀብረ ቀለሞች ታዩዋት።

* * *

"ሺት!" አለ ሲራክ መሪውን በቡጢ እየነረተ፣ ቴዎድሮስ አደባባይን በከፍተኛ ፍጥነት አሽከርክሮ ወደ ቤቱ ነጐደ። አዜብ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ በድንገት ከአልጋው ተነስታ "እቤት ካላደረስከኝ" ብላ ወጥራ ያዘችው፣ ይሄው ነች። ቀድሞውኑ እሱ ጋ ለማደር ውጥን ባይኖራትም ያን ያክል አምሽታ ሳታድር የምትሄድ አልመሰለውም ነበር። "ለምን አታድሪም?" አልመለሰችለትም። ልብሷን ብቻ ትለባበሳለች፣ እየተነጫነጨ ካልጋው ተነሳ።

መኪና ውስጥ ከገባች ጀምሮ አልተነጋገሩም። እሱ ጋ እንደምታድር ገምቶ ስለነበር፣ የጋብቻውን ጥያቄ አዘግይቶት ነበር። የአሁን ሁናቴዋ ግን አቅዱን እንክትክቱን አወጣበት። ቢሆንም ሳይጠይቃት ወደ ቤቱ ሊመለስ አልፈገም። ከመኪና ከመውረዷ በፊት ጥያቄውን አቀረበላት። ተደነቀች፣ ያልጠበቀችው ጥያቄ፣ ትክ ብላ ለተወሰነ ደቂቃ አየችው። እሱም ግራ ገብቶት ተጨነቀ።

"አላሰክኩበትም" አለችው ኮስተር ብላ። ምን እንዳስቆጣት ገርሞት— "እንድታስቢበት'ኮ ነው" አላት ፊቱን ቀጭም አድርጎ ይውጣላት በሚል ስሜቱ።

"ላስብበት አልፈልግም"ኝ እያለች በሩን ከፍታ የጠየቃትን ጥያቄ ላለግሰብ፣ እየተጣደፈች ሄደች። ድቅድቅ ጨለማ ውጦ እስከሚያስቀራት ድረስ ፈዞ ተመለከታት። ደግሞ መለስ ብሎ ሰአቱን አየ። ለሰአት አላፊ የቀረው አምስት ደቂቃ ብቻ ነው።

'የበለጨት ስንት ሞልተው' አለ በሃሳቡ፣ ቤቱ ገብቶ አብረው ያጎደቱትን ውስኪ በመለኪያ ቀድቶ ከጨለጠ በኋላ። በሃሳቡ የተንኳኩበትን ቃላት አምኖ አልተቀበላቸውም። ደግሞም "በዛ" አለ፣ ድንገት በመግደርደሯ። የሴትነት ወጉ ሆኖ ነው እንዳይል አዜብን ያውቃታል። ንግግሯ ግልፅና ፊት ለፊት ነው። የመሰላትን ከቀማድረግ ወደኋላ አትልም። ከሷ ያቆራኘውን ቀን አሰበ። ሊረግመው ግን አልፈለገም።

የሰርግ ግብዣ ላይ ነው። ለብቻዋ ቆማለች። በብቸኝነቷ የተከፋች አትመስልም። ብዙ ጠጥታለች። ቢሆንም ታዛቢ እንጂ እንደ ተጋባዥ አልሆነችም። አሻግራ ሙሽሮቹን ታያለች። ግን ጭራሽ አላስተዋለቻቸውም። ብቻ አይኗ እነሱን የሚያይ ይመስላል።

"ይቅርታ!" አላት ሲራክ ከጐኗ መጥቶ፣ ደህና አድርጋ አየችው። ግራ እንደገባት ያስታውቅባታል። ከዚህ ቀደም አንድ ቦታ እንደሚያውቃት፣ ግን የት እንደተዋወቁ እንደጠፋበት ይገልፅላታል። ትውውቃቸውን በማስታወሱ ልትረዳው አልቻለችም። መሥሪያ ቤቷን ጠየቃት፣ ነገረችው። እዛም አይደለም። የተማረችበትን ት/ቤት ጠየቀ። ከነዝመኑ ነገረችው

"አይ ሲ!" አለ ስፍራውን አስታውሶ። አዎ ያኔም ያስተዋላት በብቸኝነቷ ነው፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ። እርሱ አንድ አመት ይቀድማታል። ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሶስት አመታት አብረው ተምረዋል።

የተመረቀችበትን ዘርፍ ጠየቃት። ነገረችው። የሱንም ነገራት። በኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት፣ ከዚያም የውጭ ትምህርት እድል አግኝቶ በዛው ዘርፍ የማስትሬት ዲግሪ መቀበሉን ገለፀላት። በአጋጣሚው የቆየውንና አቧራ የሸፈነውን ትዝታ እያራገፈ ያጫውታት ገባ። በአራት አመት ውስጥ ብዙ ትዝታዎች ይኖራሉ። ስለተማሪው ስለ መምህራኑ ብዙ የሚያስቁ ነገሮች አጫወታት። ከዛም በውጭ ሀገር ስላጋጠመው ሁኔታ አወጋት።

"ያልጠበኩት ጥሩ ጊዜ አሳለፍኩ" አላት በምስጋና አስተያየት እየተመለከታት፣ የኮክቴሉ ግብዣ ወደመገባደዱ ነው፣ ሙሽሮች ተነስተዋል።

Scanned with CamScanner

“በጣም አመሰግናለሁ። እኔም ጥሩ ጊዜ አሳለፍኩ” አለችው በወዳጅነት አይን እያየችው።

መኪና አለመያዟን ስላወቀ፡እንዲሸኛት ጠየቃት። አላቅማማችም። መኖሪያ ቤቷ አደረሳት።

እንደትውውቃቸው እንዲሁ መለያየቱ ቀላል አልሆነለትም። በጭራሽ ሊያስበውም አልፈልግም። አንዳንድ ጊዜ ማንም ሊቀርባት ባልቻለበት ጊዜ ውስጧን ጠልቆ የተረዳና የራሱን ያህል ያወቃት ይመስለዋል። ግልጥልጥ ያለች ፍጥረት ትሆንበታለች። ግን ይህ ስሜቱ አይዘልቅም፣ ጭራሽ የሚያውቃት ሆና አትታየውም። ድፍን ያለች ፍጥረት ትሆንበታለች። ይሄን ጊዜ ይጨነቃል። ድሮ ተማሪ እያለና ስራ ከያዘ በኋላ፡ በሴቶች ላይ የነበረውን ትምክህት እያስታወሰ ራሱን ሊያፅናና ይሞክራል። ለዛሬው አሱነቱ ግን አጋዥ ሆነው አልተጋፈጡለትም። ሳይወድ በግድ ስለሷ እንዲያስብ ያደርገዋል። እሷ ደግሞ ይሄው ነች። ለሱ ደንታ ያላት አይመስለውም። ቀዝቃዛ ነች፣ ግን ቅዝቃዜዋ ደግሞ በርትቶ የሚያቃጥል ስሜት አለው። ለሱ ከሷ የበለጠ ሰው ያልተፈጠረለት ያክል እስኪሰማው ድረስ።

“ኤጭ!” አለ፣ የያዘውን መለኪያ የቡፌ ጠረጴዛ ላይ እየወረወረ። መለኪያዋ ተሽ አለች። አላስደነገጠውም። እንዳውም ስትሰበር የተሰማው ድምፅ እፎይታ ሰጠው። መንፈሱን ጨምድዶ የያዘው ነገር አብሮ ተሽ ያለለት ያክል ሰውነቱ ተወራጨ። ከሃሳቡ የቀሰቀሰው የስልኩ ጩኸት ነው። በዚህ ሰአት ማን ሊደውልለት እንደሚችል እያሰበ በሁለተኛው ጥሪ አነሳ። አዜብ ነች። “ምነው ደህና?” አላት የደወለችበትን ምክንያት ለመረዳት ቸኩሎ።

“ደህና መድረስህን ላረጋግ ፈልጌ ነው። ስላስቸገርኩህ ይቅርታ ልልህ እፈልጋለሁ። ቤቴ ማደር ስላለብኝ ነው እንድንሄድ ያስገደድኩህ። ነገሩን ብዙ እንድታስብበት አልፈ.ለግም። አብሬህ ማደር ጠልቼ እንዳይመስልህ፣ ነገር ግን ደስታ አጥቼ አንተንም አበሳጭቼ ላሳድርህ አልፈልግሞ። እና ቤቴ ማደር ነበረብኝ። ገባህ… እ..? ዋናው ነገር ደግሞ እላክህ ሁለተኛ የጋብቻ ጥያቄህን እንዳታነሳብኝ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም የግል ጉዳዬ ነው። ላንተ መግለፅ የሚገባኝ አይመስለኝም። ብቻ ለማንኛውም ግንኙነታችን በዚህ መንገድ እንዲቀጥል ከፈለክ፡ ብታስብበት

አይከፋም። ሳትተኛ ስላገኘሀህ እድለኛ ነኝ። መልካም እረፍት እመኝልህ ለሁ።… ቻዎ! ደህና እደር!” አልጠበቀችውም። ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋችበት። መነጋገሪያውን በእጁ እንደጨበጠ እየተገረመ አሰባት። ቃላቱ ሃይለቃል የላቸውም። ለማግባባትም አይሞክሩም። እንደሷው ቀዝቃዞች ናቸው። የገረመው ግን እሱም ጠንከሮ ሊናገራት አለመድፈሩ ነው። ቅዝቃዜዋ የተጋባበት መስሎት ፈራ። አሁንም “ሺት!… አለና መነጋገሪያውን ወርውሮ ጠረቀመው። አልጠቀመውም፣ ሄዶ የመኝታ ቤቱን በር በኃይል አስጮኸው። ቤቱ የፈረሰ እስኪመስል ድረስ ተነቃነቀ።

የቤት ሰራተኛዋ አስካለ ከሰመመናዊው እንቅልፏ የባነነችው የሲራክ መኝታ ቤት በር ሲዘጋ ነው። የጓዳዋን ስራ አጠናቃ እቃዎቹን ሁሉ አጣጥባ የተኛችው ሲራክ አዜብን ሊያደርስ ከመውጣቱ በፊቱ ነበር። የምታድር እንጂ ከመሸ የምትሄድ አልመሰላትም። ሲራክ ሊያደር ሳት ሲነሳ ግን እሷም ከእንቅልፏ ነቃች። እነሲራክ ከወጡ በኋላ ገበየሁ የውጭውን በር ዘግቶ እየተንደረደረ ወደ አስካለ መኝታ ክፍል መጣ። ገበየሁ ከሲራክ ጋር ሁለት ዓመት አብሮ የኖረ ዘበኛ በመሆኑ፡ ከተቀጠረች ሁለት ወር ያልሞላትን አስካለን የሚመለከታት በበላይነት ስሜት ነው። አልጋዋ ላይ እንደተቀመጠች፣ አጠገቧ ሄዶ ቁጭ አለ። ትከሻዋን በጠንካራ እጁ ያዘው። አመናጨቀችው። ይህን ግድርድር አመሷን ለምዶታል። አንድ ቀን በሰላም ፍቅር ሰጥታው አታውቅም። ይህ ድርጊቷ አያስጨንቀውም። ትከሻዋን ቸብ አደረጋት ውይ!….” ብላ ካጠገቡ ፈንጠር አለች። ፊቷ መቅላት ጀምሯል። እየተጠጋት ሄደ። እየተርበተበተች ሌላ ነገር ልታወራለት ፈለገች “ይች… ይች ሴትዮ እኮ ጋሼን አሰቃየቻቸው” አለችው ልቧ ለሁለት ተከፍሎ። በአንድ በኩል ልታወራ እየፈለገች፣ በሌላ በኩል ደግሞ የገበየሁ ድሪያ እያሽኮረመማት። የሰማትም አይመስል። በአንዳች ነገር ተወጥሯል። የማታየው እሱ ከላይ እሷ ከስር ሲሆኑ ብቻ ነው። አስካለ ትንሽ ጊዜ አስቸግራ ተረታች። እንደ አሳቡ ሆነለት። “አውሪልኝ” አላት እሷ ደግሞ ትንሽ እረፍት ፈለገች።

ብዙ አላወሩም። የመኪና ሙሩምባ ድምፅ ሲሰማ ከአልጋዋ ተስፈንጥሮ ተነስቶ ሮጠ። ተሳቀቀች። በውስጧ አርግዛው ያልወጣላት የስሜት እንጥፍጣፊ ነበር። በር ከፍቶ ጌታውን አስገብቷል፣ ተመልሶ ግን አልመጣም። የፈረጠመው ገላውን እያሰበች ናወዘች። እንደሰመመን

Scanned with CamScanner

እያደረገ አሸላባት። አሁን ያስበረገጋት የበር መዘጋት ድምፅ ነበር። መኝታ ቤቷ ጋር የተያያዘ ነው። ከፍታ ገብታ መብራቱን አበራች። ጭር እንዳለ ነው። የእንግዳ መቀበያውን፣ ምግብ ቤትና ወጥ ቤቱን የሚያገናኘውን በር ከፈተች። ምግብ ቤቱ በጨለማ እንደተዋጠ ነው። መብራቶቹን አበራች። ቤቱን በአይኗ ቃኘች፣ አልተሳሳተችም። በሰመመን የሰማችው የስባሪ ድምፅ ትክክል ነበር "የለም፣ አልተኛሁም፣ እሰማ ነበር።" አለችና ሁኔታውን ለራሷ አረጋገጠች። ስባሪውን ሰብስባ ስታነሳ እንደኛው ስባሪ ጣቷን ዘልቆ ገባ።

ሲራክ በር ሲክፈትና ሰው ሲገባ የሰማውን ድምፅ በፀጥታ ይከታተላል። ክአልጋው አስፈንጥሮ ያስነሳው ጩኸቷ ነው። የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ ሲወጣ፣ ደም የሚፈሰውን እጇን ይዛ ስትንዘፈዘፍ ተመለከታት። አይኖቿ ተጎልተው ወጥተዋል። ያለዛፉ የጣቶቿን ውበት አስተውሎ አያውቅም። ምንጊዜም ቢሆን ሴት ሠራተኞቹን በሙሉ ዓይኑ አይቷቸው አያውቅም። ይህ የራሱ ጥብቅ ዲስፕሊን ነበር።

ውስኪ ውስኪ በሚጋረፈው ትንፋሹ እንድትከተለው ተናገራት። ከመኝታ ቤቱ ቁምሳጥን ውስጥ አልኮልና ጥጥ አውጥቶ ደሟን ይጠራርግላት ጀመር። የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ሊያደርግላት እጇን ከያዘው ጀምሮ ነው 'ምናለበት'ን አዕምሮው ያረገዘው። ሕክምናውን እስኪጨርስ ከሀሊና ሙግቱ አልተገታም። ስሜቱ ሰብአዊነትን ከለላ አድርጎ እኩልነትን፣ የሰው ልጅ እንድነትን ተንተርሶ፣ በምናለበት ጦር ሀሊናውን ከተጫነ በኋላ ወደ አልጋው ወሰዳት።

ለገበየሁ የምታሳየው አመል ከሲራክ ጋር ሆና አልለቀቃትም። በግድርድርነቷ ተፈታተነችው — እስኪቻላት፣ ገፍትሮ ባለ ስፕሪንግ ፍራሽ ላይ ሲያነጥራት፣ ትንፏ ልቧ ዘላለም ከሱ ጋር አብራ ብትቀር ብዙ ተመኘች። የገበየሁ የበላይነት ይቀራል፣ የመጀመሪያ ተግባሯ የሚሆነው እሱን ከቤት ማባረር ነው። ያለዛ ይህ ልክስክስ አመሉን አይተውም። ጌታዋን ልታስደስት ቆረጠች፣ በአልጋው ላይ እንደሚፈልገው ልትሆን ለት።

ወደመኝታዋ እንድትሄድ ሲነግራት በልቡ አንድ ነገር ወስኖ ነበር። ዳግም በቤቱ ላያት። በውሳኔው ፀና።

ግታ ሲሟገቱለት የነበሩት የስሜቱ ሽፋኖች፣ የልቦናው ሲደርስ ለሀሊናው አጋልጠውት ዞር አሉ። ጥዋት የመኪናውን ሞተር እያሞቀ

ገበየሁን ጠራው። ከወር ደሞዟ ላይ አስራ አምስት ብር ጨምሮ እንዲሰጣትና ግታ ሲመጣ ሊያያት እንደማይፈልግ ገልያለት አባሯት እንዲቆየው አዘዘ። ገበየሁ ደንግጦ በእሺታ ትእዛዙን ተቀበለ። ድንጋጤውን እንዲያውቅበት አልፈለገም።

ከጌታዋ ምን እንዳጣላት ብቻ ነበር የጠየቃት። አስካለም የመሄጂን ቁርጥ ስታውቅ ሌሊት መኝታ ክፍሏ ድረስ መጥተው ልድፈርሽ እንዳሏትና እምቢ እንዳለች ነገረችው። ገበየሁ ባያምናትም ያዘነ መሰለ። ደሞዟን ሰጥቶ አሰናበታት። ከአስራ አምስት ብሩ ላይ የራሱ አስመስሎ አምስት ብር ጨመረላት። ውለታውን በከንፈሯ መለሰችለት። እየመጣች ልትጠይቀው ቃል ገብታ።

ገበየሁ የውጭውን በር ከዘጋ በኋላ ፈገግ አለ። "የምትቀጥለው ደግሞ ምን አይነት ትሆን?" ብሎ ወደ ስራው አቀና።

ሲራክ ብቻ ቀኑን እንደረገመ ዋለ። አዘነ፣ ደግሞ አስካለን፣ ይበልጥ ደግሞ ራሱን… "እንዳንዴ እንዲሁ ነች?" አለ ሲራክ ሕይወትን እያሰበ።

ምእራፍ አምስት

አዲስ አበባ ከዳር—ዳር አኩርፋለች። እንደወትሮ በጥዋት ከወደም ሥራቅ ብቅ የምትለው ፀሀይ ዛሬ በዳመና ተጋርዳ፣ ብርሃን አልባ ድምቀቷን ንጋትን አብስሯል። የወፎቹ ድምፅ ጎልቶ ስለማይሰማ ያኮረፉ ቢመስሉም፣ የንጋት ብስራት ዜማቸውን አላቋረጡም። የመንደሩ ውሾች ጭራቸውን በየጉያቸው ሸጉጠው ያላዝናሉ። የከተማው ነዋሪዎች የፀሀይዋ ኩርፊያ ተጋብቶባቸው በያሉበት ያዛጋሉ። ደብቷቸዋል።

ሙቀቱ አጓጉቶት ከብርድ ልብሱ ለመውጣት የጨነቀው ሽፈራው፣ በብርድ ልብሱ እንደተሸፋፈነ ሶስት ጊዜ አዛጋ። ግታ ቦሰና ቤት የጨለጠው አልኮል ጡንቻዎቹን አኮማትሯቸዋል። እዚያው እንደተኛ እግሮቹንና እጆቹን ዘረጋግቶ ወጣጠራቸው — ተንቋቁ።

መልሶ ሰበሰባቸው።

ሕይወት እጅ እጅ ብላዋለች። ብርድ ልብሱን በፊቱ ላይ ገልጠ በመስኮትና በበር እያሸለቀ በሚገባው ብርሃን ጠባብ ክፍሉን ለመቃኘት

Scanned with CamScanner

ሞከረ። የቆሸሹ ካልሲዎቹ ሲሚንቶ ላይ ተዝረክርከዋል። ያልታጠቡ ብርጭቆዎችና ሲኒዎች በሩ ጥግ ተቀምጠዋል። ማንቆርቆሪያው ክፍቱን በጎኑ ተጋድሟል። የሰሞኑ ጋዜጣዎች በአልጋው ፊት ለፊት ያለ ትንሽ ጠረጴዛ ላይ ተመሰቃቅለው ተቀምጠዋል። ሥርዓት የያዘ ነገር የለም። የወንደላጤ ኑሮው ከእሬት መርሮ ተሰማው። ብቻውን ደክሞ የሚኖርበት፣ ለዛውም ልፋቱና ድካሙ ሁሉ ለአንድ ነፍሱ ሆኖ፣ ደስታን ሊሸምት፣ እርካታን ሊጎናፀፍ፣ አለመቻሉ ሌላ ችግር ሆነበት። ዘለዓለም የሆቴል ቤት ምግብ ቀላውጦ እንደፍላጎቱ ሳይሆንለት፣ ከሆቴል ቤት ዶሮ የሰው ቤት ሽሮ እያስመረጠው፣ ከቡና አትም እንኳን እራት ራት ከሚል የቡና ቤት ቡና በመንደር ሲያልፍ የሚሸተው የሚቆላ ቡና ምራት እያስዋጠው፣ ነጋ ብቻውን፣ መሸ ብቻውን፣ ታዲያ ለምን ሕይወት እጅ እጅ አትለው?

ሕይወት ትርጉም እጥታለች።

በአልጋው ላይ ሆኖ ይፈላሰፋል። ‘‘መኖር ምንድነው? የሰው ልጅ የመኖር ፍላጎት መነሻው ምን ይሆን? እንዲሁ ኖሮ ለመሞት? የለም መሆን የለበትም። እያንዳንዳችን ልንኖርለት የሚገባ ነገር መኖር አለበት።

ተብሎ ተብሎ ያበቃላት ጉዳይ ይመስለዋል። ሰለችው። ‘እና ለምንድነው የምኖረው?

ምንም።

ሌላው ቀርቶ ሊኖርላቸው የሚገባ ቤተሰብ እንኬን የለውም። ቤተሰብ እንኳን ለመኖር ምክንያት ይሆናል። ለምን እንደሚኖር ቢጠየቅ፣ ለሚስቱ፣ ለልጆቼ፣ ለቤተሰቦቼ ይላል። የቤተሰብ ትርጉም ቀላል አይደለም። ለምን እንደምንኖር፣ ለምንስ መኖር እንደምንፈልግ ትርጉም ይሰጣል። ምክንያታዊ ነው።

ሽፈራው እናት አባቱን ለመጦር እንኳን አልታደለም ። ልጅ ሆኖ እንዲማውታን ሲጠሩት ሽፈራው እንዳለ ይሉታል ። እንዳለ በስም ብቻ የሚያውቀው አባቱ ነው ። ቀይ ይሁን ጥቁር ፣ አጭር ይሁን ረጅም ፣ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም ። የእንዲማውታኑ የጥንት ዘበኛ እንዲት ሴትዮ አምጥተው በድርጅቱ እንዲያድግ ሲሰጡት ፣ ‘ልጂ አይደል ወገኔ ፣ ስለነፍስ ብዬ እንጂ’ ማለታቸውን ነግረውታል ። ታዲያ የአባቱን ስም

ያሳደገው ድርጅት ወይንም ሴትዮዋ ያውጡለት የሚያውቀው ነገር የለም ። ለማወቅ እምብዛም አልተጨነቀም ። ብቻ ያለ እና ያለአባት የተፈጠረ ይመስል ወላጆቹን የመጦር ማእረጉ ቀርቶበት ‘ነበሩ’ ለማለት እንኳን ምንም አለማወቁ ይከነክነዋል ። አንዳንድ ጊዜ ስለወላጆቹ ባሰበ ቁጥር በውስጡ ጥላቻ ያቆጠቁጣል ። በማያውቃቸው ወላጆቹ ላይ ጨነኝ አመለካከት የለውም ። ያም ሆነ ይህ የአባቱ ይሁን አይሁን በማያውቀው ስም እየተጠራ ለዚህ በቅቷል ። ለዛውስ ወልዶ በጣለ አባት ስም መጠራት ምን ያስደስታል ! አንዳንዴ ሲያስበው አባቱን ባለማወቁ ደስ ይሰኛል ። ማማሾቹ ‘ትግራ ትመስላለህ ይሉታል ፡ የለም ጉራጌ ነህ’ የሚሉትም አሉ ። ይህ ለሱ ጭንቁ አይደለም ። ኢትዮጵያዊ መሆኑን ማወቁ ብቻ በቂ ነው ። በእንለማውታን ማሳደጊያ ድርጅት ውስጥ እያለ በችግርና በተለያዩ ምክንያቶች ልጆቻቸውን ለማሳደግ አቅም ያጡ ቤተሰቦች ፡ በጤንነትና በእንክብካቤ እንዲያድጉላቸው ለድርጅት ሰጥተው በየበዓላቱና በየሰንበቱ ብቅ ሲሉ ፡ የቤተሰቡን ጣዕምና ፍቅር በመጠኑ አስገንዝበውታል ። ይህም ብቻ አይደለም ፡ ቅናትና ከፍተኛ የቤተሰብ ፍቅር ስለጠነሰሰበት ይህንንም ሊያገኘው ባለመቻሉ ተነጫንጮ ፡ እብሪተኛና ተደባዳቢ ሆኖ ነበር ። ቀስ በቀስ እየጎረመሰ ሲሄድ ፡ ራሱን እየገዛና ከአካባቢው እየተገለለ ብቸኝነትን መረጠ ። ብዙ አልቆየም ፡

ንግድ ስራ መለስተኛ ኮሌጅ የሚያስገባ ውጤት አግኝቶ ስራ ያዘ— ራሱንም ቻለ ።

ችግሩ ተንጠራርቶ የጨበጣቸው የኑሮ እርከኖች መና እና ትርጉም የለሽ እየሆኑበት መምጣታቸው ነው ።

መኖር ፡ ራስ መቻል ፡ ለራስ መሆን ብቻ ሲመስለው ቆይቶ ፡ ራሱን ከቻለ በኋላ ግን የመኖር ትክክለኛ ፍቺ ይህ አለመሆኑን ተረዳ ።

የሰው ፍላጎት መጨረሻ የለውም ። ፍላጎትና የመኖር ትርጉም አንድ አልሆነለትም ። ‘ሰው ኖርኩ የሚለው ወይንም እየኖርኩ ነው የሚለው መቼ ነው ?’ — መልስ የሌለውም ጥያቄ ሆነበት ።

‘ሰው ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፡ ሲሰራና ፡ መኖር ሲችል … ይሆን ኖርኩ የሚለው ?’ አጥጋቢ አልሆነለትም ። ይህንን ሁሉ የማያደርግ ግን በሕይወት እያለ በፈፀመው ተግባሩ ህያው ሆኖ ለዘለዓለም የሚኖር ሰው አለ አይደለ ?

Scanned with CamScanner

'ታዲያ ይህችን አለም የሚኖሩባት ጀብደኞች ብቻ ናቸው ማለት ነው?'

ለራስ ብቻ ሳይሆን ስለሌላው ሲኖሩ ነው የመኖር ትርጉሙ የሚታወቀው ።

በሁለት ከተሞች ወግ ውስጥ የቻርልስ ዲክንስ የህልውና ትርጉም ትዝ አለው ። ሲድኒ ካርተር ያጣጣመው ኑሮ ።

'ታዲያ ለማን ስል እኖራለሁ? ከቤተሰብ ቤተሰብ ፣ ከዘመድ ዘመድ የለኝ ፣ እንደጠመለ አንድ ሆኜ የቀረሁ !'

የጊዜው መርፌድ ከአልጋ አፈናጥሮ አስነሳው ። ደመናው ብሶበት ካፊያ ጀምሯል ። ቢሮ እንደምንም ብሎ መድረሱ ራሱን የቻለ ጣጣ ሆነበት ።

ከግማሽ ሰአት በኋላ ቤቱን ጠርቅሞ ወደ መስሪያ ቤቱ ነጎደ ።

ጥቁሩ ጀበና በስተቀኝ ፣ ሲኒዎች ደግሞ ከግንደጀው ፊት ለፊት በረከቦት ተቀምጠው አጠገቡ ያለው መሶበወርቅም የፈካ የግሽላ ቆሎ ይዟል ። ቁጢማው ፣ ሳሩ ፣ ጠጅ ሳሩም ፣ ተደበላልቆ ተንዠርዟል ። ደመቀች ተስተካክሎ የተቆላውን ቡና አወጣችና ረጠብ ባለ ሳህን ገልብጣ ቡናው መንጠሽጠሽ ሲጀምር ወይዘሮ ቦሰና እንዲሸታቸው ሳህኑን ነቀነቀችው ። እጃቸውን እያራገቡ ያጉተመትሙ ጀመር ። ገበያ እንዲደራላቸው ፣ እንዲከብሩ ፣ እንዲከበሩ ··· የልጅ ነገር እንኳን ተስፋ ቆርጠዋል ። ከወንድ ወንድ አማርጠው አልሆን ያላቸው ነገር ነው ። ከጠንቋይ እስከ ሀገር መድሐኒት አዋቂ ፣ ከቤተክርስቲያን ታቦት ምልጃ አለ እስከተባለ ጠበል ያልደረሱባቸው አድባራትና ገዳማት ውሱን ናቸው ።

ዘመናዊው ሀኪም ቤት ጥንት ተስፋ አስቆርጧቸዋል ። በእፍላ ዘመናቸው በተጠናወታቸው ደዌ ሳቢያ የልጅ ጉጉት ናፍቆት ከግማሽ እድሜ በላይ አስግሰናቸው ። ገንዘባቸውን አስበተናቸው ። የጥንቷ የውቤ በረሃዋ ቦሰና ፣ ኋላም የካዛንቺስ በተባለለት ዝናቸው የት እንደሚደርሱ ሲጠብቁ እንደተባለው ሳይሆን ቁራ መንገድ ላይ በማተራ እካባቢ እንዲት ቤት ይዘው አልኮል እየቸረቸሩ መኖር ከጀመሩ ሰባት ከረምት አሳልፈ ዋል ። ስምንተኛው ከረምት 'መጣሁብሽ' እያላቸው ነው ።

ቤቷቿው በፀጥታው የተወደደ ነው ። ሙዚቃ የለውም ፣ ጫጫታም አይበዛም ። እንዳንዴ ብቅ እልም ከሚሉ አዝማሪዎች በቀር በፀጥታው የታወቀ ነው ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንዲት ነጥብ ቢገኝ እቀጣለሁ እያሰኝ ሰውን የሚያወራርደው የፈታቸው ጥራት ማዲያት እያበለዘው ሄዷል። እሳቸው በሚሉት ሳይሆን ከትክክለኛ እድሜያቸው አንፃር ሲታይ ግን ደህና ነው ። እንደብዙዎቹ የቡና ቤት ባለቤቶች የሚናገሩት እድሜያቸውና የሰውነት አቋማቸው ተራርቆ ወ/ሮ ቦሰናን አላላጣቸ ውም።

የተወቀጠውን ቡና ደመቀች ከሙቀጫው ካወጣች በኋላ ወደ ጀበናው መጨመር እንደጀመረች በሩን ትልቅ ጥላ ጋረደው ።

"እቤት ! እቤት ! ··· እዮሱ ላይ ደረስኩ" አለ ሽፈራው ቡናውን ፡ ደመቀችና ባንኮኒው አጠገብ የተኮፈሱትን ባለቤቷን እየተመለከተ ።

"እንተኮ ገዴ ነህ" አሉት ወ/ሮ ቦሰና ፈገግታ ፊታቸውን እያጥለቀ ለቀው ። ደመቀች በፀጥታ ጀበናዋን ትመለከታለች ። ሰላምታ አልሰጠች ውም ። እንድ ቀን አብሯት አድሮ ገንዘብ ስለከለከላት ብታየውም ገላምጣው ነው ፡ እሱም ሲያያት ይስቃል ። አልታሻ ብጤ ነች ። ስትተኛ ፈርታ ፡ ሲገናኙት ደግሞ አልቅሳ ነው ። ለሁለቱም ያልደበዘዘ ትውስታ ። እሱን ሲያስፈግግ ፡ እፂን አኮሳትሯል ።

"ቦሴ ባሬ ቤትሽ ቀዘቀዘ ምነው ?" አላቸው ። አንቱ የሚሏቸውን የቡና ቤት ደንበኞቻቸውን እያኮረፉ አንቺ ማለት አስተምረዋቸዋል ።

"ቦሴ የሰቆጣዎ ! የሚቀዘቅዝ የፅ ቤት ነው ?" አሉና ግድግዳውን እሻግረው በተመስጦ እየተመለከቱ "··· አንተ የት ታውቅና ፡ ገዳም ሰፈር ብትሄድ ወይም ካዛንቺስ ··· እንደው ምን አለፋህ 'የቦሴ ቤት የቱ ነው ?' እየተባለ ፡ 'ቦሴ የት ቤት ነው ያለችው ?' እያሰኘው ድፍን ካዛንቺስንና ገዳም ሰፈርን ያንጫጫው ሴት ነበርኩ ። ባራም ምን ጠፍቶ ? ···" አሉ ። የተላላጠውን ግርግዳ ሲመለከቱ እርጅናቸው እንዳይታወሳቸው ፡ ፊታቸ ውን ወደ ሽፈራው እየመለሱ "··· ባሬስ ቢሆን እናንተ እናንተ ኑሩልኝ እንጂ ቤቱ ደማቅ ነው ። ግንባሬ ሰው ያቀርባል ። 'ደግሽን እንጂ ክፉሽን' የሚለኝ የለም ። ተመስገን ! ···" አሉ ጣራውን እየተመለከቱ ። ኮርኒሱ ተሸርጎርጉሯል ። ማየት የማይፈልጉት ስለነበር እይታቸውን ከሰቀሉበት ጣራ ላይ በፍጥነት ዘወር አደረጉ ።

ሽፈራው የለመደውን ቀዝቃዛ ቢራ ይዞ ወደ መቀመጫዎቹ አመራ ። ደመቀች እንዳኮረፈች ናት ። ሁለት ሰዎች ተከታትለው ገቡ ። ጫማቸው የፈጠረው የጣውላ ሲጥሲጥታ ለጆሮ ይቀፋል ። ሽፈራው

Scanned with CamScanner

ፊቱን ጨመደደ ፡ አንደኛው ለፍላፊ ቢጤ ነው ። ያገኘውን ሰው ሁሉ ሰላም ማለት ይወዳል ። ሲናገር ሾክክ ካላለ አይሆንለትም ። ሲያወራ ወደ ጆሮ መጠጋት ይወዳል ። ከሽፈራው ጋር በዚሁ መጠጥ ቤት ነው የሚተዋወቁት ፡ የወ/ሮ ቦሰና የቆየ ደንበኛ ነው ። በሳቸው በብዛት ይታማል ። እንዳውም ብሞት ወራሼ እሱ ነው ብለዋል እየተባለ በሰፈው ይነገርለታል ። አብሮት ያለው ገራገርና ዝምተኛ ቢጤ ነው ። በጣም አስፈላጊ ካልመሰለው አያወራም ። ወሬው የተወሰነና ቁጥብ ነው ። ሽፈራው ሁሉ የሚደነቀው በሁለቱ ጓደኛነት ነው ። ምንጊዜም አይለያዩም ። ሊጠጡ የሚመጡትም ሆነ ጠጥተው የሚሄዱት አንድ ላይ ነው ። አንደኛው አፍ ፡ ሌላኛው ጆሮ ናቸው ። ሁለቱም የለመዷትን ጂን ይዘው ባንኮኒው አጠገብ ተኮፈሱ ። ደጀኔ ያወራል ፡ ሙሉጌታ ያዳምጣል ።...

ሽፈራው ሁለተኛውን ቢራ አገባዶ ሦስተኛውን ጀምሯል ። ደመቀችም ቡናዋን አክትማ ተነስታለች ። የወ/ሮ ቦሰና ቡና ቤት ደመቅመቅ ማለት ጀምሯል ። ደንበኞቻቸው ከያሉበት እየተጠረቃቀሙ ነው ። እንደወትሮ ድምፁን አጥፍቶ ገብቶ ጠጥቶ የሚወጣው ሰዩም ፡ ከበሩ ጓላ ተቀምጧል ። ከአንገት ሰላምታ በስተቀር ከማናቸውም ጋር ንግግር የለውም ። የሚገርመው ግን ወ/ሮ ቦሰና ቤት ሴት ከገባች የሚቀድመው አለመገኘቱ ነው ። ስራው አይታወቅም ። ማማሹ ደላላ ፡ ሌላው ደግሞ የመንግሥት ሠራተኛ ነው ይሰዋል ። ግን እንኳን የሚሰራበትን መኖሪያ ቤቱን አረጋግጠ የሚናገር ሰው አይገኝም ። ዘወትር የሚጠጣት የተወሰነች ነች ። ይህች መጠጡ ሁሌም ወ/ሮ ቦሰናን ታስደንቃቸዋለች ። በምንም አይነት የሰው ግብግ አይቀበልም ። ሰው ሲጋብዝ ታይቶ አይታወቅም ። በዚህም በዛም ቤቷ ደንበኞቿን አሰባስባ ለች ።

“ክንፈ ! ...” አለ ሽፈራው ከበሩ አጠገብ ቆሞ እንዳየው ። “ከወዴት ብቅ አልክ ባክህ ?” እያለ አቀፈው ። አመጣጡ ሽፈራውን አስደንቆታል ። ክንፈ ትዳር ከያዘ በኋላ የቤቱን ደንበኝነትን እርግፍ አድርጎ ትቶታል ። “ካለሁበት” አለ ለሰላምታው አፀፋ እየመለሰ ።

“አይኔ ሲርገበገብ የዋለው አንተን ሊያሳየኝ ነው ?” አሉ ወ/ሮ ቦሰና ወንበራቸው ላይ ሆነው እየተቅበጠበጡ ።”

“ተስማምቶህ ነው ለካ የጠፋኸው ?” አሉት ሄዶ እንደጨበጣቸው ቁመናውን እየገመገሙ ።

ሽፈራው ዝም ብሎ አስተዋለው የጥንት ወዳጁን ። ትዳር ከመሠረተ በኋላ አግኝቶት አያውቅም ። የዛሬን አያርገውና ፡ ፊትም ሮጠ እሱ ቢሮ ይሄዳል ። ካለዚያም ከቤቱ የማይጠፋ ጓደኛው ነበር ። የወ/ሮ ቦሰናን ቤት ከጅምሯ አዳምቀው ለዚህ ያበቋት እነርሱ ናቸው ። ለውለታው ምላሽ አላጣም ። ለሰርግ ምን የመሰለ ሙክት በግ እያስጐተቱ ላይታረድ ቤቱ አልገባም ብለው ደጃፉ ላይ አሳርደው ገብተዋል ። ወ/ሮ ቦሰና ዛሬ አመጣጡ ቢያስደስታቸውም በአንድ በኩል አስገርሟቸዋል ።

ክንፈ ቢሮው ውስጥ ተቀምጦ ሲበሳጭ ነበር የዋለው ። ተላላኪው ማኪያቶና ቡና ማመላለስ እንደዛሬ ሰልችቶት አያውቅም ። በአንድ በኩል ምን ነካቸው ? እያለ ሲያወጣና ሲያወርድ ዋለ ። ሳምንቱን በሙሉ ቤቱን ታቅፎ ያመሸው ብቻውን ነው ። እፀገነት ለማምሸቷ አንድም ቀን መልስ ሰጥታው አታውቅም ። ሁለት ሶስቱን ቀናት በትእግስት አሳለፈ ። እያደር ግን ከትእግስቱ በላይ እየሆነበት ሄዶ ። በአንድ ወገን ያለመቆጣቱና አልፎም ሊመታት ያለመቃጣቱ የሚያስንቀው እየመሰለው ሊመታት ይከጅልና መልሶ ደግሞ አንድ ችግር እንዳለባት ይሰማዋል ። ለአፍታም ቢሆን በእርጋታ ሊያናግራት አልቻለም ። ያስጠላው ነገር ቢኖር ቤቱን ለብቻው ታቅፎ ማምሸቱ ነው ። ከፒያኖው ጋር ማንጎራጎሩ ሰልችቶታል ። የጥንት ወዳጆቹን ደግሞ ከትዳር በኋላ እየራቃቸው በመምጣቱ በቅርቡ ሊያገኛቸው አልቻለም ። ብቻውን መቅረቱ እንደዚህ ሳምንት ተሰምቶት አያውቅም ። የጥንት ወዳጆቹን ሲያስታውስ በመጀመሪያ ትዝ ያለው የወ/ሮ ቦሰና ቤት ነበር ። ሌላው ቢቀር “ሺፈ” ሽፈራውን እንደማያጣ ገምቷል ።

“እኔኮ ...” አሉ ወ/ሮ ቦሰና መኝታ ቤት አስገብተው ወትሮ እሳቸው ቤት የሚጠጣትን ዊስኪ እየቀዱለት ፡ “...ነገሬ መሬት ጠብ አትልም ። እንደው ቀኑን ሙሉ ማንን ሊያሳየኝ ነው ስል እስቲ ...” አሉ ክንፈን ፡ ደግሞ ሽፈራውን እየተመለከቱ ። ለጥብቅ ወዳጆቻቸው ብቻ የሚፈቅዱት መኝታ ክፍላቸው ዛሬ ለክንፈ ሲባል ተከፍቷል ። ባጋጣሚው ሽፈራውም ከክንፈ ጋር ተሰይሞበታል ። ወ/ሮ ቦሰና ሽፈራውን ከአቅኚዎቻቸው ጋር ቢደምሩትም መኝታ ክፍላቸውን አላስደፈሩትም ። ምክንያትም አላቸው ። የሽፈራውን ደፋርነት ያውቁታል ። ከሠራተኞቻ

Scanned with CamScanner

ቸው ጋር ካልጋ ለወደቀ ሰው እራሳቸውን አያስደፍሩም ። በዚህ ኩሩ ናቸው ።

"ቦሴኮ መጠጥ ቤቷን ዘግታ ብትጠነቁል ያዋጣት ነበር" አለ ሽፈራው እያሾፈባቸው ።

"እኔ ቦሴ ! ማንም አይለኝም !"

ክንፈ የጥንት ወዳጆቹን በየተራ አስተዋላቸው ፣ ብዙ ለውጥ የላቸውም ። ጨዋታቸው ፣ ለዛቸው ፣ ሁሉ ነገራቸው ፣ ያው ነው ። ሁሉም ተለዋውጦ የሚቆየው መስሎት ነበር ። ቤቱ ውስጥ አዲስ የሆነበት ነገር ቢኖር የቅጥር ሠራተኞቻቸው መለዋወጥ ብቻ ነው ። ወ/ሮ ቦሰና ወደ ቁምሳጥናቸው መስታወት ሄዱና ይሄውልህ ክንፈ አንተ ወጣት እየሆንክ ስትሄድ እኛ ደግሞ አረጀን ..." አሉና ከትከት ብለው የውሸት ሳቅ ሳቁ ። የሳቃቸው መንስኤው ትርጉም የለሽ ነበር ።

"አረ ገና ልጅ ነሽ" አላቸው ክንፈም እየሳቀ ።

"ሙች በለኝ እስቲ !"

"ቦሴ ሙች !"

ቦሰና ከዚህ ሌላ ምንም አልፈለጉም ። እየተውረገረጉና መቀመጫቸውን እየገለባበጡት "መጣሁ" ብለዋቸው ወደ ሳሎን ባንኪኒያቸው አመሩ ። ወጣት ነሽ ከመባል ፣ ልጅነታቸውን ከሚመስክርላቸው ሰው በላይ አንጀት የሚያደርስላቸው ሰው የለም ። በእጃቸው መኖሩንና መሸሹን ሳይገነዘቡት ያመለጠ ወጣትነታቸው ያሳሰባቸው ፣ በፊት "ንጪት ነው ፣" ኋላም "ከዘር ነው" እያሉ ፀጉራቸውን ቀለም መቀባት ከጀመሩበት እለት ጀምሮ ነው ።

"የቦሴ ቤት ይግደለኝ ብለሃል አይደል ?" አለ ክንፈ ወደ ጥንት ወዳጁ ሽፈራው እየተመለከተ ።

"ምን ላድርግ ? ወይእሷ አርጅታ አትሞት ፣ ያለዛም እኔ መምጣቴን አልተው ፣ ግን አንተ ምን እግር ጣለህ ?" አለው በአንክሮ እያየውና ከገፅታው አንዳንድ ነገር ለማንበብ እየሞከረ ። የተከፋበት ነገር እንዳለ እርግጠኛ ነው ።

"ለለውጥ ነው !..." አለ ክንፈ በረጅሙ ተንፍሶ "... ሕይወት ለውጥ ካልታከለባት ሀልውናህ አይታወቅም ። የህልውናህ ምልክቱ መገላበጥህ ነው ። ያለ በለዚያ ባለህበት አረህ መቅረትህ ነው ፣ እና

ባመጣጤ አትደነቅ ። ትንሽ እረፍት ፍለጋ ነው ። እረፍትን ከሰዎች በመሸሽ ለብቻዬ በመሆን የማገኛት መስሎኝ ነበር ፣ ግን ተሳስቼያለሁ ። እውነተኛው እረፍት የሚገኘው ከሰዎች መሃል ነው ።"

ሽፈራው በአንክሮ እያየው "እወነትስ ደህና ነች ?" አለው ከጋብቻቸው በኃላ ከአንድም ሁለት ሶስቱ ሄዶ ጠይቋቸዋል ።

"እሷም የራሷን እረፍት ትሻለች ። እናም ከኔ አስቀድማ ፍለጋውን ጀምራለች ።"

"የተጣላችሁ መለሰኝ " አለ ሽፈራው ጥርጣሬው ትክክል መሆኑን ገምቶ ።

"በምን አወክ ?"

"ሁኔታህ ይናገራል !"

"እንዴት ?"

ሽፈራው ትንሽ ፈገግ ብሎ የሚጠጣውን ቢራ እየተመለከተ "ይህንን ለመገመት ብዙ ማሰብ አይጠይቅም ። ቀላል ነው ፣ አንዴ ያልከኝን ታስታውሳለህ ?"

"ምን ያልኩህን ?"

"ለምን ይንበኝነትህን ከቦሰና ቤት እንዳቆምክ ስጠይቅህ የመለስክልኝን ነዋ !።"

"እንጃ !"

"ትዝ አይልህ ይሆናል ፣ ሁለት ሶስት ዓመት አልፎታል ። ያገባሃት ሰምን እዚን ለማን ትቼ ? ነበር ያልከኝ ፣ እና አሁን ለማን ተውካት ?"

"እረፍት ፍለጋ ጉዞ ጀምራለች እያልኩህ ?" አለና ውስኪውን ተጎነጨ ። የክንፈን ስሜት ፊቱ ላይ ማንበብ በጣም ያስቸግራል ።

"ተለያያችሁ ? ..." አለ ሽፈራው አይኖቹን አፍጥጦ ፣ መደንገጡ ፊቱ ላይ ያስታውቃል ።

"ሳይሻል ይቀራል !" አለ ክንፈ በሆዱ ያመቀውን ትኩስ አየር እያስወጣና በምትኩ ውስኪውን እየጨለጠበት ።

"ደስ አላልከኝም !" አለ ሽፈራው ።

ስሜቱን እንዳጋባበት የተረዳው ክንፈ ገፅታውን አስከፍቶ ጠረጴዛውን በብርጭቆ እየደበደበ "ይልቅ ሁሉን እርሳ ፣ ዛሬ ደግሞ ቢራውን ተውና ውስኪ ጠጣ ። የብዙ አመት የተጠራቀመብኝ እዳ ነው" አለ በወዳጅነት ሰሜት እየተመለከተው ።

Scanned with CamScanner

ወ/ሮ ቦሰና መጡ "ውይ ክንፍዬ ፡ ጥዬአችሁ ሟልጥ አልቡ ... ምን የዛሬ ሠራተኞች የልብ አያደርሱ ። ከስር ስራቸው ተከታትሎ እሽ ካላሏቸው የወደቀ እንኳን አያነሱም ... ጠጡ ምን ጎደለ ?" አሉ ከቆሙበት ቦታ በእጃቸው ወስኪ እንደያዙ ።

"ሙሉ ጠርሙስ የለሽም እንዴ ?" አለ ቀና ብሎ እያያቸው ።

"ሞልቶ ! ሞልቶ እንደው የኔ ነገር ! ሲሆን ሲሆን ራሴ ነበርኩ ውስኪ ማወረድ የነበረብኝ" አሉና ሳጥናቸው ውስጥ የነበረ ፡ ያልተከፈተ ውስኪ አምጥተው ጠረጴዛው ላይ አስቀመጡ ።

ለጥንት ወዳጁ ፍቅር ሲል ውስኪውን እንዲከፍት አስገደደው ። ሽፈራው በሶስት መለኪያ ለክንፈ ፡ ለወ/ሮ ቦሰናና ለራሱ ቀዳና "ቺርስ !" ተባባሉ ለክንፈ ጤንነት ። "እንደው ያንተ ነገር ደስ የሚለኝ ፡ ውቃቢዬም የሚቀርበኝ ገና ሳይህ ነው ..." ብለው ወ/ሮ ቦሰና ሙስኪ ፖቹን ተጎነጩና "መጣሁ" ብለው ወደ ባንኩኒያቸው ተመለሱ።

ክንፈ ውስኪ በማውረዱ በሙሉ ልቡ ያልተደሰተው ሽፈራው ብቻ ነው ። የወዳጅ ህመም ተሰምቶታል ።

"ክንፈ የእፀገኔትን ነገር አልጨረስክልኝም" አለው ሁለት ጊዜ ውስኪውን ተጎንጭቶ ።

"ሽፈ ሰላም ፍለጋ መምጣቴን አትርሳ !"

"እኔም ያንተ ሰላም መደፍረስ አስጨንቆኛል ።"

"ለጊዜው ቢቆየንስ ?" አለው ክንፈ የተበሳጨበትን ምክንያት ማንሳት እያስጠላው ። ዳግም ስለ ብስጭቱ አላነሱም ።

* * *

እፀገኔት ባሏን ያየችው በከፍተኛ ሃዘን ነው ። ሰክሮ ለመግባቱ ቀጥተኛ ተጠያቂ ራሷን አድርጋለች ። መኪናው ጋራዥ ከገባች ጥቂት ወራት አልፏታል ። ብዙ ቦታ የተኮረኮመች ፮ልስ ዋገኑ ቤት እየሰሩ ስለነበር ያለ የሌለውን ዕቃ ሲያግዝባት ውልቅልቋ ወጥቶ በመጨረሻ አልሄድም ብላ በማኩረፍ ጋራዥ አስገባት ። የመጣው በእግሩ ነው ፤ ገና በረንዳው ላይ ሆኖ ነበር እየተንተባተበ "የሕይወት ጥቀርሻ !" ሲል የሰማችው ።

ጓደኛው ሽፈራው ቤቱ አድርሶት ነው የተመለሰው ፡ አምስት ሰአት ከሆነ ደቂቃዎች አልፈዋል ። እፀገኔት መኝታ ቤት ሆና የእግሩን ኩቴ ታዳምጣለች ። የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ አተኩሮ ከአያት በኋላ "ደህና ዋልሽ-ውዴ?" አላት አፉን ያዝ እያደረገው ። መልስ አልሰጠችውም ። ቅር አልተሰኘም ። በሩን ዘግቶላት ወደ ሳሎኑ ተመለሰ ። የ"የሕይወት ጥቀርሻ!" አለ በድጋሚ ። "እንደዛ ...ቆርቆሮ...አእምሮዋችን ያዥ ጀመር!... መቼ ይሆን ...የሰውነታችንን...ልክ...የምናውቀው... ትፋት! የሕይወት ትፋት! አ-ክ እንትፍ!" አለ እርሱነቱን እየኮነነ በመኩላተፍ ።

ውጥናቸው ሁሉ በስካር መንፈስ እንደሆነ አስታወሰ ። በመጀመሪያ ቤት ሰርተው ያሉበትን የኪራይ ቤት መልቀቅ ...ከዛም-ከዛም ብዙ ዘመን የጓጓበትን ልጅ አምሮቱን መወጣት ...ሌላም ሌላም ፡ "የሕይወት ጥቀርሻ!" አለ ለሶስተኛ ጊዜ በጣም ዝግ ብሎ ፡ ገና በጅምር ያለው ቤቱ በአይነ ህሊናው ታየው ። በመሠረቱ አግጥጦ መቆሙን አስቦ ፈገግ አለ ። የውሸት ፈገግታ ፡ የምፀት አይነት ፡ እያሽሟጠጠ ሳቀ ። ሳቁን ለቀቀው ። ለምን እንደሳቀ ሲያስብ ግራ ገብቶት ደገመና ሳቀ "እውነትም ሟንቅላታችን ማገጥ ጀምሯል" እሱም አሳቀው ።

እፀገኔት የመጀመሪያ ሳቁ አላስገረማትም ። በሁለተኛው ግን ግራ ተጋባች ፡ ሶስተኛ ላይ ተነስታ ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል መጣች ፡ ሲያያት ሳቁን ወዲያው አቆመ ፡ እሷ ግን አትኩረው የሚያዩዋትን አይኖቹን መቋቋም አልቻለችም ። እይታዋን ወደ ወለሉ አቅጣጫ ቀየረች።

አፍታ ቀና ብላ "አትተኛም?" አለችው ።

መቆም እንዳቃተው ያስታውቅበታል ። ደገፈችው ። ቀስ እያለች መኝታ ቤት አልጋው ላይ አስቀምጣው ጫማውን ትፈታለች ጀመር ። ደስ እያላት ፡ የመንፈስ ሰላም እየሰጣት ፡ ለበደሏ ካሳ የከፈለች እየመሰላት ። በፊት እንኳን ሰክሮ ትንሽ ሞቅ ብሎት ስታይ ቁጣዋ ፡ ኩርፊያዋ ለብቻ ነው ። ጫማውን አውልቃ እንደጨረሰች ፒጃማውን አመጣችለት ።

"ዕዕ...ሽት ...ትወጂ...ኛለሽ..?"

"አዎ ክንፈ ፡ ቅንጣት አትጠራጠር ። አሁንም ካንተ በላይ የማፈቅረው የለኝም..."

Scanned with CamScanner

"እ....ንጃ እፅሽ ፡ እ....እንጃ....ትፋት! የህይውት ትፋት! እንትፍ!.
..." አፉ ግን ምራቅ የለውም ።

እፀገነት መወሰን እንዳለባት ታወቃት ።

ለእፀገነት ህይወት ባሰበችው መንገድ ልትመራላት አልቻለችም ። ለማቅናት ስትሞክር ስትደፋ ፤ ስታስተካክል መልሳ ስታዘምባት ፡ ቀድማ መምራቱ ተስኗት ኋላ ኋላ እየተንደፋደፈች ስትዘልቅ ፡ ወስና ባሻት መንገድ እንደመመራት ፡ መንገድ በቀደዱለት በኩል እንደሚጓዝ የቦይ ውሃ ስትጠማዘዝ ከመዋል በቀር ፡ ይበጀኛል ብላ ያበጀችው መስመር የላትም ።

ሄኖክ በአፍላ ስሜቱ ከሚለማሳት እሳታዊ የስሜት ርካቦት አንፃር የክንፈ የእርጋታ ፍቅሩ ግራ እያጋባት መንፈሷ ተጨንቋል ። 'ኤዲያ ! የኑሮ ትርጉሙ ምንድን ነው? የፍቅር ትርጉም ሰጥቶ መቀበል ነው ። ከሚለማስሽ የደስታ ስሜት ባሻገር ምን ትፈልጊያለሽ ? ይህንን ቀዝቃዛ ሕይወትሽን ወዲያ በይና ከሄኖክ ጋር ፅኚ ሲላት' በሌላ በኩል ደግሞ 'ፍቅር ማለት ፀጥተኛ ባህር ፡ ውስጡ ጠሊቅ ነው ። የስሜት ነዲድ እሳት አይደለም ፡ ያ የስሜት ነዲድ እሳት ባጋጣሚ ሲናጥ በውሃ ላይ እየተንሳፈፈ ሰም ሆኖ መገኘቱ የማይቀር ነው ። ክንፈ እኮ አፍቃሪሽ ብቻ አይደለም ባለውለታሽም እንጂ!' ይላታል ።

'ታዲያ የዕድሜ ልክ ደስታ የሚያስገኝልሽን ሰው እንዴት ላንድ ጊዜ ውለታ አላልሰሽ ትሰጪያለሽ ?'

'ክንፈኮ የሶስት ዓመት የትዳር ጓደኛሽ ነው!'

'ሄኖክም ቢሆን የልጅነት ፍቅረኛሽ አይደል?'

የህሊናዋ ንትርክ ሊያሳብዳት ይደርሳል ። ጩሂ ያሰኛታል –በባዶ ሌሊት ። ክንፈ ከጐኗ ተኝቷል ። የህሊናዋ የእርስበርስ ጦርነት ያደክማትና አሸናፊው ሳይለይ ሽለብ ያደርጋታል ።

የጭንቅ ሌሊት ይረዝማል ።

ብዙ አታርፍም ። በሁለት አሳብ ተከፍላ እንደተወጠረች መልሳ ነቃች ። አማካሪ ያጣችለት ፡ የምታማክረው ሰው ብታገኝም ምን ብላ እንደምታማክር ግራ ይገባታል ። ማንም እንዲያውቅባት አትፈልግም ። ደግሞ በባሌ ላይ ልሸፍጥ ልትል? አታደርገውም ። ወይንስ ሄኖክን መተው ? ይሄም የማይመስላት ጉዳይ ነው ።

የህሊናዋ ሁለት ክፍሎች እንደገና ፍልሚያ ጀመሩ ። ጐራዴ ተማዘው ጋሻ ደግነው ። በሁለቱ ጐራዴዎች ፍጭት የሚፈጠረው ብልጭታ መንፈሷን እያሸማቀቀው ።

'ሁለት ወዶ አይሆንም ፡ ይገባሻል? የመኖር ትርጉሙ የሚጀመረው አካባቢያችን በሰጠን ዕድልና አማራጭ ተጠቅመን የራሳችንን ምርጫ መወሰን ስንችል ነው ። ሕይወት የግለሰብን ቆራጥነት ትፈታተናለች ሲባል አልሰማሽም? እና መወሰን አለብሽ....መወሰን!'

'እሺ .... ምን ልወስን?'

'ምርጫው የራስሽ ነው ። ሁለት አማራጮች አሉሽ ። አንዱ ክንፈን፡ ሌላው ሄኖክን ...' ይሄኔ ልቧ ክፉኛ መምታት ይጀምራል ። 'አዎ ደስታን ሊለግስሽ የሚችል ሄኖክ ነው ። የነኚህን ሳምንታት ምሽት እንኳን አታስታውሺም? ...' የደስታ ስሜት በሰውነቷ ተሠራጨ

'...ደስታን ሊሰጥሽ የሚችል እሱነው ፤ አንቺም ለሱ ፡ እሱም ላንቺ የንፁህ ማር ጣዕም አላችሁ ። ብቸኛው ሄኖክ ፡ አንቺነትሽን ሊረዳ የሚችል ሰው ሄኖክ ፡ ሴትነትሽን ሊያጣጥምሽ የሚችለው ሄኖክ ፡ አስቢበት! በይሉኝታ ገመድ ታስረሽ ፡ በውለታ ተተብትበሽ የወደፊት የእድሜ ዘመንሽን በምንይሉኛል አታስቀሪው ። ከፈለግሽ ገና ወጣት ነሽ። ምንድነው ችግርሽ ? ልጆች እንኳን የሏችሁ ።'

'ክንፈስ? ክንፈ'

'ክንፈማ ምን ይሆናል ብለሽ ነው ። የእድሉን አያጣም ። ደግሞም ድሮም ቢሆን አንቺ ወደ ህይወቱ ገባሽበት እንጂ እሱ በህይወትሽ አልሰመጠም ። ዘለሽ እንደገባሽበት መንጭቀሽ ውጪ ።'

ማመን ይዳዳታል 'አዎ ....' ትላለች ለራሷ '....እውነትም ህይወት የባለቤቷን ቆራጥነት ትፈታተናለች ። ከክንፈ ጋር ከማሳልፈው የተደጋገመ ሌሊት ይልቅ ከሄኖክ ጋር በማሳለፋት የቅፅበት የፍቅር ልውውጥ ህይወቱ በልፅጋ ትለመልማለች ።

መልሶ ይዘገንናታል ።

ብዙ አትቆይም በፍልሚያ የተዳከመ ሰውነቷ በውሳኔዋ አልፀና ሲላት ተስፋ ቆርጣ በሌላዋ ጐኗ ትጋድማለች ።

ሌሊቱ ሊነጋ ወፎች ይንጫጫሉ ። እፀገነት ከዋጣት የቅዠት አለም ለመወጣት ትታገላለች ።

Scanned with CamScanner

'ስትገርሚ!' ይላታል የክንፈ ወፍራም ድምፅ ። 'ከኔ ጋር ያስተሳስረሽ ውለታ ብቻ ነው? በመሃከላችን ፍቅር የለማ! እስከዛሬ ከኔ ያኖረሽ ያንቺ ርህራሄ ነው? አንቺስ ህይወትሽ ተመቻቸ ፡ እኔስ? አስ–ስ–…' ድምፁ እንደገደል ማሚቶ በጭንቅላቷ ይንዝራል ።

'ተናገሪ እንጂ እወገኔት !….ክንፈ ፍቅር የለውም ? ፍቅር አያውቅም አሉሽ? ይገርማል ። እይንሽን ጊዜያዊ የፍቅር ሰፈፍ ጋርዶት እንጂ ፍቅርሽ በትዳራችን መሃል የከረመና የረጋ ነበር ። ስርዶ አጠላበት እንጂ ። ቢስተዋልሽ ግን ስርዶ ለመተብተብ እንጂ እራሱን ችሎ ለመቆም አቅም የለው' ። ምስሉ እየደበዘዘ ይታያታል ።

'ምን ላድርግ?' አለች እየፈራችና የሽሽት ሩጫዋም ከንቱ እየሆነ ባት ፡ ስትነሳ ስትወድቅ ፡ ደግሞ ስትሸሽ ፡ የሕልም ሩጫ!

'እንጃልሽ ! ወደሽ የገባሽበት ነው ።'

'አይደለም! አይደለም!'

የክንፈ ግዙፍ ሰውነት ይበልጥ እየገዘፈ መጣ ። 'ወደሽ ነው! ወደሽ!…' እጆቹን አሹሎ ፡ አይኖቹን በሽታው እንደተነሣበት እብድ እያጉረጠረጠ በእጆቹ አንገቷን ፈጠረቃት ።

ጩኸቷ አባነናት ።

"ምን ነካሽ ውዴ?" አላት ክንፈ ፡ ጩኸቷ እሱንም ከእንቅልፉ አባኖት ወፍራም ክንዱ አንገቷ ዙሪያ አርፎ ። ቀስ አርጋ እጁን ከአንገቷ ስር አነሳችውና በረጅሙ ተነፈሰች ።

"ምነው እቃገሾሽ እንዴ?" አላት የራስጌውን መብራት ካበራ በኋላ፡ የማታው የስካር መንፈስ የራስ ምታት አሻራውን ትቶለታል ።

"ኡሀ…. መጥፎ ሕልም ! ኡሀ ··ቅዠት ነው" አለች አውንም ባልተረጋጋ ስሜት ። ከዛ አሰቃቂ ሕልም የዘፈቃት ጣጣ እስጨነቃት ፡ ህይወት ሽክሚ የሚቀለው የምታቋድሰውን ችግር በጋራ ሊወጡት ሲችሉ ነው ። ያለዛማ ከማንም ጋር የትስ ይታደር የለ ። የትዳር ትርጉሙ ችን ካልተወጣነው ። አብሮ የመኖር ትርጉሙ ምንድነው? 'ወተት ሞልቶ መካፈል ከሌለ ፡ ትዳር ማለት የራስን ነፃነት የራስን ፍላጐት ለክንቱ ነገር አሳልፎ መስጠት ነው ። አብሮ በመኖር ደስታ ካልተሸመተ እንዲሁም

አብሮ ከመኖር መዋደድ ፡ መተሳሰብ ፡ ብሎም አካላዊና መንፈሳዊ ውህደት ከሌለ ፡ ትልቁ የምድራችን ሲኦል ፡ ጋብቻ ይሆናል ።

እንዲጋቡ የወሰንበትን የመጀመሪያውን እለት ለመጀመሪያ ጊዜ ረገመው ። ሳይታወቀው የማታውን ቃል ደገመው "የሕይወት ጥቀርሻ!"

"ምነው?" አለችው እወገኔት አተኩራ እያየችው ።

"ምንም!"

ምእራፍ ስድስት

ሄኖክ ለስራ አዲስ አበባ በመመደቡ በጣም ተደስቷል ። ለአላማው ግብ መምታት እንዳይጎተኝ እድል ቆጠረው ። ትናንትም ፡ ዛሬም ፡ ነገም እወገኔት የኔ መሆን አለባት ለሚለው ግትር አቋሙ ማለዘቢያ መድኃኒት አላገኘለትም ።

ለእልፁ መጠናከሪያ የሆነለት ደግሞ የተመደበበትን መስሪያ ቤት አውቆ የቅጥር ጉዳዮን በሚያስጨርስበት ፡ ለፊርማና ለመሳሰሉት ከቢሮ ቢሮ በሚሯሯጥበት ወቅት አንድ ቢሮ ውስጥ ከዙሪያሽ ጋር መገናኘቱ ነው ።

ዙሪያሽ ስታየው ደንግጣለች ። "ምን ልታደርግ መጣህ?" አለችው ናፍቆት በመሰለ ሁኔታ ከሳመችው በኋላ ፡ አፍ እየተርበተበተባት ። በአእምሮው ጓዳ ከአመታት ብዛት ጨለማ ተላብሶ ፡ ተቀብሮ ፡ የነበረው ትዝታ ፡ የጨለማውን ድንበር እየጣሰ ከፊት ለፊቱ ድቅን አለ ።

'ሲገርም ! ዙሪያሽ ያ ውብ ገፅታዋ ትንሽ ከመወፈሩ በቀር የተቀሩት እንዳሉ ናቸው' አለ በሃሳቡ ፡ ድንገት ካዘገመበት የሃሳብ ጐዳና ተመለሰ ። የመጣበትን ጉዳይ ዘርዝሮ አጫወታት ። ጉዳዩን ከነመረጃው ይዛ አሰቃዋ ቢሮ ገባች ። የሰውነቷ ማራኪነት እጅጉን ንሯል ። ሴቶች ከአፍላነታቸው ይልቅ እየጐለመሱ ሲሄዱ እያደር እየለሰለሰ እንደሚጥም የወይን ጠጅ እያማሩና እየጣሙ እንደሚሄዱ ተሰማው ።

ዙሪያሽ ሁለተኛ ደረጃ ት ቤት በነበረችበት ጊዜ ሄኖክን ወዳው ነበር ። መውደድ ብቻ ሳይሆን ፡ አፍቅራው ነበር ። ባላት ውበትና የደም ግባት እንዲሁም በሴትነት ኩራቷ ምክንያት ብዙ ጊዜ ጥየቁው ከርሱ

Scanned with CamScanner

እስኪመጣ ታገሰችው ። ሄኖክ ውኔታዋን መግንዘብ አላቃተውም ። ፍላጐቷን በማጤኑ እሱም ዋጋውን ጨመረ ። አሳስቻላትም ጠየቀችው ።

"ላስብበት" ማለቱ አናደዳታል ። 'ምነው ምሳሴን በቆረጠው' አለች ። 'ቆይ እጂ ይግባ' እንዳለች አብረው ሲከርሙ ፡ ኩራቱ በሱ እየባሰ ፡ ፍቅሩ በዩ እየጠና አንድ አመት አሳለፉ ።

አንድ ቀን ከአስቻለው "ጉልቤ" ጋር ያያት አለት የተሰማውን ስሜት መቼም አይረሳው ። አውንም አንድ ላይ ይሆኑ? ሲል አሰበ በልቡ ውስጥ ተዳፍኖ የከረመው ቅናት እየተንፈራገጠ ።

'ህይወት በዘፈቀደ ነች ። በተገኘው የህይወት ቀዳዳ እየሰረገች ፡ እየከሰመች የተፈቀደላትን እድሜ ቋጭታ እስክታከትም ህይወትን እየታዘበች ታዘግማለች ። አዛኟ ግን ማነው? የለም! ። ግን ይሁን ግን ፡ በቀይደው የህይወት ጉዳና እንጓዛለን ። ግን አሰስ ገሰሱን ተሸክመን ከመጓዝ በራሳችን መንገድ ላይ እማናዘግመበት ምን ምክንያት ይኖራል?' እፀገነትን በድጋሚ አሰበ ።

'እና ··· እና እፀገነት የኔ እንጂ የማንም ልትሆን አይገባትም ። ባለትዳር ነች ። አግብታለች ። ግን ····ግን በትዳሯ ደስተኛ ካልሆነች ለምን··· ለምን በአንድ ወቅት ባጋጠማት የህይወት አስከፊ ገጠመኝ ሳቢያ እራሷን እስከወዲያኛው ···የለም መሆን የለበትም ። እኔንም ሞራልቢስ ሊያሰኝ ይችላል ። የለም! በፍፁም ···ደግሞ ····'

የሁሪያሽ መመለስ ከሃሳቡ ገታው ።

"የምሥራች ! ዋናው ምሥሪያ ቤት ሆነሃል ።"

"እዚሁ!"

"እም!"

ሄኖክ እጅግ ተደሰተ ። ስራውን ከሁለት ቀን በኋላ እንደሚጀምር ተነግሮታል ። ቅልቁ ሃሳብ ተቃለለ ። ከዚህ በኋላ ቀስ በቀስ ሃሳቡን ለመጨረሻ ግቡ አመቻችቶ የእርምጃ ቃታውን መሳብ ብቻ ! ያለጥርጥር አላማው እንደሚሳታለት በእጅጉ ተማምኗል ።

እሱም ሁሪያሽም ከቢሮ ተከታትለው ወጡ ። በሁሪያሽ ልብ ውስጥ የከረመው የፍቅር ስሜት ላይነሳ በልቧ ከተዳፈነ አመታት አልፈዋል ። ከንፁህ እፀትነት በስተቀር ለእሱ የሚሰማት እንዳች ስሜት አልነበራትም። ፍቅሯ ወደ ወንድማዊ መውደድ ተለውጧል ።

ወደ መስሪያ ቤቱ ከበብ ወሰደችው ። ሁሪያሽን ያሳጣው መንቀባረሩ ሳይሆን የአስቻለው ጉልበት ፡ ንደለኝነትና የራሱም ፈሪነት ይመስለዋል ፡ እና ይናደዳል ። ይበግናል ። ያኔ የዕልህ ፍቅር ይጀምረዋል ። ምንጊዜም ባሳው ነገር ላይ ፍላጐቱ ይንራል ።

ሄኖክ በሃሳቡ ያውጠነጥናል ። መጠቃትን ···ግባትን ፡ መቁሰልን ···ሽንፈትን ። ሁሪያሽን ሲያስብ አብሯት የነበረው አስቻለው "ጉል ቤው" እንደገና ትዝ አለው ።

'ህይወት እንዲሁ ነች!' አለ የሁኔታዎች መቀያየር እገጋሚ ቢመስለውም ፡ ሁሉ ነገር እንዳልነበር ፡ አልያም በትዝታ ጓዳ ተቀምጦ ሲያልፍ እያስተዋለ ።

ስለነበረበት ሃገር ጠየቀችው ። እሚወታት ። ጨወታዋ ንፁህ ነው ። ደስ የሚል ለስላሳ ፈገግታ አላት ። አለማግባቷን ከተረዳ ቆይታል ፡ ያ አሰቻለው አሁንም አብሯት ይሆን? ።

ቅናቱ እንደገና አገረሸበት ። እራሱን ለመገሰፅ ሞከረ ከንቱ ድካም። ሁኔታዋ ሳይለወጥ ተለየቸው ።

ሁሪያሽ ፍቅሯ ከመጠን ባለፈበት ሰአት ኩራቱን ብዙ አላስተዋለች ውም ። እንዳውም ኩራቱ እልህ ውስጥ ቢከታትም ሌሎች ሴቶችን ስለማያቀርባቸው አልጠላችውም ። ቢሆንም ግን እያደር ከልክ ያልፍባት ጀመር ። ሲፈላሰጉ እፀ እንጂ እሱ አይሄድም ። አንድ ቦታ አብራው ማሳለፍ እያማራት እሱ አላቡን ስለማያቀርብ ብቻ ፍላጐቷን አምቃ ታሳልፈዋለች ።

የአንድ ቀኑ የእንባዋን ብዛት ትራፅ ታዝቧታል ። ሶስት ጊዜ ቤቱ ተመላልሳ አላገኘችውም ። በአራተኛው አገኘችውና ናፍቆትና የሴትነት ወጉ ጥላቻውን አጥልተውባት ቀድሚ እኔ ልውጣ እኔ··· ሲርካከሩ በመሃሉ ኩርፊያዋ ብቅ አለና ከንፈሯን ጣል እንዳደረገች ፡

"የት ነበርክ?" አለችው ።

ፈገግ አለና "ምነው ?" አላት ።

"ሶስት ጊዜ ፈልጌ አጣሁህ ።"

"ይሆናል" አላት ፡ በግድ የለሽነት ስሜት ።

ተናደደች ። ተንጨረጨረች 'እኮ እንዴት' አላት ሃሳቧ ፡ 'እኔ ልጅት' አላት እፀኔታ ፡ እንባዋ አካኪ ዘራፍ እያለ ሲተናነቃት ፡ ልቧ ብቻ

Scanned with CamScanner

ያወላዳል ። ጉንጩ በሲቃ ፡ በእልህ ፡ በንዴትና በፍርሃት መርበትበቱ ይታያል ።

“ምን ማለትህ ነው ግን…?”

እንደዘወትር ብሽቀታ አድርጐ ቆጠረው ። ሊቀልድባት ፈለገ ።

“አሁንማ በቃ ፡ ደንበኛ ሚስት ሆንሽ ኮ!”

ብልጭ አለባት ።

“ምን ታደርግ አንተ ምን ታደርግ እኔ ነኝ አህያሞ…” እልሁ አላናግር ፡ ቁጣዋ ሥርዓት አልይዝ እያላት “እቤትህ ድረስ እንደበግ ተጐተትኩልህ! አንተ…ምንታደርግ ፡ እግሬን ይቁረጠው ! ሁለ…ሁለ ተኛ!”

ሊፈነዳ የደረሰው እንባዋን እንዲመለከትባት አልፈለገችም ። ፊቷን አዙራ ወደቤቷ ተጣደፈች ።

ሄኖክ ሊጠራት ፈለገ ። ደግሞ አመነታ ። ሂዶ ሊያስቆማት ፈልጐ ነበር ። “መምጣቷ አይቀርም” አለ ለራሱ ፡ ግን በዛው እንዳትቀር ፈርቶ ነበር ።

“እንቺ እንቺን ነው” አላት ከንጉዋ ጐርነን ያለ ድምፅ ፡ የሄኖክ አይደለም ። ዞር አለች ። አይታው የማታውቀው ወጣት ነው ። እየጐተጐተ እያዋራት ቤት አካባቢ ድረስ አብሯት ሄደ–ያለውጤት አልተመለሰም ።

ወጣቱ አስቻለው ነበር ። አስቻለው ጉልበ ወንዳወንድ ገፅታው ማረካት ። በዚያ ጉልበቱና ዋንካፊው ለሷ መረታቱ ኩራቷ ሆናት ። ሴትነቷን ታመልከው ጀመር ። ሴትነቷን አስወደዳት ። ሄኖክን ለመርሳት ብዙ አልተቸገረችም ። ሄኖክ ከጊዜ በኋላ ያንገበገበው ወሬ ቢኖር ዙሪያሽ ‘አስቻለው ወንዳወንድነቱ ይማርከኛል’ ያለችውን ሲሰማ ነው ። የስድብ ያክል ቆጥሮታል ።

ከዛን በኋላ ወንዳወንድ የሚል ቃል ያስጠላዋል ። ቃሉ ብቻ አይደለም ። ሙንቻው ያፈረጠመ ወንድም ያስጠላው ጀመር ። ሁሉም አስቻለውን አየመሰሉት ።

* * *

የዕለቱን ሥራ አጠናቆ ወደቀየው የሚሯሯጠው ህዝብ ከተማዋን አስጨንቋታል። ካዛንቺስ፡ ቴዎድሮስ አደባባይ፡ ለገሃር፡ ማዕከላዊ እዝና

ሚክሲኩ፡ ያለው የመኪና ብዛት እልህ ያስጨርሳል። ምሳቸውን የቋጠሩ የቢሮ ሠራተኞች አንዳንዶቹ በላስቲክ ከረጢት፡ የተቀሩትም ቦርሳ በመሳሰሉት ሰሃናቸውን ይዘው ግራና ቀኝ ናላን የሚበጠብጡ ጡሩምባዎችን በጆሮዎቻቸው እያስተናገዱ ሽቅብ ቁልቁል በንዳናው ላይ ያዘግማሉ። አለሁ መጣሁ የሚለው አስፈሪ ዝናብ ለየህሊናቸው መልዕክቱን አድርሶ እግረኞች ጥድፊያ ይዘዋል።

ትእግስት ያጣው ሹፌር ጡሩምባ ይነፋል። ይሳደባል። አንዳንዱ መሪውን እየነረተ ያልፋል። ከአለቃው የተጋጨ፡ ቤቱ ነገር ያለበት፡ ሁሉም የየራሱን ሃሳብ እያውጠነጠነ ይጓዛል፡ ወደየፈለገበት።

ሲራክ እየገሰገሰ አዜብ ጋ የደረሰው ከቢሮዋ ወጥታ አካባቢውን ስትቃኝ ነው። እንዳየችው ፈገግ ብላ ወደ መኪናው ስታዘግም በሩን ከፍቶ ቆያት። አይናቹ እሷን ተርበዋል፡ ከንፈሮቹም ጉንጮቿን ናፍቀዋል። ገብታ በሩን እንደዘጋች ጉንጯን አስጠጋችለት። የዘወትር ልማዳቸው ነው።

ከቦርሳዋ ጋር አብራ የያዘችው አንድ ድልብ መጽሐፍ አለ ። ‘መቼ ይሆን ከመጽሐፍ የምትለየው?’ አለ፡ መጽሐፉን በጥላቻ አየት አየት አድርጎት።

“ታዲያስ!” አላት የመኪናውን የኋላ ማርሽ እያስገባ።

‘ደህና ነኝ፡ አለሁ’ እንደማለት ከንፈሮቿን አሞጥሙጣ እራሷን ላይና ታች በመወዝወዝ መለሰችለት።

መኪናዋን ወደ ቴሌ ባር መራት። ከመኪናው መውረድ አላሰኛቸውም። ለሱ ቡና፡ ለሷ የብርቱኳን ጭማቂ አዘዙ።

“አዜብ…” አላት ሲራክ ሰውነቱን ወደሷ አዙሮ የመኪናውን በራፍ ተደግፎ። በቅንድቧ ብቻ ምላሽ ሰጠችው። የማታውቀው አዲስ ፀጥታ በራሷ ውስጥ ይሰማታል። ግን ደስ አይልም። የመቃብር ስፍራ ፀጥታ አይነት፡ የሚቀፍ ፀጥታ፡ የሚያስጠላ ሰላም።

“…ኸ… የሰሞኑ ድብርት ለቀቀሽ?” አላት ከሰሞኑ ዛሬ ተሽላ ያገኛት መስሎት። ውስጣዊ መረጋጋትና ሰላም ያጣው መንፈሷ ሰሞኑን እሱንም አስጨንቆታል። የሰውን መንፈሳዊ ጣር ከማዳመጥ ይልቅ እራስ መታመሙ ሳይሻል አይቀርም። ሊያስደስታት፡ ሊያረጋጋትና ሊያረሳሳት የማይፈጥረው፡ የማይሞክረውና ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም። አልተሳካለትም እንጂ።

Scanned with CamScanner

“አልመስልም?” አለች መልሳ እየጠየቀችው።

“አዎ… ግን በፍፁም ሊገባኝ አልቻለም። ለምንድነው ራስሽን ይህንን ያክል የምታሰቃይው አዜብ? ሁሉነገር እኮ ከልኩ አያልፍም?” አላት አጋጣሚውን በመጠቀም ሊመክራት እየሞከረ።

“ይገባኛል!”

ደረቅ መልሷ ለጥያቄ ባያንደረድረውም መናገሩን አላቋረጠም። “ችግሮችን ለብቻችን አብሰልስለን መወጣት አንችልም። ለሰው በማማከር፣ አቅልሎ በማየትና በተለያየ መንገድ ካላስታመምነው መጨረሻ ወዴት እንደሚመራን ታውቂያለሽ?” አላት እትኩሮ እየተመለከታት።

“አማኑኤል ልትሰኝ ነው?” አለችው በፈዘ ፈገግታ እያየችው።

“አትጠራጠሪ” አላት እንደተኩሳተረ።

“ሚይ— ቢ!”

“ምንም ጥርጥር የለውም!”

“ቢሆንም አያስደንቅም። እያንዳንዳችን በየቀኑ ለተወሰነች ደቂቃ ማበዳችን ቀረ ብለህ ነው? ለዚህች አለም እብደት ተገቢ በሽታዋ ነው”

“ተሳሳትሽ አዜብ!”

“ተሳሳትሽ ማለትህ እራስህን በራስህ ተታረንክ። ምክንያቱም ተሳሳትሽ ማለትህ ራሱ እብድ ያስኝሃልና ነው። የመንፈስና የህሊና ጠጣሮች የምንላቸው በኔ ግምት፣ የዚህች አለም ምንነት ያልተከሰተላቸው፣ አለም እሷነቷን ጠቅጥቃ ለመንፈላሳቸውም ሆነ ለሕሊናቸው ያላሳየቻቸው መሆን አለባቸው። በተረፈ ፍጡሮች ሁሉ ዕብዶች ናቸው።”

“ልክ አይደለሽም አዜብ!”

“ልክነኝ ሲራክ፣ በርግጥ እብድ የሚባለው ጨርቁን አውልቆ የጣለ፣ በየመንገዱ የሚለፈልፍ ብቻ ከሆነ ያንተ አባባል ያስኬዳል። ግን አፋችን ባመንቀሳቀሱ፣ ልሳናችን ድምፅ ባለማውጣቱ እንጂ ሀሊናችን ዘወትር ለኛ እንደለፈለፈልን ነው። ሀሊናችን ጨኽት ቢኖረው ኖሮ አለም በኡኡታ ታውካ የሁሉም ማበድ በታወቀ ነበር።

“እብድን እብድ የሚያሰኘው የህሊናውን ጣርና ስሜት በንግግር ይፋ ማድረጉ፣ ያም የተናገረው ነገር ህብረተሰቡ የማይቀበለው ሲሆን አይደል? ዘወትር ማኅበረሰቡ የሚቀበለውን የሚናገር ሰው ግን እብድ አይባልም። ታዲያ ስንቶቻችን ነን በውስጣችን ከሕሊናችን ውጪ ሌላ

ሰው ቢሰማው ሊዘገንኑና ሊያስጠይፉ የሚችሉ ነገሮችን ስናብሰለስል የምንውል? ዕበድ ያሻውን ያደርጋል ሲባል አልሰማህም? እኛም የሌላውን ፍላጎትና ስሜት ሳንረዳ በራስ ወዳድነት የምናደርገው ሁሉ እብደት ነው። ራስ ወዳድነታችን ደግሞ የእለት ከእለት ስራችን ነው። ዘወትር እያበድን ነው። እብደት የእለት ተእለት ክንዋኔያችን ነው። አንድ ነገር ጥሩ ወይንም መጥፎ የሚባለው ሕብረተሰቡ መጥፎ ስላለውና ስላላለው ነው። ታውቃለህ! ማኅበረሰብ ተስማምቶ የተቀበለው ነገር እመኔታ ይኖረዋል፣ ውሸቱ እውነት ነው እስኪባል ድረስ። ጉዱ ካሳ ለምን እብድ ተባለ? የሚሰማውን ስለሚናገር፣ ሕብረተሰቡ የማይቀበለውን ነገር ስላስተጋባ! እብደት መጥፎም ይሁን ደግ የኔነት ድፍረትን መታደግ ነው። ተግባባን?” አለችው አይኖቿን አጉረጥርጣ ኃይል ባለው ስሜት ቃላትን እያጠበቀች።

“በፍፁም አልተግባባንም…” ከማለቱ አስተናጋጁ የታዘዘውን ይዞ በመስኮቱ አጠገብ ቆመ። ሲራክ የመኪናውን መስኮት ካወረደ በኋላ፣ የሷን የቀዝቃዛ ጭማቂ ቀጥሎ የሱን ቡና ተቀብሎ መልሶ ዘጋው፣ እንደቀድሞው ሊቀመጥ እየተመቻቸ።

“እና አብጃለሁ ነው የምትይው?” አላት በከፊል እየቀለደ። የቀረበለት ቡና ውፍረት ፍላጎቱን አርክቶታል።

አዜብ ጭማቂዋን ቀምሳ ካጣጣመች በኋላ “በመጀመሪያ በእብደት መሠረተ ሃሳብ አልተስማማንም። እብድ ነው ወይንም አበደ የምንለው ምን አይነት ሰው ነው? አማኑኤል የነባ፣ ያለዛም ጨርቁን ጥሎ በየመንገዱ የሚንከራተት፣ ወይንስ የሕይወት ትርጉሙ፣ የኑሮ ሽክሙ በዝቶበት ባቀናና ባዘገመ ቁጥር ከራሱ ጋር እየተጨቃጨቀ ለራሱ የሚለፈልፈው? ወይንስ እኔ?” አለች የመጨረሻዋን ቃል ስትናገር ፈገግ እያለች።

“የጠቀስሻቸው በሙሉ!” አለና ትንሽ ካቅማማ በኋላ “…ከተለ ምዶ አዊው የሕብረተሰብ አኗኗር ያፈነገጡ ከሆኑ በኔ በኩል ዕብዶች እላቸዋለሁ” ሲል አዜብ ፈገግ አለች።

“ትክክለኛው ፍቺው የአዕምሮ መቃወስ፣ መዛባት ማለት ይመስለኛል” አለ፣ ተጨማሪ ግንዛቤ ለመስጠት ፈልጐ።

ማጠናከሪያው አላጠገባትም “የአዕምሮ መቃወስ ማለት?” ብላ ጠየቀችው

“ኡፍ!” አለ የውይይቱ አሰልቺነት ተሰምቶት።

Scanned with CamScanner

ፈገግ አለች፣ ቀዝቃዛ ፈገግታ፣ እሱም አስተዋላት። እዝነ ልቦናው ድረስ ስሜታ ጠልቆ እየተሰማው።

''የሆነ በሽታ ያደረብሽ ትመስያለሽ'' አላት አትኩሮ እያያት፣ ፈገግ ብላ ተመለከተችው፣ ጭግቂዋን ፉት እያለች።

''የማይድን በሽታ ይሆን?'' አለችው እንደፈገገች።

እንጃ! የልቡ መልስ ነበር

''በሽታ!···ቁስል ነው። የማይሽር የአእምሮ ቁስል! የእድሜ ልክ ደዌ፣ ቢጠነቀቁለት፣ መድሃኒት ቢያገኙለት የማይድን ስውር የሰሜት ሕመም፣ አዎ የማይድን በሽታ።''

ሲራክ በድጋሚ አትኩሮ ተመለከታት። የለበሰችው ጥቁር ቀሚስ ቁርጭምጭሚቷ ድረስ ወርዷል። ከወገቡ ሽብሽብ ብሎ እየሰፋ የሚወርደው ቀሚሷ በጣም ስስና ለስላሳ በመሆኑ ከጭኖቿ ወረድ ሲል ጉልበቷ ላይ አርፎ ሰአሊ ሽራ ላይ እንደነደፈው ስእል ቅርጿን ያጎላዋል። ከላይ የለበሰችው ድፍን ሹራብ ጡቷን ወጥሮ ይዞታል። ደረቷ የአንገቷን መጋጠሚያ የመጠጠው ይመስላል። የትንሿ አጥንቶች ጎላ ብለው ከወደታች እየተሰረጎጉ ሄደው የራሳቸውን ጥላ ይፈጥራሉ። ለአንዳፍታ ሃሳቡ ከተወረወረበት የውበት ንባብ ተመልሶ፡

''ምን በሽታ ይሆን የተጠናወተሽ?'' አለ እየፈገገ።

''የቀለም ሽታ፣ የነጭ ወረቀት ናፍቆት፣ ግን እንዳልኩህ መካን ነኝ። አዕምሮዬን ይኮረኩረኛል። ያሳክከኛል። ይበላኛል። ታዲያ ቁስሉን ማሽት፣ ማከክ ሲያቅተኝ ያመኛል። ጤና ይነሳኛል።'' ፈገግ አለችና··· ''የሚገርምህ ደግሞ ምን መሰለህ! ልታከው ስትሞክር ደስ የሚል ስሜት ይሰማሃል። እከክኝ ይልሃል። ታከዋለህ። የስቃይ ደስታ ትሸምታለህ። እንዴት ደስ ይላል መሰለህ! የደራሲ ህይወት ይሄ ነው። ካልኖርክበት እንዴት ይገባሃል!'' አለች አተኩራ እየተመለከተች።

እያሳዘነችው ቡናውን አጣጣመ። ''ግሩም ቡና! በሽታው ለክሮ ሻል! የደራሲን ህይወት ተቃምሰሻል!'' አላት ተክዞ።

''በሽታው የጥንት ነው'' አለች፡ ኮስተር ብላ ''···እሁን የጨመር ኩት ነገር ቢኖር የቃላትን መካንነት መታገል መጀመሬ ነው። ቁስሌን ለማከክ እየሞከርኩ ነው። እናም ጣፋጭ ስቃይን መቅመስ እያወቅሁ ነው።''

ሲራክ ቡናውን ጨልጦ···''ድርሰት መፃፍ ጀመርሽ ግለት ነው!''

''እም፣ ግን እስካሁን የተቃና ፅሁፍና የሰመሩ ቃላት አልወጣልሽ ብሎኛል። እፅፋለሁ፣ እቀዳለሁ፣ እፅፋለሁ፣ እቀዳለሁ። መካን እናትነቴ አከትሟል። ግን እያረገዘች፣ እያማጠች የሚጨነግፉባት እናት ሆኛለሁ። ሌላው ቢቀር የምጥን፣ የመገላገልን ምንነት የምታውቅ እናት ሆኛለሁ። መቼም ማርገዝ ከማትችለው እናት ሳልሻል አልቀርም። ምክንያቱም ሌላው ቢቀር ዘጠኙን ወር እንኳን በተስፋ ትኖራለች።''

''የምትናገሪውን ብትጽፈ እንኳን በቂ ነው'' አላት ከልቡ በሆነ ስሜት። ቀዝቃዛ ፈገግታዋን እያሳየችው ''የሚገርምህ ነገር ቢኖር ነጭ ወረቀት ላይ እንደምናገረው መፃፍ አለመቻሌ ነው። የማስበውን በቃላት መግለፅ አልችልም። ሲያጠና ውሎ ፈተና ላይ ሲቀርብ ድንግርግሩ እንደሚወጣበት ተማሪ፣ የኔም ሃሳቦች ወረቀት ሲመለከታቸው ይርበተበታሉ። ይፈረጥጣሉ። ይበታተናሉ።'' ጭግቂዋን አጋመሰች።

''አቤት ፍዳችሁ!'' አለ ሲራክ።

''እንግን?''

''የኪነጥበብ ፍጡሮች።''

''ፍዳ አልከው?'' አለችው በእንክሮ እያየችው።

''የፍጹም ፍዳ።''

''አይደለም። የእናት ምጥ ፍዳ አይባልም። ምጡ እስኪወለድ ያንድ እፍታ ነው። ጭንቀቱ ምጡ የበዛ ዕለት፣ ያለዛም እንደኔ ጭንጋፍ የሆነ እንደሆነ ነው።''

''ፍዳ ማለት እሱ አይደለም!''

''ቀምሰህ ባየኸው፣ ምጥ ፈርታ መውለድ የተወች እናት ታውቃለህ''? ሲራክ ሳቀና ''በርግጥ ተለክፈሻል አንቺ ሴትዮ!'' አላት።

''ትጠራጠራለህ?''

''አዘንኩኝ''

''ለኔ?'' አለችው አተኩራ እያየችው። የአሽሙር ፈገግታ ከንፈሯ ላይ ያንጎራብባል።

''ሳይሆን···''

''ለራሴ'' አላት ሲራክ።

''ለምን?'' አለችው ባልጠበቀችው መልሱ ተገርማ

ሲራክ ካቅማማ በኋላ ''እ···'' አላት በረጅሙ ተንፍሶ። ···

Scanned with CamScanner

የኪነጥበብ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለሰው አትመቹም። ግራ ፍጥረቶች ናችሁ። እናም ለራሴ አዘንኩ'' አላት።

''አይምሰልህ!'' አለችው ድምጿን ከረር አድርጋ።

''እንዴት?''

''ለሌላው ሲሉ እራሳቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ክቡር ፍጥረቶች ናቸው። ተፈጥሮ ለሰው ተጨንቃ የፈጠረቻቸው... የግጎበረሰቡ መስታወቶች...የአካባቢያቸው ውጥረት ፍጥርቅታዎች፣ ምግባራቸውን ከአድማስ አድማስ የሚያስተጋባ!....'' አሳቧን ተናግራ ሳትጨርሰ ወደመኪናው መስታወት ፊት ለፊት እያየች በሃሳብ ትብሰለሰል ጀመር።

'እም ነዲድ ሻማዎች። የኅብረተሰቡ አንጡራ ሀብቶች፣ ተሰፈንጣሪዎች፣ በዋጋ ሊተመኑ የማይችሉ የግጎበረተሰቡ ፍልቃቂዎች። ሕይወት አጣፋጮ ቅመሞች። እም! ቅመሞች። ሆናም ቅመም በአብዛኛው ለራሱ መራር ነው።' በድንገት ከአሳቧ ወጥታ ''ይልቅስ ለራሳቸው አይሆኑም ስትል አንድ ጊዜ የነገርከኝ ልክ ይመስለኛል። ለሌላው ሳይሆን ለራሳችን ነው የማንሆነው።''

ሲራክ ፈገግ ብሎ ''ለራስሽ ካልሆንሽ ምኑን ለኔ ሆንሺው?'' አላት

''እንዴት!''

''አብራሽ መታመሚ ይቀራል?''

''በሽታው እኮ ተስቦ አይደለም።''

''ገባኝ'' አላት ፈገግ ብሎ።

''ስለዚህ አትስጋ'' ጭማቂዋን ጨለጠች።

''ግን ከአካል ይልቅ የመንፈስ ሕመም እንደሚብስ ታውቂያለሽ?'' አላት ትንሽ ካሰበ በኋላ።

''አውቃለሁ!''

''ስለዚህ በመንፈስ አብራሽ መሰቃየቱ አይቀርማ።''

መልስ አልሰጠችውም። ዝም አለችው። ትንሽ ጊዜ ጠበቃት። እንደገና አንድ ጥያቄ ሊያነሳ ፈልጓል 'እሺ ወይ እንቢ' አለ ለራሱ 'ምናባቱ!...' አለና

''ያለፈውን ጥያቄ አሰብሽበት?'' አላት ሌላ ቦታ እየተመለከተ።

''የቱን?'' አለች ተኮሳትራ እያየችው።

'ምናባቱ' አለ እንደገና በልቡ ''ጋብቻውን!''

ብልጭ አለባት። ሰውነቷን አንዳች ነገር ወረረው።

''አልመለስሽልኝም'' አላት ትንሽ ጊዜ ጠብቋት። አልተቆጣችም። ብቻ ያልጠበቀውን መልስ ሰጠችው ''ግንኙነታችን በዚሁ እንዲቋጭ ትፈልጋለህ?''

ደንግጦ ''ለምን?' አላት።

''እንግዲያው ሁለተኛ ይህንን ጥያቄ እንዳታነሳብኝ!''

''ሺት! እውነትም ግራ ፍጡሮች'' አለ

''አሳዘንኩህ?'' አለችው በቀዝቃዛ ፈገግታዋ እያየችው።

ጥያቄዋ አስገረመው። አሳዘንኩህ ብሎ ነገር፣ ስንት ጊዜ ሲያወጣ ሲያወርድ ከርሞ ሲጠይቃት ይህ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም። 'ምንድነው አሳቧ?' አለ ለራሱ፣ መልሱ ግራ እየገባው። መልስ አልሰጣትም። ዝም ብሎ ተመለከታት።

''እዝናለሁ....'' አለችው፣ ድምጿ ተቀይሯል። ''ጥያቄህን በማጥላላቴ አዝናለሁ፣ ምክንያቴ አይገባህም ይቅር፣ ግን እወድሀለሁ። አንዳች ጥርጣሬ አይግባህ። ካንተ የማቀርበው ማንም የለም። አፈቅርሃለሁ። ሲራክ....''

ዝም ብሎ ተመለከታት።

''ወይ አትለኝም?'' አለችው።

''ወይ!''

''ስምተኸኛል? አፈቅርሃለሁ። ይገባሃል? ለጊዜው ይህ በቂ ነው፣ እሺ?... አትጠራጠር አፈቅርሃለሁ'' እጇን ሰዳ እጁን ፈለገች። አገኘችው፣ ከአንደበት የተሻለ እጇ ልዩ ምስጥራዊ ቋንቋ ይናገራል።

'ግራ ፍጥረት!' አለ ሲራክ በልቡ፣ ነገሯ ሁሉ ግራ እየገባው።

* * *

በሞንቅላታ ውስጥ የሚደንሱት ቃላት ወረቀት ላይ ሲሰፍሩ፣ ለዘመናት በችግር፣ በድርቅና በቸነፈር እንደተሰቃየ ገላ ገጠመ፣ ወዘናቸው ተሟጠ ጣዕረ ሞት የሚያሰቃያቸው ይመስል መልሰው ያስፈሯታል። ''ኡፍ!'' አለች በመሰላቸት፣ እስክሪብቶዋን ጠረጴዛው ላይ ወርውራ ''ድሮስ ማን ደራሲ አደረገኝ?፣ ስሜት ሌላ ተሰጥዎ ሌላ!፣'' አጠገቧ በስኒ የተቀመጠውን የቀዘቀዘ ቡና ጨለጠችው። ውስጧ እየተተራመሰ ልውጣ ልውጣ እያለ የሚተናነቃት የስሜቷን ማእበል ቢያጸፍነው ብላ፣

Scanned with CamScanner

“ድሮም የድርሰት ተሰጥዎ ለጥቂቶች ብቻ የታደለች ክቡር ስጦታ ናት”

“ከጥቂቶች አንዷ የማትሆኚበት ምን ምክንያት አለ?”

“ኡፍ……” አለች በድጋሚ። ወረቀት ሲያዩ አሳቦቿ ለምን እንደሚደነብሩና እንደምንም አምጣ የወለዶቻቸው ቃላት ለምን እጣው እንደሚያስቀይሟት እያሰበች፣ ወረቀቱ ላይ እንዳፈጠጠች ተከዘች።

“ቢተውት ዕረፍት አይሰጥ፣ ጥዝጣዜው፣ ኡኡታው ሀሊናን ያደነቁራል። ያቅበጠብጣል። ሰላም ይነሳል…ኤጭ!”

የሼክስፒር ፀጉር ተንጨባሯል። ሊነቀል የደረሰ ይመስላል። አይኑን እጉረጥርጦ ብዕሩን አሹሎ ይቃትታል….አሚሉዌል በየደቂቃው ሲጋራዋን ትለኩሳለች፣ የተቀመጠችበት ክፍል በጭስ ታፍኖ በውስጡ ትወራጫለች፣ ጠብ የሚል የቅኔ አባዜ ፍለጋ…ባልዛክ ያዛጋል። ይንጠራራል። አውንም አውንም ቡና… ዳቪድ ኸርባርት ብቻውን ይዘላል፣ እንደእብድ ልብሶቹን ሁሉ አሽቀንጥሮ ይዘላል። ራቁቱን…የፈጠራ ችቦው አልነድ ብሎት ይወራጫል። ኢጣሊያዊው ከዛኖቫ ተዳፍኖ አልወጣ ያለውን ስሜት በውሃ አጥቦ ሊያወጣው የባኞ ገንዳ ውስጥ ተዘፍዝፎ… ደራሲው ዴዝሪሊ ይፅፋል። ብቻውን ተቀምጦ አጠገቡ በግሩም ብርጭቆ የሞላትን ሻምፓኝ እያጣጣመ… ፕሌቶ ይጽፋል፣ ይሰርዛል፣ ደግሞ ይጽፋል። አምሳ ጊዜ ዶጋማዋ የፃፋቸው እርቃናቸውን እየሆኑበት፣ መልሶ ሃምሳ ጊዜ እየሰረዛቸው…. የድርሰትን አባዜ ለማሳደድ ከባቡር ባቡር የሚንጠለጠለው ጆጅ ኤም ኮህን ይጓዛል! ይጓዛል! ግብ የለሽ ጉዞ በባቡር….

‘ድርሰት ተሰጥዎ ሳይሆን ልክፍት ነው’ አለች አዜብ በአሳቧ። ዛሮች ተሰባስበው የሚያጫፍሯት የመናፍስት ቅጥረኛ… ከአምላካቸው ሊፎካከሩ፣ ፈጣሪ ሊሰኙ እፍ ብለው እስትንፋስ ሊሰጡ…”

እግዚአብሔር አለ። ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር። የባህር ዓሶችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንሰሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ… አቤት ስልጣን!—ባረካቸው። ብዙ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሏት፣ ግዙአትም—ዲያብሎስ ተቆጣ፣ ተንከለኛው ዲያብሎስ ስልጣኑ አስቀናው፣ ብልጡ ዲያብሎስ። ወንድን የምታስት ሴት መሆኗን ተረዳ። አታለላት። ሄዋንን ‘ሞትን እንዳትሞቺ፣ አይኖችሽ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም እንድትሆኚ…’ የጥፋት ፍሬ ያስጎመጃል። ግመጡኝ ግመጡኝ ይላል። ቀመሰች ያቺን የተረገመች ፍሬ ፣ አይኗተገለጣ ። መልካም መሆኑን አየች ። ሰው ሆነች ። እሱንም አቀመሰችው ። አይኑ በራ ። ተፋፈሩ ። እግዜሩም ተቆጣ ። ተራገመ ። ምድር ባንቺ የተነሳ ትረገም። እሾህና አሜከላ ታብቅል። የአዳም ዘር ደክመሀ ብላ፣ ዞረህ ወደ አፈር ተመለስ።’

ኪሩቤል የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፉን ይዞ በኤደን ምሥራቅ በር ቆመ። ማንም እንዳይገባ የጌታውን ቃል ለመጠበቅ።

ዲያብሎስ አሳረፈም። በእግዜሩ ስራ ገባ። ሰውን ሊፈጥር፣ ቀለምን ከወረቀት አቡክቶ፣ ጠፍጥፎ በእምሳያው ሊፈጥር፣ ከፈጣሪው የተማረውን የፈጣሪን ሚና ሊፈጥር ሲታገል ጣሩ ይበዛበታል። “በፀነስሽ ጊዜ ጭንቁ ይበዛብሻል” የሚለው የቀድሞው አያቶቹ እርግማን አለበትና።

“ከዚህ ሁሉ….” አለች አዜብ፣ “ምነው የኤደኑ ገነት ጠባቂ ኪሩቤል ከነሰይፉ ቢነሳና የገነት በር ወለል ብሎ ቢከፈት?” ደግሞ አመነታች።

“በገነት ምን ይፃፋል?”

ለራሷ ፈገግ አለች። ‘ደራሲ በገነት ቢያስቀምጡትም ልፃፍ ከማለት አይመለስም። ልፃፍ ካለ ደግሞ ማማጥ ይኖራል። በገነት ደግሞ ምጥ፣ ድካም፣ ልፋት የለም። ታዲያ….ታዲያ ደራሲ በገነት እንዴት አድርጎ መኖር ይችላል?’

‘ግን እሺ፣ ኖረ እንበል፣ ግን ሰለምን ይፅፋል? አዲስ ነገር የለ። የሰው ልጅ ውጣ ውረድ ድካምና ልፋት የለ። ሰለምን ይፃፋል?’

‘ስለ እግዜሩ ነው!’

መልሷ እጅግ አድርጎ አሳቃት። ፅንባ ከአይኖቿ ተንከባለው እስኪወርዱ ድረስ ደስ እያላት፣ የውስጧ ስሜት እያፍነከነካት ሳቀች።

በድንገት በጉንጮቿ የወረዱትን ፅንባዎቿን በጣቶቿ ዳበሰቻቸው። ከሰውነቷ ሙቀት ያዘሉ ፅንባዎች በእንድ አፍታ እጆቿ ላይ ሲቀዘቅዙ ተሰማት። ቀስ እያለ ወደ ስሜት ሕዋስ የሚሰራጭ ለዛዛ ቅዝቃዜ፣ ትርጉሙ ሊገባ የማይችል ሃዘን፣ ትካዜና ብሶት ያዘለ ስሜት በመላው ሰውነቷ ሲያሰራጭ ታወቃት። የአፍታ የደስታ ስሜቷ ተኮማተረ። የአሳብ ፍልሚያዋን ትታ በንጭ ወረቀቷ ላይ ለቅፅበት አይኖቿን ሳታረግብ እንዳፈጠጠች ቀረች…

Scanned with CamScanner

ምእራፍ ሰባት

የእፀገነት አባት አቶ ጌታቸው የተከናነቡትን ጋቢ እያስተካከሉ ወደ ሳሎን ዘለቁ። የውጭው ቅዝቃዜ ጋቢውን ዘልቆ በመግባቱ ሳላቸውን አስነሳባቸው። ሚስታቸው ወ/ሮ አሰለፈች የባለቤታቸውን ሁኔታ ተመለከቱ። "ከመሽ መውጣት ምነው ቢቀርብህ?" አሉ። ብለው፣ ብለው፣ መክረውና ተቆጥተው ያቃታቸው ነገር በመሆኑ ስልችት ብሏቸው።

"ነፋሱ፣ እየሩ፣ ሲል ደግሞ እንደዛፈው ደመና ካልጋረደው ጨረቃውና ከዋክብቱን አንድ አፍታ ብትመለከቺ እንዴት ውብ መሰለሽ" አሏቸው ከውስጥ የሚተናነቃቸውን ሳል ለመቆጣጠር እየሞከሩ።

እፀገነት እናቷ ጎን ተቀምጣ ቡና ትቆላለች። ቤተሰቦቿ ዘንድ ስትመጣ በተለይ ከእናቷ ጋር ሽር ጉድ ማለት ትወዳለች። ልትጠይቃቸው የምትመጣው ሳምንት ከርማ፣ ያለዛም በአስራ አምስት ቀን ስለሆነ እጅግ አድርጋ ናፍቃቸዋለች።

አባቷ የዛሬ አመጣጧን አልወደዱትም ። ለወትሮ የምትመጣው በእረፍቱ ቀን እንጂ እንዲህ እንደዛፈው በስራ ቀን አይደለም ። ደግሞ ከመሽ ፣ በዛ ላይ ከንፈ አብሯት የለም ። መኪናም አልያዘችም ። ስለከንፈ የሰጠቻቸው ምክንያት አላጠገባቸውም ። ደክሞት ቀርቷል ብሎ ነገር ። "እንዴት መጣሽ?" ሲሏት እናትየው ጣልቃ ገብተው "እንዴት መጣሽ ይባላል እንዴ? እንኳን መጣሽ ነው እንጂ!" ብለው ቀንዳቸውን ሲሏቸው አፋቸውን ለጥመው ዐጥ አሉ ። ደግሞ አላስቻላቸውም ፡ ደገሙና ከንፈን ጠየቋት ።

አመጣጧ ቢያሳስባቸውም እናቷ አፍ አውጥተው አልተናገሯትም። ብቻ በመጥፎ እንዳይሆን ፈጣሪያቸውን በሆዳቸው እየተማጠኑ ሁኔታዋን ለማወቅ ፊቷን አትኩረው ያዩታል ። ከወትሮው የተለየ ሁኔታ አላዩባትም ።

አቶ ጌታቸው እንግዳ መቀበያ ሶፋ ወንበራቸው ላይ ገላ ብለው የቋጠሩትን ሃሳብ በአንደበታቸው ይተረትራሉ ።

"ከንፈ እዚህ መሆንሽን ያውቃል?" አሉ እፀገነትን እየተመለከቱ ፣ እናትየው በስጨት አሉና "ምነው አንተ እንዲህ ጨነቀህ?" አሏቸው እያፈጠጡባቸው ።

"እረ የለም ፡ አላወቀ እንደሆን እንዳይሰጋ ብዬ ነው ።"

"ያውቃል!" አሰች እፀገነት ፊቷን ቅሙም አድርጋ ።

"እረ ተይው ፡ ምን ላውራ ነው! ባያውቅስ የት ትሄዳለች፣ እዚህ አይደውልም? ድሮም የያዘ ይዟት እንጂ ልጂ እኔን ሳታይ ማደር አይሆንላትም ነበር ። ብቻ ..." አሉና እይታቸውን የምትቆላው ቡና ላይ ተከለው እንደመተከዝ አረጋቸው ።

አቶ ጌታቸው የሚስታቸውን ንግግር አልወደዱትም ። "የምን መቀባጠር ነው? ባራ ጊዜ ምን ያመጅል ብለሽ ነው ። ቀን ስራ ተውሎ ማታ ሲገባ ይደክማል ። በዛ ላይ ደግሞ ቤት ሌላ ስራ ይቆያል ።"

"ኤዲያ!..." አሉ እናቷ "ምን ጊዜ አለ ብሎ ነገር ፡ አውን እስቲ አንድ አፍታ ጭራ ብሎ እናትን ቤተሰብን እንዴት ዋላችሁ እንዴት አደራችሁ ለማለቱ ነው ጊዜ የሚጠፋው ? ጊዜ ብሎ ፊሊጥ አይገባኝም ። ልጅ የለ ፡ ምን የለ ፡ እቤት የሚቆይ ስራ ?" አሉ የእፀገነትና የከንፈ ልጅ አለመውለድ ሲከነክናቸው እንደከረመ ሁሉ አውንም አገርሽቶባቸው ። "... ወይ እንደኛችሁን ልጆች ወልዳችሁ ከነሱ አልሆናችሁ ወይ ደግሞ ...?" አሉና ለጥቂት ጊዜ አረፉ ብለው "ለሁለት ሆድ ሩጫ እኔ አይገባኝም!" አሉ ።

"እማማ ቤት እየሰራን እኮ ነው ። እዛም እንሄዳለን ። እቃ ለማግኘት ደግሞ ወዲህ ወዲህ ስንልኮ ነው ። " አለች እፀገነት የናቷን ቅሬታ ለማስተባበል ብላ ።

"ኤዲያ! አውን ያላችሁበት አንሏችሁ ነው?"

"እሱኮ ኪራይ ቤት ነው ።"

"ቢሆንስ ፡ ለሁለት ነፍስ ደግሞ ቤት ቤት የምትሉት ፡ ማን ሊሮጥበት ማን ሊቦርቅበት ነው? አግብቶ ልጅ ሳይወልዱ ደግሞ ሌላ ጣጣ" አሉ ከአንጀታቸው እገሃ ብለው ።

"መጀመሪያ ቤቱን ሰርተን እንጨርስ ብለንኮ ነው" አሰቻቸው ።

"ኤዲያ! ለአንድ ነፍስ መሆን አትቺችሁ ነው ። እስቲ አንድስ ልጅ ቢሆን ምን አለበት ። አሁንማ ይኸው ሶስቱ አልቯችሁ አራተኛችሁን

Scanned with CamScanner

ልትይዙ አይደል? ይሄኔ የአራት ገብ ትሆኚ ነበር ።''

እወገነት ሃሳባቸው ታይቷት ፈገግ አለች 'የአራት ልጆች እናትነ የሆነ ነገር ታሰባት ። ከክንፈ ጋር ያጋጠማት ችግር ብዙ ልጆች ከወለደች በኋላ ቢሆን ኖሮ!··· ዘገነናት ።

''ምን አለው ብለሽ ነው ይደርሳል ። የዛሬ ጊዜ ልጅ ። ዋናው እርስ በርስ ተሳስቦና ተፈቃቅሮ መኖር እንጂ የልጅ መአት ትዳር አያለመል ምም ። እንዳውም ዘመናዊዎቹ በእቅድ በፕሮግራም ማሰቡ ዕጣ ፈንታቸው ሆኗል ። እነሱው እንደሚሆነው ያቀዱት ይበጃል'' አሉ አቶ ጌታቸው ለልጃቸው ድጋፍ ለመስጠት ፈልገው ። ካለ ነገራቸው ከሲቶቹ የመጀመሪያ ልጃቸውን እጅግ ያቀርቧታል ። ከእናቷ ይልቅ እሷም ለአባቷ ነው የምታደላው ።

ከአስቴር መኝታ ቤት የባህር ማዶ ዘፈን ይሰማል ። ቤት ውስጥ ለመኖሯ ዋናው ምልክቷ የምታዳምጣቸው ሙዚቃዎች ናቸው ። ቤቱ ዐጥ ካለ አንዳች ነገር የሚወራት ይመስላታል ። ሙዚቃ ከከፈተች ደግሞ ሬሜክ ማለት አለበት ። ያለዛ የሙዚቃው ካድማ አይታረቃትም ። ስሜትን እየሸነሸነ ጆሮ የማይደልቅ ሙዚቃ ሙዚቃ አይመስላትም ። የትዝታን ዜማ ለይታ አትወድም ። ከሬዝ ለዛውን ያጣል ፡ ቀስ ካለ ደግሞ 'የምን መሚዘገ ነው' ያሰኛታል ። አቶ ጌታቸው ጆሮ ከሚበጥስ የከበሮ ኳኳታ የሚገላግላቸው ነው ያጡት ። በልጃቸው የጥዋት ማታ ሙዚቃ ምርጫ ይደነቃሉ ። ''ምን በሽታ ነው?'' ሳይሏት አያልፉም። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አገባዳ ቤት መዋል ከጀመረች ወዲህ ዋነኛ ስራዋ ሙዚቃ ማዳመጥ ሆኗል ። መዕሀፍ ማንበብ ከጀመረች አምስት ቢበዛ አስር ደቂቃ ከሆናት ጭንቀ ጭንቅ ይላታል ። መዕሀፉን የያዘችበት እጇ ሳይቀር እየዛለ ድካም ይበረታባታል ። 'የምን እዳ ነው?' ብላ ወርውራው ትንሳለች ። ትንሽ የምትበረታው የወንድ ጓደኞቿ ስልክ የደወሉላት እለት ነው ። ሶፋው ወንበር ላይ አንዴ በግራ ጐኗ ፡ መልሳ ደግሞ በቀኟ ጋደም እያለች ፡ ያላት ቀን ከመቀመጫዋ ዘርጠጥ ከወገቧና ከትከሻዋ ዝቅ ብላ እግሯን ከፊት ለፊቷ ካለው ጠረጴዛ ላይ ዘርግታ በእጅጉ እየተገናኘች በስልክ ግውራቱን ታውቅበታለች ። የምትፈጀው ሰአት እጅግም አይስተዋላ ትም ።

አቶ ጌታቸው ከሚያዳምጡት የአስቴር ሙዚቃዎች ተመልሰው ስለ እወገነት ያውጠነጥኑ ገቡ 'ዛፊ ደሞ ያለወትሮዋ አመሸች ሶስት ሰዓት

ሊሆንኮ ነው ።?

ከውጭ ወደ ግቢው መኪና ሲገባ ይሰማል ። ማን እንደሆነ ሁሉም አላጡትም ። የመጀመሪያ ልጃቸው ኤርምያስ ነው ። አቶ ጌታቸው የመኪና ሞተሩን ድምፅ ሲሰሙ የተመለከቱት የእጅ ሰአታቸውን ነው።' ''ዛሬስ በጊዜ ገባ'' አሉ እያጉተመተሙ ።

ኤርምያስ ሳሎን ሲገባ ግራ የመጋባት መልክ ፊቱ ላይ ይነበብበታል። እወገነትን ለአፍታ ከአያት በኋላ ፈገግ ብሎ ፡ ''ዛፊ እንዴት ነው?'' አላት በጐርናና ድምፁ ከላይ እስከታች አያስተዋላት ።

በእወገነት አይን ፡ ጥቁሩ የኤርምያስ ዒምች አስጠልተውበታል ። አጥንት አሟኝተው የሚቀራመት የጉንዳኖች ይመስላሉ ። እጐንበስ ሲስማት ''መኪናህ ነዳጅ አለው?'' አለችው ።

''አዎ ምንው?''

''ታደርሰኛለህ!''

ኤርምያስ ይበልጥ ግራ እየተጋባ ''አልመሸም እንዴ? ሳይሽ የምታድሪ እንጂ የምትሄጂ አልመሰለኝም'' አለ የአገጩን ስር ዒም እየሎተተ ።

''እውነቱን ነው መሽቷል! ለምን አታድሪም? ለክንፈ ደውለሽ ንገረው ። ዳሩ ስተቀረበት እሱስ መደወሉ ይቀራል?'' አሉ እናቷ ።

አቶ ጌታቸው አስተያየት አልሰጡም ። እንዳልሰማ ሆነው ሁናቴውን ይከታተላሉ ።

''በፍፁም!'' አለች እወገነት በድንገት ከመቀማጫዋ እየተነሳች'' እንዳውም አሁን መሄድ አለብኝ ፡ በጣም መሽቷታል ።''

''እንጂ ደግሞ!'' አሉ እናቷ ፡ ''እናት አባትሽ ቤት ብታድሪ ምናለበት'' አሉ በተቀመጡበት አካላቸውን እያንቀሳቀሱ ።

''የለም መሄድ አለባት!'' አሉ አባትየው ቆፍጠን ብለው ።

ወ/ሮ አስለፈች መታወሙ የሚያዋጣ አልመሰላቸውም ፡ ''ባይሆን ቡናው ይክተም'' አሉ መንፈሏቅ ብለው ።

እወገነት አሳቧ ለሁለት ተከፈለ ። ብታድር ደስታዋ ነው ። በተለይ ሰሞኑን ክንፈ ያመጣው ወባይ ከትእግስቷ በላይ ሆኖባታል ። እሱ እንደዛ ሲበሳጭ ላለማየት የትም ሄዳ ብታድር ግድ አልነበራትም ። እንድ ዕት አላማ ያለው ክቡር አካል ያረከሰች ያህል ይሰማታል ። ከንፈን ስታይ ፡

Scanned with CamScanner

ምክንያቱ እሷ እንደሆነች ስለሚሳማት ፡ መንፈሷ እየተሰቃየ ሀሊናዋ በጥፋተኝነት ጦር ይጠቁጠቃል ።

''መሄድ አለብኝ'' አለች በመጀመሪያ ሃሳቧ ወንታ ።

የእናቷን ጉንጭ ስማ ፡ አባቷን እጅ ነስታ ተሰናብታ ከኤርምያስ ጋር ተያይዛ ከመውጫቷ በፊት አስቴር መኝታ ቤት ገባች ።

''አታድሪም እንዴ? አለቻት አስቴር በእንክሮ እያየቻት ። አስቴር ብዙ ጊዜ ከቤተሰቧ ጋር አትቀላቀልም ። መኝታ ቤቷ ተቀምጣ እንቱ ፈንቶውን ስታብሰለስል ፡ የባጥ የቆጡን ስታወጣ ስታወርድ ጊዜውን ብቻዋን ትጨርስዋለች ። በሷ አሳብ ስሜቷ በፍፁም ከቤተሰቦቿ ጋር የሚገጥምና የሚሰምር አይመስላትም ። የዛሬ ነች ። እነሱ ደግሞ የትናንት! ገና በልጅነቷ የእለፀ ፡ የማን አለብኝነትና የበላይነት ስሜቶች ተጠናውተዋታል ። የመጨረሻ ልጅነቷ ደግሞ ቤተሰቦቿ ያሰችውን እንዲቀበሉ ዳርጓቸዋል ። አስቴር ታላቅ እህቷን እፀገነትን እንደ የዋህና ጅል ትቆጥራታለች ። እንደሷ ሃሳብ ቀዝቃዛና የማትሞቅ ነች ። ያ ባይሆን ኖሮ ከንፈን አታገባውም ነበር የሚል አመለካከት አላት ።

በአስቴር አይን ከንፈ ስሜት አይሰጥም ። ሽቅርቅር አይደለም ። እናም ውበት የለውም ። ደግሞ ዝምተኛ ነው ፡ እንዴት ስሜቷን ሊኮረኩር ይችላል? የሚገርመው እፀገነት በከንፈ ፍቅር ተጨምድዳ መያዟ ነው ።

እፀገነት አስቴርን ተሰናብታ ስትወጣ ፡ አስቴር ለመጀመሪያ ጊዜ የእህቷ ህዘን ተሰማት ። እንደ ታላቅ እህት የበላይነት ስሜት አሳይታት አታውቅም ። ብታናድዳት እንኳን ጨዝቷን እንደገደል ማሚቶ መልሳ ስለምታስተጋባላት ሁለቱም ተያይዘው ይጫጨኺሉ እንጂ አንዳቸው ለአንዳቸው የበላይነት ስሜት አሳይተው አያውቁም ። ሁሉን በፀጋ ይቀበላሉ ።

''ዒምህ አልበዛም?'' አለችው እፀገነት በጨለማው ውስጥ ወደጐን ልታየው እየሞከረች ። ኤርምያስ በአንድ እጅ መሪውን በሌላው ደግሞ የታዘበችውን እየዳበሰ ''ይሄን ያክል ያስጠላል'ንዴ?'' አላት በመጠኑ ፈገግ ብሎ ።

''ማስጠላት ነው! የገዳም ባሕታዊ መስለሀል ።''

ኤርሚያስ ፈገግ አለና ''በእያንዳንዳችን የሀሊና ንዳ የራሳችን ገዳም ሳይኖረን ቀረ ብለሽ ነው? እካላችን ባይመንን ሀሊናችን ይመንናል ። ያን ጊዜ ሁሉም ይረሳል'' አላት አሁንም በመዳፉ ፂሙን እየፈተገ ።

መኪናው ጨለማውን እየቀዶደች ከልደታ በሚከሲኮ በኩል አድርጋ ጉሙዋን ወደ ገነት ሆቴል ቁልቁል ተያይዛዋለች ።

በእፀገነት ሕሊና ውስጥ አንድ ቁም ነገር አለ ፡ ልውጣ አልውጣ እያለ ከሃሳቧ ጋር ጋሻና ጦር ተማዞ የተፋጠጠ ።

'ኤዲያ! ለአንድ ነፍስ መሆን አቅታችሁ ነው ። እስቲ አንድስ ልጅ ቢኖራችሁ ምናለናበት'

'ሰይሆን ፡ እማዬ ሳይሆን...'

'እና ምንድነው?'

መልስ የለም ። ከአዕምሮዋ ጓዳ ጉልበት አጥሮት ወኔ አጥቶ ተልፈሰሰ የቀረ መልስ አለ ። የድፍረት ፡ የቆራጥነት እርምጃ የሚጠብቅ።

''ስራ እንዴት ነው?'' አለች እፀገነት ታላቅ ወንድሟን እያየች ፡ ወደመንደሯ መዳረሷ ነው ።

''ምን ስራ አለ ብለሽ ነው! ዒልት ፡ ፈዝና ቀልድ አደናቁረውት ። ያንንም አጣጥመን እንድንውጥ በየደቂቃው በየሰአት ሻይ ፡ ቡና ማኪያት... ወጪ ብቻ ፡ የምናስገባው አንድም ነገር የለም ። ለስራ የሚያነቃቃ አንዳች መንፈስ የለም ። የስራን ፍሳጐት የሚያነሳሳ ሁኔታ የለም ። ቢሮክራሲው እግር ከወርች አስሮ መፈናፈኛ አሳጥቶናል ። ያላንሰን ደግሞ እርስ በርስ በምቀኝነት ፡ በስግብግብነት በተንኮል ፡ እንዱ ላንዱ የተንኮል ገመድ ሲገምድ ፡ አንዱ ባንዱ ጀርባ ተንጠልጥሎ ለመውጣት የሌላውን ላብና ድካም እንደፈረስ ኮርቻ ሲያደላድል ፡ አልሆንለት ካለው በሾኪ ሲያወርደው እያየን ፡ እንዳንራመድ ሾኪውን ፈርተን ፡ ተንጠላጥለን እንዳንወጣ ገመዱ ርቆብን ፡ ያውም ምን ሊሰራ ብቻ እንዲሁ ባለንበት ለመርገጥም ዋስትና አጥተን አለንልሽ'' ብሎ በእጅ መዳፍ መሪውን መታና ''ጡሩምባ ላሰማልሽ?...'' አላት የቤቷ አጥር በራፍ ላይ መኪናውን አቁሞ ።

''አሰማቸውና ልውረድ'' አለችው የመኪናውን በር መክፈቻ በእጅ ጻበሳዋ እየፈለገች ።

''ለምን ወይውስጥ አላስገባሽም?''

አቅማማች ። ''ግዴለም ፡ ምንም አትሠራም ፡ መሽቷል ። ደግሞ አባባ እንዳይቆጣ በቀጥታ ወደ ቤት ተመለስ'' አለችው በፈገግታዋ እያባበለችው ።

Scanned with CamScanner

“አይ ማዬለም ፡ እንድ ለመንገድ ብዬ እመለሳለሁ ። ዛሬ ያንቺ ውቃቢ ነው መሰልኝ በጊዜ አክለፍልፎ ቤት ያስገባኝ ።”

“ብዙ ታመሻለህ እንዴ? “አለችው አተኩራ እያየችው ። ብዙ ጊዜ እንደሚያመሽና ሲለውም እንደሚያድር ቤተሰቦቿ በምሬት ሲናገሩ ብትሰማም ከሱው አፍ ለመስማት እየፈለገች ።

“እም ባይበዛም ።”

“ምን ስትሰራ?”

ኤርምያስ ፈገግ አለ ። የምዕት ፈገግታ ። “ህሊናዬም ፡ አካሌም ፡ መንፈሴም ሲሸረሙጥ ፡ ያን ሰአት ነፍሴ ብጤዎቿን ፍለጋ አስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ትማሰናለች ። ለዚሁ ነው” አላት ።

“ተው ኤርሚ!…” ከማለቷ አቋረጣት ፡ አሳዛኝ ምልጃዋን ሊሰማ አልፈለገም ። በመዳፉ ማንባሩን በ;ንይል እየፈተገ “ምክርሽ ይገባኛል እዚ! ጭንቀትሽም ይሰማኛል ። ያንቺ ብቻ አይደለም ። የእናቱ ፡ የአባቱ ፡ የሁላችሁም ። ግን ምን ታደርጊዋለሽ! ህይወት እንቆቅልሽ ነች ። ከትናንት ወዲያ አብዮት ፡ ዐረ አብዮት ፡ መሃል ሰፋሪ ፡ አድርባይ… እያሉ መማቢያ መውጪያ እንዳላሳጡን ፡ እንዳላንከራተቱን ፡ ዛሬ ደግሞ ትናንት ወጣት በአይናችን አንይ ባሉበት መንፈስ በየመስሪያ ቤቱ ፡ በቢሮክራሲው ትብታብ ራሳቸውን አቆላልፈው የሰራተኛውን የመስራት ፍላጐት ያሽመደምዱታል ።

“ ‘እኛ ብቻ ነን የምናውቅልህ’ ሲሉ ትንሽ እንኳን ይሉኝታ የላቸውም ። ትናንት በጠመንጃ አፈሙዝ እንዳላራወጡን ፡ ዛሬ ደግሞ መልካቸውን ቀይረው በቋንቋችን እያዜሙ ፡ በቁስላችን እያላገጡ ፡ ቁልቁል እየተመለከቱ ይላለቁብናል ። ለኔ ሕይወት ‘ትራጀዲ’ ለመሆኗ ከዚህ የበለጠ ምስክር አልሻም ። እሺ ፡ ለሌላውስ ይሁን ፡ እኛ ግን ማለት የትናንት ማንነታቸውን የዛሬ ምንነታቸውን እምናውቅ ምስኪኖች ፡ ጩኸታችን የቁራ እየሆነባቸው እንደእብድ ፡ ሰካራምና ከንቱ ነገር እንቆጠራለን ። ብቻ እዚ አይገባሽም ። ግን… ግን እኔ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም?” አለና በምሬት ደረቱን በ;ንይል ደለቀ ።

“ኤርሚ ፡ አውንም ይህንን ነገር አልተውክም እንዴ?” አለች እወገነት በስጋት አይን እየተመለከተችው ።

“አይገባሽም ‘ኮ እዚ! አይገባሽም! ስራ በጥሩ ሁኔታ እንዲካሄድ ሃሳብ መስጠት ፡ በየሳምንቱ እየተሰበሰቡ ‘ውይይት’ እያሉ በስራ ሰዓት አብሯቸው አለማላገጥ የሥራ ጠር ያሰኛል? ‘እንዲህ ይሁን ፡ ይሄ ይደረግ’ ብሎ ሃሳብ ማቅረብ ሠራተኛ ማሳደም ነው? እዚ ዛሬ ኮ አፈሙዛቸውን ያነጣጠሩብን አካላችን ላይ ሳይሆን ፡ ሞራላችንና መንፈሳችን ላይ ነው ። መልሰው ‘ሰካራም! ሽርሙጣ!’ እያሉ ሊያላግጡብን!

“…እዚ ያኔ ጀርባዬን ያልተፈቀፈቀ የሽንኩርት መከተፈያ እን ጨት አስመስለው የተለተሉኝ ምን ባጠፋሁ ነው? ታስታውሻለሽ ያን ቀን?” ብሎ አፈጠጠባት ፡ ያሳለፈው ክፉ ቀን እየታሰበው ።

አም! ታስታውሳለች ።

በር በተንኳኳ ቁጥር ስትበረግግ ። አልፎ አልፎ እንደምንም ጨክና ጀርባውን ስትመለከት ስሜቷ ሲሳቀቅ ፡ የጀርባውን ቁስል ለማድረቅ የሚቀባው መድሀኒት በቆጠቆጠው ጊዜ የሚያሰማው የስቃይ ሲቃ ሊያሸማቅቃት – በዛ ላይ ብቸኛ ወንድሟ ነው ። ለቤተሰባቸውም ብቸኛ ወንድ ልጃቸው ።

በቤተሰቦቻቸው ብቻ አልነበረም መቅሰፍቱ የወረደው ። በመላው ኢትዮጵያ እንጂ ፡ አብዮተኛ ፡ ዐረ–አብዮተኛ ፡ ግራ ተራማጅ ፡ አናርኪስት ፡ ትሮትስካይት ፡ ማኦይስት ፡ ማርክሲስት ፡… እየተባለ ፡ ምላጭ ለመሳብ ፡ አካሄድ ፡ አሳሳቅና አለባበስ ሳይቀር ምክንያት የሆኑበት፡ ከምንጊዜ ይበልጥ የሽብጥና የጠመንጃ አፈሙዝ አፋቸውን ከፍተው ብዙሃኑን የሰለቀጡበት ወቅት ነበር ።

ኤርምያስ በዐረ– ደርግ አቋሙ በመጠርጠሩ እስር ቤት ከገባ ወር ከሞላው በኋላ ነበር ቤተሰቦቹ ባደረጉት ከፍተኛ የምልጃ ጥረት ጀርባው በጅራፍ ተተልትሎ ውስጥ እግሩ መራመድ በማይችልበት ሁኔታ ቆሳስሎና ከሰውነት ውጭ ሆኖ ነው የወጣው ። ያም ሆኖ የልጃቸውን በህይወት መትረፍ የተአምር ያህል እያወሱ ሲኖሩ ፡ እሱ ግን የህሊናም የአካልም ጠባሳ ይዞ ቀረ ። የገላው ጠባሳ ቢሽርም የህሊናው ጠባሳ ግን በህይወቱ ሙሉ ያገረሽበት ጀመር ።

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየባሰበት መሄድ ጀምሯል–ምክንያት አለው ። “ኤርሚ ፡ መርሳት አለብህ’ኮ ። ሁኔታውና ወቅቱ ካለፈ ብዙ ጊዜ ነው ። ያ ሁሉ ዘመን አልፎ በሰላም እዚህ መድረስህ ቀላል አይደለም። ስንቱ ሞቶና ተረስቶ ቀርቶ የለ’ንያ?” አለችው በውስጧ የተፈጠረው ጭንቀት እንደምንም ልውጣ እያለ እየታገላት ።

Scanned with CamScanner

"መረሳቱ አይደለም የሚገርመኝ" አለ በረጅሙ እየተነፈሰ "እኔስ ቤተሰቦቼ የግፈኛን ጉልበት ስመው ፡ ተበድረውም ሆን ተለቅተው ያከፈሉት ገንዘብ ህይወቴን ከአረመኔዎች እጅ ታደጓት ። ምንም የሌላቸው ምስኪኖችስ እዚ? የስንቱ ደም ነው በአውላላ ሜዳ ላይ ፈሶ ወሐይ ያንጨረጨረው ። ዛሬ ያ ሁሉ ተረሳና…" የዕንባ ሲቃ ተናነቀው ።

እፀገነት የምታደርገው ጠፋት ። እንዴት እንደምታዕናናው ግራ ገብቷት እያለ፡ "ደግሞኮ ስካራም ሽርሙጣ ይሉኛል ። አዎ ነኝ! ሽርሙጣም ስካራምም ነኝ! እንግዲህ ምን ይጠበስ!" አለ ለራሱ እንደሚያወራ ።

"የፈለጉትን ቢሉ አንተ ምን ችገረህ ኤርሚ?" አለችው በእህትነት እየተቆረቆረችለትና በሌላ በሁልም ልታዕናናው ፈልጋ ።"

"ይህንን የሚለው አለቃዬኮ ነው ። ታውቂያለሽ? አለቃዬኮ ነው!"

"ይሁን! አንተን ምን ችገረህ?" አለች ሆን ብላ እያናናቀች ።

"ምንችገርህ አልሺኝ እፀገነት? እስቲ አንድ ነገር ልጥይቅሽ?" አላት አትኩሮ እየተመለከታት ።

"ምንድነው?"

"ያኔ ተገርፌ ስወጣ ሰውነቴ እንዴት እንደነበር ታስታውሻለሽ አይደል?" አላት ገፅታዋን እያስተዋለ ።

እፀገነት ማስታወስ ባትፈልግም ዳግም በአይነ ህሊናዋ መጣ ። የተተፈተፈ ጀርባ … ቆሳስሎ የፈነዳ የእግር መዳፍ … የከሳና የበለዘ ፊት… ሌላው ቢቀር ጀርባው ላይ የቀረው የጅራፍ ቁራጭ ፡ ውስጥ ተቀብሮ በቅርቡ አመርቅዛ የወጣችው በቀዶ ጥገና ነው ።

"አዎ!"

"ጥሩ! እንዲያ ቆሞ ያስገረፈኝን ሰው ብታገኚው ምን ታደርጊዋ ለሽ?…"

ታያት! ጥፍሮቿን እሹላ ፊቱን ስትቦጫጭቀው ፡ በጥርሷ ሰውነቱን እየነከሠች ስትገነጣጥለው ፡ የወንድሟ ገላ እንደተተፈተፈ የሱም ገላ… ስሜቷ አወራጫት… ጥቂት ቆይታ ግን ጥያቄው ግራ አጋባት ።

"እንጃ ፡ አውን ምን እንደማደርገው አላውቅም " አለች በእርግጥ ብታገኘው ምን እንደምታደርግ ግራ ገብቷት ።

"እዎ እኔን ግራ ያጋባኝ ይሄው ነው ።"

"እንዴት?"

"ያ ሰው!… ያ ሰው ዛሬ መስሪያ ቤት አለቃዬ ሆኗል ።"

"ዋቴ? "እፀገነት ይበልጥ ተደናገጠች ።

"ሲገርፈኝ ሲያስገርፈኝ የነበረው ራሱ!"

እፀገነት አይኖቿ ፈጠጡ ።

ኤርምያስ በእሽሙር ፈገግና "አይድነትሽ እዚ! ዛሬ እሱ አልጨነቀኝም ። ባለፈው በተደረገብኝ ሁኔታ ቂም አልይዝም ። ልክ ስራ ስራ አልሰራ ፡ ለመሰለው አላማ የመሰለውን አድርጓል ። እኔን ግን የሚያቃጥለኝ ከሱ ወዲያ ለስራ አሳቢ የሌለ ይመስል ፡ በተለያ ባለፈው የፖለቲካ ትግል ድል የባረቀብን ፡ ከሀገር ውድመትና ጥፋት በቀር ሌላ የማንመኝ ተደርገን መታሰባችን ፡ ሞራላችን እንዲላሽቅ ፡ የስራ ፍላጐታችን እንዲሞት ለምን እንደሚደረግ ነው ። የጓደኞቼና የወገኖቼ ደም በከንቱ የፈሰሰ እስኪመስለኝ ድረስ እየተሰማኝ የምሰታየው አንሶ ፡ እኔን እንደ አንድ የሀገር ኑቀርሳ ለምን ይመለከቱኛል ። ይኼኔ ነው የህሊናዬ ሰላም እየደፈረሰ ፡ ሳልወድ በግድ በውስጤ ያልነበረ ቂም እየፈጠሩብኝ መልሶ እንዲያገረሽብኝ የሚያደርጉኝ ። እያወቅን እንዳላዋቂ፡ እየሰራን እንዳልሰራን ፡ ያም አንሶ በቢሮክራሲው ገመድ ተብትበው እርስ በርሳችን ሊያባሉን ሲያናክሱን ሳይ ነው ፡ ምን ልበልሽ መንፈሴ የሚቧጠጠው"

"ሁኔታውን ለምን ለበላይ አታሳውቅም?" አለች በትካዜ ተውጣ ።

ኤምርያስ ፈገግ ብሎ ፡ "አይ እዚ! አላይ ላለ ጆሮ ማን ይቀርብ ብለሽ? ለዚያውስ ምን ሊፈይድ? 'የዓሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ' ሲባል አልሰማሽም ። ቀድሞ ነገር እነማን ምን ሆኑና" ብሏት የመኪናውን ሙሩምባ ተመኒነው።

"ለምን ሌላ መሥሪያ ቤት አትቀይርም?" አለች ለጊዜው የተገለጠላት መፍትሄ ይሄው ብቻ ስለነበር ።

"እሱንም ሞክሬ ነበር ። ግን በዛሬ ጊዜ መስሪያ ቤት መቀየር መች እንዲህ የዋህ ነው!

"ታዲያ እንዴት ይሻላል?" አለችው ጭንቅ ብሏት ።

"አይዞሽ እዚ…" አላት እየሳቀ "… እስከዛው አካሌንና መንፈሴን አሸረሙጠዋለሁ ። መቼም የህሊና ሽርሙጥና ያህል አይከፋም" አላትና ትርጉም የለሽ ፈገግታውን ፈገገላት ። ይህን ተባብለው እሷ ወደቤቷ ፡

Scanned with CamScanner

እሱም ወደ መንገዱ ።

እፀገነት ፡ እንደዛን ቀን ፡ ፈገግታው አስጠልቷት አያውቅም ።

* * *

ክንፈ ያመነታል ። ድካሙ ፡ ጥረቱና ልፋቱ ሁሉ መና እንደሆነበት ሰው በሃሳብ ይባዝናል ። ቤት የመሥራት ጣጣው ፡– ሲሚንቶው ፡ አሸዋው ፡ እንጨቱ ፡ ድንጋዩ ፡ ቀለማቀለሙ ፡ መስኮት ፡ በር ፡ መስታወት፡ ቆርቆሮ ፡ ኮርኒስ ። ለዚሁ ሁሉ ወረቀት ··· የድጋፍ ወረቀት ··· የቀበሌ ··· የፍርድ ሽንጎ ··· ጣጣው እጅ እጅ ብሎታል ።

በዚያ ላይ ገና ከትምህርት ቤት ሲወጣ የገዛት ቮልስ ዋገን መኪናው፡ ለዛውም አሮጌዋን ነው የገዛው ፡ ጎማ ፡ የፍሬን ሽራ ፡ የማርሽ ጥርስ ፡ አስታርተር ፡ ··· ሰሞኑን ደግሞ ካቅም በላይ እየጫንካት ምናምኗን ሰብረሃል አሉት ። የጋራዥ ሠራተኞቹ እንኳን የሚጠሩት የእቃ ስም ራስ ያዙራል ። ለዛውም እነሱጋ የሌለ ዕቃ !

ያን የሰጡትን የዕቃ ስም ይዞ በየዕቃ መለዋወጫ ሲሄር ··· የለም ! ··· የለም ብቻ ። ያው የፈረደበት ሱማሌ ተራ ይገላግለዋል "የለም ··· ካፋቸው አትወጣም ። ባይሆንም የከበቡት ጮሌዎች ሮጥ ብለው ሄደው ሲመለሱ ፡ መኖር አለ ፡ ግን ···" ይሉና ለዘይቱም ለግራሶውም እንደ ፎጣ በመጥረግ የሚጠቀሙበትን "ኪንኪ" ፀጉራቸው እያከኩ ···" ዕቃው አልጠፋም አሉ ፡ ውድ ነው'ንጂ አለ" ። ይሉታል ። ለሱ የተወደደበት እነሱን ያሳዘነ ይመስል እያስተዛዘኑ ፡ ያውስ መኪና ይዞ ላልመጣ እነሱ መቼ ግድ ይኖራቸውና ። እሱን እያዋሩ ባለመኪና ከመጣ ከአጠገቡ ይሰውሩብታል ።

ቶሎ መናደድ ትቷል ። ዝም ብሎ ብቻ ይስቃል ። አንዳንድ ጊዜ እሱ ራሱ የኑሮ ስርአትን ያንደለና ያቃወሰ እየመሰለው ይጨነቃል ። በስንት መከራ ከስንቱ ተዋክቦ የገዛውን አሮጌ የመለዋወጫ ዕቃ ይዞ ወደ ጋራዥ ገሰገሰ ።

መኪናው የለችም ።

"የት ሄደች ?" አለው ባለጋራዡን እየተመለከተ ።

"ትመጣለች ፡ ለሙከራ ይዘዋት ወጥተው ነው ።"

"ዕቃውን መች አመጣሁና ነው ለሙከራ የምትወጣው ?"

"ከሌላ መኪና አውጥተን ገጥመንላት ነው" አለና እጥመተመ ባለጋራዡ ።

አልተቆጣም ። ሳቁ ብቻ ሳቁ መራራ ሆነበት ። "እሺ !" አለና የገዛውን መለዋወጫ ዕቃ ሰጥቷቸው ተመለሰ ።

መንገድ ላይ አመነታ ፡ በመጨረሻ አምኖበት ወደ ቤቱ አዘገመ ። ሰሞኑን እጅግ እንዳበዛው ታውቆታል ። ያለ ልክ ይጠጣል፡ አንዳንድ ጊዜ ያለበትን አስኪረሳ ድረስ ። እንዳንዴ እፀገነት ስታማርር ይሰማታል ። ምንም አይላት ብቻ ይስቃል—መጥፎ ሳቅ ።

'ጠንካራ ሰው ማለት ···' ይለዋል ሀሊናው ፡ 'ጠንካራ ሰው ማለት በደረሰበት መጥፎ አጋጣሚ ሳይረበሽ ፡ ሊወጣው የሚችለው መሰላል የሚያበጅ ነው ። ያለዛ ! ያለዛ !' ··· ዛቻው እሸበረው ።

'ያለዛ ! ምን ?'

'ያለዛማ ! ያለዛማ ! አወዳደቅህ የሳጥናኤል ፡ የአላማህ ግብ ደግሞ እንደ ባቢሎን ግንብ ይሆንብሀል ።'

ፈገግ አለ ። ከመንገዱ ዳር ባለው ቤት በር ላይ ቆማ የነበረች ኮማሪት ትቅለሰለሳለች ። አላስተዋላትም ። ዝም ብሎ አለፋት ። በሩ ላይ እንደደረሰ ሳያንኳኳ ጥቂት ቆየ ። የቆርቆሮው አጥር መዝመም ጀምሯል ፡ ቤት ሰሪ ከሆነ ወዲህ የኪራይ ቤቱን መንከባከብ ትቶታል ። አትክልቶቹ እየጠወለጉ ናቸው ። የመኪናው መግቢያ በር እንኳን ተስተካክሎ መዘጋቱን ከተው ብዙ ጊዜ ሆኖታል ።

በድንገት ሽፈራውን አስታወሰ ፡ የቦሰና ቤት በአይነ ህሊናው መጣበት ። ሽፈራው ከማግባቱ በፊት አ ሮት የሚኖር ወንደላጤ ጓደኛው ነው ። ጥሩ ጓደኛ ። ለውጥ የሚወድ ፡ አዲስ ነገር የሚናፍቅ ፡ ለዛም ሲል ከማድረግ ከመለወጥ የማይቦዝን ታታሪ ፡ ያኔ አብረው ሲኖሩ በየቀኑ ቤቱ ውስጥ አንዳች ለውጥ ሳያይበት አይቀርም ነበር ። የወንበሮ ቹን አቀማመጥ ይለዋውጣል ፡ ወይ ደግሞ የሁለቱን አልጋዎች ቦታ ይለዋውጣል ። በእመት አንድ ጊዜ የቤቱን ቀለም በራሱ ፈቃድና ምርጫ ራሱ እየቀባ ይለውጠዋል ። ክንፈ በዚህ ተፈጥሮው ያደንቀዋል ። ይወደዋልም። 'የቦሴን ቤት ብቻ ነው ሰልችቶት ያልተወ' አለና አሁን ፈገግ አለ ። ከማግባቱ በፊትና ካገባ በኋላ የነበረውን ህይወት ሲያወዳድር ፈልጎ ልዩነቱን ሳያጤን በሩን መቆርቆር ጀመረ ።

Scanned with CamScanner

በአንድ ሳሎን ፡ መኝታ ቤት ፡ ባኞ ቤትና ወጥ ቤት ከውን ያለችው ቤቱ ፡ እርሱ ከሰራላት የሰራተኛ መኝታ ቤትና ዕቃ ቤት ጋር ። ለቤቱ ልዩ ፍቅር አለው ። ቤቱ ቤቱ ማለትን አስተምራዋለች ። በተለይ ወንደላጤ በነበረበት ጊዜ በቤቷ ውስጥ ብዙ ትዝታዎች ነበሩት ፡ የሱ ብቻ ሳይሆን የጓደኞቹም ።

የማግባትና ልጅ የመውለድ ሃሳብና እቅድ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ቤቱን የመቀየር ፍላጎት ፈጽሞ አልነበረውም ። እውንም ቢሆን ቤቱን ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት አይሻም ። እሱ ሲለቅ እንደምንም አግባብቶ ሽፈራው አንዲገባበት ነግሮታል ። ቤቱ ፡ ያኔ ሊያገባ ሲል ፡ ሽፈራው አንደቀባው ነው ። እፀገነት መጥታ አንዳንድ አዳዲስ እቃዎች ከመጨመራቸው በቀር የእቃዎቹ አቀማመጥ እንኳን ብዙ ለውጥ የላቸውም ። መልቀቃችን አይቀርም በሚል ስሜት ዕፀገነትም ብዙ እተጨነቅም ። ከንፈ ሳሎን ገብቶ ትልቁ ሶፋ ወንበር ላይ ተቀመጠና ከፊት ለፊቱ የነበረውን ባለአራት ተደራቢ የመፅሀፍ መደርደሪያ ተመለከተው ። መደርደሪያው በመጻሕፍት ቢሞላም ሁሉም ከሶስት አመት በፊት የገዛቸው ናቸው ። ካገባ በኋላ መፅሀፍ ገዝቶ የማንበቡን ፍላጎት ምን እንደሰለበው እያሰበ ግራ ገብቶት ተገረመ ። መልሶ ደግሞ ራሱን አዕናና ፡ ብዙ ጣጣ ነበረበት ። አውንም አለበት ። ባለትዳር ጣጣው ብዙ ነው ። የጐደለ ይሞላል ። በተሰበረ ይተካል ። ለቅሶው ፡ ሰርጉ ማህበሩ ፡ በሁለት ወገን ይሆንና ይበረክታል ። ጊዜውም የዛኑ ያክል ያጥራል ። ከትዳር በኋላ ኃላፊነቱ ይከብዳል ። ቤተሰብ ዋስትና ይፈልጋል ። እና መመጥረጥ የለም። መስሪያ ቤት ሀላፊነት ያሰጣል ። ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ባሉት የህይወት ጥርቅሞች ውስጥም ያሳትፋል ። እድር ተፈልጎ ይገባል ። ወደፊት ሊሚመጡት ነፍሶች መቀበያ አንቀልባ ፡ ለህመም ፡ ለድንገተኛ ነገር መጠባበቂያ ገንዘብ ፡ የጎጆ ቅሪት ፡ ድንገት እንኳን ቤት ውስጥ የሚበላ ቢታጣ ሮጥ ብሎ ሆቴሎች ደጃፍ መንቀዋለሉ ሁሉ ይቀራል ። ጥራጥሬ መጀጠሪያ ከረጢት ፡ የእህሉ በርሜል ሁሉ ሳይቀር ማጀት ያጣብባል ። ለዚያ ሁሉ ደግሞ ደህና ቤት ያሻል ። አቅም በፈቀደ ሁሉም ማደሪያውን ያቀናል ። ይቀልሳል ። ትደር ስፋት ነው ። ትዳር መብዛት ነው ፡ እኔነታችንን አውልቀን እኛነታችንን የምንጎናፀፍበት ሽማ ነው ። እና ጣጣው ብዙ ነው ።

'ቢሆንም !' አለ ከንፈ ከንፈ 'ቢሆንም ለማንበብ ጊዜ ማጣት

አልነበረብኝም ። መፅሀፍ ገዝቶ ለማንበብ አቅም አያንሰኝም ።'

ፒያኖው በስፋት ጥጉን ይዞ ተኮፍሷል ። ጣዕሙን ፡ ለዛውን ለማያውቅ ሰው በጥግ በኩል ተቀምጦ ሲያዩት የሚያሟርት ይመስላል ። እንደ ራሳ ሳጥን በጥቁር ቀለም ተደርብቦ የተኮፈሰ የእንጨት ሳጥን ። ሲመለከተው አንዳች እርይታ ተሰማው ። አብሮት አልቆየም ። ትዝታ ወደኋላ ይወንፍጨው ጀመር ።

እፀገነት የምትወድሰት የፒያኖ አጨዋወቱን ብቻ አልነበረም ፡ ወፍራም ድምፁን ሞምር እንጂ ። ስለፍቅሩ ብዙ እንጎራጉሮላታል ፡ አዜሞላታል ፡ አስቋታል ፡ አሳዝኗታል ፡ አስለቅሷታል ። መች ይሄ ብቻ ! አስተምሯታልም ። ጣቶቿን ፒያኖው ላይ እንዲያርፉ እያደረገ ፡ የምትፈጥራቸው ድምፆች ቢሳካም ባይሳካም በጣቶቿ መጠንሰሳቸው ስሜቶቹን እየኮረኮሩት እያስፈነደቁት ... ደግሞ ሲያስተምራት ፡ በርግጥ ሶስት አመት በጣም አጭር ነው ፤ ትዝታው ግን የሕይወት ዘመኑን ሲያካልል ተሰማው ። የትናንቱ ህይወት ርቆ ታየው ።

የዛሬው ህይወቱ ለውሳኔ ተቸግራለች ። ባዝናለች ፡ ሌላው ቢቀር አቅጣጫዋን ማወቅ ተስኗታል ። ከእፀገነት ጋር ያለውን የወደፊት ትልም በምን መንገድ አንደሚቀጥለው ያለዛም አንዴት እንደሚቋጨው በውል አልተረዳም ። ስለርሷ አንዳች ነገር ማወቅም ሆነ መረዳት አለመቻሉ አስገርሞታል ። ስለጥፋቷ ያለማወቁ ደግሞ ለውሳኔ አስቸግሮታል ። ጣጣው ደግሞ አናት ባናት እየተደራረበ ነው ። ቤቱ በጅምር ቀርቷል ። መኪናውም እንዳሰበው በቀላሉ የምትከወን አልሆነችም ። በዛ ላይ ቤቱ ሰላም የለም ። መንፈሱ እረፍት አጥቷለች ። ያመሻል ። ይጠጣል ። ይሰክራል ። ማታ ባልጋው ተደሳች አይደለም ። እንደቀዘቀዘ ሰውነት የሚጠላው ነገር የለም ።

ከንፈን ካገባችው ወዲህ አንደዛሬው ተናግሯት አያውቅም ። ባህሪው ፍፁም ተለውጠባታል ። እንደሰሞኑ ጠጥቶ ወይንም ሰክሮ አልቆያትም ! ወንድሟ ቤቷ አድርሷት ሲመለስ ያለወትሮው በሩን የከፈተላት ከንፈ ነው ። ያልጠበቀችው ስለነበር ገረማት ። የሁለቱም ሰላምታ ካንገት በላይ ነበር ።

"የት አመሸሽ ?" ሲላት አተኩራ ተመለከተችው ። እኳኋኑ አስፈራት ፡ ሀይለቃል ልትናገረው አልደፈረችም ። "እ ... እንአባባ ጋ ሄጀ ነበር" አለችው ለስለስ ብላ ።

Scanned with CamScanner

አልተጠራጠረም ። ይህንኑ በር ላይ አድርጊት የተመለሰው መኪና ተገንዝቧል ። ተያይዘው ወደ ቤት ገቡ ። ብዙ ነገራት ። ብዙ አወራት ። ራሷ ዞሮ ማሰብ አስኪያቅታት ድረስ ፣ አላቅማማም ። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ መቼም ድረስ ሊገፋው እንደማይችል ነገራት ። እንደሚያፈቅራ ትም አወጋት ። አስቀይሚት እንደሆነም ጠየቃት ።

መልስ የለም ።

እፀገነት ማማረሩ ታውቋታል ። በዚህ አለም ከራሱ አብልጠ የሚወዳት ክንፈ እንኳ ከምንጊዜም ይበልጥ ራሷን ገበች አደረገባት ። እንደተጣለች እንከርዳድ ሆና ተሰማት ። አም ማንም የማይፈልጋት ርካሽ አድርጋ ራሷን ቆጠረች ።

ሄኖክን ልትረሳው ትፈልጋለች ። ግን አይሆንላትም ። ከክንፈ ጋርም ልታወዳድረው አትፈልግም ። ክንፈ ለሷ ሙድ ስጠታዋ ነው ። ግን ከሄኖክ የሚያቆራኝ ሀያል ብርታት ይፈታተናታል ። ለምን በክንፈ ገላ ሄኖክ እየተመሰለ ይመጣል ? ከክንፈ ጋ ስትሆን ለምን ሄኖክን ታልማለች? ሳትፈልገው ያባረረችው ሄኖክ ጨለማ ባያግደው የመኝታ ቤት በሯ ሳይከልለው የእንቅፍል ድንበሯን ጥሶ በህልሟ ብቅ ይላል ።

ሄኖክን ረስታ ከክንፈ ጋር እያለች በአልጋ ላይ ጨዋታቸው ደስተኛ ነበረች ። አውን ግን ... ግዙፍ ገላው በላይዋ ላይ ይደንሳል ፣ እሷም ልታዳንሰው ትሞክራለች ። ይደናነሳሉ ። ክንፈ አልተለመጠም ። ጠንካራና ብርቱው ሰውነቱ አንዳለ ነው ። ደስ ይላታል ። ስሜቷን መኮርኮር ይጀምራል ። የሱም የሷም በአንድ አይነት ቅኝት እየተመሩ እኩል ለማጣጣም ይወራጫሉ ። ይደንሳሉ የህይወት ጣዕም ወለላ ምላሳቸው ላይ ጠብ ይላል ። ክንፈ አጣጥሞ ይረካል ። የሷ ነፍስ ደግሞ እንደታተተች ትቀራለች ። ክንፈ ሲደክም ፣ የሷ ነፍስ ሄኖክ ላይ ትንጠራራለች ። ሄኖክ የለም ፣ ስሜቷ ይፍነከነካል ። እናም ወደተድሞው ለእት ለመመለስ ጥቂት ጊዜያት ይወስድባታል ። ባዶነት በመላው ሰውነቷ ይሠራጫል ። በእንድ በኩል ከክንፈ ጋር ሆኖ ሄኖክን ማለሚ ሕሊናዋን ሲያሰቃያት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሷ ዋትቶ ፣ ስሜቷ ቃትቶ ፣ አለመርካቷ ያንገበግባታል ።

ይህ ሁሉ ሆኖ አውንም አንድ ነገር ታውቃለች ። ከጥቂት ደቂቃ በፊት ሀይለ ቃል ሲናገራትና ሲቆጣ የነበረው ክንፈ ፣ አቅፍት ከነኗ

ተጋድሟል ። እንቅልፍ እንዳልወሰደው ታውቃለች ። በጀርባዋ ተንጋላ ግሰቢን ትታ ወደ እሱ ዞረች ። አይናቹ ገርበብ ብለዋል ። ቀስ አድርጋ አይናቹን ላመቻቸው ። ያ የምታውቀው ነገር ምን እንደሆነ ግሰብ አላስፈለጋትም ። እጅግ አድርጋ ትወደዋለች ።

ክንፈ ድርጊቷን በአድናቆት አስተዋለው ። የድሮዋ የበፊቷ እፀገነት መሰለችው ። ደግማ ላመችው ። አውን አላረፈችም ። በሁለት እጆቹ እንት አድርጋ አቅፋ ጉንጩን ፣ ግንባሩን ፣ ከንፈሩን ፣ በክንፈሯ ቀያየረቻቸው ።

ክንፈ ተገረመ ።

አራሱ ካረጋገጠው በላይ እንደምትወደው ይበልጥ ለራሷ እርገጠኛ ለመሆን ጣረች ። እርገጠኛ ነበረች ።

ፍቅር ያረገዘቻትን ስሜት በዛን ጊዜ ዳንኪራዋን ጀመረች ። እያዜመች ታጫፍራለች ። ነገሮች ሁሉ እይህለሷቸውን ወደ'ሷ ልከው በእንከር ያከታተሏታል ። ከዜማዎች ሁሉ የላቀ ዜማ ለሁለቱም ይሰማል። ሕብረ ቅኝቱ እኩል ይፈሳል ። የክንፈ ሰውነት መዛል ሲጀምር፣ በሁለት እጆቹ እንት አድርጋ ያዘችው ። እንዲለያት አልፈለገችም ። ከላይዋ ሲነሳ ሄኖክ መንጭቆ የሚወስዳት መሰላት ። ተሳቀቀች ። ሊያድናት አልቻለም ። ቦታውን በሙሉ ሄኖክ ሸፈነው ።

ክንፈ ለምን እንደምታለቅስ ግራ እየገባው ያባብላታል ። ከሱ የተፈጠረው ጉድለት ምን እንደሆነ ለማወቅ ተጨነቀ ። ማወቅ ግን አልቻለም ።

ተስፋ መቁረጥ በመንፈሷ ሲሰራጭ ተሰማት ።

* * *

የእጁ ሰዓት አስር ሰዓት መሆኑን ሲያመለክተው ፣ ክንፈ ቀጥታ የገሰገሰው ወደ ጋራዥ ነው ። መኪናው በሚገባ ተከውና ጠበቀችው ። ሞተሯን አስነሳ ። ፈታተሻት ። ጉድለት አላገኘባትም ። ለእት አላጠፋም ወደ ቀጠሮው ጋለበባት ።

የቦሰና ቤት ከወትሮው ደመቅ ብሏል ። የልደታ ሰሞን ልምድ ነው ። የቦሰና ጓዳ ጉድጓዳ ሳትቀር 'በተከበሩ' ሰዎች ተይዛለች ። ወ/ሮ ቦሰናም እንደወትሮዋቸው ባንኮኒያቸው ላይ ተኮፍሰው ደንበኞቻቸውን በአይና

Scanned with CamScanner

ቸው ይቀላውጧቸዋል ። የውጭው ብርድ ደንበኞቻቸው ከመጣው ጋር እንዲፋቀሩ አድርጓቸዋል ።

ሀይወት ከአልኮል ጋር ዳንስ ጀምራለች ። ጊዜ አላት ። ታሞቃለች ። ታጫውታለች ። ታዳምቃለች ። ኩርፊያዋ ደግሞ አይጣል ነው ። ለሱም ጊዜ አላት ። ከንፈ ወደ ወ/ሮ ቦሰና ባንኮኒ ጠጋ ብሎ ሰላምታ አቀረበላቸው ። ፈገግታቸው ፊታቸውን ሸበሸበባቸው ።

ሽፈራው አልመጣም ። ከንፈ ደብል ውስኪውን አስቀድቶ ይጣብቀው ጀመር ። ሀይወትን እያሰበ ፡ እፀገነትን እያሰበ ፡ ሁሉን ነገር እያሰበ ደግሞ ... አልኮሉንም እየተጎነጨ ። አልኮሉ በጉሮሮው ሲወርድ ፡ ብርታት የሰጠው ይመስለዋል ። ግን ያስባል እፀገነትን ! በፊት ሲያስባት ብርታት ትሰጠው ነበር ። አሁን ግን ብርታቱን ትፈታተንበታለች ። ሲያስባት ይፈራል ። ተምታቶበታል ።

በድንገት ብርጭቆውን ከባንኮኒው ጋር አጋጨው ። መድገም ፈልጎ እንኳን አልነበረም ። ምን ተፍረቱን ደገመ ። ሰውነቱን ሞቅ እያደረገው ሄደ ። በዛኑ መጠን አሳቦቹም እየተበታተኑና እየቀለሉ ሄዱ ። 'የሰው ልጅ የሚኖረው አንዴ ነው' ... 'ኧ የሰው ልጅ የሚኖረው አንዴ ነው ። ለዛውስ ተሳክቶለት ሙሉ አድሜ ከተኖረ ይህንን ልንሳሳት የሚገባንን ሀይወት በየምክንያቱ ሸራርፈን ልንጨርሳት ነው ። አብርሃም ለምን ቤት አትሠራም ቢሎት ፡ 'ለምን ብዬ ፡ ለዚህች አጭር እድሜ ?' አለ አሉ ። ሆ—ሆይ ! እኛስ ምን እንበል ?' ብሎ መለኪያውን ተጎነጨ ።

ወ/ሮ ቦሰና ፈገግ ሲል ምላሹን ሰጡ ።

"ምነውሳ ያ ጓደኛህ ጠፋ ። ወትሮ ቀድሞ ደራሽ እሱ ነበር" አሉ ። እስከ ዛሬ በደንብ አስተውሎት የማያውቀውን ንቅሳት ጥርሳቸውን ተመለከተው ። እናነሱ እንጂ ጥሩ ጥርሶች ነበሩ ።

"ይመጣል ። እንዳውም ቀጠሮ አለን" አላቸው ።

"ኧረ ዕድሜው ረጅም ነው ስናነሳው ከች አለኮ'!" አሉ ወደበሩ እየተመለከቱ በሁኔታው ተደንቀው ።

ሽፈራው እጀንዳው ስለሉ መሆኑን ከሁናቴያቸው ገምቷል ።

"በክፉ ስታነሳኝ ደረስኩ በደግ ?" አለ ሽፈራው ፡ የከንፈን ቀኝ ትከሻ ተደግፎ ቀኝ እጁን እየጨበጠ ።

"እንዲያውም ዕድሜህ ረጅም ነው ስትልህ ነበረ" አለ ከንፈ ።

"ወዳ መሰለህ የኔን ዕድሜ የምታሰላ ፡ ያለኔ ቤቱም ቤት አይሆንላትም ። አይደል ቦሴ !"

"ድንቄም" አሉና አሽሟጠጡ ።

"ልትከጂ ነው ?"

"እስቲ ይሁን !" አሉ ወ/ሮ ቦሰና በረጅሙ ተንፍሰው ።

አስተናጋጂ ወደሱጋ ቀረበች ።

"ያን ጭማቂ አምጪልኝ !" አላት አዲስነቷን እያስተዋለ ።

ግራ ተጋብታ ቆመች ።

"ምነው ግር አለሽ እንዴ ? የገብሱን ጭማቂ አምጭልኝ" አላት አይኗ ጉልላት መስሎ አይነ ልቦናውን እየሰለበው ።

ባሰባት ። ተቅለሰለሰች ።

"ቢራ ነው የሚልሽ የኔ እህት" አላት ከንፈ የልጅቷን ሁናቴ ተመልክቶ ። እየተቅለሰለሰች ሄደች ። ሽፈራው ከኋላዋ በደንብ ተመለከታት ። ሴት ልጅን አፍ አውጥቶ ማድነቅ አይወድም ። አቃቂር ማውጣት ይቀናዋል ።

"ከየት አመጣሻት ደግሞ ይቺን ጎራዳ !" አላቸው ወ/ሮ ቦሰናን እየተመለከተ ።

ወ/ሮ ቦሰና በተቀመጡበት ወፍራም ሰውነታቸውን አወራጩና

"በደላላ ነዋ ! ሲገቡ ሰው ይመስሉና እያደር መርዛቸውን ይተፋሉ—የባብ መርገ !"

አስተናጋጂ መጥታ ቢራውን ባንኮኒው ላይ ከፍታ በብርጭቆ ልትቀዳው ስትል "ተይው" ብሎ ጠርሙሱን ተቀበላት ። ስትመለስ ቂጧን አውረገረገችው ። አሽሟጠ ሳቀባት ! ተጠንቅቆ እያያት ።

ሲመሽ ቤቱ ሞቅ ደመቅ እያለ ይሄድ ጀመር ። ጠጪዎች ፊታቸው እየወዛ እየተብረቀረቀ በዛ ላይ የፍሎረሰንት መብራት ድምቀቱን እየሰጠ፡ ጣውላው ብቻ አቤቱታውን ያሰማል ። ከውጭ የሚገባው ቀዝቃዛ ንፋስ አጥንት ድረስ ዘልቆ ስለሚሰማ በሩ በመጠኑ ገርበብ ተደርጓል ።

"እንዴት አደረክ" ? አለው ሽፈራው ከገብስ ጭማቂው ከደጋገመ በኋላ ።

Scanned with CamScanner

“ምንም ለውጥ የለውም” አለ ክንፈ ።

“እንዴት ?”

ክንፈ በቆመበት እንደመንጠራራት አለና “ሁኔታዎቹን በትክክል በመሰለኝ መንገድ ላስረዳት ሞክርኩኝ ፣ የተግባባን መስሎኛል ። መፍትሄ ግን አላገኘንም ። ምን እንደበደልኳት እንኳን ልትገልጽልኝ አልቻለችም። ለኔ በፍፁም ግልፅ አይደለችም ። ልትሆንልኝም አልቻለችም ። በዚህ አይነት ሁኔታ ደግሞ ልንቀጥል እንደማንችል ነገሬያታለሁ ።”

“ጊዜ ልትሰጣት እንደሚገባ አስበህበታል ?”

“አይ ሽፌ ! ነገሩን ባንተ በኩል ሆነህ ስታየው እንዲህ በቀላሉ የምታየው አልመሰለኝም ። ጠልታኛለች እንዳልል መውደዷን ደጋግማ ትነግረኛለች ። ፍቅሯን ሳስብ ደግሞ ፍፁም ግራ ይሆንብኛል ። እፀገነት እንዲህ አልነበረችም ። አርቆ አሳቢ ፣ አስተዋይና ጠንካራ ሴት ነበረች ። ዛሬ ግን ፍፁም ተለዋውጣለች ። ጭራሽ ቤቷንም ትታለች ። እኔንም እርግፍ አድርጋኛለች ። ብቻ ፍፁም ሊገባኝ ያልቻለ አንድ ነገር አለ” ። የውስኪው ብርጭቆ ላይ አቀርቅሮ ቆየና “ብቻ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ልንቆይ እንደማንችል በደንብ ይገባኛል ።”

“ቤተሰቦቿ ውናቴያችሁን አውቀዋል ?”

“ይመስለኛል ። ባለፈው አሁድ እናቷ በአሽሙር ሲነካኩኝ ነበር ፣ ብቻ በመሃከላችን ሰላም እንደሌለ ገብቷቸዋል ።

“እስቲ ለማናቸውም ጊዜ ስጣት” አለው ቢራውን እየጨለጠ ። ቀጠለናም “አየህ ጊዜ የማይፈታው ፣ ጊዜ የማይሽረው አንዳች ውልና ጠባሳ የለም ። ዛሬ ከብዶ የታያት ነገር ፣ ነገ በጉሥ ክርን ላልቶ ቁጭ ይላል ። ዛሬ ያልታየ ነገር ነገ ብቅ ይላል ። ዛሬ ያልተገኘ ጥንካሬ ነገ ከች ይላል ። ጊዜ ስጣት ፣ ጊዜ ስጣት” አለውና የጨለጠው ቢራ እንዲደግም ለት ጠረጴዛውን መታ ።

“ላልታወቀ ነገር ጊዜ መስጠቱ እኮ ይከብዳል ‘አትሊስት’ ነገሩን ባውቀው እንኳን እሺ ። ያለዛ ግን እንጃ ፣ በኋላ ጠጥሮ ፣ ገዝፎ ልወጣው የማልችለው ማጥ ውስጥ እንዳልገባ ነው የምፈራው ፣ ገባህ ?” አለው ክንፈ በአንክሮ እያስተዋለው ።

“በርግጥ ልክ ነህ ፣ ግን ደግሞ ሁሉን ነገር ማለት አትችልም ።”

“እንዴት ?”

“አትችልማ ! ብታውቅ ኖሮማ በማታውቀው ነገር ግራ አትጋባም ነበር ።”

“አለማወቄማ ነው ግራ ያገባኝ ። ማወቅ እንኳን እንዴት ይሳነኛል ነው የኔ ጭንቀት ።” የውስኪውን ብርጭቆ ከጠረጴዛው እያጋጨ “አየህ ‘ሲምቦል’ ባል መሆን አልፈልግም ። ያለዛም እንደመፅሀፉ ለባለቤቴ የክብር ዘውዷ ብቻ እንድሆንም አልሻም ። ወስጧን በርብራ ማወቅ አለብኝ ። እሷም እንደኔው ፣ ያለዛ ግን ትዳር አይደለም ። ደባሎችም እንኳን ችግራቸውን የሚገላለፁበት ደረጃ አላቸው ። የኛ ግን ባሰ ፣ የምንጋራው ስጋዊ ስሜት ብቻ ሆነ ። ያውም ...” አለና ተወው ።

ለሽፈራው አሁንም አዲስ ቢራ ተከፈተለት ። አቅራቢዋን በአይኑ አሽኮርምሞ ሸኛት ።

“አየህ ፣ ስሚትህ ይገባኛል ። ግን መገንዘብ ያለብህ ነገር ማንም ሰው ለማንም ቢሆን ሊገልፃቸው የማይችለው ፣ የራሳቸው የሆኑ ምክንያቶች ያላቸው ብዙ ነገሮች ይኖሩታል ። እስቲ በዚሁ በኩል ተመልከታትና ጊዜ ስጣት ።”

“እንዴት ይሆናል ? እንዴት ይሆናል ?” አለ ክንፈ አሳቡ ተዘበራርቆበት ። እፀገነት ከኔ የምትደብቀው ምን አይነት ችግር ይኖራል ?” ፍፁም የማያውቃት መስላ ታየችው ። ከማንም በላይ የሚያምናት እፀገነት ፣ ሁሉመናው የሆነችው እፀገነት ፣ በውስጧ ነገር አርግዛ ከሱ ልትሸሽገው ? ደግሞ እውነት ነው ፣ አንድ ነገር እንደሆነች ያውቃል ፤ ያንንም እንደሸሸገችው ። ተመሰቃቀለበት ፣ አስተሳሰቡን ማረጋጋት አቃተው ። ውስኪውን ተጎነጨ ።

ሽፈራው አስተዋለውና “ገባህ ! ነገሩ ለክፉም ላይሰጥ ይችላል ። እንዳልኩህ በመታገስና ጊዜ በመስጠት ብቻ ቀስ ብሎ አረጋግቶ ነገሩን በማወቅና በማብረድ ውጤት ማግኘት ይቻላል ። ታዲያ ይህ የሚሆነው ቀስ ብለህ ነገሩን ቦታና ጊዜ ሰጥተህ ስትመለከተው ነው ። እይመስል ሀም?” አለው ክሱ መልስ እንደሚጠብቅ ሰው አይን አይኑን እየተመለከተው ።

“እሱ’ኮ አይደለም የጨነቀኝ” አለ የማያዩ አይኖቹን ባንኮኒው ላይ ተክሎ ።

“ታዲያ ምንድነው ?”

Scanned with CamScanner

"ከኔ ልትደብቀው የምትፈልገው ፡ ያለዛም የደበቀችኝ ነገር መኖሩ ነው ።"

"ይህ ምን አዲስ ነገር ነው ። በማንም ዘንድ ያለ ነው ። ግንም ለማንም ሙሉ በሙሉ ራሱን አሳልፎ ፡ ምስጢሩንም ሁሉ ዘክዝኩ ሊናገር አይችልም ። ያ ከሆነማ የእኛነታችን አንዳች ነገር በውስጣቹን ይጠፋና ባዶ እንቀራለን ።"

"የለም መሆን የለበትም ።"

"እንዴት ?"

ክንፈ በረጅሙ ተነፈሰና "በቃ ይቅር ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ማሰብ አልፈልግም" አለ ።

"ለምን ?"

ክንፈ ተቆጣ ። "አልፈልግማ ! አልፈልግም ፡ እፀገኔትን እንደዛ ማሰብ አልፈልግም ።" ውስጡኑ ሲያንገፈግፈው ታውቀው ።

ሽፈራው ተመልክቶ ከልቡ አዘነለት ።

"እንደምትወዳት ልጠይቅህ ብዬ ጊዜህን ላጠፋ አልፈልግም ። ግን ለምትወዳት ሚስትህ ለምን ጊዜ መስጠት እንደተሳነህ ነው ሊገባኝ ያልቻለው ። ለነገሩ እኔም ምንም እንደማላውቅ ታውቃለህ ። ስለዚህ በማናችሁም ወገን ሳልሆን ነው አስተያየቱን የምሰጥህ ። በተረፈ ለምን ከኔ የተደበቀ ነገር ይኖራል ካልክ ሕልውናዋን መፃረር ይሆንብሃል ። እስቲ በራስህ ሕይወት አስበው ። በስተኋላህ እፀገኔት የማታውቀው ያለዛም በውስጥህ ተቀብሮ የቀረ ስንት ታሪክ አለህ ። ያንን መግለጽ ለጊዜው አስፈላጊ መስሎ ላይታይህ ይችላል ። ይህ ሁኔታ በትዳር ላይም ሊያጋጥም ይችላል ። ለተጓዳኝ መግለፁ አስፈላጊ መስሎ ካልታየህ ምን ታደርገዋለህ ? ደግሞ ይህ ጉዳይ ያጋጥማል ። ሰው ደግሞ ፍፁም አይደለም ።"

ክንፈ የሚያዳምጥ አይመስልም ። በሃሳብ ነጉዷል ። ሽፈራው ሊቀጥልለት አልፈለገም ።

ቀስበቀስ ቡና ቤቱ ሞር እያለ ሄደ ። ክንፈ ውስኪውን ደጋግሞ ለመሄድ አኮብኩቧል ። ሽፈራው ግን መሄድ አላሰኘውም ። ሰአቱን ተመለከተ ። አራት ሰአት ተኩል ነው ።

"በል ልሂድ! ከፈለክ አንተ ቆይ" አለ ክንፈ የሽፈራውን የመቆየት

አዝማሚያ አስተውሎ ፡ የሁለቱንም ሂሳብ ለመክፈል ኪሱን እየዳበሰ ።

ሽፈራው አላቅማማም "በልሂድ ፡ ባለትዳርና ወንደላጤ እኩል አይደሉም" አለው የክንፈ ሂሳብ መዝጋት ሳያግደረድረው ። በወዳጆች መሃል ባለ የጥቅም ውለታ አያምንም ።

ክንፈ እንደሄደ ወገቧ ላይ ያደረሳትን ቢራ ይዞ መቀመጫዎቹን በእይኖቹ ማተረ ። አብዛኞቹ ባዶ ናቸው ። ብዙ ሰአት የቆመበት እግሩ ደክሟል ። እግሩ ብቻ አይደለም አይኑም ቦዟል ። ሁለት አዛውንቶች ወ/ሮ ቦስናን ከበው ያጫውታቸዋል ። ከመጠጡ ሞቅታ ስሜት ጋር ጉንተላውና ጸበሳው ግልጽ እየሆነ መጥቷል ። ሽፈራው ትእይንቱን ማትሮ ሄዶ ተቀመጠ ።

ለሁለት ተከፍሎ ይባክን የነበረው ሀሳቡ ክንፈ እንደሄደ ፡ በሁለተኛው ቢራ አንድ ወገን ይዞ ተቀመጠ ፡ ከአዲሷ ሴት ጋር ለማደር ወስኖ ።

እሱን ለመምሰል ብላ ይሁን ወይንም ምርጫዋ ሆኖ እርግጠኛ አልነበረም ፡ ቢራዋን ይዛ አጠገቡ ተቀመጠች ።

"ከምትመላለሺ ፡ ለምን ላንቺም ለኔም ሁለት ሁለት ቢራ ይዘሽ አትመጪም?" አላት ፡ "እሺ!" ብላ ተነስታ ሄደች ። ለግላጋ ቢጤ ነች ። ሃያ ሶስት አያልፉትም ። የተስተካከለ የሰውነት ቅርጽ አላት ። መስህብነቷ ጉልቶ የሚታየው እንደ ፈርጥ በሚንቦገቦጉ አይኖቿ ላይ ነው። አካሄዷ መግነጢሳዊ መስሕብ አለው ። ሁለቱን ቢራ በእንድ እጇ ሌላዎቹን ደግሞ በሌላው እጇ አድርጋ በእርጋታ አስቀመጠቻቸው ።

አካሄዷ ኪነታዊ ስልት አለው — ወደዳት ።

"ከዚህ በፊት ቡና ቤት ሰርተሽ ታውቂያለሽ?" አላት ። የሚያያት ፡ የሚያስተውሰው ገላ በጥንቃቄ እንዳስቀመጡት ገል ከነወዘናው ተቀምጦ በማየቱ ።

ጉራዳ አፍንጫዋን በጣቶቿ እንደማሽት አለችና አይኖቿን አስተባ ብራ "እም" አለችው ፡ ቅንድቦቿ ወደ ላይ ሲንጠራሩ አይኖቿ እየጐሉ ።

አዘነላት ። ስሟን ጠየቃት ፡ ነገረችው ። የልጅነት ስሟ ለመሆኑ አልተጠራጠረም ። ከተማ ቀመስ ስም አይደለም ። ስሟን ለመቀየር ለምን አንዳላሰበችበት ደነቀው ። "ከኔ ጋር ታድሪያለሽ?" አላት ። "እሺ" አለችው።

ተስማሙ ።

Scanned with CamScanner

የሚመለከተው ነገር እውነት እንደሆነና የመጠጡ ኃይል እንዳልጋ ረደው ለራሱ አረጋገጠ ። እውነት ነው ።

እውነት ነው ።

መኝታ ክፍል እንደገቡ ልብሷን ለማውለቅ አልቸኮለችም ። በሚንከባለሉት አፋራም አይኖቿ አየችው ። ሰረቅ አድርጐ አያት ። አፍሪ ፈገግ አለች ።

"መብራቱን ላጥፋልሽ?"

"ደስ እንዳለህ!"

አልጋው ላይ ተቀምጣ ልብሷን ማወላለቅ ጀመረች ። ቀድሟት አውልቆ አልጋው ውስጥ ገባ ። ይመለከታታል ።

ብዙ ሴት ያውቃል ። ብዙ ገላም ያውቃል ። ትክለ–ገላ እንዳሁኑ አፍዝዞት አያውቅም ። በቅርጿ ተደነቀ ። በገላዋ ጥራት ተማረከ ። ሰርቃ አየችው ። አፍጥጦባታል ። አፈረችው ። እጇን ውስጥ ልብስ በሸፈነው ጭኖቿ ላይ አድርጋ ዝም አለች ። ከአልጋው ቀና ብሎ ጐተታት ።

"ቆይ እሺ! ላውልቅ ።"

ሰውነቷን መዳበሱ ሀይወት ሰጠው ። አካሏን ሸጣ የምትኖር ሴት አልመሰለችውም ። ሳማት ። በደንብ አድርጐ ሳማት ። ሰውነቷን ዳብሶ ፣ ከንፈሯን መጦ አልጠግባት አለ ። እሷን አልጋው ውስጥ ማስገባት ጊዜ ማጥፋት ፣ ውበቷንም መደበቅ መሰለው ። እሱ ቢወጣ ይቀላል ።

ሞገዱ በላቀ ፣ ቅኝቱ በመጠቀ ፣ ደብሩ በሰፋ ፣ አድማስ ዙሪያው በሁለቱ ስሜት በታጠረ የሀይወት ባህር ውስጥ ቀዝፈው ሲመሰሱ ፣ ተዳከሙ ። ሁለቱም በየፊናቸው ብርድልብሱን ገላልጠው ገቡ ።

"ላጥፋው?" አላት እጆቹን በድጋሚ ወደማብሪያና ማጥፊያው ልኮ፣ ደከሟታል ። ደግሞም ቢበራም ቢጠፋም ግድ አልነበራትም ። መልስ መስጠትም አልተሳናት ። ዝም አለችው ። እሱም አጠፋው ።

አቀፋት ። ጀርባዋን እንደሰጠችው ነው ። ሙቷን ፣ ደረቷን ፣ ወገቧን …ብትተኛ ደስ ይላታል ። እሱ ደግሞ ሊያሰተኛት አልፈለገም ። እንደሌላው ጊዜ ገንዘቡን አስቦ ሳይሆን ፣ ታሪኳን መስማት ፈለገ ። ንግግሯን ባቆመችበት እንድትቀጥል አደረጋት ።

"ትምህርትሽን ለምን አቋረጥሽ?"

የግትወደውን ጥያቄ ወደሱ ሥራ እንድታወራለት አደረጋት ።

"ጓደኛዬ ናት ። የጓደኛ ምክር ፣ አዲስ አበባ እንሂድ ብላ ውጥረ አደረገችኝና መጣን!"

"ገሞድና ነበራችሁ?"

"አረ የለንም ።"

"አግብተሽ ነበር?"

"አም ።"

"ልጅስ?"

"አልነበረኝም ።"

"ጓደኛሽስ አሁን እዚህ አለች?"

በረጅሙ ተነፈሰች "የለችም! አንድ ሹፌር 'ወድጀሻለሁና ይገርሽ ካልሄድኩ' ብሎ ይዟት ወደናዝሬት ሄደ ። ከዛን ወዲህ ተያይተን አናውቅም ።"

አጥብቆ እያቀፈ ወደራሱ አስጠጋት ። ርህራሄው ተሰማት ። በገንዘባቸው ከሚያወጧቸው ወንዶች ርህራሄ ማግኘት ብርቅዬ ነገር ነው። ያውም አብዛኛውን ጊዜ ሰክሮ ከሚያድር ወንድ!

በድጋሚ በስሜት ይዳስሳት ጀመር ። ቅድም ያፀዳችው ጭኑ በድጋሚ ሲሞቅ ታወቃት ። ገላው ባዕድ አልሆነባትም ። አቀፈችው፣ ተቃቀፉ ።

ገላዋ እሽት ነው ። ልስላሴዋ እንደተአምር ታየው ። ከሩቅ ደወል ያንቃጭላል ። በኩለሌሊት ወፎች ያዜማሉ ። አሶች ይደንሳሉ ። መለከት ይነፋል ። እንቢልታ ይጐሰማል ። ሰይጣን ፀናፅሉን ይዞ ፣ ጋኔሎችም ከመላዕክት ጋር አብረው ያሸበሽባሉ ። ሂትለር ስለአለም ሰላም ይጮሃል። እያጐ ስለፍቅር ይቃኛል ። ያዜማል ። ቄሱ በረሃ መሃል ቆመው "አላህ–ወክብር" ብለው ይጮሃሉ ። ሼኩ ማዕድ "በስመአብ" ብሎው ይባርካሉ። ድንቅ አለም! ጣፋጭ አለም! ሁሉም ይከወናል ።…

ሁለቱን ያስደነቃቸው ንጋቱ ነው ። የገሃዱ አለም አውራ ዶሮ ሲጮህ አልሰሙም ። የወፎቹ ዜማ ግን ታወቃቸው ።

ከላዩ ላይ ተነስታ ግንባሩን ሳመችው ። በአድራጐቷ ከብልል አይኖቿ አያፈሩ አላጢት ። እጇን ጐተተና እላዩ ላይ ጥሎ አይኗን ሳማት ። ቀድማው ተነስታ አልጋው ላይ ቁጭ አለች ። ልብሷን ስትለባብስ በጀርባው እንደተጋለለ በላዩ ላይ የቀረው ጠረኗ እያወደው አሰባት ። በፍቅር ፣ በሃዘኔታ …

Scanned with CamScanner

ተነስቶ ለባብሶ እንደጨረሰ ከኪሱ ውስጥ ድፍን የአምሳ ብር ኖት አውጥቶ እጇ ላይ አደረገላት ።

"ዝርዝር የለህም!"

"እንዳለ ያዢው ።"

ደነገጠች ። ብሩንም እሱንም በየተራ አየቻቸው ። "አልፈልግም" አለች እንገቷን እየነቀነቀች "አልፈልግም" አለችው ደገመችና ።

"ግዴለም ያዢው ።"

"እንዳውም አይሆንም" አለች ውብ አይኖቿ በሱ ላይ እየተንጐማለሉ ። "የአልጋውን ኪራይ ብቻ ስጠኝ ፣ ሌላ ምንም አልፈልግም" አለችው ።

ሽፈራው ደነገጠ ፣ "ለምን?" አለ አተኩሮ እየተመለከታት ።

"በቃ አልፈልግም ።"

"ለምን?"

"ኡፋ!" አለች እነኛ ውብ አይኖቿ ደም እየመሰሉ ። "አልፈልግም! አልፈልግም! "ደስ ካለኝ ሰው ጋር እንዲሁ ማደር አልችልም?"

"ቢሆንም..." አንጀቱን በላችው ። "ቢሆንም ሰራሽ ኮ ነው ።"

አይነውሃዋ ውስጥ ያሉት የደም ስሮች ከመቅጽበት ደም ሲሞላቸው ያስታውቁ ጀመር "አውቃለሁ ። ሽርሙጣ መሆኔን አውቃለሁ" ቱግ አለችበት ።

"እንደሱ ማለቱ አይደለም ።"

"እንደፈለክ በል ብቻ!" አለችና አይኖቿ እንባ ሞሉ ። "አውቃለሁ። ማለት የፈለከው ይገባኛል ። ግንእኮ ባንተ አልፈርድም ። የተሰማኝን የማውቀው እኔ ነኝ ። ደስአልከኝ በቃ ባፊ ሌሊት የሰጠኸኝ ፍቅር ገንዘቤ ነው ። ከፈለክ የአልጋውን ሂሳብ ስጠኝ ። ካልፈለክም ተወው ።"

የአንድ ቀን አዳር! ሁኔቴዋ አስገረመው ፣ አስደነቀው ፣ አሳዘነው ። ይበልጥ ወደዳት ። የተመኘው ሆነለት ። በገንዘብ ሳይሆን በፍቅር ያንን ያመለከበትን ገላ መግዛት በመቻሉ የሀሊና እርካታ ተሰማው ። ደጋግሞ እየሳማት ጥብቅ እድርጐ አቀፋት ። ጉያው ውስጥ ገብታ ታለቅስ ጀመር ።

'ማን መስያት ይሆን? ወይንስ ፍቅር ነው?' ያም ሆነ ይህ ተቀብላዋለች ። ተደስታበታለች ። በጠቅላላው ሀይወትና ኑሮ ታክቶት ነበር ።

የሰው ልጅ ደግሞ በድንገት የዋዠቀውን መንፈሳችንን ፣ የላሸቀውን አይምሮአችንን ፣ አንዲሁም መመርቀዝ የጀመረውን ሕሊናችንን ላይታ ወቀው ያዐዳልናል ። ነገ ከተስፋዎች ሁሉ የበለጠ ተስፋ ሆኖ ታየው ። ከሰው ልጅ ጋር አብሮ የመኖር ጥልቅ ደስታ ፣ የላቀ ሰላም ፣ ታላቅ የሀይወት ተልእኮ መስሎ ተሰማው ። ስለሰው ከሰው ጋር አብሮ መኖር አንድ ታላቅ ተልዕኮ ነው ። የመኖር ምክንያት ሰዎች ናቸው ።

ነገ ከተስፋዎች ሁሉ የበለጠ ተስፋ መሆኑን እያሰበ ፣ ሰዎች ለሰዎች ሲሉ መኖራቸውም እየተሰማው ፣ ደስ ብሎት ተለያት ። በእዝነ ልቦናው እያሰባት ።

ሰአት ደርሶ ወደ ስራ ገበታው ለመድረስ ከሚጣደፈው ህብረተሰብ ጋር ተቀላቀለ ። እየታየው ፣ እየታሰበው ፣ እያለመው ...

ነገ! ከተስፋዎች ሁሉ የበለጠ ታላቅ ተስፋ!

ምእራፍ ስምንት

ኳሷ ተንከባላ ፣ ተሽከርክራ የተደረደሩትን ብርሌዎች በትና ወደ ጉድጓዱ ጥልቅ! አንዱ አንዱን እየጣለ ተያይዞ እልም... የተረፈ አልነበረም ። ሚዳውን ባዶ አስቀረተው ። ሲራክ በኃይል አጨበጨበላት ። አንዳንድ ተቀማጭ ተመልካቾችም አድናቆታቸውን ሲገልፁላት ፈገግ አለች ። ቀዝቃዛ ፈገግታ...

ሮቤርቶ ርቆ ከባንኩኒው አካባቢ መሎቲ ኮኛኩን ይዞ ይመለከታት ነበር። "ብራቮ! አዚብ ብራቮ!" እያላት መጣ ፣ በአመታቷ ጥበብ ተደንቆ። ድምፁ ጐርናና ነው "ድንቅ ተጫዋች ወጥታት የለንዴ!" አለ አዚብንም ፣ ሲፉከንም በየተራ እየተመለከተ ። አዚብ ለሁለተኛ ዙር ኳሷ እስከሚመጣላት ጣቶቿን በፎጣ ጠርጋ ንፋስ መስጫው ላይ አድርጋዋለች ።

ኳሷ ተሽከርክራ መጣች ።

"ያሁኑን ከደገምሽ ውስኪ አወርዳለሁ!" አለ ሮቤርቶ መለኪያውን አስቀምጦ ወፍራምና ዐጉራም እጆቹን እያሻሸ ። "አትጠራጠር!" ብላው

Scanned with CamScanner

አቋሟን አስተካክላ ተንደረደረች ። ለጥቂት ሁለቱን ብቻ ሳተቻቸው ።
በሱም ቢሆን ሮቤርቶ ተደንቋል ። የቦውሊንግ ጨዋታ ከጀመረች አጭር
ጊዜዋ መሆኑን ስለሚያውቅ ፡ በጐርናና ድምፁ አድናቆቱን ገለፀላት ።
ሮቤርቶ የሲራክ ወዳጅ ነው ። የረጅም ጊዜ እውቂያ አላቸው ፡ አባ
በእንቧይ መስክ የቦውሊንግ ሜዳ ። በአባቱ ኢጣሊያዊ ፡ በእናቱ
ኢትዮጵያዊ ነው ። መልኩ ወደ አባቱ ወገን ያደላል ። የአማርኛ ቋንቋ
ጥራቱ መካለሱን ካልተናገረ በቀር ክልስነቱ አይታወቅም ። አባቱ
ትውልድ ሀገራቸው ጣሊያን ሲሆን ፡ በወጣትነታቸው ጣሊያን ኢትዮጵያ
ገብቶ በቆየበት የአምስት አመት የወራሪ ዘመን ፡ ከጥቂት ኢጣልያዊ
ዜጐች ጋር አገሪቱን ለማልማትና ለማበልፀግ በሚል ምክንያት ገብተው
እዚሁ ከቀሩት ኢጣልያኖች መካከል አንዱ ናቸው ። የስራ ሰው
በመሆናቸው ፡ በከተማው ውስጥ የተለያዩ የንግድ ቤቶች ከፍተው
ደረጃቸውን ያሳደጉ የተሳካላቸው ቱጃር ነበሩ ። ዛሬ ጃጅተው ቤት
ውለዋል ። አንዱን ንግድ ቤት ሮቤርቶ ሲያስተዳድር የተቀረውን
መንግስት በትርፍነት ገቢ አድርጐታል ። ሮቤርቶ ድንቅ የቦውሊንግ
ተጫዋች ነው ። በፍፁም ከቦውሊንግ መጫወቻ ስፍራ አይጠፋም ።
በመውለዱ ቢታማም አላገባም ። ከሲራክ ጋር ላጤ ጓደኛሞች ናቸው ።
ሲራክን ብትፎካከረውም ረታት ። የቦውሊንግ ጨዋታ ከጀመረ ብዙ
ጊዜ ሆኖታል ። “ቶሎ ቤት መድረስ አለብኝ” አለችው ጨዋታቸውን
ጨርሰው ወደ ጫማ መቀየሪያ ክፍል እየሄዱ ።
“ሮቤርቶ ራት ልጋብዛችሁ ብሏል” አላት ሲራክ ከኋላዋ እየተከተ
ላት ።
“አልችልም!”
ምን እንዳናደዳት ግራ ገባው ። በመሸነፏ እንዳልሆነ ያውቃል ። ከዚህ
በፊት ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ሲያሸንፋት ፡ የመናደድ ስሜት አላሳየችውም ።
ጫማዎቿን ቶሎ ቀያይራ ወደውጭ መንገድ ስትጀምር “ቆይ‘ጂ አትሊ
ስት እንደማይመሽሽ ንገሪው” አላት ቆም ብሎ ።
አጠገቡ የነበረውን የቁማር መጫወቻ ማሽን በእጁ እየጠበጠበች ፡
ምናሉ እንተ ብትነግረው ። አልችልም ካልኩ አልችልም ነው ። አንተ
እንኳን ቢገባህ ምናለ?” አለችው ።
ጥሏት ወደውስጥ ገባ ፡ እየተናደደ ።
“ጨረሳችሁ” አለው ሮቤርቶ ወንበር ላይ ተዝናንቶ እንደተቀመጠ

ሲራክን ወደ ላይ እየተመለከተ ።
“አዎ ግን ግብግቧህን ለሌላ ቀን ብታደርግልን?”
ሮቤርቶ በስጨት አለ ። ያወጣው ፕሮግራም ሲቃወስበት ያበሳጨ
ዋል። “ሂሳብ እኮ አይደለም የማወራርደው ።”
ሲራክ ጨነቀው ፡ “እሺ ከነቅጣቱ ሌላ ቀን እኔ ጋብዛለሁ ።”
“ግን ምን አዲስ ነገር ተገኘ?” አለ ሮቤርቶ በጥቂት ጊዜ ውስጥ
ሃሳባቸውን መለወጣቸው አስገርሞት ።
“እንጃ!”
“እንዴት?”
“ባስቸኳይ ቤት መድረስ አለብኝ አለችኝ ።”
“ለምን?”
የሚገርምህ ነገር ፡ ለምን እንደሆነ እኔም አላውቅም ።”
“ናፍቃህ ይሆናል” አለ ሮቤርቶ እየሳቀ ።
ሲራክ አልሳቀም ። አመሏ አልጨበጥ እያለው ናላውን አዙሮታል ።
መቆረጥ አልቻለም ። በሱ ቤት መቁረጥ የማይችል ሰው ደካማ ነው ።
አሳቡን ሰበሰበና “ከእንግዲህ ወዴት ነህ?” አለ ጓደኛውን እየተመለ
ከተ ።
“እንግዲህማ ወደቤት ነኝ ። ራቴንም ብቻዬን መብላቴ ነው ። ገና
በጊዜ የሚያባላኝ እንዳልፈልግ እድሜ ለናንተ” አለ ቅሬታውን በቀልድ
እየገለፀ ።
“አዳባሪዎችህስ ዛሬ የት ጠፉ?” አለው ሲራክ ።
ሮቤርቶ በጐርናና ድምፁ በረጅሙ ሳቀና “ማን አለ? ማንም የለም ።
ዛሬ እንደምታየው ቤቱ ጭር ብሏል ። ወትሮ የሚያዳምቁት ሴቶች ምን
እንደዋጣቸው አላውቅም ። አሁን አሁንማ ቤቱን የሞሉት የአስራ
አራትና የአስራ ስድስት አመት ልጃገረዶች ናቸው ። ዘመኑ በጣም ፈጣን
ሆኗል ። ያለዕድሜያቸው አድገዋል ። ‘ጋሼ’ ማለቱ ቀርቶ ‘ሃይ! ጆኒ! ሃይ
ሃኒ!’ ሲሉህ ምን ታደርገዋለህ! ከነሱው ጋር መወዝወዝ ነው ።” እንደገና
ከት ብሎ ሳቀ ። የሚጠጣው መሎቲ ኮኛክ እየሰራ መሆኑ ያስታውቃል ።
“በል ጠንቀቅ በል ወዳጄ ፡ ከነሚሚ ፡ ፒፒ ጋር ስትንጐዳጐድ ተያህ
ውስጥ ቅርት እንዳትልብህ” ብሎ ሰአቱን ተመለከተና “በል እየጠበቁ
ችኝ ስለሆነ ፡ ልሂድ ። ሰሞኑን እዚሁ እንገኛለን” ብሎት ወጣ ።
አስፋልቱ በውሃ ርሷል ። ውስጥ ሆነው መዝነቡ በፍፁም አልታወቃቸ

Scanned with CamScanner

ውም ነበር ። መኪናቸው ውስጥ ገብተው ያንን ድቅድቅ ጨለማ በቢጫው የመኪና መብራት እየቀደዱት ሲያልፉ ፣ በድንገት "ወዴት ነው የምንሄደው?" አለችው ፡ የዝምታውን ወሰን ጥሳ ። "ወዴት" አላት ንግግሩ ደረቅና ከራራ ነው ። መልስ ልትሰጠው አስፈራት ። እመላለሱ አስደንግጧታል ። ዞር ብላ ተመለከተችው ። እየሸሸ የሚሄደው ፀጉሩ ግንባሩን አግዝፎ አፈጠጠባት ። ተርበተበተች ። ፍርሃቷ ከየት እንደመጣ ማወቅ አልቻለችም ። ሰረቅ አድርጉ ተመለከታት ። ተከራምታ ተቀምጣለች ። ፊቷ ተተረማምሷል ።

"አዜብ!"

"አቤት"

በድጋሚ አስተውሎ ተመለከታት ። "ምን ሆነሻል? አመመሽ?" የመኪናውን ፍጥነት ቀንሶ ወደዳር አወጣው ።

"ደህና ነኝ እንሂድ" አለች በሚንቀጠቀጥ ድምጿ ራሷን ለማረጋጋት እየሞከረች ።

አስተውሎ ከተመለከታት በኋላ ፡ ገሰገሰ ። ወደቤት ።

የአልጋው መመናቀር ሲለፉ የዋሉ አስመስሏቸዋል ።

"'በጉያችን በጓዳችን የቋጠርነው የአእምሮዋችን ምስጢር ሳናስ በው ሳንፈልገው ባልጠበቅነው ጊዜ ይወጣል ። ታዲያ ይህ አደገኛ የሚሆነው የማንፈልገውና የምንሸሸው ነገር ከሆነ ነው' ይል ነበር በዩኒቨርስቲ የሳይኮሎጂ አስተማሪያችን" አለች አዜብ በደጋገመችው ውስኪ ተበራታታ መንፈሷን ካረጋጋች በኋላ አልጋው ላይ በጀርባዋ ተንጋላ "... ሳይታወቀኝ ከራሴ ጋር ብዙ ታግያለሁ ።"

ለማለት የፈለገችው ምን እንደሆነ ሲራክ አልገባውም ። ዝም ብሎ ያዳምጣል ፣ እሱም አልጋው ላይ ተንጋሎ ።

"ታውቃለህ ! ከልጅነቴ ጀምሮ አብሮኝ ያደገ አንድ ነገር አለ ፣ እጅግ አድርጌ የምጠላው ፣ ስለምጣላውም የምፈራው ። ስለአባቴ አጫውቼህ አላውቅም አይደል?" በአንክሮ ተመለከተችው ። እሱንም አትኩሮቷ ሳበው ። ገና ሳትናገር ግልፅነቷ ታወቀው ። እስከዛሬ ስውር የሆነበትን የሕይወቷን እን�ቅልሽ ለማወቅ ጓጓ ። ያስጨበጠችውን የቋጠሮዋን ጫፍ ሊለቅ አልፈለገም ፣ በአካሉ ይበልጥ ተጠጋት ።

ሊያቅፋት እየሞከረ ፡ "አዎ ነግረሽኝ አታውቂም" አላት ፡ እጁን እያንተራሳት ። የራስጌውን መብራት አበራችና ትልቁን መብራት አንዲያጠፋላት ጠቆመችው ። አጠፋላት ።

"በአጋጣሚ የስነልቦና ተማሪ በመሆኔ ፡ የችግሬን መንስኤ ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልፈጀብኝም ። ያቃተኝ ግን መድሃኒቱን ማግኘት ነው ። እስከ አሁን በአእምሮዬ የሚታየኝ ስእል አለ ። ግን መሰለህ የአባቴ መልክ ። ለእና በዚያ ጊዜ ምንም ነገር ለማያውቀው ወንድሜ ይሼን ያህል ክፉ አልነበረም ። ለምንወዳት አንዲ እናታችን ግን እጅግ መራራ ሰው ነበር ። በጣም ይጠላል ። በኃይልም ሰክሮ ይገባል ። ታዲያ ሲሰክር ልዩ አመል አለው ። ብሶቱን እየተቆጣና እየተናደደ መናገር ይወዳል ። በዚያም አያበቃም ። እልሁ የሚበርድለት እጁን እናታችን ላይ ሲያሳርፍ ነው ።

"ይገርምሃል ! አባቴን ሳይሰክር ያየሁበት ምሽት ያለ አይመስለኝም ። ሁሌ ሰክሮ ይገባል ። ታዲያ ገና ከውጭ ድምፁን ስንሰማ እንደመቦረቅና መደሰት ለመደበቅ ስፍራ ስንማትር ፡ በየስርቻው ስንሟዳሙድ ፡ ኩኩሉ የምንጫወት እንመስላለን ። ፍርሃታችንን ልነግርህ አልችልም ። እኔ ቆሜ ስንቀጠቀጥ ታናሽ ወንድሜ ሄኖክ እጭሩን ጫሚሴን አንቆ ይዞ በፍርሃት ሲመለከተኝ ትዝ ይለኛል ። ሲያሰኘው ቀቢጸውን ፈቶ እስኪደክመው እናቴን ሲመታት ይቆያል ። ያለዛም በርግጫ ፡ በቡጢ ፡ በተመቸው ሲቀጠቅጣት ይቆይና ፡ አልጋው ላይ በጀርባው ይንጋለላል ። የሚገርምህ ይሄ ሁሉ ሲሆን ፡ እናቴ አልፎ አልፎ ከማቃሰት በቀር ድምፅ አታሰማም ። የኋላ ኋላ ግን ምክንያቱ ገባኝ ። ያንን ሁሉ ስቃይ እየተቀበለች ፀጥ የምትለው ለኛ ለልጆቿ ስትል እንደሆነ እየታወቀኝ ሲሄድ ..." እንባ እየተናነቃት መናገር አስቸገራት ፡ ሲራክ ተጨነቀ ። ያባብላት ጀመር ። ከውስኪው ቀድቶ እንዲሰጣት ፈለገች ። መልሳ ተወችው ።

በረጅሙ ተንፍሳ ፡ "ብቻ ለዚህ ሁሉ መንስኤ የሆነኝና ፡ እድሜዬን ሁሉ ምስሉ እየተከተለኝ የሚኖረው የአንድ ቀን ሁኔታቸው ነው ። አባቴ ከመግባቱ እናቴን መቀጥቀጥ ይጀምራታል ። እየሮጠች ከቤታችን ወጣች። እየተሳደበና እየተራገመ ተከተላት ። ወዲያው ድምፃቸው ጠፋ ። እኔም ማንም በሌለበት ጓዳው ውስጥ መቆየቱ ስላስፈራኝ ሄኖክን ይዤ ቀስ ብዬ ወጣሁ ። አሁን ድረስ ትዝ ይለኛል ። ጀንበሯ ጠልቃለች ። ጨለማው እያየለ ቢሄድም የጨረቃዋን ብርሃን አልዋጠውም ። ቀስ

Scanned with CamScanner

እያልኩ ወደበሩ ተጠጋሁ ። እኔም ሄኖክም በባዶ እግራችን ነን ። ከበሩ ስር ያለው ድንጋይ ላይ እናታችን ተቀምጣለች ። ያ ድንጋይ ዘወትር ከመተኛታችን በፊት እናታችን እግራችንን የምታጥብበት ስፍራ ነው ። እንደተመለከትኳት ቶሎ ብዬ ከአጠገቧ ደረስኩ ። ፊቷ በደም ተጨማልቋል ። ደሟን ለማቆም በጀርባዋ ተንጋላ ራሷን ወደ ላይ አድርጋ አፍንጫዋን ይዛዋለች ። 'እማዬ ...' ብዬ ገና ከመጨረሼ ትንሽ ራቅ ብሎ ሽንቱን እየሸና ያለው አባቴ አይቶኝ ፣ እኔ ግን አላየሁትም ነበር ፣ በጣቱ የቤቱን በር እያሳየኝ 'ወደቤት!' ሲለኝ እዛው በድንጋጤ ደርቄ ቀረሁ ። መንቀሳቀስ እንኳን አቃተኝ ። እግሮቼ ብርክ ያዛቸው ። ሄኖክ እሪታውን አቀለጠው ። ይሄን ጊዜ እማዬ በአንድ እጇ የሚነስረውን አፍንጫዋን ይዛ በሌላው እኛን እየገፋች ወደቤት አስገባችን ።

"ያ ከሆነ ብዙ ዘመን አልፎታል ። በኋላ ፡ እናቴ እንደምትለው አባቴን መጠጡ ገደለው ። ቢሰክርም ቢጠጣም የቤቱ ምሰሶ እሱ በመሆኑ፣ እሱ ከሞተ በኋላ ችግሮች በላይ በላይ ይደራረቡብን ጀመር ። እናቴም አንድ 'ሲን ሆና ለሶስት ጉሮሮ ደፋ ቀና ስትል በዛው ቀረች ። ጭራሽ ቤተሰባችን ተበተነ ። እኔም ውንድሜም ተለያየን ..." ብላ በድንገት ከአልጋዋ ተነሳችና "መጣሁ" ብላው ወደ ሳሎን ሄደች ። ተመልሳ ስትመጣ የውስኪ ጠርሙስና ሁለት ብርጭቆ ይዛለች ። ግሩም የሌሊት ልብስ ለብሳለች ። ምርጫው የሲራክ ነው ። ባለአበባ ንድፍ ሆኖ እጅግ የሳሳው የሌሊት ልብሷ ዳሌዋ ላይ እየተንሸራተተ ሲወርድ አለሳልሶ ስሜት ይማርካል ። "ልቅዳልህ?" አለችው ፣ ለራሷ ቀድታ ራስጌ ኮመዲኖ ላይ ካስቀመጠች በኋላ ፡ አመስግኖ መጠጣት ያለመፈለጉን ነገራት ። ሁለት ጊዜ ተጉንጭታ አልጋው ውስጥ ገባችና ታሪኳን ቀጠለችለት ።

"እናቴ ዘወትር ስትፀልይ የምሰማት አንድ ፀሎት አለ ። 'አምላኬ ሆይ ! ለልጆቼ የኔን አይነት ዕድል አትስጣቸው ። አደራህን !' የሚለው ሁልጊዜ ከእኛ የማይለይ ቃል ነው ። በጊዜው ይህን ያክል ችግሯን ጠልቀ ባላውቀውም አንድ ነገር እገነዘብ ነበር ። እናቴ በጉሮዋ ተደሳች አለመሆኗንና የእናቴ ፍርሃትም እየተጋባብኝ ሄዶ እኔም የሷን አይነት ስቃይ እንዳይገጥመኝ እሰጋ ጀመር ። እንዳልኩህ ይህ ሁሉ ነገር ካለፈ ቆየ። ቤተሰባችንም ተበተነ ። እኔና ወንድሜም በተለያየ ቤት ማደግ

ጀመርን ። እኔም በተቻለኝ አቅም ከሚያሳድጉኝ ቤተሰቦቼ ጋር በሰላም መኖር ጀመርኩ ። እናቴ ከሞተች በኋላ ያሳደጉኝ ቤተሰቦቼ ጋ ስመጣ አስራ ሶስት ወይም አሥራ አራት አመት ነበረኝ ። እንድምታውቀው ይህ የእድሜ ወቅት ለሴት ልጅ የእድገት ፍጥነት መጨመሪያዋ ወቅት ነው ። አንድ ሁለት አመት እንደ ተቀመጥኩ ቁመቴ መመዘዝ ጀመረ ። አዳዲስ ለውጥም በሰውነቴ ላይ ይታይ ጀመር ። ትልቅ ልጃገረድ መሰልኩ ። እና ምን አጋጠመኝ መሰለህ ፡ አልፎ አልፎ እየመጣ የሚጠይቃቸው የሴትየዋ ወንድም ነበረ ። ቋሚ ስራ የለውም ። አንድ ሰሞን በስራ ይወጠራል ። አንዳንድ ሰሞን ደግሞ ስራ ይፈታል ። ዘወትር በመጣ ቁጥር እኔንና የቤትየዋን ልጆች ይዞን ይወጣና ከረሜላና ብስኩት ፡ ከፍ እያልን ስንሄድ ደግሞ ቡና ቤት ወስዶን ፡ ሻይ ፡ ወተት እንዲሁም ኬክ እየገዛ ይመልሰን ነበር ። አንድ ቀን እንደወትሮ መጣ ። ቤት ውስጥ ከእኔና ከሰራተኞቹ በቀር ማንም አልነበረም ። እኔም ገና ወደሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሸጋግሬ ስለነበር ትምህርቱ ከብዶኝ አጠናለሁ ብዬ ከልጆቹ ጋር ሽርሽር ከመሄድ ቀርቼ ነበር ። ብቻዬን ሲያገኘኝ ተደስቶ 'ምነው ዛሬ ብቻሽን ጥለውሽ ሄዱ?' ሲለኝ ፡ ለማጥናት መቅረቴን ነገርኩት" ቀና ብላ ውስኪዋን ተጐነጨች ።

"ከዚያ ስለትምህርት እያነሳ ያጫውተኝ ጀመር ። በመሃሉ እንደል ማዱ 'ወተት ጠጥተሽ ትመለሻለሽ ፡ በዛውም እኔን ትሸኚኛለሽ' ሲለኝ አላቅማማሁም ። ደብተሬን አጥፌ ተነሳሁ ። በቃሉ መሰረት ጋብዞኝ ወደ ቤት መመለስ ጀመርን ። የሴላ አቅጣጫ መስመር ሲይዝ 'ወዴት ነው?' አልኩት 'ቆይ እዚህ ዕቃ እወስዳለሁ' አለኝ ። አላመነታሁም ፡ ተከትዬው ሄድኩ ። መንገዱ ሲለለቸኝ ፡ በድጋሚ 'የት ነው የምንሄደው?' አልኩት ከረር አድርጐ 'ወደቤት !' አለኝ ። በጣም ደነገጥኩ ። ያስደነገጠኝ ምኑ መሰለህ! 'ወደቤት ሲለኝ' የኛ ቤት ይሁን የሱ ምንም አልገባኝም ፡ ግን ከአንድ ነገር ጋር ተመሳሰሉብኝ ። ከአባቴ ሁኔታ ጋር ! ለመጀመሪያ ጊዜ የአባቴን መላጣነት ከሱ ጋር አዛመድኩት ። ያን ሰአት ምን እንዳሳሰበኝ አላውቅም ። መብረር መሮጥ አሰኘኝ ። በጣም ፈራሁ ። ቀና ብዬ ላየው እንኳን ፈራሁ ። መንገዱ ምን ያህል ጊዜ እንደፈጀብን አላውቅም ። ቤቱ ደረስን አሰገባኝ ፡ ደንዝዣለሁ። ከመቼው እንዳደረሰው አላውቅም ሻይ ሰጠኝ ። በደመነፍስ ጠጣሁት ። በኋላ ግን ሳስበው ሻይ ውስጥ የተጨመረ ነገር ሳይኖር አይቀርም ። በዚያ ሰአት ይፈራረቅብኝ የነበረው የአባቱና

Scanned with CamScanner

የእናቴ ምስል ነበር" ብላ በኃይል በረጅሙ ተነፈሰች ። ሲራክ ለውጡን ሲቆጣ ታወቀው ።

"ሊስመኝ ይታገለኝ ጀመር ። ልታወመው አልቻልኩም ። ሰውነቴ እንደ አንዳች ነገር ይንዘፈዘፋል ። በስሜት ተወጥሬ የምታት መሰለው መሰለኝ 'አይዞሽ' እያለ ወደ አልጋው ወሰደኝ ። ሰውነቴን ምን እንዳደከመው አላውቅም ። አሁንም በአይነ ህሊናዬ ምስሎች ይፈራረቁ ብኛል ። የአባቴ ፣ የእናቴ ፣ በተለይ እናቴ ደም በደም ስትሆን ሁሉ ይታየኛል ። ህሊናዬን ሳትኩ ! ።

"ብቻ ባጭሩ ምን አለፋህ ፣ ዐጥሩ የተመለጠ አስተማሪ'ኳን ገብቶ ሲያስተምር መንፈሴ ይታወካል ። 'አይዞሽ !' የሚል ቃል አልወድም ። ይገርምሃል መኪናው ውስጥ እያለን 'ወደ ቤት' ስትለኝም ስሜቴ የታወከው በዚህ ምክንያት ነው ። በፍፁም እነኚህን ቃላት አልወዳቸውም ።

ሲራክ እይታውን ለረጅም ጊዜ ጣራው ላይ እንደተከለ ቆይቶ "ግን ይሄ ብቻ ነው የታሰበሽ?" አላት ቀዝቀዝ ባለ ስሜት ፣ የድምፁ ቃና ተለውጧል ።

"ጥያቄህ አልገባኝም" አለችና በጥያቄ አስተያየት ተመልክታው ፣ ውስኪውን ከኮመዲኖው ላይ አንስታ ተጐነጨች "ማለቴ ወደቤት ስላልኩሽ ብቻ ነው ያን ያክል ስሜትሽ የተነካው?"

"ነው ። ግን ..." ብላ ትንሽ ካቅማማች በኋላ "ልክ ወደቤት ስትለኝ ወዲያው አየሁህ ። ቶሎ የተመለከትኩት ጭንቅላትክን ነው ። የፀጉርህ መሸሽ ላልፈለግ ወደ ኋላ እንድመለስ አደረገኝ ። ያባቴን ምስል አስታወሰኝ ..."

ውስኪ ቀድታ እንድትሰጠው አዘዛት ። ቀዳችለት ። ቀና ብሎ ትራሱን ተደገፈና ወስኪውን ተጐንጭቶ ያሰላሰል ጀመር ።

ነገሩ ቀላል ሆኖ አልታየውም ። "ታዲያ የሁለታችን የወደፊት እጣ ምንድነው?" አላት ከሷ የሚመጣው መልስ እጅግ እያስፈራው ።

ልታስበው የማትፈልገው ጥያቄ ፣ ግን መልስ መስጠት ያለባት ። እሷም ግራ የሚገባት ይሄኔ ነው ። ሕይወት ውስብስብ ፣ አስደናቂና የተአምራት መጨረሻ የምትሆንባት ይህንን ስታስብ ነው ። እድሜ ልኳን እየተከታተለ ሲያሰቃያት ከቆየውና ከምትሸሸው ምስል ጋር ፍጥር

መውደቋ ፣ ከራሰ በራ ጋር መገኘቷ ፣ በይበልጥ ደግሞ አጋጣሚው መደጋገሙ ።

"አላውቅም ሲራክ" ድምጿ ኮስምኗል " በሽታዬን ነገርኩህ እንጂ መድሃኒቴን አላውቅም ። እናንተን ከአባቱ ጋር የሚያዛምዳችሁ አካላዊ እንጂ ውስጣዊ ፣ ወይንም መንፈሳዊና ባሕርያዊ ተዛምዶ እንደሌላችሁ ራሴን በሚገባ ማሳመን እንዳለብኝ በትክክል አውቃለሁ ።"

"ማመን እንዳለብሽ ካወቅሽ ታዲያ ለምን መተው አቃተሽ?" አላት በአባባሏ ተደንቆ ።

ተለምዷዊውን ቀዝቃዛ ፈገግታ ፈገግ አለችና "የስነልቦና ትልቁ ረቂቅና ስውር ምስጢር ይህ ነው ። በአእምሯችን ጓዳ ተደብቀው ሲያሰቃዩን የኖሩትን ነገሮች ካወቅናቸው በኋላ ነቅለን ለማጥፋት መድሃኒት አለመኖሩ ነው ። መድሃኒቱ ጊዜ ብቻ ነው ። ጊዜ ሰጥቶ ከሁኔታው ጋር መለማመድ ።

"አየህ ነገሮቹን ፣ የስነልቦና ችግሮችን ፈልገሃቸው አይመጡም ። እና የችግሮቹን መንስኤ አመሳገህህ ልዩነታቸውን ከማጤንህ በፊት ያስደነግጡሃል ። ከደነገጥክ በኋላ ነው ምክንያታቸውን አስተውለህ የምትረጋጋው ። በቅድሚያ ግን ችግሩ በድንገት ከመምጣቱ በፊት በተደጋጋሚ ጥረት ከነገሩ ጋር ከተለማመድክ ፣ ከነገሩ ጋር ያለህ ቅራኔ ይጠፋል ። ያለዚያም የሚፈጥሩብህ ጉዳት ዝቅተኛ ይሆናል ። የስነልቦና አማካሪዎችህም ሊያደርጉልህ የሚችሉት ይህንን ነው ። በቅድሚያ በሽታህን ማወቅ ፣ ከነ ከነገሩ ጋር እንድትለማመድ ማድረግ ፣ ሌላ ምንም ተአምር የለውም" አለች የብርጭቆዋን ውስኪ እየጨለጠች ።

ሲራክ በውስጡ አርግዛ ያስታመመችውን በሽታዋን እያሰበ 'በያን ዳንዳችንስ ጓዳ ምን አይነት የህይወት ጠባሳ ይኖር ይሆን? ስንቶቻችንስ በግናውቀው የውስጥ ደዌ እየማቀቅን ይሆን? እያለ ሳይታወቀው በወስጡ እደነቃት ። ሳያስበው ከበፊቱ የላቀ አክብሮት ለጣት ። በውስብስብ ማኅበራዊ ውጥንቅጥ ውስጥ ለማለፍ እንደምትታገል ነፍስ አድርጐ ተመለከታት ።

"ከዚህ በፊት ተመሳሳይ ችግር አጋጥሞሽ ያውቃል?" አላት ።

ቅንድቦቿን ወደላይ አድርጋ ለማስታወስ ሞከረችና "አ–ዎ ግን በተለየ መልኩ ነው ። እንዳልኩህ ክፍል ገብቶ ከሚያስተምር አስተማሪ ጀምሮ በአካባቢው በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ እስከሚያጋጭኝ

Scanned with CamScanner

ሰዎች ድረስ እንዳንዷ እቸገራለሁ ። ይበልጥ የሚያስጨንቀኝ ግን እንዲህ እንዳንተ በወዳጅነት የቀረብኩት ሰው ሲሆን ነው" አለችና ወደሱ እየተመለከተች "ክንፈን ታውቀዋለህ?" አለችው እየተጠራጠረች ።

"ክንፈ ማን?"

"ክንፈ ወልደአምላክ !"

ሲራክ በሁኔታው ተደንቆ "ስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ነበር ..." አላትና የሚሰራበትን መስሪያ ቤት ጭምር ነገሯት ትክክለኛነቱን አረጋገጠችለት ።

"በደንብ ትተዋወቃላችሁ?" አለችው ተደንቃም ፣ ተደስታም ።

"አ–ዎ! ግን ይሄን ያህል የቀረበ ወዳጅነት የለንም ። ብቸኛና ጭምተኛ ነው ። ከፍተኛ የሙዚቃ ፍቅር ስለነበረው ነው ለይቼ የማውቀው ። የተለያየ ዲፓርትመንት ብንማርም አንዳንድ ኮርስ አብረን ተምረናል ። አዘውትርን ስለሙዚቃ እንጫወት ነበር ። በተለይ ጥሩ የፒያኖ ችሎታ ነበረው ። ከሚሽነሪዎች ጋር በማደጉ ነው ፣ የፒያኖ ጨዋታ ችሎታውን ሊካነውና በራሱ ጥረት ሊያዳብረው የቻለው ። ከዩኒቨርስቲ ቆይታ በኋላ ግን እየተራራቅን መጣን ። ማግባቱን–ኳን የሰማሁት ከሌላ ሰው ነው" አላት እንዴትና ለምን እንዳነሳችው ለማወቅ ፈልጎ ።

"የት ጋ-ተዋወቃላችሁ?" አላት ።

"ወዳጄ ነበር ። አሁንም ጥሩ ጋደኛዬ ነው ።"

ሲራክ በመልሷ ደነገጠ ። ፍፁም ያልጠረጠረው ነበር ። "ወዳጄ ስትይኝ አልገባኝም ። ወዳጅነታችሁ ምን ደረጃ ድረስ ነበር? ማለቴ ቅርበታችሁ በምን መንገድ ነበረ?" አላት በተጨማሪ ሊል የፈለገው ነገር ተምታቶበት ።

ትንሽ ፈገግ አለችና "በምን አይነት ልበልህ ፣ እንደኔና እንዳንተ ማለቴ ነው ። አሁን ግን በጓደኝነት ላይ የተመሰረተ ንፁህ ወዳጅነት ነው ያለን ።"

"ለምን የጓደኝነት መስመራችሁን ለመቀየር ፈለጋችሁ?" አላት የቅናት ስሜቱን ለማላወቅ እየታገለ ።

"ስለሱ ላጫውትህ ነበር ወሬ እጅማመሬ ። ክንፈ ግሩም ሰው ነው ። በተለይ ለእንደኔ አይነት ባህሪይ ላለው ሰው መሬት ነው ። ለሰው አስቸጋሪነቴ ይታወቀኛል ፣ ይሰማኛልም ። እንዳይሰማኝ ያደረገኝ ሰው

ቢኖር ክንፈ ነው ። ከትውውቃችን ጀምሮ እወደው ነበር ። ይበልጥ በቀረብኩት መጠን በጣም እየወደድኩት መጣሁ ። የሱ ግን የተለየ ነው ።

"ከሚገባው በላይ እንደሚያፈቅረኝ ይታወቀኛል ። በፍቅሩም ሙሉ እምነት ነበረኝ ..." አለችና በረጅሙ ተንፍላ "ግን ምን ታደርገዋለህ! የስቃዩ ምንጭ ራሴን እያደረኩ መጣሁ ። ያለምክንያት አልነበረም ። በሽታዬን በሱ ላይ ወዲያው አልተረዳሁትም ። ብቻ የሚሰማኝን አላውቅም ። ደስታ ግን በውስጤ መጥፋቱ ይታወቀኝ ነበር ። ተስቃይቼ ማሰቃየቱን አልፈለኩትም ። እሱ ደግሞ እኔ በምሰጠው ስቃይ እየተደሰተ የሚኖር ፣ እጅግ አድርጐ የሚያፈቅረኝ ሰው በመሆኑ ፣ ያ ሁኔታው ደግሞ እኔን በይበልጥ እያሰቃየኝ ባጠቃላይ ባየሁት ቁጥር ፍርሀት ፣ ጭንቀትና ሰላም ማጣት እየተፈራረቁብኝ ፣ ምን ልበልህ ... ደስታን አጣሁ። ምክንያቱ ግን እኔ ነበርኩ ። ልለየው አልወድም ፣ ግን ደግሞ እሱን ማግኘት አያስፈራኝ እሽሽው ጀመር ። የተወሰነ ጊዜ ፣ በሆነ አጋጣሚ ካልተከተለኝ እኔው ራሴ እንደሸሸሁት አቀርበዋለሁ ። በአብዛኛው ግን ይከተታለኝ ስለነበር ፣ አቅጣጫችን ግብ የሌለው መስመር እየሆነብኝ እቸገር ጀመር ።

"አንድ ቀን ግን ቁርጥ ውሳኔ አደረኩና በግልጽ ፊት ለፊት ነገርኩት። የግንኙነታችንን መስመር መለወጥ እንዳለብኝ አስረዳሁት ። እንጉን እየወዘወዘ ሊቀበለው እንደማይችለ ገልፀልኝ ። ሥህኩበት ። ፊቱም እለቀስኩ ። በፍፁም በዚህ ዓይነት መንገድ ልንቀጥል እንደማንችል ፣ በውስጤም ሰላም እንዳጣሁ ነገርኩት ። ሊቀበለኝ አልቻልም ። እንደዛው ተለያየን ። ጠፍቶ ቆይቶ ልደውል አልደውል እያልኩ ላመነታ፣ ራሱ ደወልልኝ ። ተጣልተን ከተለያየን ሶስተኛ ቀናችን ነበር ። ድምፁን ስሰማ ከመቃብር የተመለስ ያህል ነበር የተሰማኝ ። ጥላችንን ሁሉ ረስቼ 'የት ጠፍተህ ከረምክ?' አልኩት ። 'ከውሳኔሽ ጋር ራሴን ሳስታርቅ' አለኝ። ደነገጥኩ ። ላዋራው አልቻልኩም ። መለያየትን መወሰኑ ታውቆኛል ። ግራ የገባኝ ግን ያን ያክል ምን እንዳስደነገጠኝ ነው ። እንደመሰለኝ የመለያየቱን ውሳኔ ያፀናሁት እንለያይ የሚለውን ጥያቄ አይቀበለውም ብዬ ስለምገመት መሰለኝ ። ከዛን በኋላ ሰው ሁሉ አስጠላኝ ። በሰው ላይ እምነት አጣሁ ። እያደር ክንፈን ለምን እሸሸው እንደነበርና በውስጤ ያለው ሰላምና ደስታ ለምን እንደሚደፈርስ እየተረዳሁ መጣሁ ። ዘወትር ገለጥ ያለው ግንባሩ ያስፈራራኝ ኖሯል ፣ ይሄን የተረዳሁ ዕለት ራሴን

Scanned with CamScanner

ጠላሁ ...” በረጅሙ ተነፈሰችና ንግግሯን ቀጠለች ።

“ያም ሆነ ይህ ፣ ንፁህ ወዳጅነቱን አልነፈገኝም ። አሁን ድረስ ንፁህ ፍቅሩን የአባቴ ምስል ከርሱ ጋር በማገናኘት ለአእምሮዬ በፀነሰው ጥላቻ ከንፈን መለየቱን ባሰብኩ ቁጥር ፣ በደሉ ጮልቶ ይሰማኛል ። ያንን ለመነካስ ግን ጊዜ አልሰጠኝም ። አገባ ።

“በማግባቱ መደነቅ አልነበረብኝም ። ግን ማመን አቃተኝ ። በራሴም እምነት አጣሁ ። ይህንን የተመሰቃቀለ ሃሳቤን ለማስተካከል ብዙ ጊዜ ፈጅቶብኛል ። ከንፈም የተቻለውን ያክል ረድቶኛል ። ከንፈ ያገባ ዕለት ያጋጠመኝን ልንገርህ ... ሊያገባ ከወሰነበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰርጉ ስንስርዓት ድረስ ስለሰርጉ ያማከረኝ ነበር ። በፊት በፊት ለማስቀናት ይመስለኝ ነበር ። እኔም የሆዴን በሆዴ ይዤ የይምሰል ድጋፌን አሰጠው ነበር ። እያደር ነው በንፁህ የወዳጅነት ስሜት መሆኑን እየተረዳሁ የመጣሁት ። ሊያገባ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ባይፈጠር ኖሮ የኔና የሱ መጨረሻ ይህ ይሆናል ብዬ መወሰን አልችልም ነበር ። ከንፈ ምን ጊዜም ላጣው የማልፈልገው ሰው ነበርና ... ሁሉ አለፈ ! ... የሰርጉ አለት ማንን አየሁ መሰለህ? ፍፁም ያልጠበኩት ሁኔታ ነበር ። ከዚህ በፊት ከሙሽራይቱ ጋር አላስተዋወቀኝም ። ያን ጊዜ ስመለከታት ደነገጥኩ ። ፈዝዤ ቀረሁ ፣ ልጅቷ የታናሽ ወንድሜ ወዳጅ ነበረች ። በዛን ሰአት ወንድሜ ለትምህርት ውጪ ሀገር ነው ። ብቻ ሳያት የተሰማኝን ልነግርህ አልችልም ። ሌላ የማላውቃት ሴት ብትሆን ይሻለኝ ነበር ። ልጅቷ እንድታየኝ አልፈለኩም ። ስሜቷን ረብሸባት ሰርጓ እንዲበላሽባት ስላልፈለኩ ፣ ተሸሽጌ ወጣሁ ። ለምን ስነስርዓቱ ሳያልቅ እንደወጣሁ ፣ ከንፈም እኔም ከሰርጉ በኋላ አላነሳነውም ። እሱ በምን እንደተረዳመው አላውቅም ” አለችውና ሰአቷን ተመለከተች ። እኩለለሊት አልፏል ። በሰአቱ መሄድ ተደንቃ “ሊነጋ–ኮ ነው!” አለችው ፈገግ ብላ ።

ሲራክ ታሪኩ እንዲቋረጥበት አልፈለገም ። “ይሁን ቀጥይ” አላት ትራሱን እያመቻቸ ። ለሱም ለሷም በድጋሚ በብርጭቆዎቻቸው ውስኪ ቀዳችና የድርሻዋን አጣጥማ “በ–ቃ ! እሱም አገባ ። ያው አስቀድመን እንደጀመርነው ንፁህ ወዳጅነታችንን ቀጠልን ። ቤቱ ሄጄ አላውቅም ። ብስልክ ፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ ፣ ባጋጣሚ አንዳንድ ስፍራዎች እንገናኛለን ። በተረፈ ሌላ ነገር የለም ።

“በኋላ ግን ምን ተፈጠረ መሰለህ? ወንድሜ ከውጭ ሀገር ትምህር

ቱን ጨርሶ መጣ ። የሚደንቅህ ልጅቷ አሁንም ከወንድሜ ጋር አብራ መውጣት ጀመረች ። ወንድሜም ማግባቷን ያውቃል ። አለ አይደል? ያላለቀ ፍቅር ... ጊዜና ሁኔታ ያልገታው ያገረሸ ፍቅር ፡ ሁለቱንም እይን አላጥቷቸዋል ፡ ልቦናም ነስቷቸዋል ።”

ሲራክ ጉሮሮውን ሳለና ... “ ክንፈ ይህንን ነገር ያውቃል?” አላት።

“አያውቅም ። ለኔ እንኳን በስልክ ያጫወተኝ ባለቤቱ ምን እንደሆነች አለማወቁን ነው ። የስነልቦና ባለሙያ በመሆኔ አንዳንድ ሁኔታዎችን እንድረዳው ገልያልኝ ነበር ። ቢቻለኝ እንዳንጋግራት ሁሉ ጠይቆኛል ። አሁን ለኔ ችግር የሆነብኝ ይህ ነው ። ላነጋግራት በፍፁም የምችል አይመስለኝም ። ለወንድሜ ጉዳዩን ላይ ላዩን አንስቼበት ነበር ፡ ሊቀበለኝ አልቻለም ። እንዳልኩህ ታውረዋል ።”

“ከክንፈ ጋር ያላችሁን አግባብ ወንድምሽ ያውቃል?” አላት ውስኪውን ተጐንጭቶ ። አንገቷን ነቅንቃ “በጭራሽ እኔም ልነግረው አልፈለኩም ። ብቻ በምን አይነት መንገድ ልረዳው እንደምችል አላውቅም” ብላ ወደ ሲራክ ዞረች ። “... ቅድም ክንፈን አውቀዋለሁ ስትለኝ አንድ ነገር ታይቶኛል ። ለሁለት ሆነን አሁን ካለበት ችግር ልናወጣው እንደምንችል ...” በፈገግታ ተመለከተችው ።

“አትጠራጣሪ !” አላት ሞቅ ብሎት ።

መለኪያዋን አስቀመጠችና በሁለት እጆቿ አቅፋ ስትስመው ፡ “የኛስ ጉዳይ?” አላት በእጁ ያለው የብርጭቆ ውስኪ እንዳይደፋበት ከመዲኖው ላይ ለማስቀመጥ እየሞከረ ።

ብርጭቆው ተፈንግሉ ውስኪው ፈሰሰ ።

ሁለቱም ደንታ አልሰጣቸውም ። የክንፈን ችግር ማቃለል የበደሏ ሁሉ ካሳ እድርጋ ቆጥራ ስትፈነጥዝ ፡ የስሜቷ መነቃቃት የሱንም አንቅቶት መተሻሸቱን ፡ መሳሳሙን ፡ መተቃቀፉን ... ቀጠሉበት ።

“የኛስ ጉዳይ?” አላት ቅድም መልስ ያላገኘውን ጥያቄ በድጋሚ አንስቶ ።

ራሷን ወደ ግራ መለስ አደረገችና “ምን እንድልህ ትፈልጋለህ?” አለችው ቆጣ ብላ ። በአፍታ የስሜቷ መለዋወጥ እያስደነቀው “ነገሩን በእርጋታና በጥሞና መመልከት ያለብን መስሎኝኮ ነው” አላት ።

“እንደኔና ክንፈ ?” አለችው ፍርጥም ብላ ።

ሁኔታዋ አላማረውም ። አዜብ በውስጡ ያለውን ሃሳብ በሙሉ

Scanned with CamScanner

አራግፋ ከነገረችው በኋላ የሚያነሳሳት ጥያቄ የማትፈልገውና የማትወደው እየሆነ መንፈሷን አሻከረው ። አበሳጫት ። አነጫነጫት ።

ለሊቱ ነጉዷል ። ሁለቱም በየፊናቸው በጀርባቸው ተንጋለው በሃሳብ ተወጥረዋል ። የምትወደው ክንፈ ፡ የበደለችው የሚመስላት ክንፈ ፡ በጥረቷ ችግሩን ፈታለት ፡ ሲያመሰግናት ደስታው ደስታዋ ሆኖ የሕሊና እርካታን ሲሰጣት ፡ ለሚወዱት ሰው የሚፈልገውን ነገር ከማድረግ የበለጠ ምን የሚያስደስት ነገር አለ? ...

በቀላሉ አትረታም ። ገና በልጅነቷ ያልጠናው ስነልቦናዊ ሕይወቷ በኑሮ አሸክላ ተወነካክሯል ። ይህንን ለማሸነፍ ረዳት ያሻታል ። በእውኑ ሰአት ከኔ የቀረበ ማን ሊረዳት ይችላል?... የሁለቱም እያታዎች ከጣራው ሲነሱ ተፈላልገው ተጋጩ ።

"ምን ነበር የምታስበው?"
"ክንፈን እንዴት አድርገን ልንረዳው እንደምንችል!"
"ሙች በለኝ እስቲ !"
"እዜቢና ሙች !"
"እዜቢና?" ድምጿ ዜማዊ ስልት ነበረው ።
"አቻን እዜቢና!"

የሁለቱም እጆች ተዘርግተው ሰውነቶቻቸውን ይፈላልጉ ጀመር .. ። እየቃተቱ ... እየዋተቱ ... እንድ ሆኑ ፡ ሁለቱ ።

ምእራፍ ዘጠኝ

ማስብ ፡ ማስብ ፡ ማስብ...የሃሳቢ ጉዳና ተጠማዞ እንኪፈተ ወደ መጀመሪያው ሐሳቢ ያመጣታል ። እንዳች የሃሳቢ መኝቻ ላይ ሳትደርስ እደክማለች ። ታሳት ተራራ በጉሀ የወጣች ያክል ሰውነቷ ይዘላል ። ሮጣ ማድረግ አስጠላት ። ቤቱ የሞት ጥላ ያጠላበት ይመስል ይቀፋል ። ቀስብላ ተነስታ ክንፈ ከሌለ የማትጠጋውን ፒያኖ ልትደበድብ ተጠጋች፡ ደንገት የፒያኖው ጨኸት በሥጉንቅላቷ የሚተራመሱትን ሃሳቦቿን ያበታትንላት እንደሆነ በማሰብ ።

አልተሳካም ።

በምትኩ የፒያኖው ድምፅ ማድቤት የነበረችውን የቤት ሠራተኛ ጉትቶ አመጣት ። የሳሎኑን በር በቀስታ ከፍታ ፒያኖው አካባቢ ተመለከተች ። ያልጠበቀችው ሰው ነው ። ቀስ ብላ በሩን ዘግታ ልትመለስ ስትል እፀገነት ጠራቻት ።

"ምን ፈለግሽ?"
"ጋሼ መስለውኝ ነው!" አለች ብርቂቱ ቅልስ—ልስ ብላ ።
እፀገነት ልቧ ሽብር አለ "ቢሆንስ! ለምን ፈለግሽው?"
"መልዕክት ልንግራቸው ።"
"የምን መልዕክት?"

ብርቂቱ አቅማማችና "እቶ ሲራክ የሚባሉት ሰውዬ ቅድም ደውለው፡ በጣም ስለምፈልጋቸው ነገ በዚሁ ሰአት ይጠብቁኝ ብለዋል ። ይሄንን ለመንገር ነው" ብላት ትንሽ ቆመችና የእመቤቷን መልስ ስታጣ ወደ ግጅት ተመለሰች ።

እፀገነት አሰበች ። ክንፈ ሲራክ የሚባል የቅርብ ጓደኛ የለውም ። ብቸኛውና የማትወደው ጓደኛው ቢኖር ሽፈራው ነው ። ለምን እንደሆነ አታውቅም ። ሽፈራውን እንዲሁ ከመራት ተነስታ ትጠላዋለች ። ደስ — ደስ አይላትም ። ክንፈን ልታገባ ሰሞን ቤቱ ስትመላለስ ሁሌ አታጣውም ። የሷን መምጣት ሲያውቅ ሰላምታ ብቻ ሰጥቷት ቤቱን የጭላቸው ውልቅ ይላል ። እሷም የሚወዳት ስለማይመስላት ይሆናል

Scanned with CamScanner

የምትጠላው ። ደግነቱ ካገባች በኋላ ቤታ ዝር ብሎ አያውቅም ። "ግንጬ ሲራክ?"

በዚች ወር በማትሞላ አጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ያህል እርስ በርሳቸው መራራቃቸው ፡ መለያየታቸውና እንዳቸው በእንዳቸው የልጓ ጓዳ የሰመጡበት ሲመስላቸው ፡ ሳይታወቃቸው ርቀው መገኘታቸው…ብ ፈት አብረው የነበራቸው የንፁህ ልብ ጊዜ እንደተሰረንጣሪ ርቂት ርቋ አምሮና ተውቦ ታያት ። ምን አይነት እድል እዚህ እጣ ውስጥ እንደከተታት እያሰበች ዳግም ነጐዶች ። ማጣፈያው እያጠራት፡ እንዲ ክንፈን ጨክና መተው ግልግል ሲመስላት ፡ ደግሞ ከሂኖክ ጋር ሆኖ ክንፈን ማሰብ ስቅይ ሲሆንባት…ደበደበችው ፡ ጢያኖውን ። ክንፈ ያስተማራትን ዜማ ለመጫወት ሞከረች ። ወፍራሙን ስትጫን ሲያንሬ ባት ፡ ቀጭኑን ስትመታ ሲያለቅስባት "ኤጭ!" ብላ ከፒያኖው በርከካ ላይ ተነሳች ።

ሰአቷን አየች ። ውለት ሰአት ሆኗል ። ክንፈ አውን ድረስ አልመጣም። ቤቱ ጭር ስላለባት ቴሌቪዢኑን ከፈተች ። ቆንጆ ወጣት የዕለቱን ዝርዝር ፕሮግራም ታስተዋውቃለች ። አብረው አድገው አብረው ተምረዋል ፡ ከቤት ምሳ ለየራስ አስቋጥረው ፡ በጋራ በልተው እንዳላደጉ…ዛሬ ለእንዴትነኝ መጠፋፋታቸው አስገረማት ። ለቤተሰቧ ስልክ አለመደወሏ ታወሳት ። ወደ ስልኩ ሄደች ፡ እናት አባቷ ቤት ሰላም የለም ። ትልቁ ወንድሟ ከዕለት ወደ ዕለት ሁኔታው እየባሰበት እምሽቶ ከመግባቱ ሌላ ፡ ያለልክ እየጠጣ ቤተሰብ ጭምር ጤና መንሳቱ ፡ ለብዙ አመታት አባቱ በከፍተኛ ጥንቃቄ ይዘዋት የነበረችውን የቤተሰቡን መኪና ከጥቅም ውጭ ማድረጉ ፡ ያ ሳያንስ ሰሞኑን ያመጣው አዲስ እመል ጭራሽ ሥራ አልገባም ማለቱ ፡ ቤተሰቦቹን አስጨንቋቸዋል። ከሁሉ ይበልጥ ግራ ያጋባት የታናሽ እህቷ ሁኔታ ነው ። ትልቀልቀነቷ ብሶባታል። 'ተይ' ሲሏት 'ምናባችሁ' 'አይሆንም' ካሏት ደግሞ 'ቤቱን ጥዬ ጠፋለሁ' እያለች ማስቸገሯን ሰምታለች ።

"ኤጭ!" አለች ተደዟል እያለ ያስቸገራትን ስልክ በሃይል ዘግታ ። ትንሽ ስትተክዝ ቆየችና ስልኩን በድጋሚ አንስታ ቁጥሮቹን አሽከረከረች። ይጠራላት ጀመር ።

"እማዬ ምን ሆነሻል?" አለች እወገነት ፡ በስልክ ውስጥ የምትሰማው የእናቷ ድምፅ ጉርነን ስላለባት ፡ እንዳለቀሱ ጠርጥራ ።

"ምንም አልሆንኩም…ምነው?"

"ድምፅሽ…ድምፅሽ ተለውጠብኛል" መጨነቋ ከንግግሯ ያስታውቃል ።

እናትዬው ቆጣ አሉና "እንቺ ደሞ! ምንም አልሆንኩ ስልሽ…! ተንፋን ቢጤ ነው መሰል ፡ ያነፋንፈኛል ።"

አላመነቻቸውም ። የውስጉም ጤንነት ጠየቀች "ደህና ናቸው" አሏት ። የወንድሟን ሁኔታ አነሳች ። "እስቲ ዐሎቱን ሰምታ እመብርሃን በለተቀኖ ብትረዳው ነገ ስራ እጀምራለሁ ብሎናል ። የሱ ነገር መቼም ከዛሬ ለነገ ሌላ ነው" አሏት ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው ።"

ጥቂት እውር፡ስ ስልኩን ከዘጋች በኋላ በሃይል ተነፈሰች ። ስለራሷ ፡ ስለቤተሰቧ ፡ ስለክንፈ….ስለሄኖክ…ስለሁሉም የተረጋጋ አሳብ አልነበራትም ። ስለምንም ላለማሰብ ትፈልግና ፡ ደግሞ እሺ አይሳትም ። ተመልላ ማጠንጠን ትጀምራለች ። ከተደጋገመ የአሳብ ድሪቶ በቀር ሌላ የለም ፡ ልይወት አስፈራቻት ፡ ይበልጥ ደግሞ ብቸኝነቷ ። ክንፈን ሳትፈልግ ርቃዋለች ። ሄኖክ ደግሞ ችግሯን ፈፅሞ ሊረዳላት አልቻለም ። እንዳውም የፅን ፍርሃትና አለመቁረጥ ነው የችግሯ መንስኤ አድርጐ የሚወስደው ። እሷ ደግሞ እንዴት ትወስን? እንዴት ትቁረጥ? ሌላው ቢቀር ከሄኖክ ጋር ያላት ቁርኝት አስተማማኝነቱ ምን ድረስ እንደሆነ እንኳን ማወቅ አትችልም ። ሳትመርጥ አቆራኝቷታል ፡ ሳትፈልግ አለያይቷታል ። መልሶ ደግሞ አገናኛት ። እንዴት ትቁረጥ? ስለ ክንፈ ሰብእና ማንሳቱ ይከብዳታል ። ማንም ለፀ ከሱ የተሻለ ሊሆንላት የሚችል ሰው እንዳለ ማሰቡ ራሱ ሃጥያት መስሎ ይታያታል ። ይህንን በምታነፃፅርበት ወቅት ፡ ሚዛኑ ያለእንዳች ማመንታት ለክንፈ ያደላና ክንፈን ማሰብ ስትጀምር ልቧ በኃል ይመታል። ደስታዋ ሁሉ ከሄኖክ ጋር አብሮ የሚጠፋ ይመስላታል ። እንዳንድ ጊዜ ሄኖክን ስታገኝ የምትሸምተውን የስቃይ ደስታ ለመምረጥ ይዳዳታል ። ህይወት መጨረሻቸው በማያታወቅ ሁለት የሃሳብ ገመዶች ተጠምዝዛለች ። ምርጫዋን ለባለቤቱ ትታ ።"

የክንፈ ቫልስዋገን ግቢ ውስጥ ስትገባ ፡ የሞተር ድምፅ መኝታ ቤቷ ድረስ ይሰማል ። የራስጌውን መብራት አበራችና ለአቷን ተመለከተች ። አራት ለአት ተኩል ሆኗል ። መብራቱን መልሳ አጥፍታ ተሸፋፍና ተኛች።

በዚያ ጨለማ የመኝታ ክፍል ውስጥ በጥንቃቄ ገብቶ ፡ ጫማውን

Scanned with CamScanner

ካወለቀ በኋላ አልጋው ላይ የተኛውን ሰው ተመለከተ ። ጨርሶ እንቅልፍ እንደወሰዳት አልተጠራጠረም ። ሊቀሰቅሳት አልፈለገም ። በጥንቃቄ ቁም ሳጥኑን ከፈተና ያወለቀውን ልብሱን አስገባ ። ወትሮም ከወገባ በላይ ራቁቱን ነው የሚተኛው ። የፒጃማ ሱሪውን አጠለቀ ። እንደገና በጥንቃቄ ፊቷን የሸፈነውን ብርድልብስ አነሳ ። የተኛች መስሎት በጥንቃቄ ሳማት።

የውስኪ ትንፋሽ አጠናት ።

ህይወት መልህቋን ጥላ አልተረጋጋችም ። ትንሣለች ። ሁሉም ለኑሮው ስኬት ይባክናል ። አነሰም በዛ ጊዜ በየእያንዳንዱ ሰው ላይ የሚፈጥረው የራሱ ስርዐት አለው ። ጥሩ ጊዜ ያልፋል ፡ መጥፎ ጊዜም ያልፋል ። ያጥራል ፡ ይረዝማልም ። በዚህ አንፃር ጊዜ ስሜታዊ ቢመስለንም የተረጋጋና ስርዓት ያለው ውህደቱን በያንዳንዳችን ላይ ያሰርፃል ። መለኪያው የሚለያየው ስርዐቱ በውስጣችን ገብቶ ስሜታችንን ሲጐዳኝ ነው ።

ክንፈ የሶስት አመት የደስታ ትዳር ዘመኑ ሳያውቀው እየተፈተለከ ሲያልፍ ፡ ለወር ያጋጠመውን ችግር ለማለፍ ግን ብዙ ጊዜያት የማላለፍ ያከል ታክቶታል ። ህይወትን አስቦ እንዳላዘመባት እንዳላጣጣማት ሁሉ እፍታውን ጠጥቶ አንቡላውን እንደጋቱት ውስጡ በምሬት ትንገሸግሿል። ዘፈኑ ለቅሶ ፡ እንጉርጉሮው ብሶት እየሆነበት ተቸግሯል ። ሲያሰኛት ህይወት እንዲሁ ነች ፡ ታቀባዥራለች ።

እስከ ዛሬ በትአምር የተኖረ ይመስል ፡ የመኖር ውሉ በድንገት ተዛብቶ እኛነታችንን ሲፈታተን ፡ በእኔነት ተገንብቶ የኖረው ማንነት በድንገት ፍርክስክሱ ሲወጣ ፡ የህልውና ክስረት በህሊናችን ሲደርስ ፡ ስንት ዘመን ሲገነቡት ከርመው በጅምር እንደተውት ባቢሎናዊያን ግንብ፡ ሚስቱ የጨው አምድ እንደሆነችበት ሎጥ የሚሰማንን ማወቅ እስኪያቅተን ድረስ እንቀባዥራለን ።

“ሕይወት ተአምሯን አትቋጭም” አለና ክንፈ ሰአቱን ተመለከተ ፡ ለስልክ ቀጠሮው ሩብ ሰአት ይቀራል ። “ሲራክ?...” ለማስታወስ ቢሞክር በፍፁም ትዝ ሊለው አልቻለም ። ትናንት ማታ ቢቱ እንደገባ ሰራተኛዋ መልእክቱን ስትነግረው ስም ተሳስታ እንደሆነ ፡ በደንብ እንድታረጋግጥለት ቢጠይቃት ፡ በፍፁም እርግጠኝነት መልሳለታለች ። የደዋዩን ማንነት አለማወቁ የስልኩን ጥሪ በጉጉት እንዲጠብቅ አድርጐታል ።

የደነቀው ነገር ቢኖር ሲራክ የተባለው ሰው እንዴት ስልክ ቁጥሩን ሊያውቅ እንደቻለና ደግሞም ለምን እንዲህ በጥብቅ እንደፈለገው ነው ። ሁሉን ሰዎች ሊያገናኛቸው የሚችል ነገር በፍፁም ሊመጣለት አልቻለም ።

ከሰላምታና ከጥቂት የትውስታ ጨዋታዎች በቀር ያወሩት ነገር አልነበረም ። በስልኩም ውስጥ ማንነቱን ሊያስታውሰው የቻለው በስንት መከራ ነው ። ክንፈ ይበልጥ ግራ የተጋባው ሲራክ የደወለበትን ምክንያት ሊያውቅ ስልኩ በመዘጋቱ ነው ።

ቤቱ ሞርታው አልለቀቀውም ። ቀድሞ ሁለቱም በጥድፊያ ቤታቸው ገብተው ለማሞቅ የሚቻኮሉበት ቤት ፡ ዛሬ አና እና መሽቶቱ እንጀቱን በላው ። የሳሎኑን ግድግዳ ሁሪያውን አማተረ ። የሙሽርነታቸው ...ለየግላቸው የተነሷቸው ፎቶዎች...የፒካሶ ስእልም በሱላ በኩል ተሰቅሏል ። ጓደኛውን ደምሴን አስታወሰው ።

ሁለተኛ ደረጃ ጨርሰው ፡ ክንፈ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ ጓደኛው ግን በቀጥታ የገባው ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ነው ። ያምሴ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት አንድም ቀን መምህር የመሆን ዝንባሌ ለክንፈ አሳይቶት አያውቅም ። የድንገት ውሳኔውም ክንፈን አስደንግጦት ምርጫውን እንዲያጤነው ደጋግሞ መክሮታል ። ለምን ዩኒቨርሲቲ አብሮት እንደማይገባ የሰጠው ምክንያት ክንፈን አላጠገበውም ።

“እኔ የምማረው ዲግሪ ለመሰብሰብ ፡ ያለዛም የግሌንና የራሴን ምኞት ፍሬ ስል አይደለም ። ይልቅ ይህንን ያልተማረ ወገኔን እንዴት እረዳዋለው ብዬ እንጂ! ለዚህ ደግሞ ካሁን በኋላ የማጠፋው ረጅም ጊዜ አልፈለግም ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን በድንቁርና የሚንከላወሰውን ወገኔን ልመራው እሻለሁ ። ወደ ብርሃንም እጠቁመዋለሁ ።” ነበር ያለው። ክንፈ በአንጋጉ ተገርሞ “ታዲያ ይህንን ሀሳብህን እስከ ዛሬ እንዴት አልገለጽክልኝም?” አለው ።

“እየህ ፡ ሰዎች የህይወት አትጫጫዎቻቸውን ለመተለም የተለየ ምክንያትና አጋጣሚ ይሻሉ ። ይህ አጋጣሚና ምክንያት ባላሰቡት ወቅት ይከሰትና የህይወት አቅጣጫ ይለውጣል ። እናም ትውልድ ሀገሬ ገብቼ ወገኖቻችንን መርዳት እንዳለብኝ ከምን ጊዜም ይበልጥ የተሰማኝ አሁን ነው ፡ ከዚህም ቀደም ብዬ አልነገርኩህም” ብሎት ነበር ። ያምሴ

Scanned with CamScanner

በምርጫው አላወላዳም ። ወደ መምህራን ማሰልጠኛው ገባ ።

የማሰልጠኛው ትምህርት ተጠናቶ ክንፉ የዩኒቨርሲቲውን ትምህርት እንዳገባደደ በፈቃድ በመምህርነት ስራ በትውልዱ ሀገሩ ሲመደብ የፒካሶን ስእል በማስታወሻነት ሰጥቶት ስለነበር ፡ ክንፈም ጥሩ ፍሬም አሰርቶለት ለቤቱ ግሩም መስህብ ሆኖለታል ። ደምሴ በህፃናት ተማሪዎቹ ታጅቦ ፡ ፊቱን የወረረው ሃም ጮልቶ እየታየ ከነጮፈፈው ተነስቶ የላከለትን ፎቶ ከስእሉ ስር ፍፈሙ ላይ ሽጉጠታል ። በትርቡ አረፍቴን አስታኮ ወደ ከተማዋ ብቅ ሲልም አግኝቶታል ። ለአላማው ያለው ቁርጥነት እንዳለ ነው ። አለባበሱ ፡ አካሄዱና አነጋገሩ ጭምር ሀገሬውን መስሏል ። እድሜውም ኑሮውም ነው መሰል ፡ ወደፊቱ ጉበጥ ግለት አምጥቷል ። በዛው ሰሞን አዲስ አበባ ብቅ ሲል ክንፈ ቤት መጥቶ የገባ ስእሉን የተመለከተ ጊዜ ልዩ ስሜት ተሰምቶት ነበር ። ትዝታ... የትምህርት ቤቱ ህይወት ፡ የጓደኞነታቸው ዘመን...ሁሉን በየተራ በህሊናው ቃኝቶታል ።

"ይህንን ስእል ለምን እንደምወደው ታውቃለህ?" — ለአፍታ አይኖቹን ከስእሉ ላይ ነቅሎ ክንፈን እየተመለከተ የጠየቀውን አስታወሰ።

"ያንተ ስእል በመሆኑ ይሆናል ።"

"ተመልከት ! አለው ደምሴ በተመስጦ ስእሉን እየተመለከተ "የፒካሶ ስእሎች የህይወትን ዝብርቅርቅ ገጽታ በተአምራዊ ብሩሾቹ አጉልተው ያሳዩናል ። የስእሎቹ እያንዳንዱ መስመር በረቂቃዊ ምናብ ብዙ ያወራሉ ። ብዙም ነገር ይዳስሳሉ ። ስራ የፈታ ሰአሊ በሸራ ላይ የሞነጫጨራቸው የሚመስሉት መስመሮችና ህፃናት ከተለያየ ቀለም እያጣቀሱ ያጨማለቁት የሚመስለን ውብ ስእሎቹ ፡ ተናግረው ፡ ተናግረው አያበቁም ። ባየሃቸው ቁጥር ይናገራሉ ። ሁሌም ድንቅና አዳዲስ ነገር ያወጉሃል" — አለው በጥልቅ ስሜት ተውጠ ። "ከፊት ለፊቱ የጥበብን ፍሬ ለመቅሰም አይናቸውን አፍጥጠው አይምሮዋቸውን ከፍተው የሚጠብቁኝን ተማሪዎች የእያንዳንዳቸውን የተዘበራረቀ ፊት እየተመለከትኩ ትዝ የሚለኝ የፒካሶ ስእል ነው ። እናም ምን ይሰማኛል መሰለህ? ፒካሶ በኔ ቦታ ሆኖ እንዴት አድርጉ ይሀንን እውቀት የተጠማ የተለያየ ውጥንቅጥ ገፅታቸውን ያወጣው ይሆን? የብሩሾቹንስ ላንታ በምን አይነት መንገድ ያናግራቸው ይሆን? እያልኩ ነው" ያለውን ሁሉ

አስታወሰ ።

ክንፈ ለአንድ አፍታ ይህ ሁሉ ለምን እንደታወሰው ለማሰብ ሞከረ። አዎ ፡ የሰጠው ስእል የፈጠረበት ሀሳብ ነው ። በጊዜው ባደረበት ወገኖቹን የመርዳት ፅኑ ፍላጐት ተነሳስቶ ፡ ታግሎ በድል እየተወጣው ነው ። አዲስ አበባ መጥቶ በተመለከተው ወቅት አካሉ ተጐሳቁሎ ፡ ጠቁሮና ከስቶ ፡ ፂሙም እንደባህታዊ ተንገሮርሞ ያየው እለት ፡ ክንፈ የተሰማው ስሜትና ደምሴ አውንም የነበረው የመንፈስ ፅናት አስደንቆት ነበር ።

"ሀገር ፡ ወገን የልጆቹን ማንነት የሚፈትነው እውን ነው ፡ በተለይ የተማሩ ልጆቹን ። እነሳሳችን ለማል ጥቅም ብለን እስካልሆነ ድረስ ይህንን ያህል አስቸጋሪ አይደለም ። ብዙዎች በህይወት ጭምር ለሀገራቸው ቤዛ ይሆናሉ ፡ ስለዚህ የኔ የአካል ለውጥ ሊያስደንቅህ አይገባም ። እንዳውም እኔ ገና ብዙ እንደሚጠበቅብኝ ይሰማኛል ። ህይወት ትግል ነው ። በተለይ ከአለማወቅ ፡ ከመሃይምነት ጋር የምታደርገው ትግል እንዴት የመንፈስ ፅናት ይሰጥሃል መሰለህ ። ህይወት የሚይጠፋበት ታላቅ ጦርነት" — ሲለው ፡ ወአው ለአፍታ ተጋብቶበት ነበር ።

ክንፈ ህይወቱ አስቀናው ። "ተፈጥሯ መፈጠሯን በተልእኮዋ የገለጠች ነፍስ ፡ ብትጠፋም የማይጠፋ ታሪክ ሠርታ የቀረች ነፍስ" ብሎ ነፍሱ ለደምሴ ነፍስ የነበራትን ክብር ገለጠችለት ። "ዋትታ ፍፃሜዋን ያላመረች ነፍስ!"

የሙገሳው ብዛት የህይወቱን ክንቱነት ጮልቶ ያሳየው መሰለው ።

"እይ ክንፈ! ጀግና ከራሱ ሕልውና አልፎ ለሌላው ሰብዕና ሲል ታሪክ ይሰራል ። አንተ ግን በጥቃቅን ማህበራዊ እዘቶት ውስጥ ዘቅጠህ ህይወትህን ተልዕኮ አልባ ታደርጋለህ ።"

አውንም በፒካሶ ስእል ላይ እንዳፈጠጠ ነው ። የፒኮሶ ስእል ይማም የህይወትን ቁርኝት ያወሳል ። አንዱን መስመር ከሌላው መስመር አያጣመረ ፡ አንዱን ሃሳብ ከሌላ ሃሳብ ጋር እያሳከረ ፡ መጨረሻ ወደ ሌላው የህይወት ጮዳና ያዘልታል ። የስእሉም ፡ የሃሳቡም ፡ የሁሉም...መጨረሻ ፡ ምንም ሆነበት ።

"አይህህ ክንፈ ፡ በእያንዳንዱ ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ለበጐ ነገር የሚደረግ ትግል ፡ አንድ ጀግና በጦር ግንባር ከሚፈፅመው ገድል ያላነሰ ትንቅንቅ ነው ። በጦር ግንባር አንድ ሞት እንጂ ሺ ሞት የለም ። አንተ በያዝከው ትግል ውስጥ ግን ሺ ሞቶች ብቻ ሳይሆን ሚሊዮን ሞቶች

Scanned with CamScanner

ናቸው ያሉት ፡ እና በርታ ሺ ጊዜ የሚሞተው ፈሪ ነው ። የጀግና ሞት አንድ ነው ። እና ያንተ ትግል የከፋ ነው ። በየደቂቃው ላለመሞት መፍጨርጨር አለብህ ። ሕይወትህን ማቃናት ፡ አላማህን ማስተካከል ፡ ጠንካራ የቤተሰብ አባወራም የመሆን ሀላፊነት ይጠበቅብሃል ። 'ቤተሰብ የህብረተሰብ መሰረት ነው' ይባል የለ ። የጠንካራ ነገር መሰረት አንተ ከምትቀልሳት ጎጆ ይጀምራል ። ገባህ?"

ሁለቱ በሀሳብ ተፋጠው ጦርነት ከመጀመራቸው በፊት ለመሸሽ ወሰነ ። ሰዓቱን ሲመለከት አሥራ ሁለት ሰአት ይላል ።

አላመነታም ፡ ኩቱን አጠለቀና ወጣ ። ወደ ቦሴ ቤት...ሲሄድ ታየው።

* * *

እፀገነት ከስራ ስትወጣ እያንዳረደረ የወሰዳት ወደ ሄኖክ ቤት ነው። አቅሏን ነስቶ የምትሰራውን አሳጥቷታል ። ችግር ነው! ለማን ታዋየው? ለማን ትንግረው? ሄኖክን በምኑ ወደድኩት ትበላቸው?

ጊዜ ብትሰጠው የባሰ እንጂ ያልሻረ ደዌ ፡ ፍቅር አትለው አንደኛውን ጠቅልላ አልሄደች ። ልቧ ለሁለት ተከፍሎ ግራና ቀኝ በሰላ ቢላዋ ይተፈትፋታል ። እትቆርጥ ነገር ለፈስፋሳ ነፍስ ነው ያላት ። በዘያ ደብቃ እንዳትይዘው ሀሊናዋ ያደናቁራታል ። ሁኔታውም ሳትወድ በግድ ያስታውቅባታል ። ክንፈም ይሰጋል ፡ ይረበሻል ፡ ይጨነቃል ፡ ሀመሟ ከሏ አልፎ ወደ ሌላው ይጋባል ። ይህ ደግሞ ይበልጥ ያስጨንቃታል ።

ሄኖክ ገና ሲመለከታት ስቀቀንና እልህ ሰውነቱን እየበሉ ያፍነከነ ኩታል ። ፍቅሩን ለመግለጽ ጊዜውም ታላቁም ሁሉም...ያጥሩታል ። እናም ይቃትታል ።

ቤቱ የደረሰው እሷ ከመምጣቷ ትንሽ ደቂቃ ቀደም ብሎ ነው ። ለመምጣቷ አልተጠራጠረም ። ያሳበው ነገር ቢኖር የግንኙነታቸው መስመር የት ድረስ እንደሆነና እስከ መቼ በእዚህ ሊቀጥል እንደሚችል ነው ። ሁኔታውን ሲያስብ እልህ ይይዘዋል ። በዙሪያሽ ከገጠመው ሁኔታ በኋላ መጠቃት ይፈራል ። ከውጪ ሀገር እንደተመለሰ እወገነት ማግባቷን ሲያውቅ ቋራሽ ጠልቷት ነበር ። እንደ ጠላት ቢቀር ይሻለው ነበር ። ቤቱ ድረስ መጥታ እልህ ውስጥ እንዲገባ አደረገችው ። ክንፈን እያውቀውም ፡ እንዲያውቀውም አይፈልግም ። ፈርቶት አይደለም ። ይጠላዋል ።

እንደ ወትሮው እወገነት እንደ መጣች መኝታ ቤት ይዟት ገባ ። ብዙዋን ናቸው ። አዜብ ከስራ አልመጣችም ። በመንገድ ላይ ነች ። የዘም ከወዳጆቿ ጋር ። ያም ሆነ ይህ ሄኖክ ግድ የለውም ። ብቻ ስትመጣበት ይመርጣል ። እወገነትን በደህና አይን የምትመለከትለት አይመስለውም ። ምክንያቱም ከወንድሟ ጋር ሆነው ስታያት ፊቷ እንደ አንሶት ነገር ሲለዋወጥ ይታወቀዋል ።

"ምነ ልታዘዝ?" አላት ሄኖክ አልጋው ላይ ካስቀመጣት በኋላ እጇቿን ወደ ኋላ አድርጌ እየቀለደ ።

"ምንም አልፈልግም ይልቅ ቁጭ በል" አለችው ፈገግ ብላ ። በሩን ቆለፈና ተመልሶ መጥቶ ከጐኗ ተቀመጠ። እወገነት ልትጠነቀቅ ሞክረች። አልቻለችም ። ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ አለ። ጭንቀቷ እንዳያስታውቅባት ስትጣጣር ቀዩ ፊቷ ፍም እየመሰለ አሳበቀባት ። ልታየው ፈለገች ፡ ግን ፈራችው ፡ እንደ አዲስ ፍቅረኛ አቅበጠበጣት ። ሰውነቷን ማረጋጋት የምትችለው ከአንድ ነገር በኋላ ነው ። እሱም ቶሎ ይረዳታል...

ቀሚሷን እያስተካከለች ቁጭ ካለች በኋላ አሰላሰለች ። ባለትዳርነቷ ትውስ አላት ። ተሳቀቀች ። ሁሉን ነገር ለመርሳት ፈለገች ። ሄኖክ በድጋሚ ደባበሳት ። ጉንጩን ማንባሯን ፡ አይኗን ፡ ሳማት ። ለእወገነት ሄኖክ አንድ አይነት ኃይል አለው ። ልዩ ኃይል! አበረድኩ ያለችውን ስሜቷን የመቀስቀስ ልዩ ኃይል...ደረቷን ፡ ጡቷን ፡ እየመላሰ ጀሮ ጥጓን ይዳብሳታል ። ከእጅ የሚተላለፈው መቀት ሰውነቷን ያጋልው ጀመር ፡ ስትታጠል ስትለበለብ ተሰማት ፡ በጭኗ መሃል መቀት ። ራሷን ታዘበች ።

እየችው...ሁሉንም አስተዋለች ። ግን ለመቃወም አልሞከረችም ። መጀመሪያ እንዳደረገችው ልብሷን ሳታወልቅ ለማከናወን ፈልጋ ነበር ። አሁን ግን ልብሷን በየተራ ሲያወላልቅ እንደታዛቢ አየችው ። ...አልጋ ውስጥ አስገባት ። ከንፈሮቹ እየተለጠጡ ሁለመናዋን አዳረሷቸው ። በምላሱ የጡቷን ጫፍ ሲደባብስ ትንፋሽ እያጠራት ትቃትት ጀመር ። ሳታውቀው ጭኖቿ ራሱ...ራሷን ሳተች ።

የሕሊናዋ ጭንቀትና የሰውነቷ ድክም ተባብረው ረጅም ሰአት ተኛች ። እሱም ሊቀሰቅሳት አልፈለገም ። አውቆ ዝም አላት ። ዛሬን የድሉ ቀን አድርጐ ቆጥሮታል ። 'መቼም ማምሸቷስ ይሁን ፡ አዳሯን

Scanned with CamScanner

እሜን ብሎ የሚተበል ባል ግን አይኖርም› ሲል ለራሱ ገመተ ። እና ካረ ከባሷ ጋር ቁርጥ ቀን ይሆናል ። ሰዓቱን ተመለከተ ። አራት ሰዓት ተኩል! እስካሁን ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዷታል ።

ቆይታ በድንገት ብንን አለች ፡ አይኗን በልጥጣ ዙሪያዋን ታኖች ። ሄኖክ ፈገግ ብሎ ይመለከታታል ። ሁኔታውን ስትገነዘብ ልቧ ስትጥ ብሎ በድንገት መስራት ያቆመ መሰላት ። አምላኳን ተማጥና ሰአቷን ስትመለከት ከአልጋዋ ተስፈንጥራ ተነሳች ። ወንድ ልጅ ፊት ራቁቷን መታየት አትወድም ። አሁን ግን አላሳሰባትም ። እየተጣደፈች ልብሷን መለባበስ ጀመረች ።

“ምን ለመሆን ነው?” አላት ሄኖክ በሁኔታዋ ተደንቆ ።

እወነት በመገረም አስተዋለችውና “ምን ማለትህ ነው? መሄድ አለብኝ” አለች የምታደርገው ተምታትባት ።

“ስድስት ሰዓት መሆኑኮ ነው ።”

“ይሁን ፡ ግዴለም” አለች ። እሷ የታያት ምንም ሰአት ይሁን ቤቷ ማደሯ ነው ። ክንፈ ታያት…

ሄኖክ ሳቀባት ። ቀና ብላ ተመለከተችው ። በሁኔታዋ የሚያፈዝ መሰላት ። “ባሁን ሰዓት ልትሂድ ብትይስ በምን ትሄጃለሽ? ጉድ—ኮ ነው! ስንት ሰአት እንደሆነ ለመሆኑ ታውቂያለሽ” አላት በድጋሚ ሰአቱን እያዩ ።

ሰአቷን ማየት አላሻትም ። እውነት ከአሁን በኋላ በምን ይኬዳል? ግራ ገባት እዛው ቆማ በአይኖቿ ሄኖክን ትማጠነው ጀምር ። “ባክህ ሄኖክ ጐረቤትም ቢሆን መኪና ለምንና እርዳኝ ፡ ታክሲም ያለው ካለ የፈለገውን እከፍላለሁ ።”

ሄኖክ የተጨነቀ መሰለ “እሺ ሰአቱኮ ሄዷል ። አሁን ቢያደርሱሽ ሲመለሱ ሰአት እላፊ ይይዟቸዋል ። በዛ ላይ ደግሞ አንድም የማውቀው ሰው የለም ።”

ምንም አማራጭ አላገኘችም ። በድንገት አንድ ነገር ብልጭ አለባት። “እሺ ስልክ ስጠኝ ሄኒ” አለችው እየተጣደፈች ። ሊያመጣላት ሳሎን ገባ ።

አሁን የታያት ነገር ቤተሰቦቿ ጋር ቶሎ ደውላ አሀቷን ያለዛም እናቷን ተማጥና ክንፈ ደውሎ የጠየቀ እንደሆነ እኛ ጋ ነች እንዲሉ ፡ ያለዛም እነሱ ደውለው እነሱ ጋ ማደሯንና እንዳታስብ ብለው እንዲነግሩ ላት ነበር ።

ስልኩን እንዳመጣላት የቤተሰቦቿን ቁጥሮች አሽከረከረች ። ተይዟል ይላል ። ቶሎ ዘግታ መልሳ ሞከረች ። አሁንም ተይዟል ። ልቧ በድንጋጤ ስንጥቅ አለ ። ልቧ አንዳች ነገር ጠረጠረ ። ያባቷን ስልክ ሞከረች ። እሱም ተይዟል ። ስልኩን ጥላ ወደቀች ።

* * *

ያን ሰአት የክንፈ ትእግስት አልቆ የመጨረሻ ሙከራውን ያደረገበት ጊዜ ነበር ። የሰችምን ሲሰማ ወትሮ የማያውቀው ቅናት ሰውነቱን ወረረው ። የእስካሁን ሁኔታ ሁሉ በድንገት የተከሰተለት መሰለው ። በጣም ሲናደድ እንደሚያደርገው ስልኩን ዘግቶ ለብቻው ይስቅ ጀመር… አሃሃሃሃሃ…ኢ,ሂሂሂሂ…ሳቁ ከህሊናው ለቅሶ ጋር ተቀላቀለበት።

ምእራፍ አሥር

ፊደል ከቃላት ፡ ቃላት ከሐረግ ፡ ሐረግ ከዐረፍተ ነገር ፡ እሱም ደግሞ ከአንቀጽ ፡ አንቀጽ ፡ ከምዕራፍ ፡ ምዕራፍ ደግሞ ከከፍል እያናበረ የሚያንበለብል መጽሐፍ ነው አዜብን የሚማርካት ፡ ስለሚማርካትም እንደሱ ለመባፍ ትሻለች ። ነገር ግን ሃሳቧ ሁሉ በአጭሩ እየቀረ በአንቀጽ እየተወሰነ በአንድ ምዕራፍ ይጠቃለላል ። ዕፁ ሳታበቃ ሃሳቧ ይቋጫል ። እጭር ልቦለድ ደግሞ አትወድም ። ህይወትን አሳንሶ የሚያሳይ ጠባብ መነፅር ይመስላታል ። ግን የምትለው ይጠፉታል ፡ ቢኖርም በትንሽ ቃላት ተብሎ ያልቅባታል ። ትናደዳለች ።

ሩሳንሶት ከእውነታ ጋር አልጣጣም ሲል ህይወት በራሷ ላይ ሲአል መግባትን ትፈርዳለች ። አለም የስሜታችን ነበብራቅ ነች ። ካጨልምን እናጨልማታለን ። ከፈካነንም አብራን ትፈካለች ። አዜብ ዙሪያዋ ከስሜቷ ጋር አብሮ ዳምኗል ።

እኩለ ሌት አልፏል ። እያስገመገመ በመብረቅ ታጅቦ በነጐድጓድ እያጓራ በየጣራው ላይ ሲንገዋቀዣች የቆየው ዝናብ ጋብ ብሏል ። ከአልጋዋ ግርጌ ከቁምሳጥኗ ጐን የተቀመጠው ጠረጴዛ ላይ ያለው

Scanned with CamScanner

የዕሀፈት ጠረጴዛ መብራት ፡ ወደታች ተደፍቶ በጨረሮቹ ወረቀቱን
ያወጋል ። አዜብ ምኞት ባለው የቢሮ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጣ
በሃሳብ ትባክናለች ፡ 'ድርሰት ጣር ነው ። የአእምሮ ፍትጊያ ውልደ
እስቲ ከምንም ተነስቶ ገፀባህሪን በህሊና ዘርቶ ፡ ህይወትና እስትንፋ
ሰጥቶ ፡ በሰዎች ዘንድ ዘለአለማዊ ለማድረግ መፍጨርጨር ፡ የፈጣሪ
ንም ገፀ ባህሪ ማዘዝ እየተሳነ ፈጣሪው እንደፈለገው ላይሆን ፡ ገፀ ባህሪው
እንደፈለገ ሲጓዝ መከታተል ፡ 'ልፋ ያለው ሰው ዶሮ በቆቅ ይሉሙጣል
አሉ ። የራስን ማንነት አጣርቶ ማወቅ እየተሳነ የሌላውን ማንነት ፈጥረ
ለማውጣት መታገል ።'

ደግሞ ለመፃፍ ሞከረች ። አቃታት ።

ቀን ከመዕሀፍ ውስጥ ያነበቧትን ዐረፍተ ነገር ማብሰልሰል
ቀጠለች 'ፍቅር የራስ ወዳድነት ምልክት ነው' ሲገርም ! በፍፁም ፍቅር
በዚህ መንገድ አይታው አታውቅም ። 'እንዳውም ሲባል የሰማችው
'ፍቅር ራስን ለሌላው አሳልፎ የመስጠት ችሎታ ነው' ነበር ። ደግሞም
አምናበታለች ። 'ራሱን ለሌላ አሳልፎ የሚሰጥ ሰው እንዴት ራስ ወዳ
ይባላል ?' ሁለቱ አባባሎች የሚቃረኑ መስለው ታዩዋት ። 'ራስን
መውደድ ሌላ ፡ ራስን አሳልፎ መስጠት ሌላ ። እንዴት ሁለቱ ለአንድ
አይነት ፍቅር መግለጫ ሊሆኑ ቻሉ? አለች ።

ትምህርት ቤት እያለች በሳይኮሎጂ ጥናት ወቅት የተለያዩ መሃሪ
ትን ስታነብ ፡ ያስደነገጣት አንድ ነገር ነበር ። ይኸውም ፡ የሳይኮሎጂ
ጠበብት በተለያዩ ወቅት ባደረጉት ምርምር ፡ ሴትልጅ ከአባቷ ፡ ወንድ
ደግሞ ከናቱ ያለው ከልክ ያለፈ ፍቅር በአብዛኛው የሚንፀባረቀው
በመሃከላቸው በሚፈጠረውና ላያውቁ በሚላበጡበት "ሴክሽዋል" ወይ
ንም ግብረስጋዊ ግፊት ሳቢያ ነው የሚል ነበር ። በዚህ ምክንያት
አብዛኛው በቤተሰብ ፡ በቤተዘመድ መሃከል ያለው ግንኙነት ጤናማነት
በእጅጉ ያጠራጥራት ጀመር ።

ከዛው ከትምህርት ቤት ሳትወጣ ፡ በራሷ መንገድ ምርምሯን
ቀጠለች ። በርግጥ ጠበብቶች አልተሳሳቱም ። የምርምር መስኳን ሰፋ
አደረጉችው ። ከቤተሰብ ወደ ቤተዘመድ ነጐዶች ። ድንቅ ግኝት !
የተወሰኑ ቤተሰቦችን መረጠች ። በቅድሚያ ያደገችበትን ቤተሰብና
ጐረቤቶቿን ፡ አጥጋቢ ውጤት መጣሳት ። ቀጠለች ... በመሃከ

ከቤተሰቦቿ ተመርታ ወጣች ። አውንም ምርምርና ጥናቷን አልገታ
ችም ። በተለይ በቤተሰብ መካከል ቀጥተኛ ቅርርብ ባላቸው የአጐት
ልጆችና የአክስት ልጆች መካከል ያለው ቤተሰባዊ ፍቅር ላይ አተኮረች ።

ልጆች ከቤተሰቦቻቸው የቅርብ ዘመዶች በተለይም በተወሰነ
የዕድሜ ክልል ከሚገኙ ፡ የአክስትና ፡ የአጐት ልጆች ጋር በሚኖራቸው
ቅርበት ላይ ያተኮረው ጥናቷ አመርቂ ነበር ። የምርምር ዕውፉ በመጀመሪ
ያው የልጅነት ዘመናቸው ወቅት ልጆች የሚያዘነብሉት ከእኩዮቻቸውና
በየታም ሳይለዩ ከሁሉም የቤተዘመዶቻቸው ልጆች ጋር ይሆናል ። ቤተ
ከቤትና ከወንድ እኩዮቿ ጋር ፡ ወንዱ ከወንድና ከሴትም ትኩዮቹ ጋር
ቅርርብ ይፈጥራሉ ።

በሁለተኛ ደረጃ የልጅነት ዘመናቸው ወቅት በአብዛኛው በአካባቢ
ያዊ ባሕሪ ተዕዕኖ ሳቢያ ወንዱ ወደወንድ ቤተዘመድ ጓደኛነት ሲያደላ ፡
ሴቷም እንደዛው በያታ አቻዎቿ ጋር ባልንጀራነቷን ታጠብቃለች ።
ድንቁና የሚያስደነግጠው ግን ወንድም ለአካለ መጠን ሲደርስ ሴቷም
ድንገታዊ የአካል ብታት ለውጥ ሲታሳይ ፡ በቤተዘመድ መካከል ያለው
ቤተሰባዊ ፍቅር እንዳለ ሆኖ የሚያደሱት ወደ ተቃራኒው ያታ ይሆናል ።
ጨዋታውም ፡ ልፊያውም ፡ ቀልዱም ፡ ትግሉም ፡ መልኩን ቀይሮ ወደ
ስጋዊ ስሜት (ሴክሽ፟ል ፊሊንግ) ያደላል ። ፍቅራቸውም ጣፋጭና ለስላሳ
ሆኖ ይስታን ያሸምታቸዋል ። ይህንን ወደስጋዊ ስሜት ያደላ ቅርርብ
በያንብ ለማጤን ፡ መልክ ቀኖ-ወይሆኑት የቤተዘመድ አባላት ያለውን
ውጪያዊ ግፊትና በመሃከላቸውም የሚፈጠረውን ውስጣዊ ውጥረት
በማጤን አቅጣጫውን መገመት እያዳሳትም ፡ የሚል ነበር የጥናቷ
ማጠቃለያ ።

ይህ በቤተሰብ መካከል የሚፈጠር ጤናማ ሁኔታ አንዳንዴ ገደቡን
አልፎ ከሚፈጠረው አንጉል ሁኔታ በስተቀር ይህንን ያህል አሳሳቢ
ባይሆንም ሁኔታውን በውል ካላጤኑት ግን አስደንጋጭና አሳሳቢ
የሚሆንበት አጋጣሚ አይጠፋም ። በዚህ የጥናት መስኳ ከአንድ እርከን
ተነስታ ወደሌላ ፡ ከዛም ወደ ሶስተኛ እያለች ለተወሰነ ጊዜ በጥናቷ
ቀትገፋበትም ፡ በአብዛኛው በአእምሮዋ ውስጥ መክነው ከመቀፋታቸው
በቀር አንዳች የሰራችውም ሆነ ለጥናት ያቀረበችው ጽሑፍ አልነበራ
ትም። ሁሉም ከዛ በፊት ተብሎ የተጨረሰ ይመስላታል ። መባል
አለመባላቸውን የምታረጋግጥባቸው የመረጃ መጻህፍት ፡ ጥናቷን የምታ

Scanned with CamScanner

ስደግፍበት ሰፋ ያለ የምርምር መስክ አልተመቻቸላትም ። ምርምር በሶስተኛው አለም እጅግ ይከብዳል ። አላማውንና ጠቀሚታውን በጨለ የሚረዱ ሰዎች እጅግ በጣም እናሳ ናቸው ።

በዩኒቨርሲቲ ትምህርቷ ወቅት ተማሪዎች የመስክ ላይ ጥናት ይሰጣቸው ነበር ። በአካባቢያቸው በሚገኙ ባለትዳሮች ፡ ተማሪዎችና የህብረተሰቡ አባላት ላይ የተለያዩ ጥናቶች እንዲያካሂዱ ይታዘዛሉ ። በአጋጣሚው መምህራቸው ከሰዉቸው ስራ በተጨማሪ በአካባቢያቸው በሚገኘው ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለተመሳሳይ ጥናት ተሰማርተው ስለነበር ፡ እሷ የደረሳት ክፍል ውስጥ ጥበታ ለተማሪዎች ስለጥናታቸው አላማና ውጤት ጠቃሚነት ትንሽ የመግቢያ ንግግር አደረገችላቸው ። በተለይ ወንዶች ከሴት ጓደኞቻቸውና ፍቅረኞቻቸው ሊያገኙት ስለሚፈልጉት ሶስት ዋና ዋና ነገሮች ብቻ በስፋፍ እንዲገልፁ ፡ ለሴቶች ተማሪዎችም በተቃራኒው ተመሳሳይ ጥያቄ አቀረበችላቸው። ሁሉም አስተያየታቸውን በወረቀት ሰፈው ለመስጠት ግማሽ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ፈጀባቸው ። ግማሹ ምን እንደሚሰሩ ገራ ሲጋባ ፡ የተቀረው ጓደኛውን ሲያማክር ፡ በመጨረሻ የሰጪትን ወረቀት ሰብስባ ወጣች ።

አስተያየቶቹን ለማንበብ በጣም ቸኩላ ነበር ። ከ"ጀመሪያ እስከ መጨረሻ እየሳቀች ስትስቅ አነበበቻቸው ። አስተያየቶቻቸው አስቂኞች ነበሩ ፡ ..."ያንቺ አይነት ፍቅረኛ ብትኖረኝ ሌላ አልሻም ...እንዳንቺ ኮስታራ አትሁን እንጂ ግደሊኝም...እባክሽን በዚህ ስልክ ቁጥር ደውይ ልኝ... በመጀመሪያ የምፈልጋትን ሴት ልታመጪልኝ ታል ግቢልኝና!... ዐይ ፍሬንድ አለሽ ወይ? ከሌለሽ..." ከሞላ ጐደል መልሶቹ አስገራሚ ነበሩ ። ጥያቄውን በተመለከተ በትክክል የመለሱ ከስልሳ ወረቀቶች ከአምስት አይበልጡም ነበር ። ያውም ከመሃከላቸው "...እኔ ስለትምህርቱ እንጂ ስለዚህ ጉዳይ አስቤበት አላውቅም" ከሚለው ጭምር ።

በዛው ጥናት ላይ አንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ስላጋጠመው ጉዳይ አጫውቷታል ። በተለይ በሁለተኛ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች አንድ ነገር በጀሮዋቸው ሰምተው ለሌላ ወገን ለማስተላለፍና ያላቸውን ብቃትና ችሎታ ለማጥናት አንድ የሙከራ ጥናት ይደረጋል ። በመጀመሪያ ረድፍ ለተቀመጠው ተማሪ በጀሮው ጠጋ ብሎ የሆነ መልዕክት ያስተላልፍለታል ። መልዕክቱም የሚለው "የሰው ልጅ የመኖር እድሉ እንዴ ነው?"

ሶሪል ነው ። የመጀመሪያው ልጅ ጐኑ ላለው በጀሮው ፡ የጐኑም ለጓለኛው ፡ የጓለኛው ሰጐኑ ፡ እንደገና የጐኑ ለጓለኛው እያለ የመጀመሪያው ረድፍ ጨርሶ ወደሁለተኛው ረድፍ... እንዲህ እንዲህ እያለ አራቱም ረድፍ ያሉትን ሃምሳ አራት ተማሪዎች ካዳረሰ በኋላ ለመጨረሻው ደረሰ ። ያንን እንዲነግረው ነበር ፡ 'ሚጥሚጣ ለቃር መድሐኒት ነው' ፡ ሲለው ሆዱ ተሙምሙ የሉለው አስቆታል ። የመጀመሪያው ልጅ ተነስቶ ምን እንደተነገረው አስኪፈርስ አደረገ ። ተማሪው በሳት አወካ ። ሁሉኔ ክፍሉን ሞሎ እንደወጣ እንዲነገር አደረገ ። ተማሪው በሳት አወካ ። ሁሉኔ ክፍሉን ሞሎ እንደወጣ ገልጸታል ። በርግጥ የምርምሩን ውጤትና አላማ በእጅጉ ባለተነዘበ ሁብረተሰብ መሃል ምርምር አካሂዶ ውጤት ማግኘት እጅግ አዳጋች ተግባር ነው ። ከመስክ የህብረተሰብ ጥናት ይልቅ ፡ የቤተሙከራ ጥናት የቀሻለ ውጤት ያስገኛል ።

ያሁሉ የልምድ ጊዜ አለፈ ። ተግባር ከእውነት ጋር ስትፋለስ ልፋት ውሉ ከንቱ ይሆናል ። የህይወት የጉዞ እቅጣጫ ደግሞ በባለቤቷ እይንደፍም ። ከአካባቢዋ ሌላ ተፈጥሮዋም አቅጣጫዋን ይቀርፃል ። ያው ብእር ጨብጣ ወረቀቱን ለመንደፍ ትዋትታለች ። በመሃሉ ስሜቷን የሚኮረኩረው የስነልቦና ሕይወት ተዳፍኖ ፡ ከርሞ እንደሚፈነዳ አስተምሯ ከች ሲል ፡ ብዕር ከወረቀት ፡ ሃሳብ ከአእምሮ ሙግቱን ይቀጥላል ።

"ድንቅ ግኝት !" አለች ፡ ላይታወቃት ሬክ ብላ ። "የፍቅርን ባሕሪይ አጉልታ ያወጣች ጥልቅ ንግግር" ምስጢሩ ሲከሰትላት ፍቅር የራስ ወዳድነት ምልክትነቱ ሲታወቅ ፡ አሰጨንቋት የነበረው አባባል ሲፈታላት ፡ ሃሴት በሰውነቷ ተሰራጨ ።

"ልክ ነው" አለች ለራሷ ። "ፍቅር የራስ ወዳድነታችን ምልክት ነው ። በርግጥም ነው ። ለምንድነው የምንወደውን ስናጣ የምንበሳጨው ? ለምንድነው ያፈቀርነውን ሰው በኛ ሆነ በሌላ ምክንያት ሳናገኘው ስንቀር ራሳችንን እስክንጠላ ድረስ ጉዳቱ ጠልቆ የሚሰማን ?

"ምንጊዜም የምንወደውን ሰው የኛ የማድረግ ከፍተኛ ፍላጐት አለን። ይህ የሚያሻማ የፍቅር ፍላጐት ነው ። ማነው ለሌላው ሲል ፍቅረኛውን አሳልፎ የሚሰጥ ? ማነውስ ፍቅሩን በወኪል የሚያካሂድ ? ፍቅር ሲበዛ ግለኛ ነው ። ግለኝነቱ ደግሞ ከራስ ወዳድነታችን የሚመነጭ

Scanned with CamScanner

ነው። ራስ ወዳድነታችን ደግሞ ከሰውነት ባሕሪያችን ጋር የተያያዘ ነው ።"

አዜብ ፈገግ አለች ። ግን በድንገት ፊቷ ዳመነ ። ዝናቡ እንደገና እያገረሸበት ነው ። ብርድ ብርድ አላት ። ተነስታ ጋቢዋን ደረበች ። ተመልሳ ተቀመጠች ። ደግሞ ተነሳች ። ያየችውን ሁኔታ ለክንፈ ዶሮ ለመንገር አመነታች ። በአንድ በኩል ሀሊናዋ መንገር እንደሌለባት ይነግራታል ። ይህንን ስታስብ ደግሞ ውጥረቷ ይበዛና ሰውነቷ በጭንቀት ይወጠራል ። "እወደዋለሁ" አለች ለራሷ ፣ ጥቃቱ ፣ በደሉ ሁሉ እሷ ላይ የሆነ ያክል ተሰምቷታል ። ከማንም በላይ "እወደዋለሁ !" አለችና ራሷን ታዘበች ። ውስጧን መመርመር ያዘች ። እስካሁን ቆይታ ፣ በአንድ ጊዜ ሃሳቧ እንዴት እንደተመሰቃቀለባት ግራ ገባት ። ስታስታምመው የኖረችው የፍቅር ሕመም እንደሆነ ታውቃለች ። እነርሱን የማየታ ሳይሆን በውስጧ ባለው ፍቅር ተገፋፍታ የመደወሉን አጋጣሚ የተጠቀመችበት መስሏት እራሷን ጠላችው ። ባሕሪዋን ኮነነች ። እውነትም ፍቅር ውስጣዊ ማንነቱ ራስን አጥብቆ መውደድ ነው ።

እየተቅነዘነዘ ያንሰራራውን ሃሳቧን ልጓም ልታበጅለት አልቻለችም ። ሰአቷን ተመለከተች ። ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሆኗል ። አመነታች። መልሳ ወሰነች ። የመኝታ ቤቷን በር ከፍታ ወደ ሳሎን ሄደች። ስልኩ በቦታው የለም ። ለአንድ አፍታ ግራ ተጋብታ ቆመች ። ትንሽ አሰበችና ወደ ሄኖክ መኝታ ክፍል ሄደች ። "ይህች ከሃዲ" አለች በሆዷ ፣ "ባሏን ባዶ ቤት ጥላ እሷ .." አልጨረሰችውም ፣ የሷስ ልብ በደረቅ ሌሊት ወደ ሰው ባል ኮብልሎ የለ !

ቀስ አድርጋ በሩን አንኳኳችው ። ከውስጥ በእንቅልፍ የታጀበ ጐርናና ድምፅ "ማነው?" አላት ። "ሕሊና ቢስ ወራዳ" ልትለው አሰበችና ተወችው ።

"ስልኩን ፈልጌው ነው" ስትለው ፣ እየተንጫነጨ ተነስቶ በሩን ከፍቶ ሰጥቷት ተመለሰ ።

"ምንሆና ነው ?" አለችው እፀገነት አልጋው ውስጥ ሲገባ ጠብቃ ።

"እንጃላት ! አንድ ቀን ማበዴ አይቀርም ። በፍፁም አትተኛም" አላት ወደራሱ አስጠግቶ እያቀፋት ።

እፀገነት ስትፈራ ስትቸር ቆየችና "ማታ እኔን ስታይ ፊቷ ደን ያክል የተለዋወጠው ምን ነክቷት ነው?" አለች ሲከነክናት የቆየውን ጉዳይ አፋረጥረጣ ።

"አንቺ ደግሞ ! የሷን አመል አጥተሽው ነው?" አላትና እንድ እግሩን ጭኖቿ መሃል ሸጐጣቸው ። ጭኖቿ የተቃጠለ ትንፋሽ ያህል ይሞቃሉ ።

እፀገነት አልመሰላትም ። ሁለቱ ሲጨቃጨቁ ነው አልጋ ላይ ሆና ከሰመመኗ የነቃችው ። ስልኩ ተይዟል ሲላት አዙሪት እንደወደቀችና አልጋ ላይ ካወጣት በኋላ ስትነቃ ፡ አዜብና ሄኖክ አይጥና ድመት ሆነው ነበር ። ልክ መንቃቷን ስታይ ከዚህ በፊት አድርጋው በማታውቀው አስተያየት ተመለከተቻትና በሩን በኃይል ዘግታ ጥላቸው ወጣች ። ሴላ ነገር በፍፁም አልጠረጠረችም "ድሮም አትወደኝም" ነበር ግምቷ ።

አዜብ ስልኩን ይዛ በሳሎን አድርጋ መኝታ ቤቷ ስትገባ ፡ የስልኩ ረጅም ገመድ በበሩ ተይዞ ከእጇ አፈትልኮ ነበር ። ያንን ቀስ አድርጋ አስለቅቃ ወደ አልጋዋ ሄደች ። በጣም ዝግ እያለችና እያመናታች ቁጥሮቹን አዞረቻቸው ።

ጐርናና ድምጽ ተቀበላት ፦

"እንደምን አለህ ክንፈ ? አዜብ ነኝ ።"

"አዜብ ምነው ደህና ?" መደንገጡ ያስታውቃል ።

አዜብ አመነታች ። ስልኩን ልትዘጋው ፈለገች "ደህና ነኝ ክንፈ ። ደህና ነኝ" ክንፈ ግራ ገባው ። ዕፀገነት ምን ሆና ይሆን ? ሲል አሰበ ። ሰውነቱ ፍርሃት ፍርሃት አለው ።

"እባክሽን አዜብ ምን እንደሆንሽ ንገሪኝ።"

አሳዘናት ። አንጀቷን በላው ። እንባዋ እየቀደመ አስቸገራት ፡ "አላውቅም ክንፈ! አላውቅም ። ብቸኝነትህን አውቃለሁ ። ብቻህን ማደርህን አውቃለሁ ። ያለሣ አልደውልም ነበር ። ይገባሃል ክንፈ ? ደደብ ነኝ! ..." አለችውና በሁኔታዋ ግራ ተጋባች ። ፍፁም ጤነኛ መሆኗን ተጠራጠረች ። ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋችው ።

ወዲያው ስልኳ ጮኸ ። ከሰመመኗ በርግጋ አነሳችው ፡ ክንፈ ነው።

"እባክሽ አዜብ ምን የምታውቂው ነገር አለ ? እፀገነት ደህና አይደለችም ?"

ሳቀች ። በጣም ሳቀች ...

Scanned with CamScanner

"ምን ያስቅሻል አዜብ ?"

"በጣም ስለማፈቅርህና በጣም ስለማዝንልህ ።"

"ለምን አዜብ ? እፀጎኔት ደህና አይደለችም ?"

"እትጠራጠር ፍፁም ደህና ነች ።"

ክንፈ ረጋ አለ ። አምኗታል ፡ "ለምን ይህንን አጋጣሚ መረጥሽ አዜብ ?" አላት ድምፁን ዝቅ አድርጉ ።

ጥያቄውን አልወደደችውም "አላውቅም ክንፈ"

"ሕይወት ነች ወይንስ እኛ ነን የምንቀልደው አዜብ ?"

"እንጃ ! ሁላችንም እንሆናለን" ዕንባዋ አፁንም አስቸገራት ።

"ለምን ታለቅሺያለሽ አዜብ ?"

"ለምን ይመስልሃል ?"

ሁለቱም ለአንድ አፍታ ዝም ተባባሉ ። የልቦናዎቻቸውን ያውቁ ታል ። የቸገራቸው ግን ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ነው ።

"አዜብ ፡ አንቺ'ኮ የልቤ ውስጥ እሳት ነሽ ። በመከራ ያዳፈንኩሽ ። " ሲላት የባሰ ትንሰቀሰቅ ጀመር ። ስልኩን አስቀምጣ ስታለቅስ ይሰማዋል። ስልኩን መልሳ አንስታ "ክንፈ.... ሕይወት ምንድነች ?" አለችው ።

"ትራጀዲም ፡ ኮመዲም ፡ ሁሉንም ነች ።"

"ለኔ ግን እንጃ ! አይደለችም ።"

"ለምን ?"

"ምንም አይደለችማ ክንፈ ፡ ለኔ ምንም አይደለችም ። ባዶ ነገር አታውቅም ? ባዶ በቃ ! ምንም ትርጉም አትሰጠኝም ። ለብቸኛ ነፍሴ የሕይወት ትርጉም የላትም ።"

"እኔ ግን ፡ አብሮኝ የቆየው ብቸኝነቱ ሲገፈፍ ይሰማኛል ። ላንቺስ?"

"ከመቼ ጀምሮ ።"

"ከደወልሽልኝ ሰአት ጀምሮ"

"እውነትክን ነው ?"

"እንደዛሬም እርግጠኛ ሆኜ አላውቅም ።"

"ታድዬ ክንፈ !" አለች ።

"ታድለን !" አለና አረማት ...

ሀይወት ድንቅ ሆናባቸው ተአምራቷን አስቆጠረቻቸው ።

ምእራፍ አሥራ አንድ

ክፉራ በግ ተራ አካባቢ የተነሳችው ቮልስ ዋገን በገነት ሆቴል አድርጋ ሽቅብ በቸርችል ጎዳና ከገሰገሰች በኋላ ፡ ቴዎድሮስ አደባባይ ሰይጣን ቤት ን ስትደርስ ወደ ውስጥ ገባ ብላ ቆመች ።

ትዳሜ ከሰአት በኋላ አስር ሰአት ገደማ ያባራው ዝናብ ጨርሶ ለማቆሙ እርግጠኛ አይደለም ። ቢሆንም ፡ ቀጠሯቸውን የሚያፈርስ አንዳችም ኃይል ያለ አይመስልም ። በተነፋፈቁበት ሰአት ተገናኙ ። ለወትሮው ለአለባበሷ እጅግም የማትጨነቀው አዜብ ፡ ዛሬ ልብስ ለመምረጥ ያክል ብቻ ከግማሽ ሰአት በላይ ወስዶባታል ። ክንፈ አልተናነሳትም ። እንደ ሕፃን ልጅ ጉንጭ እንዲለሰልስ በጥንቃቄ ተላጭቶ የተቀባው ሽቶ ለብዙ ሰአታት ይቆያል ። የት እንደሚወስዳት አለማከራትም ። መኪናውን ሽቅብ በቸርችል ጎዳና አስጋለባት ። በሲኒግ ኢትዮጵያ አድርገው መሐል ፒያሳን እየሸነሸኑት ከሄዱ በኋላ አራት ኪሎ ብት ሲሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ተነጋገሩ ።

"መስመራችን ወዴት ነው?" አለችው ቀስ አድርጋ እየተመለከተ ችው ። እንደልዩ ጣዕመ ሙዚቃ የሚያጣጥመውን ድምጿን ሰምቶ ዞር አለና "ፀጥታው እንደገነት የተጠበቀ ፡ ሰላሙ በመላዕክት የታጀበ ፡ ሀብረ-ዜማው በእእዋፋት ወደተታኘ ስፍራ" ብሏት ፊቱን ወደ መንገዱ መለሰ ።

ቮልስዋገኗ በድሮው ወመከማ አድርጋ ፡ በሽ ሰማንያ በኩል ታጥፋ ወደ ቀበና ገሰገሰች ። ቀበና ላይ የተቀበላት ዳገት እያስጓራ ሾላ ሊያደርሳት፡ የገበያው ትርምስ ፡ የበጎች ድንብርታ ፍጥነቷን አስቀንሶ በላም በረት ወደ ኮረብታ ሆቴል አሻገራት ። ቀጭኑ አስፋልት ግራ ቀኝ ተንቀዋለው በተንገፐረገጉት ዕዶች መሐል አሳልፏቸው ሽቅብ ዳገቱ ከወጡ በኋላ ፡ ቡናቤቱን በስተቀኝ ትተው በስተግራ በሚገኘው ሰገነት ፕልት አሉ ።

ክንፈ እንዳለው በመላእክቶች የተከበረው ሰላም ፡ የአእዋፍ ሀብረዜማ ያስዋበው ሲመስል ፡ ከቡና ቤቷ በትላልቅ የድምፅ ማጉያ እያለሳለሰ የሚሰማው በሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበረ ዜማ ደግሞ ፡ ከተፈጥሮ

Scanned with CamScanner

ጋር ወግ የያዘ ይመስላል ጆሮን አይቆረቁርም ። አሳት የላቡ የዘቲሉ አስተናጋጆች መስተንግዶው አልጠፋቸውም ። በተለይ ሁለት ሆነው የሚመጡባቸውን እንግዶች ፍላጎት ማጤን አይቸግራቸውም ፤ ፈጣኖች ናቸው ።

"ሀይወቴ ውድንቅው ወጥቶ ፡ የማደርገው ባጣሁበት ሰአት እንዲህ ዓይነት እዑብ ድንቅ ሰዓት ይፈጠራል ብዬ አልጠረጠርኩም ነበር" አሳት ክንፈ ቦዩ ያሳያቸው ክፍል ገብተው ኮቱን አውልቆ ወንበሩ ላይ እያስተካከለ ።

"እኔም ያለፈን ጥሩ ጊዜ ወደ ኋላ በትዝታ መነጽር ማየት እንጂ ዳግም ይመለሳል ብዬ በተስፋ መነፅር ተመልክቼው አላውቅም ። አደገርምም፣ "አለችው በፊቷ ላይ የሚንፀባረቀው ደስታ ጥርሷ አልበቃ ብሎት የአይኖቿ ዙሪያ እየተሸበሸቡ ፡ በልዩ ስበት ተስበው በደስታ የሚዳከሩ ይመስላሉ ።

አዜብ ከክንፈ ጋር ስትሆን ሰላም ይሰማታል ። ውስጧን ፡ ማንነቷን የሚረዳ ፡ ስብእናዋን ያጤነ ፡ ሰውነቷን የተቀበለ መስሎ ይታያታል ። አብራው ስትሆን ፡ ያለባም ስልክ ሲደውልላት የመንፈስ ቅለት ይሰጣታል ። ሁሉን ነገር ፡ ምንም ሳትደብቅ ልትነግረው ፡ ልታጫውተው ፡ ልታማክረው ፡ የምትችለው ሰው ቢኖር ክንፈ ነው ። እሱም ይሀና ይረዳታል ፡ ይቀበላታል ። ከማንም የተሻለ ሰብዕናዋን አክብሮ ፡ እንዳውም ካጋጠሙት ማናቸውም አይነት ሴቶች መሐል የሷን ያክል ክብደት ያገኙ አልነበሩም ። የደስታው ምንጭ በሷ ደስታ ላይ የተመሰረተ ቢሆን ይወዳል ። ምንም ያደርግ ምን ፍላጎቱን ከሷ ፍላጎትና ምርጫ በኋላ ያስከትላል ። ምንም ይሁን ምን ምርጫዋን ይቀበላል ። መቀበል ብቻ አይደለም ፡ ያከብረዋልም ። ከዚህ ቀደም መለያየት መምረጧን በነገረችው ጊዜ ባይቀበለውና ባይዋጥለትም ፡ ለሷ ሲል በፍቅሯ ወላፈን የሚቃጠለውን ልቡን አዳፍኖት ቀርቷል ። ባሻት ሰአት ደግሞ ተዳፍኖ የኖረውን ፍቅሯን ቆሰቆሰችበት ። አላመናትም ፡ አይኑን ጨፍኖ ገባበት ።

"ክንፈ!" አለችው አጠገቧ መጥቶ እንደተቀመጠ ።

"አቤት የኔ እመቤት!"

"ለማግባት ለምን ቸኮልክ?"

ይህንን ጥያቄ ለምን እንዳነሳች ገርሞት አስተውሎ ተመለከታትና "ቸኮልኩ ብለሽ ነው?" አላት እዝን ብሎ ።

የምትሰጠው መልስ አጣች ። ይቸኩል አይቸኩል እርግጠኛ አልነበረችም ። ለሷ ማን መሰላት ። በአጭር ጊዜ ክንፈን የምታጣው አልመሰላትም ነበር ። "መለያየት አለብን" ስትለው ፡ ለመለየቷ እርግጠኛ አልነበረችም ። ጊዜ ጅረት ነው ፡ ሳይታወቅ ሳይሰማ ሽርሽሮ ለያያቸው ፡ በመልክ እንኳን በሚራሽ የማይገናኙበት ደረጃ ድረስ ...

"ቸኮልኩ እንኳን አይመስለኝም" አሳትና አገጯን በእጁ ቀና አድርጎ እየተመለከታት "እንቺስ? ለመለያየታችን ምክንያት የሆነሽ ምን ነበር? " አሳት አስተውሎ እያያት ።

ማስብም ማስታወስም የማትፈልገው ጥያቄ ፡ ምንም ልታደርገው የማትችልው ስህተት እንደሆነ ተቀብላዋለች ። የህይወቷን አቅጣጫ የለወጠ ትልቅ ስህተት! ጭንቅላቷን ወደጎን አወናጨፈችና "አንዳንዴ ምክንያት ሳይኖርህ የምትፈጽማቸው የጎሉ ስህተቶች የሉህም? በቃ እንደዛ ነው ፡ ገባህ?" አለች ዓይኖቿ በዕንባ እየተሞሉ ። መልእክቷ በትክክል ከልቡ ገባ ። ማለት የፈለገችው ማንነቷን ፡ ውስጧን ፡ ስለሚረዳ በቶሎ ተገነዘባት ። አሳዘነችው ። አገጯን ቀና አደረገና ከንፈሮቿን ሳማቸው ።

የምትናፍቀው አጋጣሚ ነበር ። እጆቿን በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥማ በሰቀቀን በእልህ ——ከዳግም ከስሯ እንዳይወጣ የመተናነቅ ያህል በክንፈሯ ባለ በሉለ ሀይሏ ተረባረበችበት ።

ክንፈሯን ከክንፈሩ ስታላቅቅ ደክሟት ነበር ። ለአፍታ ተያዩ ። ድንቅ ውበት ፡ የጠራ ፍቅር በመሃከላቸው ፍንትው ሲል ታወቃቸው ፡ ጊዜ አልፈጁም ።

እንደመንፈሷና ሀሊናዋ ግልፅነት አካሏን ልትሰስትበት አትሻም ። ልብሶቿን በየተራ አወላልቃ ወንበሩ ላይ በስርዓት አስቀመጠቻቸው ። እርቃኗን ሆነች ።

ያን ክቡር ገላ በስሜት ሲቃ ተጋርዶ እንደ እንስሳ ሊዳፈረው አልሞከረም ። ትእግስቱን ደማምሮ ስሜቱን እፍኖ በጥንቃቄ ተመለከታት ። በመጨረሻ ያለ የሉለ ሀይሉን ስብስቦ "ይህቺ ቀኗ በህይወቴ ካጋጠሙኝ ወርቃማ ቀናት የመጀመሪያውን ስፍራ ይዛለች" አላት ፡ ሰውነቷን እየናፈቀ ።

ልትናገር ፈለገች ። አንደበቷ ተሳሰረባት ። አይኗን ጨፈነችና እንደ ቄልፊት ተወርውራ እንደ አልቅት ተጣበቀችበት ።

Scanned with CamScanner

ድንቅ አለም! …የፍቅር ግርሻ! ጨረቃ ድምቀቷ ከሩቅ ይጣራል፣ ፀሐይም አብራ ወጥታለች ። የሌቱ ጨለማ በግርማ ሞገስ ሲያስፈራ፣ የቀኑ ብርሃን በብርሀኑ ይኩራራል ፡ ሙሴ የጨበጣት በትር እባብ ሆነች … የባቢሎን ግንብ ፈረሰ… የግብጽ ፈርኦን ከተሞችን በጢፌዝ አስዋበ… በቤተልሄም አንድ ህፃን ተወለደ… በአረብ ምድር አንድ ታላቅ ነብይ ተነሳ… ጊዜም አለ ። ሁሉም እንዳልነበረ ተረሳ… ቃል ኪዳን ተወሳ… ቃል ነበር ፡ ሁሉም ነገር ሳይፈጠር… ድንቅ አለም!… ተአምራት የሞላት አለም! አደመቋት…

በስሜት ማእበል ተናውጦ በፍቅር እሳት ሲቃጠል የቆየው ሰውነታቸው ቀስ በቀስ እየሰከነ እየተረጋጋ ወደ ቀድሞ ስፍራው መመለስ ጀመረ። የወሲብ ድሎቷን ጎልቶ የሚሰማውና ክብር የሚያገኘው በመሃከሉ ፍቅር ሲኖር ነው ። ፍቅር ያልተንዳንው መሲብ ርካሽና ተራ ይሆናል። መገኛውም እንደዛው ።

በቀስታ የሚደባብሳቸው ጡቶቿ ከቀድሞ ግዝፈታቸው ቢጨምርም፣ ልስላሴያቸው ልዩ ነው ። በጡቶቿ መሃል ወደ እንብርቷ የሚወስደው የሆዷ እካባቢ ዳብሱኝ የሚል ምትሀታዊ ሀይል አለው ። ተፈጥሮ አፍቅሮ ለቃኛት ቃኝቶም ላጣጣማት ለሴት የሰጠው የውበት ምስጢራዊ ገፃ መጨረሻ የለውም ። የሴትም ልጅ ውበት ከተፈጥሮ ጋር ይላከራል ፡ ተምሳሌዋ አበቦች ናቸው ። አበቦች ለተንከባካቢው ውቦች እንደመሆናቸው አክብሮ ለያዛቸው ፀዳላቸውን ያለስስት ያካፍላሉ ። ሴትም ልጅ እንደዛው የአባባን መዓዛ ካጣጣመ ሰው በበለጠ ስሜትን ታጥባለች ፡ መንፈስን ፀአዳ ታላብሳለች ፡ ሴቶች ፡ በፍቅር ላጨናቸው ተዓምራዊና ድንቅ ፍጥረቶች ናቸው ።

አዜብ በፍቅር ደመና ተንሳፋ ፡ በስሜት ማዕበል እየተናወጠች ከምንም ከማንም ስትልቅ ፉሰማታል ። ክንፈ ምኞቷ እንጂ እውኗ አልነበረም ፡ እውን ሆነ ። ከወዲሁ የከበዳት ከፊት ለፊቷ ያለው ሰፊ አለምና ጊዜ ነው ። አሁንን እየሮነች አሳቧ ማዶ ተሻግሯል ። ክንፈ ከእንግዲህም አብሯት እንደሚኖር እርግጠኛ አይደለችም ። እንዳውም አይመስላትም ። ርሀራሄው ፡ ለሷ ያለው ታላቅ አክብሮት ፡ ሰብዕናዋን የመረዳት ተሰጥዕው ፡ እሷንቷን የመቀበል የግንዛቤው ልቀት ፡ የእጆቹ መዳፍ በሰውነቷ ላይ ሲያርፍ አንዳች ነገር የማስረዳት ታላቅ ሀይል አላቸው ። ቀሪው እድሜዋ ከሱው ጋር ቢቀጥል… ። የሰማይ ከዋክብት

እንደርሷት ተሰበጣጥረው ሲፈነጣጠቁ… ከሰማይ አንዳች ሞገድ ቢያስገመግም ፡ ሐምራዊ ቀለም ያለው ዳመና እንደጥጥ እየተባዘተ ዙሪያቸውን ሲያጥር ፡… ከተለምዶው የላቀ በብዙ እጅግ በርካታ የቀለበት ስብጥር የተዋበ ቀስተደመና ተወርውሮ የሁለቱን ልብ እኩል ሁለት ቦታ ሰንጥቆት ሲጓዝ… እልፍ አዕላፍ አዕዋፋት በዜማቸው ሲንጫጩ… እጆቹ መላ አካላቷን አዳርሰው ወደ ከንፈሮቿ መጡ ። ከንፈ ቀስ እድርጎ እያሰላሰሰ የከንፈሯን ዙሪያ በጣቶቹ እየደባበሰ ፡ ከአፍ የሚወጣ ሞቅ ያለ ትንፋሿ በጣቶቹ ሰርጎ መላው ስሜቱን እያሞቀው ከንፈሩን አስጠጋላት ። የፍቅር ማገዶዎች ተዳምረው ተለኮሱ…

ከአፍታ በኋላ ሰአቶቻቸውን ሲመለከቱ ጊዜው ነጉዷል ፡ ቅር አልተሰኙም ። ጊዜው አጭር ቢመስላቸውም ፡ በሚገባ እንደተጠቀሙበት ለሁለቱ ተሰምቷቸዋል ።

ወደ ቡና ቤቷ ጎራ ብለው ቀዝቃዛ ቢራቸውን ከተጎነጩ በኋላ ፡ ከንፈ ቅዝዝ ብላ ወደ ተቀመጠችው አዜብ እየተመለከተ "ምነው ያዘንሽ ትመስያለሽ?" አላት

ቀና ብላ ተመለከተችው ። ለአፍታ አይኖቻቸው ተጋጩ ።

"ሕይወት በሁለት ፍቅረኞች ስትጠመድ ምን እንደምትመስል ለማስተዋል እየሞከርኩ ነው" አለችው ረጋ ብላ ።

ምን ለማለት እንደፈለገች ወዲያው ተገንዘበ "መፅሀፍሽ እንዴት ሆነልሽ?"

"እስካሁን እየታገልኩ ነበር ። ከአሁን በኋላ ያለው ነው ግራ የገባኝ።"

"እንዴት?"

"እኔም ማወቅ የምፈልገው እሱን ነው" አለችው ፈገግ ብላ እሱም ፈገግታዋ ተጋብቶበት "ካስፈለገ ለእርዳታው አለሁ" ሲላት

"…ታድዬ! ሃሳብህ ብቻ ይበቃል" ብላው ለመሄድ ተነሳች ።

* * *

ክንፈ አዜብን ቤቷ ካደረሳት በኋላ እግረ መንገዱን ቦሰና ቤት ጎራ አለ። የቦሴ ቤት የደሞገ ሰሞን በመሆኑ ደመቅመቅ ብሎ ቆይቷል ። ገና በመግባቱ አይኖቹ ያማተሩት ሽፈራውን ፍለጋ ነው ። ሊያገኘው አልቻለም ። ወ/ሮ ቦሰና ባንኮኒ ቀረበ ። ወ/ሮ ቦሰና ድንገት ዞር ሲሉ ተመለከተውት "ልጅ ክንፈ!" አሉት ገፃቸውን ፈገግታ እያጥለቀለቀው።

Scanned with CamScanner

በስጋ ተወጥሮ ሊፈነዳ የደረሰውን እጃቸውን ጨበጠና "ደህና ነሽ?" አላቸው ባንኮኒያቸውን የከበቡ ጠጪዎችን መጋፋት ጠልቶ ወደ ጎን እየተንሸራተተ ።

"ደህና ነኝ..." አሉና "ያ ወዳጅህ ዛሬስ ጠፍቷል" አሉት ደንበኞቻቸውን በአይናቸው እየቃኙ ።

ክንፈ መውጣት አሰኘው ። ይሉኝታ ደግሞ እግሩን ቀፍድዶ አሰቀረው። "እስቲ ቢራ ስጭኝ?" አላቸው ። ከባንኮኒ ጎን ወዳለው መጠጥ ሠሮ አሻሻጫን እያየ ፡ የቀዘቀዘ ቢራ ከፍሪጅ አውጥታ ከፈተችለት ። በብርጭቆ ለተቀዳ ቢራ ግድ የለውም ። ከነጠርሙሱ ማንደቅደቅ ይመርጣል ።

የቦሰና ቤት የጥንት ደንበኞች ደጅኔና ሙሉጌታ አሉ ። እንደልማዳቸው፡ ደጅኔ ያወራል ፡ ሙሉጌታ ያዳምጣል ። ከበሩ ኋላ ያደፈጠው ስዩም ወጥ ብሎ ይጨልጣል ። ከክንፈ ጋር ከአይን ትውውቅ የላቀ አግባባ የላቸውም ። ተቀምጦ ሲያየው ከድሮው ይልቅ ጀርባው የጎበጠ መሰለው። ሰውነቱም አልቋል ። ክንፈ የሚያውቀውንም የማያውቀውንም አጢነና ቢራ እንዲደገምለት ባንኮኒው ላይ ገጭ አደረገው ። ጥቂት ደንበኞች ወደሱ ዞር አሉ ። ክንፈ ባጋጣሚ አይን ለአይን የተጋጨው ከደጅኔ ጋር ነው ። እንደወትሮ ልማዱ እጅ እየነሳ ሰላምታ ሰጠው ።

የመጠጥ ቤቷ ሁካታ ደርቷል ። ወ/ሮ ቦሰና ባንኮኒያቸው ላይ እንደተቀመጡ ያ ቀይ ፊታቸው እየወዛ እየወረዛ የጋለ ብረት እየመሰለ ሄዷል ።

አንድ የቡና ቤቷ ደንበኛ ወደ ክንፈ ጠጋ አለና ብዙ ጊዜ እንደሚያውቀው ሰው ያወራለት ጀመር – በስካር መንፈስ ። ብሶቱን ፡ ችግሩን ፡ ሁሉንም ። መጠጡ ለግልፅነት እያደፋፈረውና እሱነቱን አጋልጦ እየሰጠው ።

"ብጠጣ ባልጠጣ እሷን ምን ዶላት?" አለ "...አየህ በየቤታችን ያሉት ሴቶች ችግራችንን አይገነዘቡልንም ። ለማወቅ እንኳን ጥረት አያደርጉም። የባልን ትርጉም ፡ የሚስትን ምንነት ያጡታል ። ቢበዛ ትፋታችንን እየጠረጉ በነገር እሳት እንደ ማንድ እያገላበጡ ሲጠብሱት ያድራሉ ። አይገርምም? ኩርፍያው ደግሞ በነሱ ይብሳል ።" የመለኪያውን ጀን ጎንጨት አደረገና "አየህ!በሁሉም ሆድ ብዙ ነገር አለ ። ይንን ታዲያ ከሚስት የቀረበ ማን እንዲያውቅልህ ትፈልጋለህ? ሺት! እነሱ ይህንን

አያውቁም ። ደደቦች ናቸው ። በማይረባ ነገር እርስ በርሳቸው ፡ እንዳቸው ከጎዳቸው እየተፎካከሩ ፡ ያም ሲያቅታቸው እልህ መወጫ ያደርጉሃል ። ከድሎትና ከምኞት ወዲያ የህይወትን ትርጉም ከአፍንጫቸው እርቀው አያስቡም ። ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደጎረቤቱ አይኖርም "አለና አይናቸን አጉረጠረጣቸው ።

"አየህ! ሴቶቻችን ቤታቸውን እንዲናፈቅ አያደርጉም ። ትልቁ ችግራቸው ይህ ነው ። እስቲ ማነው የሚናፈቅና የሚወደድ ቤት እያለው በየመጠጥ ቤቱ ጉልበቱን ሲያቃጥል የሚውል? እስቲ ንገረኝ? በጊዜ ቤትህ ብትገባ የሚቆይህ ሰላም ከሌለ ፡ ሚስትህ እና ልጆችህ ፡ ስርዐት አጥተው ቤቱ ሰላም ሲነሳህ ፡ ይታይህ! እንግዲህ ደክሞህ ነው የመጣ ሽ፡ እንደገና የባጡን የቆጡን እየለፈለፈች ቆሽትህን ስታደብን አንተን ከጎረቤትህ ፡ ከጎረቤትህ እያፎካከረች በነገር ምላስ ስትጠብስህ ፡ ያኔ ምን ታደርጋለህ? ቤትህ አያስጠላህም? ውጣ ፡ ውጣ ፡ ብረር ፡ ብረር ለያለኝህም? ሙት ነው የምልህ ፡ የዚያን ጊዜ ቤቱ ሲኦል ይሆንብኛል ። ሚስቱ ፡ ባለቤቱ፡ የጓዳዬ ፡ የቤቱ እመቤት እያንቋሸሸች ከሰደበችኝ ፡ ከብጀቱ ፡ ከጥንካሬዬ ይልቅ ድክመቱን እየፈለገች በነገር ዱላ ከነረተችኝ ከሷ የቀረበ ማን አይዞህ ሊለኝ ነው? የኔ ያልኳት ከናቀችኝና ከዋረደችኝ ማን ሊያከብረኝ ነው ” አለው ።

ክንፈ የሚለውን ሁሉ ያዳምጠዋል ። ሞቅ ቢለውም ሟራሽ አልለከረም ። ብቻ ትንሽ ስለጠጣ ብሶቱን ማውጣት ፈልጓል ። ብሶት የሚነግረው ሰው ፈለገ ። ክንፈን አገኘ ። ከዚህ በፊት አያውቀውም ፡ አይተዋወቁም ። ግን መሰለው ፡ አወራለት ።

በየመጠጥ ቤቱ እንዲህ አይነቱ ዓይኖነት የተለመደ ነው ። ከሰዎችም ጋር መግባባት ተራራ የሚሆንበት ሰው በእንደዚህ ዓይነት ቦታ በእንደ ጊዜ በቀላሉ ብዙ ወዳጆች ሊያፈራ ይችላል ። የግንኙነታቸው ወሰን ግን በአብዛኛው ከደጃፉ አያልፍም ። ለክንፈ ሲያወራለት የነበረው ሰው ለአፍታ ዝም ካለ በኋላ ክንፈን እየተመለከተው ።

"መቼም አግብተዋል ብዬ እገምታለሁ" አለው ።

"አዎ" ሲል መለሰለት

"ልጆች አሏችሁ?"

ክንፈ ለምን እንደሚጠይቀው ግር እያለው "የለንም" አለ ።

Scanned with CamScanner

ሰውየው ይህና አድርጉ ተመለከተውና "ምን ዋጋ አለው ብለህ ነው! ቶሎ መውለድም በጠዋት ቆሽት ማድበን ነው ። በዛሬ ጊዜኮ ላልወለዱት ሳይሆን ፣ ለወለዱት ነው የሚታዘዝን..." አለውና "... እውቃችሁ ነው ወይንስ?..." ብሎ አንጠልጥሎ ተወው ።

"እውቀን ነው" አለ ክንፈ ፣ የሰውዬው የጨዋታ አቅጣጫ ወደራሱ ህይወት በማምራቱ ስሜቱ እየተለዋወጠ ።

"ገና መጋባታችሁ ነው?" አለው ሰውዬው ።

'ይሄ ሰውዬ አለቀቀኝም' አለና በሃሳቡ ፣ "ቦስተኞችንን ጨርስን አራት አመት ሊሆነን ነው" ሲለው ሰውዬው በአድናቆት አፍጪና "በጣም የምትገርሙና ጠንካሮች ናችሁ ። እንዴት ይህንን ያህል ጊዜ አንድም ልጅ ሳይኖራችሁ ፣ የልጅ አምሮት እንኳን ሳያሸንፋችሁ ቀራችሁ?" አለው ።

"በዕቅድና በፕሮግራም ይሁን ብለን ነው ፣ ደግሞም..." አለና አሳቡን ሳይጨረስ ንግግሩን አቋረጠው ።

"መቼ ለመውለድ አሰባችኋል?"

"መቼም!" አለ ክንፈ ታሳቱን ጠብቅ አድርጉና ቆጣ ብሎ ፣ ሰውዬው አላጨነውም ። ያስደነቀው ግን መልሱ ነው ፣ "ሜራሽ ለመውለድ አታስቡም ማለት ነው?" አለው በውኔታው ግራ ተጋብቶ ።

"እንወልድማ በቃ!" ብስጭቱ ታሳቱ ላይ ያስታውታል ። መልስ ለመረጋጋት እየሞከረ "የምንወልድ እንኳን አይመስለኝም ፣ ተለያይተናል" ብሎት የሚለውን ለመስማት አይን አይኑን ተመለከተው ።

የሰውየው ገጽታ ወደ ሃዘን ሲለወጥ ክንፈ አስተዋለ ። ለአፍታ ወጥ ካለ በኋላ "የማይሆናችሁን የህይወት አቅጣጫ ተረድታችሁ በጥቂት ጊዜ አጭማችሁን ማስተካከላችሁ ራሱ አንድ ታላቅ እርምጃና ጥንካሬ ነው" ሲለው ፣ ክንፈ በደመ ነፍስ ሞንቅላቱን ወዘወዘና ቢራውን ጨልጦ ሂሳብ ለመክፈል እጁን ወደ ኪሱ ሲሰድ ፣ ሰውዬው ፣ ተጣድፎ እጁን እያከላከለው "ሂሣብ በኔ ተዘግቷል" አለው ። ክንፈ አላቅማማም እጁን ወዲያው መለሰ ። ሰውዬው ችኮ ቢጤ በመሆኑ ቶሎ ሊገላገለው ፈልጓል ። ከመለያየታቸው በፊት "ማን ልበል ወንድሜ ስምህን?" አለው ሰውዬው ረጋና ፈገግ ብሎ ።

"ክንፈ ወ/አመላክ" አለው ፣ ጣጣ ሊያበዛ አልፈለገም ።

ሰውዬው ስሙን 'ኪዳኔ ይስሃቅ እባላለሁ' ብሎ ከኪሱ ውስጥ

አጭር የአድራሻ መግለጫ ካርድ አውጥቶ ሰጠው ። ክንፈ የተሰጠውን ካርድ ተቀብሎ ኪሱ ከተተና ስለግብግቡ አመስግኖት ፣ እሱንም ወ/ሮ ሰለናንም ተሰናብቶ ወጣ ።

መኪና ውስጥ ገብቶ የመኪናውን ሞተር ካስነሳ በኋላ ፣ ከመሄዱ በፊት የመኪናውን የውስጥ መብራት አብርቶ ፣ ከኪሱ ውስጥ የተሰጠውን አድራሻ አውጥቶ መመልከት ጀመረ ። ስሙን እንብዮ እንደጨረሰ ከሥሩ ያለውን ተመለከተና በረጅሙ አኻጨ ። ያልጠበቀው ሁኔታ ነበር። በተለይ ካሳየው ባህሪና ጠባዩ ጋር አልሄድለት አለው ። የእንድ ትልቅ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ነው ። ይሄኔ ቢሮው እሱን ለማግኘት ሊያገኘመው የሚችለው ቢሮክራሲ ታስበውና ፈገግ አለ ። ወዲያው ፊቱን ቀጭም የመኪናዎን የኋላ ማርሽ አስገባና ኮልስዋገኗን አስጓራት ።

* * *

እዚህ ክንፈ ቤታ አድርሷት ከሄደ ጀምሮ የተረጋጋ መንፈስ አልነበራትም ። በቤት ሰራተኛዋ በኩል የቆያት መልእክት አስጨንቋታል ። የሲራክ የስልክ ጥሪ ነው ። 'እንደገባች እንድትደውልልኝ' ይላል ። በነበረችበት ሁኔታ ደግሞ ልትደውልለት አልፈለገችም ። ለመጀመሪያ ጊዜ ልጁ ለሁለት ሰው ተከፍሎ ሲያመነታ ታውቃት ፣ መወሰን አለባት ። ለልኩ ደግሞ ለውሳኔ ጊዜ አልሰጣትም ። እንቃጨለ ። በሁለተኛው ጥሪ አነሳችው ።

"እንደምን አመሸህ!" አለችው ድምጿ ቀዝቅዞ ።

"የት አመሸሽ?" ቃሉ ከረር ብሏል ።

እናደዳት ። የት አመሸሽ የት ዋልሽ ብሎ ነገር ደሚን ያፈላዋል ። ራሷን አረጋጋችና ፣ "ቀጠሮ ነበረኝ ፣ እሳው ቆይቼ ነው" አለችው ።

"እኮ የት?"

ብልጭ አለባት ። 'የት እንድለው ይፈልጋል' አለች በሀሳቧ ፣ ስትፈራው የነበረው ነገር እንደደረሰ ገመተች ። የምታደርገው ግራ ገባት ፣ ብዙ ጊዜ ሰዎች እውነቱን እንዲነግሯቸው ይፈልጋሉ ። አስጨንቀውም ይይዛሉ ። ሲነግሯቸው ግን ያንን እውነት መቀበል ያቅታቸዋል ። ምንጊዜም በሰዎች መሃል እንደልብ ተግባብቶ መኖር የሚቻለው በደረቅ እውነት ሳይሆን መቀበል የሚፈልጉትን ውሸት ፈጥሮ ሲነግሯቸው ነው። እናም የምታደርገው ጨነቃት ። ውሸት ደግሞ አይሆንላትም ። በተለይ ደረቅ ውሸት እጅግ አድርጋ ትጠየፋለች ። አሁንም እውነቱን ብትነግ

Scanned with CamScanner

ረው የሚቀበላት አልመሰላትም ። ሊቀበላትም አይችልም ። እንዳትቀ
ሸው ጨነቃት ። ደግሞ ከክንፈ ጋር የፈጠረችው ግንኙነት ወሰን ስላ
እስከምን ድረስ እንደሆነ ገና በውል አላጤነችውም። 'የቆጡን አወርድ
ብላ ...' አይነትም እንዳይሆንባት ፈራች ።

"የዋልሽበትንም አታውቂ?" አላት መልስ ሲያጣ እያስገረመው ።

"ምን ይሰራልሃል?" አለችው ረጋ ብላ ።

"ግድ የለም ንገሪኝ ።"

ግራ ገባት ፡ "ከ... የራሴ የሆነ ጉዳይ ከሆነስ?"

"እኔ ላውቀው የማልችለው ወይንም ያላስፈለገበት ምን ጉዳይ
ቢኖርሽ ነው?"

"አልፎ አልፎ ይኖራል" አለችው ረጋ እንዳለች ።

"አዜብ ሙች ቀልዴን አይደለም..." አላትና ለአፍታ ዝም ብሎ
"ልትነግሪኝ ያልፈለገሽ ከሆነም ፡ መልካም ላትነግሪኝ ትችያለሽ ። እኔም
ልወቅ ብዬ የማስገደድ መብት የለኝም ። ግን ግንኙነታችን ለእንደዚህ
ዓይነት ነገር አመቺ አይመስለኝም ። ገባሽ? ማለቴ ይህን ያህል አስቸጋሪና
ከባድ የሆነ ነገር ልትገልጪው የማትችይው ምን እንደሆነ ነው
ያልገባኝ" አላት ፡ ንግግሩ የማስፈራራትም የማግባባትም ዓይነት ነው ።

አዜብ ትዕግስት አጣች "ብትተወኝ ምናለ? መንገር አልፈለኩም ፡
በቃ! አይገባህም?"

"መንገር ለመፈለግሽ ይገባኛል ። ያልገባኝ የት እንደዋልሽ
ለመንገር ለምን እንዳልፈለግሽ ነው ።"

የመጨረሻ ትእግሥቷን ተፈታተነባት ። ልትገላገል ወሰነች ።
እንዴት እንደምትነግረው ጨነቃት "እ... በቃ ከአንድ ወዳጄ ጋር
ነበርኩ" አለችው ። ስሙን ገልፃ ልትነግረው አልፈለገችም ። ምክንያ
ቱም ከዚህ ቀደም ለእወገነት ጉዳይ ብላ ስልክ ቁጥሩን መስጠቷን
ታስታውሳለች ።

"ምን ለማለት ፈለግሽ ነው አዜብ?"

የፈራችው ሆነ ። ለምን እንደነገረችው ራሷኑ አናደዳት ። ድምጿን
ከረር አድርጋ "አይሆንም ስልህ ካልነገርሽኝ ትለኛለህ ። ስነግርህ ደግሞ
አትቀበለኝም ። ምን ይሻለኛል!" ሲታ ተናነቃት "... በቃ ነገርኩህ
አይደል ሌላ ጥያቄ አትጠይቀኝ በቃ!።

ሲራክ አልሀም ንዴትም በአንዴ ወረሩት ። አንደበቱ ተሳሰረበት ።
አስከዛሬ መሞኘቱ... ሁሉም ነገር ተዘበራርቆ ታየው ። ሰድቦ ስልኩን
ለዘጋበት ፈለገ ። ስድቡ ሁሉ ጠፋው ። አዜብ ሲቃዋን አስታግሳ
ረሚለውን ትጠባበቅ ጀመር ። ለአፍታ ተፈጥሮዋን እየረገመች ፡
አፏንቷን እየኮነነች ።

"ጥፋቱ ያንቺ አይደለም ። የኔ ነው...." በሎ ንግግሩን ሊቀጥል ሲል
አቋረጠችው ።

"እንደሱ አትበለኝ..." አላትና "ጨዋ ሰው ትመስይኝ ነበር ።
ቆይ አስጨርሺኝ..." አለችው ።

የቤቶቹ ሁሉ አውራ አድርጌ እመለከትሽ ነበር ።"

"በቃህ ሲራክ ፡ በቃ!"

"...አንቺ ግን..." ስድብ ጠፋው ። "... አዎ ያታለልሽኝ መስሎሽ
ይሆናል ። ግን እራስሽን አታለልሽ ፡ ግን ለምንድነው?"

አሁንም ለአጭር ጊዜ ሁለቱም ፀጥ ተባባሉ ።

ከዚ መልስ ሲያጣ "ወይንስ በየቀኑ እየቀያየርሽ እንደምታነቢያ
ቸው የመዓሕፍት ቁጀሮች መኪናዬ ጀጉዋር ፡ ስሜም በአለም የገነነና
የታወቀ ስላልሆነ ነው?...."

"በቃህ አልኩህኮ ሲራክ በ...ቃህ?"

እሱ ግን ንግግሩን አላቋረጠም "በይኮ ንገሪኝ ፡ ወይንስ የሚሰሩትን
አጥተው ለገና እንደሚዳክሩ 'አድቬንቸሪስቶች' ስላልሆንኩልሽ ነው?
አይምሰልሽ በብዛት የምትይጎርቸው መፃህፍት ባብዛኛው አንቺ ካለሽበት
እውነታ ጋር የሚሄዱ አይደሉም ። ብዙ ተቃርኖ አላቸው ። አትሞኚ
እሺ!" አላት ፡ የቆሸቱ መድበን በድምፁ እያስታወቀበት ።

"እይገባህም ሲራክ ።"

"እሱን ልክ ነሽ አዜብ ፡ እስከዛሬ ስትጫወችብኝ መኖርሽ
አይገባኝም ነበር ። ደደብ!" አለና ስልኩን ጆሮዋ ላይ ጠረቀመው ። እሷም
ስልኩን ወርውራው መኝታ ቤቷ ገባች...

ያለፉ ሁኔታዎቿና የአሁን ድርጊቷ ተዘበራረቀባት ። የቱን ጨብጣ
የቱን እንደምትለቅ ግራ ገባት ። የምትፈልገውን ሳታገኝ ከሷ ጋር የነበሩ ፡
ትፈልጋቸው እትፈልጋቸው ለይታ ያላወቀቻቸው ሁሉ ያመልጧታል ።
የኑሮ ቅኝቷ ምንም ይሆንና ተስፋዋ ባዶ ይሆናል ። አንድ ነገር ተሰማት ፡
ለጋብቻ የታደለች አልመስላት አለ ። የብቸኝነቷ ዝግመት መቋጫው

Scanned with CamScanner

የተቃረበ ሲመስላት ውሉ እየጠፋት ተቸገረች ። ከንፈ ሞላንቲል ተስፋዋ ነው ። በጣም የጓጉለት ሁኔታን ደግሞ ካገኙት በኋላ ማጣት እያስቸገረ ያጠራጥራል ። እናም በተስፋዋ በከንፈ እርግጠኛ አልሆነችም። ሲራከም አመለጣት ። እጆቿን ለምፅዋት ዘርግታ ተስፋ ያልቆረጠች ተመፅዋች መሰለች ። መኝታ ቤቷን ታንኘችው ። ሰፊው የሞዝቫልድ አልጋ የመኝታ ቤቷን ግማሽ ይዞ ተንጣሏል ። ሰፊው መኝታዋ ብቸኝነቷን አጉላባት ። በቁምሳጥኑ መስታወት ራሷን ተመለከተች ። አስጠላት ። ሥር ስትል ጠረጴዛዋ ላይ አዳዲስ ነጭ ወረቀቶች በስርዓት ተቀምጠዋል ። ወደነሱው ሄደችና ብዕሯን አንስታ በትልቁ ትልቅ ዜሮ ደግማ ደጋግማ አዞረችባቸው ።

ምእራፍ አሥራ ሁለት

የሀምሌ ዝናብ ችኳል ። ከሰማይ እየተወረወሩ የሚወርዱት የውሃ እንጥብጣቢዎች ጣራ ላይ ሲያርፉ የራሳቸውን ድምፅ ይፈጥሩና በዛው ዳንኪራቸውን ረግጠው ቦታውን ለተረኛው ይለቃሉ ። የተጠራቀመ ውሃ ቦይ ላይ ሲያርፍ ለአፍታ ዘውድ ይጭንና ወዲያው ከስም ይላል ።

እፀገነት ይሄ ሁሉ አልረበሻትም ። በጥልቅ ተመስጠ አይኗን መፅሀፉ ላይ ተክላ ታነባለች ። የተሰጣትን የምፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ልትጨርስ የቀራት ጥቂት ቁጥሮች ብቻ ናቸው ። ነገር ግን ቁጣቸው በዛ። ዘለፋቸው አስፈራት ። እሷን የሚናገሩ መሰላት ። ደግማ አነበበቻቸው ።

'ልባም ሴት ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል ። የባሏ ልብ ይታመንባታል ፣ ምርኮም አይጐልባትም ። እድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርግለታለች ፣ ክፉም አታደርግም...' ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል ። 'መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ ። አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ ። ውበት ሀሰት ነው ፣ ደምግባትም ከንቱ ነው ። እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች።'

ሳታውቅ ራሷን ፍርድ ሚዛን ላይ አስቀመጠች ። አንዳች ነገር ሰውነቷን አንቀጠቀጣት ። ያለፈው ቅዳሜ ከሰዓት እንደሆነችው አይነት።

ለብዙ ጊዜ ሲከታተላት ሲያጠናት የከረመ የመሰሪያ ቤቷ ባልደረባ አንድ ቃን አጋጣሚው ይሳካለትና መፅሀፍ ቅዱሱን ይዞ ቢሮዋ ከች ይላል። ከእንግዳ በላይ ከሆነ ሰላምታ በቀር የቀረበ እውቂያ አልነበራቸውም። ስለጤንነት ፣ ስለስራ እንድ ሁለት ይላትና ስለመንፈሳዊ ህይወቷ እንዳንድ ጥያቄ ያቀርብላታል ። ፊት እየነሳች የሚለውን ብሎ እንዲወጣላት ያክል አናገረችው ። ተስፋ አልቆረጠም ። የሰይጣን እንቅፋት ነው በሚል ፅኑ እምነት ይጋተራታል ። በመጨረሻ እንደምንም ብሎ ለቅዳሜ ከስአት ቀጠሮ ይይዝላትና ፀሎትም ቤት ይመስዳታል ።

ቀጠሮ ቀጠሮ ነው ። ያ ቅዱሚ ይደርሳል ። ከስራ ሰአት መውጫ ሰዓት ከስአት አብራው ትጓዛለች ። ብዙ ሰዎች ቤቱን ሞልተውታል ። ተደም ብሎ ቢሮዋ ይመጣና ያስታውሳታል ። አልረሳቸውም ። 'ምን ይገኝ ይሆን?' በሚል ጉጉትና ሁልጊዜ ከሚጨቍጭቀኝ ሄጂ ልገላገል በሚል ስሜት ከስአት በኋላ ፀሎቱ ተጀመረ ። የፕሮግራሙ መሪ ይፀልያል ። ከተቂት ሰአታት በኋላ ፀሎቱ ተጀመረ ። የፕሮግራሙ መሪ ይፀልያል ። ያለማጀረጥ ከአምስት ደቂቃ በላይ በዚህ አይነት ቀጠለ ። የኋላ ኋላ እየፈራች እየተሸበረች መጣች ። መውጣት ፈለገች ። አመነታች ። በኋላ የመከረቻ ፀሎቱ አልቆ የቆሙት አማኒያን ከተቀመጡ በኋላ ተጋባዥ እንግዳው ወጥቶ እንዲያስተምር ተደረገ ። የሚናገራቸው ቃላት ፣ የሚጠቀማቸው ኃይለ ቃላት ልብን ይሰነጥቃሉ ። የጠንካራን ሰው ልብ የመፍታት ፣ ካልሆነም የመፈታተን ኃይል አላቸው ። እፀገነትንም በቀላሉ ረታት ።

ደካማ ጉኗን አግኝቶታል ። በፍፃሜው የፀሎት ስነ ስርዓት ላይ ሰባኪው ይፀልይ ጀመር "ይሰማኛል" አለ ሰባኪው ፣ "የእግዚአብሔር ድምፅ...." ይነግረኛል ። እዚህ ከመሃከላችን ልቡን ለክርስቶስ መስጠት እየፈለገ የሚያመናታ እንዳለ ተናግሮኛል ። አይዟችሁ ሰይጣን በጥርጣሬ ልባችሁን ሞልቶ እምነታችሁን ቢፈታተናችሁም በክርስቶስ! በክርስቶስ ስም በድል እንደምትወጡት አውቃለሁ...."

ሁሉም በያለበት ያጉተመትማሉ ። ለእፀገነት የሚሉት አይገባትም። ሲገዘፈዘፉ ያስፈራሉ ። "ምንጉድ ውስጥ ነው የገባሁት አምላኬ!" ስትል በልቧ አምላኳን ተማፀነች ። አሁንም ይፀልያል ።

"... አይዟችሁ! አሁንም እያመነታችሁ ነው ። በክርስቶስ ኃይል የሚፈታተናችሁን ሰይጣን አሸንፋችሁ ወደኔ እንድትመጡ በክርስቶስ ስም እጠይቃችሁዋለሁ ። አታመንቱ..."

Scanned with CamScanner

እወገነት ተጨነቀች ። ማመንታቷን ማወቁ ግራ አጋባት ። ፈራች ።

“...አሁን ጊዜ አላችሁ ፡ ወደኔ ኑ ። የወለዩላችኋል ። ይታየኛል ። አውቃ ልባችሁ እንደሚያመነታ ፡ ልውጣ አልወጣ እያላችሁ እንደምትጨነቁ አውቃለሁ።...”

እወገነት ከቁጥጥር ውጭ ሆና እየተንቀጠቀጠች ወደ ሰባኪው ቀረበች ። የሷ ቢጤዎች ሁለት ሰዎች አብረዋት አሉ ። ተወለየላቸው ፕሮግራሙ ተጠናቅቆ ወደየቤታቸው አመሩ ።

መፅሀፍ ቅዱሷን እያነበበች ጥሩ ስሜት ነበር የተሰማት ። ተቀምጣ ያለችው ቤተሰቦቿ ቤት ነው ። ቤቷን ጥላ ከወጣች ሶስተኛ ሳምንቷን ይዛለች ። ለጊዜው የእህቷን መኝታ ክፍል እንደድሮዋቸው ቢጋራ ይጠቀሙበታል ። ሁለቱን እህትማማቾች አንድ አድርጋ ባስተኙት አልጋ ውስጥ ሆኖ ነው መፅሀፍ ቅዱሷን የምታነበው ። እህቷ አልም ያለ እንቅልፍ የወሰዳት ትመስላለች ። ቤቱ ውስጥ እንቅልፍ ያደ ወሰዳት ብቻ ሳትሆን አትቀርም ።

የጀመረችውን የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል ብትፈጽርስም በዚህ አይነት ስሜት መፅሀፉን ልታጥፍ አልፈለገችም ። አይኗ ሰረቅ አድርጎ ተከታዩን ገጽ ተመለከተ ። የዳዊት ልጅ ንጉሡ የተናገረው ቃል ነበር ። ማንበብ ስትጀመር ሳባት ። ቀጠለች ።

‘ሰባኪው ከንቱ ፡ ከንቱ ፡ የከንቱ ከንቱ ፡ ሁሉ ከንቱ ነው’ ይላል ። ‘ከፀሀይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ የሰው ትርፉ ምንድነው ትውልድ ይሄዳል ። ትውልድ ይመጣል ። ንፋስ ወደ ደቡብ ይሄዳል ፡ ወደሰሜንም ይዞራል ። ዘወትር በዙሪቱ ይዞራል ። ነፋስ በዙሪቱ ደግሞ ይመለሳል ። ፈሳሾች ሁሉ ወደባህር ይሄዳሉ ። ባህሩ ግን አይሞላም ። ፈሳሾች ወደ ሚሄዱበት ስፍራ እንደገና ወደዚያ ይመለሳሉ ። ነገር ሁሉ ያደክማል ። ሰው ይናገረው ዘንድ አይችልም ። አይን ከማየት አይጠግብም ። ጆሮም በመስማት አይሞላም ።’

ካነበበችው ውስጥ ‘ነገር ሁሉ ያደክማል’ የሚለው ይበልጥ ተሰማት። የልቧን የነገራት መሰላት ። መጽሐፉን አጣጥፋ ራስጌዋ አደረገችና ‘ከንቱ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ፡ ሁሉ ከንቱ ነው’ የሚለውን በቃሏ ደግማ የራስጌዋን መብራት አጥፍታ ተሸፋፈነች ።

ትዝ ሲላት ወሎት አላደረገችም ። እንዳትረሳ ጥብቅ ማሳሰቢያ ሰጥታታል ። እንደገና አሳቧን አሰባስባ አልጋዋ ውስጥ እንዳለች በደረቷ ላይ ድንጋይ ተልበቶቿን ከሰበሰበች በኋላ ፊቷን ቁልቁል ትራሷ ላይ አድርጋ እያለቀሰች ትወልደ ጀመር ።

እህቷ አስቱር አድራጎቷን ሁሉ የተኛች መስላ በፅሞና ትከታተላት ነበር። “ምስኪን” ብላት እህቷ ስትጸልይ በገፈፈቻት ብርድ ልብስ ራሷን ተከናንባ ተኛች ።

የማማስቱ አየር እንደ አዳሩ አልጨፈገገም ። ፈካ ያለችና የጠራች ሀሀይ ከሰማይ ለምድራቱ ብርሃኗን ትረጫለች ። ሰዎች ወደ የእለት ስራቸው ለመሰማራት ደፋ ቀና ይላሉ ። ሴቶች በየማድቤቱ ይርመጠመጣሉ ። ሀሳናት ከእንቅልፋቸው ዶጋማው ያፋሽካሉ ። ዶሮዎች ከንጋት ጀምሮ የንጋትን መምጣት ሲያበስሩ ቆይተው ፡ አረፍ ማለት ጀምረዋል ፣ ከሆረባቸው ዶሮዎች በስተቀር ።....ምድሪቷ እንቅስቃሴዎን ጀምሯለች።

እወገነት በጊዜ ከአልጋዋ ተነስታ ተንጎዳጉዳ ካበቃች በኋላ የሳሎን ምግብ ቤት ጠረጴዛ ላይ ተተምጣ ታሰላስላለች ። መስሪያ ቤት መሄዱ አስጠልቷታል ። ሳታስፈቅድ መቅረቱ ደግሞ ከበዳት ። ወንበሩ ላይ እንዳለች ዶጋግማ አዛጋችና ወደታችኛው ሰርቪስ ቤት አመራች ።

ወንድሟ ኤርምያስ እንደተኛ ነው ። መስሪያ ቤት ከገባ ሳምንት ሆኖታል ። ፍታቷ አልወሰደም ። ገዙም ብሎ ቀርቷል ። የመኝታ ቤቱን በር እንኳኳች ። መልስ የለም ። ዶጋግማ መታችው ከውስጥ ጎርናና ድምፅ “ማነውና?” አላት ፡ ቁጣ የተቀላቀለበት ድምፅ መሆኑ ያስታውቃል ።

“ዕፀገነት ነኝ ክፈትልኝ” አለችው ።

ጥቂት ዘግይቶ በሩን ከፈተላት ። ተዘግቶ የከረመው የመኝታ ቤቱ ጠረን አወዳት ። መኝታ ቤቱን ሙሪያውን ቃኘችውና “እኔ ደግሞ እዚህ ውስጥ ምሽግ የሰራሁ መስሎኝ ነበር” አለችው ፡ ልትቃለደው ፈልጋ ።

“ከህሊናችን የተሻለ ምሽግ የለም ። ሌላው ጊዜያዊና ፈራሽ ነው ።” አላት ። ንግግሩ ደረቅ ሆነባት ። አልጋው ላይ ቁጭ አለች ። እሱም ትንሽ ተንቆራጠጠና ፈንጠር ብሎ ቁጭ አለ ። የሚሙ መብዛት ያስከፋል ። አይኖቹ ጎድጉደው ወደውስጥ የሰመጡ ይመስላሉ ። የጉንጩ አጥንቶቹ እንደመግጠጥ ብለዋል ። ፀጉሩ ተንጨብሮ ባሕታዊ አስመስሎታል ። ጠቅላላ ገፅታው ያስቀይማል ።

Scanned with CamScanner

እወገነት ስትፈራ ስትቸገር ቆየችና "ዛሬ ስራ አትገባም?" ገፅታዋ ንና ቅላፄዋን አስተዛዝና ።

ኤርምያስ አተኩሮ ተመለከታትና "ለምንድነው ስላሚን ሰዎች እያሳደዳችው የምታስጨንቂኝ? ማረፍ ስፈልግ ለምን አታሳርፉኝም ። መግባት አለፈለኩም ፡ ቢታ! አልፈለኩም ። ስፈልግ እገባለሁ ።"

"እንዳያስወጡህ ብዬ ኑ ነው" ሳቀና "አያስወጡኝም ።" እኔን በቁሜ ተጫውተው የበላይነታቸውን ሊያሳዩኝ እንጂ ሊያስወጡኝ አይፈልጉም። እሱማ ወግ ነበር " አላት ከንፈሩን እያጣመመ ። "ይልቅ እንቺ ስራ አይርፈድብሽ" አላትና የእጅ ሰአቱን ሊያይ ቢፈልግ አጣው ። ትግ ሲለው ግታ ሰአቱን ከተመለከተ በኋላ ተበሳጭቶ "ጊዜ ቢቆጠር ሀይማት ትርጉም ካጣ እሱስ ምን ትርጉም ይኖረዋል" ብሎ ከእጁ መንጭቆ ከግድግዳ አላትሞታል ።

በአዘኔታ አትኩራ ተመለከተችው ። ደረቱ አካባቢ ያገጠጡት አጥንቶቹ ነሳቱን ያሳያሉ ። 'ምን ይሻላል? ከቀን ወደቀን እየባሰበት ሲሄድ ዝም ብሎ አይታይ' አለች ለራሷ ።

"ለምን መጽሐፍ ቅዱስ አታነብም?" አለች ፈራ ተባ እያለች ።

ዞር ብሎ ተመለከታትና "የየራሳችን መፅሀፍ ታሪክ መቼ ተነበ አለቀ ብለሽ ነው? 'ራሳቸውን አጥንተው ማንነታቸውን ፍለጋ የሚዋትቱ ሰዎች ናቸው ማንነታቸውንና ምንነታቸውን ለማወቅ መፅሀፍ ቅዱሳቸውን የሚገልጡት ። የኔ ነፍስ ከመሬት በላይ ከሰማይ በታች የምትንሳፈፍ ናት ። የሚሆነውን ከማየት ሌላ ምንም አትፈልግም ። ይልቅ ስራ አይርፈድብሽ ማታ ስትመጪ ታሪኳውቺኛለሽ ።"

ኤርምያስ እወገነትን ይወዳታል ። ከቤተሰብ ሁሉ የሚያቀርበው እሷን ነው ። ከታናሽ እህቷም ጋር ያለው አግባብ ደህና ነው ። ብቻ ሁኔታዋን እያየ "ትንሿ ፈንጣ " ይላታል ። በራሱ በጣም ይመካል ። ቢሆንም ለሰዎች ያለውን አክብሮት አልቀነሰበትም ። አንዳንዴ ግን በራሱ ያለው ፅኑ እምነት ሲናጋ ፡ ሲደፍርስ ፡ ከራሱ ፡ ከአካባቢው መጣላት ይጀመርና ራሱንም ሰውንም ማኩረፍ ይጀምራል ።

"ቅዳሜ ቸርች እንሄዳለን እሺ?" አለችው በማግባባት መንፈስ ። ፈገግ አለና "እዛም መሄድ ያለባቸው የመንፈስ ድህነት የተጠናወታቸው ሰዎች ናቸው ። መንፈሳቸውን በእንዳች ኃይል ሊሞሉ ።"

እወገነት እንዴት እንደምታግባባው ግራ ገባት "ግዴለም አብረን እንሄዳለን።" ኤርምያስ ቆጣ አለ ፡ "ነገርኩሽ የምሄድበት አላጣሁም።"

"የሚሄድበት ያጣ ነው እንዴ እዛ የሚሄደው?"

"አላውቅም።"

"አላውቅህም" አለች ፡ እወገነት ሁኔታውን አስተውላ ። "ተነሳበት እንግዲህ" አለች ። እወገነት ከጀመረ ምንም መልካም ነገር ቢነገር አይጥመው ። እንዴ መቆጣት "ደህና ዋል" ብላው ልትወጣ ስትል ፡ ከከንፈ ጋር እንዴት ሆናችሁ?" አላት ።

አስበበት አስታውሶ መጠየቁ አስደነቃት ። ለምንም ነገር የሚያስ ብና ትኩረት የሚሰጥ አይመስላትም ነበር ። "ምንም የለም! " አለች የምትመልሰው ግራ ገብቷት ።

"እንዴት ነው? እሱ እንኳን ጥሩ ሰው ይመስለኝ ነበር ። ይሄን ያክል የሸሸው ምን ቢያደርግሽ ነው? " አላት የጥያቄውን ክረት በፈገግታ እያረገበ ።

እወገነት ስሚታ ሸምቀቅ አለ ። የጥሏን መነሻ ለአንዳቸውም የቤተሰብ አባል አልገለፀችላቸውም ። ዳሩ ምን ብላ! ቢሆንም ሁሉም የነመቴት 'ቢያስከፋት ነው' በሚል ነው ። ገና በመሃከላቸውም ሽማግሌ አልገባም ። ነገራቸው ከሽማግሌ ጆሮ ርቋል ።

መልስ አልነበራትም። "በል ደህና ዋል ፡ በጊዜ መጥቼ አጫውትሃለሁ" ብላ በሩን ዘግታለት ሄደች ። ተነስቶ በሩን ቆልፎ ገና ከመቀመጡ እናቱ እያንኳኩ "ኤርምያስ! ኤርምያስ! ይህችን አፍህ አድርግ ፡ ከፈትልኝ" አሉት በሩን ለመክፈት እየታገሉ ።

ተናደደ ፡ 'ጠዋት ማታ ለከርሳችን የምንዋትት ሕዝቦች! ለዛም አቅሙ ጠፍቶ ፡... ሕሊናውን በነገር እሾህ ጠቅጥቀው ላኮሰመኑት ሰው ለሀሊናው እንጂ እንዴት ለሆዱ ይታሰብለታል? ባዶ ጭንቅላት የሚበላው ምግብ እንስሳት ከሚበሉት መኖ አይሻልም ። ልዩነቱ አይገባውም' አለና "ይቆየኝ እማዬ" አላቸው ።

"ልጄ አፈር ስሆን!"

አንጀቱ ራርቶ በሩን ሊከፍት ተነሳ ። በሩን ሲከፍት ግን ያገኘው ቁርሱን ሳይሆን ሁለት መስቀል የያዙ ቄሶችና ያስቸግራል ተብሎ ስለተፈራ ሁለት የመንደር ጠረንገሎች ነበሩ ። አልተቃወማቸውም ።

Scanned with CamScanner



በልቡ አፈዘባቸው ። እናቱን በጥላቻ አይን እያያቸው ።
…ዕፀገነትን ይዟት ይሮጣል ። በኃይል ይሮጣል ። አንዳንድ ጊዜ
እየደከመችበት የመሸከም ያክል እያቀፈ ይጎትታታል ። ከንፈ ሊደርስባ
ቸው ነው ። ትንሽ ከሮጡ በኋላ ሄኖክ ወደ ኋላ ዞሮ ቢመለከት ከንፈ ወዳት
እንደገባ ይጠፋዋል ። ሩጫውን በዛው ይገታል ። ዞር ሲል እጅግ ተውቦ
የለመለመ መስክ ይታየዋል ። እየተጉራጉሙ ወደመስኩ አመሩ ። ቅርባ
የመሰላቸው መስክ ቢሮጡ ቢሮጡ እየራቃቸው ይሄዳል ። የሄኖክ
ትዕግስት ተሟጠጠ። በጀርባዋ ጎትቶ እምድሩ ላይ ጣላት ። የጎንበትን
ሰውነት ፡ የናፈቀውን ገላ እየታገለ እምቢ እያለችው እሸንጉት ናኘበት ።
አታግላው እንደልጃገረድ አለፋቸው ። ቀና ሲል ከንፈ ከበላያቸው ቆሟል።
ድንጣጠ ባነነ ።

ሰውነቱ በላቡ ተጠምቋል ። ድካም በመላ ሰውነቱ ተሰራጭቷል ።
ውጪ በነበረበት ጊዜ ሲያጋጥመው የነበረውን ሁኔታ አስታወሰው ። ነጋ
ጠባ የሚያጥባቸው ውስጥ ሱሪዎች ያበሳጩት ነበር ። ከሀገሩ ደግሞ ይዞት
የሄደው ተረት ነበር ።

‘ሴት ሰይጣን ወዳጅነት ይዛሃለች ። አውቃ በፍቅረኛህ ተመስላ
ትመጣለች’ ይባላል ። ሰጋት ያድርበታል ።

ያ ሁሉ ሁኔታ ያስቸገረው አስከተወሰነ ደረጃ ነበር ። ከዛ በኋላ ግን
ከተማሪዎች ጋር የነበረው ግንኙነት እየሰፋ ሄደ ። ከአነስታዮችም ጋራ
እየተቀራረበ መጣ ። አልፎ አልፎ ካልሆነ ሰይጣኗ ወ/ሮ አትመጣበትም ።
ዛሬ ግን መጣች ።

ያውም ጣውንቷን አስከትላ …

“ናፍቃኝ ይሆን” አለ በአልጋው አንድ ወገን እየተገላበጠ ፡ ካገኛት
ሳምንት ሊያልፈው ነው ። ከባሏ ተጣልታ ቤተሰቦቿ ጋ ከሄደች ጀምሮ
እንደጓጓው በየጊዜው አላገኛትም ። ሁለቱ ብቻ ነው ።

አንድ ነገር አልሞ ወይንም ወጥኖ ለማበ ተቃረብኩ ሲል ለምን
አልሳካ እንደሚለው እያውጠነጠነ ከአልጋው ተነሳ ። እዚህ ከወራተኛዋ
ጋር ስትጎታረክ ድምጿ ተሰማው ። ከሷ ጋር ያለው ግንኙነት ካንገት በላይ
እየሆነ መጥቷል ። ምክንያታቸው እወገኑት ነች ። በፊት በፊት ቤቷ ድረስ
ይዟት ስለሚመጣ እየመሰለው ይበሳጭ ነበር ። አንድ ቀን ግን ‘እሷኮ
ባለትዳርነች’ ስትለው በምን እንዳወቀች ግራ አጋብቶታል ። እውን ግን

ለሰዓቷ ግንኙነታን ትታለች ። የመስሪያ ቤት ሥራ ደግሞ ቀዝቅዟል ። ብዙ
የሚሰራ ስራ የለም ። አንዳንድ ጊዜ ስራ እየበዛ ‘ሱራ ባንጎት’ የሚሆንበት
መች ሲኖር አልፎ አልፎ ደግሞ እንዲህ እንደሰሞኑ ለፊርማ ብቻ
የሚገዙበት ጊዜ አለ ። ከኖረበት ከተማረበት ሀገር የስራ ሁኔታ ጋር
ይሀንን እያነፃፀረ እጅግ ይገረማል ። ውጭ እያለ እንዳስተዋለው ባከና
የቻልፍ ሰአት በጣም አነስተኛ ናት ።

ከቤት ከመውጣቱ በፊት ካፖርቱን አጠለቀ ። አየሩ ግን ደህና ነው ።
ከቆምኑና ዘለግ ካለው ቁመናው ጋር የሚሄድለት ደማቅና ጥቁር
ካፖርቱን አይዘነጋም ። ሁለት ምክንያት አለው ። አንዱ የጊዜው
ከፖምትነት ፡ ሌላው ደግሞ እንደሚያምርበት ያውቃል ። ቁርሱን እንኳን
ሳይቀምስ እየተጣደፈ ወጣ…

ለሊት የዘነበው ዝናብ ሰፈሩን አጨቅይቶታል ። የአስፋልቱ
እርግበት በማለጻዋ ወሐይ እያብለጨለጨ እንፋሎቱ ወደ ላይ ይተናል ።
ደስ የሚል ቀን ነው ። ረጃጅም ቦት ጫማ ያደረጉ ሴቶች ጃንጥላዎቻቸውን
ዘርግተው ይወጣሉ ይወርዳሉ ። ወንዶችም በአለባበሳቸው ደንስንስ
ብለው ይጣደፋሉ ። ከየመኪናቹ የሚወጣው ጭስ አየሩ ላይ እየተነነ
የቸርችልን ጎዳና ሽቅብ ቁልቁል ይርመሰመስበታል ።

ሄኖክ መንገድ ተሻግሮ ከቆመ በኋላ ወደ ስታዲዬም የሚወስደውን
ታክሲ ይጠብቃል ። ቶሎ አላገኘም ። ታክሲዎች በአብዛኛው እየሞሉ
ይመጣሉ ። ቦታ ያላቸውም ቢሆኑ ሰው ተሯሩጦ ይደነቅርባቸዋል ።
ወያላው ‘ቀስ በሉ’ ይላል ። ሕዝቡ ይተራመሳል ።

ቢሮ የደረሰው አርፍዶ ነው ። እንደገመተው ሥራ የለም ። ጋዜጣው
ገናአልመጣም ። ደብዳቤ ። አብሮት የሚሠራው ሀሰን የባሰ ድብርታም
ነው ። ሴት ልጅ ሲያነጋግር ብቻ ፊቱ ይፈታል ። በተረፈ እንደጨጓጣው
ይውላል ። የጉንጨቱን ሂም ደግሞ ቶሎ ቶሎ ስለማይላጨው ፊቱን የባሰ
አጨፍግጎታል ። ብዙ ጊዜ አያስቅም እንጂ ፍልጥ ፍልጥ የሚያካክሉ
ፕርሶች አሉት ። ዘወትር የሚሰራው አያጣም ። የስነዕሁፍ ሰው ነኝ ይላል
። ዘወትር የሚወጡትን የአማርኛ ልቦለድ መፃህፍት እያነበበ ይሄዳል ።
ሂሱንም ለጋዜጦች ይልካል ። በአብዛኛው የተዋጣለት አለት ብቻ
ይደሰታል ። በመልክ-ባያው-ቁትም ብዙ ደራሲዎች ብእሩን ይፈሩታል ።
ርሀራሄ አያውቅም ። ብእሩን ካነሳ አይመለስም ። ዘወትር ስለሂስ ሲነሳ

Scanned with CamScanner

የሚናገራት ፈሊጥ አለችው “እኛ የጀማሪ ፀሀፍት መለማመጃ እያደረክ
ንም ። ብቃትና ጥራት ያለው ስነፅሁፍ እንሻለን ። ለዛ ገና ብዙ ይቀረናል ፣
እናም ርሀራሄ አያስፈልግም” ይላል ። ሀሰን ከሁሉ የሚጠላው ነገር ቢኖር
በፅሁፉ ላይ የሚሰነዘርበትን ተቃውሞና የደራሲን ትምክህት ነው ። እሱ
ያቀረበውን ሂስ የተቸ ወየውለት ። ያኔ ብእሩ ከማስተማር ወደ ስድ
ታዘነብላለች ። ከመሄስ ወደ ማንጓጠጥ ትወርዳለች ። ከትችት
የተቺውንም ማንነት ፈልጋ በደካማ ባህሪው ትዘምትበታለች ።

ሄኖክ አቀርቅሮ የሚፅፈውን ሀሰንን ተመለከተና “ደግሞ ብእርህን
ማን ላይ ደገንክ?” አለው ። መቼም ከትችት ሌላ ስራ የለውም ብሎ ፣
ደራሲ ተብዬዎችን ነዋ” አለው ከፊቱ ላይ የምትንከባለለውን እይኑን
በልጥ ።

“ቃላት ከቃላት ከገጠሙ ፣ ያንን አዳምረው ልቦለድ ይሰኛል የሚሉ
ይሻላል ። ታዋቂው የስነ ፅሁፍ ሰው ወሌ ሾይንካ ያለውን ልንገርህ ፣
‘ስነፅሑፍ ለማንኛውም ሰው ሳይሆን ነገሮችን አመሳጥሮ መድረስ
ለሚችል ሰው ብቻ ናት’ ይላል ። አይመስልህም? ብእሩን ደግሞ ወረቀት
ያበላሸ ሁሉ ደራሲ አይምሰልህ ። አንድ የአገራችን ደራሲ ያልሙን
ላስታውስህ” አለና ፂሙን ወደታች እየጎተተ “መጥረቢያን መጥረቢያ
ማለት ጭካኔ ሊሆን አይችልም ። ገዘም ከማለት የቀለለ ነገር የለም ።
የሚያስቸግረው የሚያስቡትንና የሚያምኑበትን ሳይፈሩ መናገር ነው”
ይላል ። አንተስ ሃሳቡ ትክክል አይመስልህም?” አለው አይኑን ፊት ለፊት
እያጨነቆረ ።

ሄኖክ አቅማማና “ማን እንዳለው አላውቅም እንጂ ‘ማንበብ ያለብህ
ለመቃረን ያለዛም የሰው ስህተት ለመፈለግ ሳይሆን ለማወቅና ለመገን
ዘብ መሆን አለበት’ የሚል አንብቤአለሁ” ሲለው ፡

“እይ ሲ! ይህች የፍራንሲስ ቤንሰን አባባል ነች...” አለው ። ሀሰን
በብዕሩ ጠረጴዛውን እየጠበጠበ “ታዲያ—ኮ ይህን የፍራንሲስን አባባል
አስተውለኸው ከሆነ ፡ ‘እንድ ሰው የሚያነበው ፡ ማለት የንባብ ጥቅሙ
የተሟላ ሰብዕና ለማጐናፀፍ ፡ በነገሮች ላይ የተብራራ ግንዛቤ እንዲኖ
ረው፡ ጥሩ ፀሀፊም እንዲሆን ነው’ ይላል ። ታዲያ አንብበን ያነበብነውን
መረዳት ካልቻልን ፡ ወይንም ደግሞ ያነበብነው ነገር ሊያስተምረን ፡

ሊያሰውቀን ካልቻለ ጥቅሙ እምኑ ላይ ነው? አሁንም ያ ቅድም
የጠቀስኩልህ ያገራችን ደራሲ ‘ኪነት የነጠረች ሕዝባዊ ሕሊና ናት ።
የኪነት ተግባርዋ መጋረጃውን ከፍታ ፀዳሉን ማሳየት ነው’ ይላል ። እኔ
እንደማየው ግን በአብዛኛው የሚወጡ ልቦለዶቻችን እንኳንስ መጋረጃ
ውን ከፍተው ፀዳሉን ማሳየት ይቅርና በግል የሚታየውን ውበትም
ያድበሰብሱታል ። ታዲያ ለነኚህ ምን ርሀራሄ ያሻል? ሩሲያኖች ምን
ይሉሉ መሰለህ... አለና እይታውን ጣራው ላይ ሰክቶ ‘ብዕር የፃፈውን
መጥረቢያ እንኳን ሊፍቀው አይችልም’ ይላሉ ፡ የብእርን ጥንካሬ
ሲገልፁ። ታዲያ ይህንን ታላቅ ሀይል ያለው መላሪያ ይዘው ስራዎቻቸ
ውን ጥይት የሌለው ጠመንጃ ሲያደርጉት አያናድድም? ስነፅሁፍ
የህብረተሰቡ ጭራ ከሆነች አበቃላት ። መሆን ያለባት አጉልታ የምታሳይ
መነጽሩ እንጂ ። ሲሆን ሲሆን የማይታየውን እንደቴሌስኮፕ መግለጥ
ይጠበቅባታል ። ያለዛ ግን በተሻለ ሁኔታ ማየት የሚችለውን ማህበረሰብ
አይን ማላወር የለባትም።”አለውና አሁንም ጠረጴዛውን እየጠበጠበ ፣
“እየህ ፡ እንዳች ፍሬ ነገር ላታገኝ ባለህ ኢኮኖሚያዊ አቅም ላይ መፅሀፍ
ሸምተህ ፡ ያንንም የሸመትከውን መፅሀፍ ለማንበብ ጊዜህን ሰውተህ
ውጤቱ ባዶ ሲሆንብህ ‘በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ’ ቢጤ
ትሆናለህ ። ታዲያ ይህንን ጉድለት ያለ ርሀራሄ ካለጠረብከው ጉዳቱ
ያመዝናል ። ብዙዎቹ ‘ባለን አነስተኛ ዶራሲያን ቁጥር አንፃር የሃያሲያን
ብዕር የታዳጊ ፅሀፊትን ብእር ያጨልማል’ ይላሉ ። ይህ በኔ ግምት ልክ
አይደለም ። አላምንበትም ። መተራረም መወቃቀስ በእድገት ኮትኳችነቱ
እንጂ በአጥፊነቱ መታየት የለበትም ። ቦታ ከሚያጣብቡ ያልረቡ
ጽሁፎች ትርጉም ያላት እንዴት ቃል ትበልጣለች ። በአለማችን አሉ
የተባሉ ታላላቅ የስነጽሑፍ ሰዎች እዚህ ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት ፡
ድከመቶቻቸው በሃያሲን እየተጨረቆላቸው ነው ፍፁም ባይሆንም
የተሻለ ፅሁፍ ይዘው የሚቀርቡት ። አየህ ደራሲያን ሁለት አይነት ናቸው
። አንደኛው ትችትን ፡ ወይም ሂስን እየተቀበለ ለሚቀጥለው ስራው
እርምጃ የሚሆነው አይነት ሲሆን ፡ ሌላው ደግሞ በተተቸና በተሄሰ ቁጥር
ሞራሉ የሚነካና እንደገና ለመፃፍ ድፍረትን የሚያጣ አይነት ነው ። ይህ
አይነቱ ደግሞ ከጅምሩም የስሜት ደራሲ እንጂ እውነተኛ ደራሲ ሊሆን
አይችልም ። ድርሰት ድፍረት ትሻለች ። ያለዛ አንድ እንግሊዛዊ ደራሲ

Scanned with CamScanner

እንዳለው ፣ ‘ድፍረት የሌለው ብዕር ወረቀት ያበላሻል’ ቢጢ መሆኑ ነው ፣ ስለዚህ ደራሲያን ከጅምሩ ሂስን መናፈቅ እንጂ መፍራት የለባቸውም ፣ ካልሆነ ግን አሸዋ ላይ እንዳነፁት ሕንፃ ይሆንባቸዋል” አለው የታችኛው ክንፈሩን ስስ ቆዳ በጥርሱ እየላጠ ፣ መቼም ስለስነውሩ ከተነሳ ሃሳቡ ቶሎ አይቋጭም ።

ሂኖክን ያስደነቀው ሰዎች የሰዎችን ስህተትና ግድፈት ፈልፍለው ለማውጣት ይህንን ያክል መጨነቃቸው ነው ። ከገፅ ገፅ አገላብጠው ከቃላት ቃላት አገናኝተው ይሄ በዛ ይሄ ጉደለ እያሉ የብእር ጦራቸውን የሚሰብቁ ሰዎች ከደራሲያኑ ይበልጥ ያስደንቁታል ።

“ለመሆኑ እንዲህ ተጨንቀህ ጽፈህ ምን ጥቅም ታገኛለህ” አለውና “ወይ እንደኛህን መፅሀፍ ፅፈህ ገንዘብ አላገኘህ፤ ያንተ ድካም የብቻ ነው” አለው ከልቡ እያዘነለት ።

ሀሰን ፈገግ አለና ፣ “ኪነትም እኮ አውን አንተ እንዳልከው በጥቅም ብቻ እየተለካች እኮ ነው እንዲህ መረን የወጣችው ። ስነፅሁፍም ብለው የተነሱ ብእሮች እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው ። የስነ ፅሁፍ ብለው የብዕራቸው ብርታት ጥቅም ያስገኘላቸው እንደሆነ እንጂ ጅምሩን ለጥቅም መፃፍ የላባቸውም ። ለጥቅም ከሃፉ ነገር ተበላሸ ። አንድ ደራሲ ሊፅፍ ሲነሳሳ ምን ያህል ጥቅም አገኛለሁ ብሎ ሳይሆን ፣ ህብረተሰቡን ምን ያክል እጠቅማለሁ ብሎ መሆን አለበት ። ያለባ ስነፅሁፋችን ከዘፈን ክሮቻችን ጋር ሊፎካከሩ ነው ። ገቢ ሲባል ብቻ እየተቸበቸቡ ጀርባ ሲያደናቁሩ እንደሚውሉ የካሴት ክሮች መፅሀፎቻችን ሕብረተሰቡን ግራ ሊያጋቡት እደገባም ። የኔ ጥረትና ፍላጐት ያ እንዳይሆን ነው እንጂ እንተ እንዳልከው ፣ ጥቅም አገኛለሁ ብዬ አይደለም ። የኔ ጥቅም ከህብረተሰቡ የተለየ አይሆንም ። ጥራትና ብቃት ያላቸው መፅሀፎች ገበያው ሲሞሉት ማየት ያረካኛል ። ይህ ነው የአንድ ስነፅሁፍ አፍታሪ ደስታና ርካታ ፣ ተግባባን!” አለውና በመቀጠል “ምን መሰለህ ፣ አንድ ፅሁፍ ስትመለከት ካለህበት ማኅበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንፃር ተመርኩዞ ለህብረተሰቡ ሊያስተላልፍ የፈለገውን እውነታ በውስጡ ሲያካትት ነው የተዋጣ ፅሁፍ የሚሆነው ። ያለ ህብረተሰቡ የሚያውቀውን እንደገደል ማሚቶ የሚያስተጋባ ከሆነ እርባና ቢስ ይሆናል ። እና በዚህ አንፃር ስትመለከተው እኛ እውን

ያለንበትን ሁኔታ በተለይ በልቦለዶች በኩል ስንመለከት ከዚህ የባሰና የከፋ ሁኔታ ላይ እንገኛለን ። ልቦለዶቻችን ህብረተሰቡ የሚያውቀውን እንኳን በትክክል መግለፅ አይችሉም ። ሀቅና ውበት በውስጣቸው ተድበስብሰው ይቀራሉ ። አንድ ነገር ለመግለፅ አስፈላጊ ያልሆነ ዙሪያ ጥምጥም ይጓዛሉ ። በዛውስጥ እውነትን ፍለጋ በከንቱ ትቃትታለህ ። ግን አታገኘውም ። ቃላት ባዶና አቅጣጫ ቢስ ይሆናሉ ። እና ትናደዳለህ ። ያኔ ርሀራሄ ከውስጠህ ይጠፋል ። ለእንደዚህ አይነት ብእር አትራራለትም ። ቢሆንም ደግሞ ፡ አልፎ አልፎ ይህን ያህል የመጠቁ ባይሆኑም ሕብረተሰቡን የቀደሙ ጥሩ ጥሩ የልቦለድ ታሪክ ስነፅሁፎች አሉን ። እነሱን ለማበረታታት ፡ የሚነቀፉትን ለመንቀፍ በሞያው የጠለቀና የነጠረ እውቀት ያላቸው ሙያተኞች ያስፈልጉናል ። ያ እስኪሆን ድረስ ደግሞ ለስነፅሁፎች የተለየ ፍትርና አክብሮት ያላቸው ተደራሲያን ነገሮች ሲበላሻሹ ዝም ብለው መመልከት የለባቸውም ። ኪነጥበብ ምንም እንኳን የጥቂቶች ተሰጥዖ ብትሆንም ፡ የማኅበረሰቡ ተሳትፎ ለጥበቡ እድገት ወሳኝ ሚና አለው ። ኪነጥበብ ያለህብረተሰብ ፣ ህብረተሰብም ያለኪነጥበብ ሕልውናቸው ተነጣጥሎ አይታይም...” ከማለቱ በሩ ተበረገደ ። ሁለቱም ደንግጠው ከእንግቶቻቸው ቀና ሲሉ ገብቶ ፊትለፊታቸው የተገተረው ተሳላኪው ተሜኔ ነው ።

“ይህን ሳምንኳኩ በር መበርገድ ተው አላልኩህም?” አለ ሀሰን ከላይ እስከታች በቁጣ እየተመለከተው ።

ተሳላኪው ተሜኔ አልመለሰም ። አለቃው እንደሚፈልጉት ብቻ መልዕክቱን ነገር ውልቅ አለ ።

ሀሰን “ሌላ ቀን በሰፊው እንጫወታለን” ብሎት ፡ ወረቀቶቹን ሰብስቦ ወደ አለቃው ቢሮ አመራ ።

ሂኖክ ብቻውን ሲቀር ፡ የቢሮው ቅዝቃዜ ዘልቆ ተሰማው ። ስልኩን አነሳና አፕሬተሯ ጋ ደውሎ የውጭ መስመር እንድትሰጠው ጠየቃት ። ትዕዛዙን ፈፀመችለት ።

እፀገነት ስታናግረው እንደ ወትሮዋ አልሆነችለትም ። ቀዝቃዛና ደካማ ስሜት ነበራት ። ምን እንዲህ እንዳደረጋት አልገባውም ። ከስራ በኋላ ሀራምቤ ሆቴል ሊገናኙ ተቃጥረው ስልኩን ዘጋው ።

Scanned with CamScanner

እፀገነት ከቢሮ አላስወጣ እያለ ያስቸግራት የአስር ሰአቱ ድንገተኛ ዝናብ አበሳጭታታል ። አለቃዋ ገና አልወጡም ። የመጥሪያ ድምፅ አሰሚት ። ሶስት ጊዜ አንኳኩታ ከፍታ ገባች ።

"እፀገነት!..." አሏት በወፍራሙና በምትወደው ድምፃቸው ። የልጃቸው ያክል ይመለከቷታል ። እሷ ደግሞ ጥሎባት ትፈራቸዋለች ። ድምፃቸውን ብትወደውም አንዳች ኃይል አለው ። ያሸብራታል ።

"አቤት!" አለቻቸው በሩን በአንድ እጇ ይዛ ትንሽ ገባ ብላ ። ከእግር እስከ ራሷ በርሀራሄ አዩዋትና "ለመሆኑ ሰሞኑን ስራ እንዴት ነው? ይበዛብሻል?" አሏት ።

የጠየቁበት በቂ ምክንያት አላቸው ። ብዙ ጊዜ ትዘነጋለች ። የምትሰራቸው ስራዎች ጥራት የላቸውም ። በአንድ ገፅ ከምትመታው የታይፕ ወረቀት ብዙ የቃላት ግድፈት ማውጣት ይቻላል ። ሁኔታው ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆን እያሉ ቢያልፉትም ፣ አልተሻሻለችም ። በፊት በፀሀፊነቷ በመስሪያ ቤቱ ካሉት ሴት ፀሀፊዎች ሁሉ የተሻለች መሆኗን ይመሰክሩላታል ። እንደ ሽሚዝ ከቢሮ ቢሮ ከሚበውዟቸው ሴት ፀሀፊዎች መካከል እሳቸው ጋ አንድ ቢሮ ይዛ ለረጅም ጊዜ እንድትቆይ የተደረገው በሳቸው ፍላጐት ፣ ኃይልና ስልጣን ነው ። እሷም እሳቸው ቢሮ መቆየቷን ብትወደውም ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመሥሪያ ቤቱ የሚወራውን አሉባልታ ትፈራለች ። እንዳውም እሷ እንደሌሎች የቢሮ ፀሀፊዎች የመበወዙ ዕጣ ያልደረሳት ከአለቃዋ ጋር ባላት የግል ግንኙነት መሆኑ እንደተወራባት ሰምታለች ። በዚህ የተነሳ ፣ በደህናው ጊዜ ከክንፈ ጋር ትወያይ ነበር ። 'ንፅህናሽን የምታውቂ አንቺ ብቻ ነሽ ። ይህ ሊያበላሟ አይገባም' ነበር ያላት ። ያላትን አስታወሰች ።

አሁን ደግሞ ፣ ከስራ ሰአት ውጭ አለቃዋ ቢሮ መገኘቱ አስፈርቷታል ። በዛ ላይ ጥያቄያቸው አልገባትም ። ከወትሮ የተለየ የስራ ለውጥ የለም ። እንዴት ጠየቁኝ? "ኧረ የለም ፣ ያው ነው ፣ ስራ አልበዛብኝም" አለቻቸው ።

አትኩረው እያዩዋት ችግሯን ከገጿ ላይ ለማንበብ ሞከሩና አቃታቸው ። "ፍቃድ መውሰድ ትፈልጊያለሽ...ማለቴ ዕረፍት እንዲሰጥሽ ትፈልጊያለሽ?"

ሁኔታቸው ይበልጥ ግራ አጋባት ። የለም አልፈልግም" አለች ። ዘወትር እየቀረፀች ከምታስቀምጥላቸው እርሳሶች መካከል አንዱን

ሳብ አድርገው ጣታቸው መሀከል አስገቡና እያወዘወዙት "ዕረፍት የምትፈልጊ ከሆነ ፣ የምረዳሽም ነገር ካለ ሳትፈሪ በግልፅ ንገሪኝ ። የአለቃና የፀሀፊ ግንኙታችን በስራ ላይ ብቻ ነው ። በተረፈ እንደቤተሰብሽ አባል እንደ አንዱ ልትቆጥሪኝ ትችያለሽ" አሏትና አቀረቀሩ ።

ዛሬ ያለወትሯቸው ይህንን የተናገሩበት ሁኔታ ግራ ገብቷት እያሰላሰለች እያለ "ቤተሰቦች አሉሽ?" አሉና ከሃሳቧ አወጧት ።

"አዎ አሉኝ ።"

"ትጠይቂያቸዋለሽ?"

አትማማች ። አብራቸው እንዳለች ልትነግራቸው ፈለገች ። ደግሞ 'ለምን?' ሊሏት ነው ። እንደአገባች ያውቃሉና ።

"አዎ!" አለች ከሀሳቧ እንደወጣች ተቻኩላ ።

አለቃዋ እያትማሙ ዝም አሉና በመስኮት ዝናቡን ተመለከቱ ፣ እያባራ ነው ። "ዝናቡም ማቆሙ ነው መሰለኝ" አሉ ጐናቸው የተቀመጠውን ሳምሶናይት ይዘው እየተነሱ ፣ እፀገነትም ማሰናበታቸው መሆኑ ገብቷት ወደ ቢሮዋ ሄደች ። የአላቀዋን ሁኔታ እያሰላሰለች ።"

* * *

ሄኖክ በየደቂቃው ሰዓቱን ይመለከታል ። ሌላ ቦታ የተቃጠርን መስሏት ይሆን ይላል ፣ ሀራምቤ ሆቴል የምግብ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጠ። አዳዲስ እንግዶች ወደ ሆቴሉ ይገባሉ ። ዘበኛውም በጥንቃቄ በሩን ይከፍትላቸዋል ። በአብዛኛው ጥንድ እየሆኑ ወደ ሆቴሉ ይጠልቃሉ። እፀገነት ግን የለችም ።

ያለወትሮው ሲጋራ አሰኘው ። አጠገቡ ካለው ቡና ይልቅ አልኮል ቢሆን መረጠ ። እጆቹን ከዕለቱ ቆፈን ለማላቀቅ አሻሸና በመሰላቸት የመነጨውን ማፋሸክ በመዳፉ ሲከልል እፀገነትን አያት ። የተቀመጠበትን ስፍራ መለየት ሲደነጋገራት አይቶ እጆቹን አወናጨፋቸው ። ተመለከተችው ።

በማርፈዷ የሰጠችው ምክንያት በቂ ቢሆንም፡ አላረካውም ። እሷም ደስተኛ አትመስልም ። ዛሬ የጀመራት በሽታ አይደለም ። ቤቷን ትዳሯን ካጣችበት ጊዜ ጀምሮ ደስታ ከእጠገቧ ርቋል ። ሁሌ ራሷን ሕይወቷን ከማከካኖፊው ጃኩሊን ጋር ታነፃፅራለች ። ልዩነት ያለ ቢመስላት የፀልጅ አለመውለድ ነው ።

Scanned with CamScanner

በሄኖክ መደሰቷ እየጨለመ መጥቷል ። አንድ ነገር ይጐለዋል ። የጐደለው ነገር ምን እንደሆነ አይገባትም ። ብቻ ይጐለዋል ። ከንፈ ገኙ፣ እየሰረቀች ስታገኘው ሄኖክ ፍፁም መስሏት ነበር ። አሁን ግን ብዙ ነገር ይጐለዋል ። ሄኖክ በፍፁም ከንፈን ሊሆንላት አልቻለም ። በጊዜ ቁርኝት የተዋሃደው አንድነታቸው ፡ በቀረ የትዝታ አሻራና የአፍላነቷ ወሲብ ትዝታ ተገንድሶ የተገነጠለ የሚመስላት ትዳሯን በፍፁም ሄኖክ ምሉዕ ሊያረገው አይችልም ። በትዳሯ እያለች ከሄኖክ ጋር ሲያቅበጠብጣ ት በነበረው ነዲድ የወሲብ ፍላጐት ትዳሯን እርግፍ አድርጋ ከተወች በኋላ በብዛት እንደተሳሰ ማር እራት እራት አላት ። ቀድሞውኑ እንደፈራችው ከሄኖክ ያቆራኛት ፍቅር ሳይሆን ፡ ባዶ ስሜትና ርካሽ ወሲብ ሆኖ አገኘችው ። ያም የስሜት ሰፈፍ እያናወጠ ወስዷት እጅግ ቀዝቃዛ ህይወት ውስጥ ጨመራት ። ያ ቀዝቃዛ ህይወት እጅግ አስገለጣት ። ከስሜት ሙቀት በቀር አንዳች ነገር በአጠገቧ የለም ። ከዛን ወቅት ጀምሮ ህይወቷ በሀዘን እንደተሸበበ ፡ መንፈሷ በቁም ምሬት እየተኮማተረ ፡ ከፊቷም የፈካ ገፅታ እየጠፋ ሄደ ።

የጠጣውን ቡናና የእሷንም የማኪያቶ ሂሳብ ከፍሎ ከሆቴሉ ይዟት ወጣ ። ወደ ቤቱ እንዲሄድ ያቀረበላትን ጥያቄ አልተቀበለችውም ። ከመጀመሪያ የአዳራሽ ወቅት ጀምሮ ቤቱን ጠልታዋለች ። የትዳሯ እንቅፋት መስሎ ታይቷታል ። ከዛን ወዲህ ቤቱ አንድ ጊዜ ብትሄድም አልተደሰተችበትም ። ከጥንት ጀምሮ የማትወዳት የምትመስላት አዜብን ማየት አትፈልግም ። ስለዚህ በምርጫው አልተስማማችም ።

ሄኖክ የሆቴል ቤት መኝታ አይወድም ። ባሬ ግን እማራሮ ስለሌው፡ ወደ አንድ ሆቴል የመኝታ ክፍል ይዟት ገባ ። የክፍሉ ዕዳት የተሟላ ነው ። አነስተኛ የመታጠቢያ ሻወርም አለው ። ክፍሉን ቃኝቶ ሀሳቡን ወደ እወገነት ሰበሰበና ሊያጫውታት ሞከረ ። ጨዋታዋ ሁሉ ካንገት በላይ ነው ። አንዳንድ ጊዜ፡ አተኩራ ታየዋለች ። ይሄን ጊዜ ይፈራታል ። እሷም ለምን እንደምታተኩርበት አይገባትም ። ከፉውም መጥፎም በሀሳቧ አይወጣም ፡ ግን አንድ ነገር እንዲያውቅ ትፈልጋለች ። አትኩራም ታየዋለች ። ምንም ።

የበፊት ልማዱን ጀመረ ። ልብሷን ራሱ አወላለቀላት ። ሌላ ጊዜ

ይሀን ሊያደርግ ፡ ፍፁም ደስታና የስሜት ሲቃ ይሰማት ነበር ። በሃላፊ ልብሷ በቶሎ ወልቆ እንዲያልቅ...ተመኘች ። ራሷን እየኮነነችና እንደር ከሽ ሴትም እየቆጠረች እያለች ልብሷን አውልቆ አልጋ ውስጥ አስገባት ። አንደ መጥሮው ትንፋሹ እየተቆራረጠ ይስማት ጀመር ። መላው ሰውነቷን እየደበሰ ፡ ሙቶቿን ወገቧን በጎኑል እየተጫነ ዋተተ ። አይኗን ብቻ ጨፍና ዐዋ አለች ፡ ተስፋ አልቆረጠም ። በምላሱ ከንፈሯን ምላሷን ፡ ላንቃዋን ሁሉ አዳረሰ ። ሌላ ጊዜ ይህን ስእት አቃስታ ሰውነቷ እየተናወጠ ጨኸት ብቻ ነበር የሚተራት ፡ አሁን ግን ትንፋሿ እንኳን አይሞቅም ። ተናደደ ። ቀና ብሎ ተመለከታት ። አይኗን ጨፍና የምታሾፍ አሻንጉሊት መሰለችው ። በጥፊ አላሳት ። ደንግጣ ስታየው ትልቅ ሰይጣን አላይዋ ላይ የተከመረ መሰላት ። ገፍትራው ተነስታ ልብሷን ትለባብስ ጀመር ።

ቤተሰቦቿ ቤት የደረሰችው እየተጣደፈች ነው ። መንፈሷ ተናውጠ ሰላሟ እጅግ ደፍርሷል ። ቤት ስትገባ ማንንም አላናገረችም ። እየተቻኮለች ወደ መኝታ ቤቷ ገባች ። መኝታ ቤቷ የቆያት ሁናቴ እንደፈለገችው አይደለም ። ሙዚቃውን አስቱር ክልክ በላይ ታጮኸዋለች ። አጠፋችው። ገና ከመጥፋቱ በመስነቱ በኩል ከንሮ ተቀምጣ ስለነበር “ማነው? ብላ አምጿቸዋች ። እወገነት መልስ አልሰጠቻትም ። ራስጌዋ ያስቀመጠች ውን መፅሀፍ ቅዱስ ይዛ ወጣች ። አቅጣጫዋን አልመረጠችም ። በደመነፍስ መፅሀፉን ይዛ ባጭ ቤት ገብታ ፡ ከውስጥ ቆለፈች ።

የሀጢያትዋ ንድፍ በሙሉ በእንባዋ ታጥቦ ይነፃ ይመስል መፅሀፍ ቅዱሷ ላይ በግንባሯ ተደፍታ ተንሰቀሰቀች ። በልጅነቷ የምትወደውን የአምላክን የመጨረሻ ጣር በቃሏ ደገመች ።

‘ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ’

አልተረጋጋችም ። የባሰ ትነፋርቅ ጀመር ። ራሷን እንደርኩስ እየቆጠረች ፡ ነፍሷን ሲአል እንደ ወረደች በደለኛ ነፍስ እየተመለከተች ፡ መንፈሷን አደከመች ፡ የሀጢአቷ መደራረብ የበዛ መሰላት ። ሰባኪው ያነበበላትን የሐዋርያው ጳውሎስን ቃል አስታወሰች ። ትንሽ ስትረጋጋ መፅሀፉን ገልጣ መፈለግ ጀመረች ። አገኘችው ‘ሚስትም ከባልዋ አትለያይ ፡ ብትለያይም ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባሏ ትታረቅ’ ልባ ሽብር አለ ። ሀጢያቷ በዝቶ መሸከም ያቅታት መሰላት ። የባሰ ተጨነቀች። አዕናኝ የመሰላት የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል በደሏን እያጐላ

Scanned with CamScanner

መንፈስን በስቃይ ወጠረው ። የመፅናኛ ቃል ፍለጋ ለማንበብ የመፅሀፍ
ቅዱስ እውቀት አናሳ ነው ። እንዳውም ሰሞኑን በተከሰተው አጋጣሚ
ነው አንጂ መፅሀፍ ቅዱስ የት እንዳለም አታውቅም ነበር ። ድሮ
የአንደኛና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበትበት ወቅት
ትማርበት ከነበረው የካቶሊኮች ትምህርት ቤት መጠነኛ የመፅሀፍ ቅዱስ
እወቀት ገብይታለች ። በተረፈ ባለ በሌላ ነፍሷ ትዋትታለች ። በምትኩ
ግን የመፅሀፍ ቃል ያሸብራት ጀመር ። በልቦናዋ ጥልቅ ዐሎት አደረበትና
ባሟውን ከፍታ ወጣች ። ቀጥታ የሄደችው ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል
ስልክ ነው ።

ቤተሰቦቿ እንደወትሮዋቸው እንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ
ተሰባስበው ቡና ይፈላል ። ሁሉም ቦታ ቦታውን ይዟል ። ትጠበቅ
የነበረችው እሷው ነች ። ይህንን ሁሉ አልተገነዘበችም ። ወደ ስልኩ ሂዳ
ከነቀለችው በኋላ ለብቻዋ ልትሆንና ልትነጋገር የምትችልበት የወላጆቿ
መኝታ ክፍል ይዛው ገባች ። ወዲያው የምትፈልጋቸውን ቁጥሮች
አሠረች።

የደወለችው መጀመሪያውኑ ጀምሮ ተከታታሉ የእምነታቸው
ተከታይ ያደረጋት የመስሪያ ቤቷ ሰው ጋ ነው ። ችግሯን በመጠኑ በስልክ
አወያየችው ። የምታነባቸውን ጥቅሶች ነግሯት ዛፈች ። ማታ ማታ
በሳምንት ሶስት ቀን መጠነኛ የምስጋና ፕሮግራም እንዳላቸውና በዛም
ስብሰባ ላይ እንድትገኝ ጋብዟት "ይባርክሽ" ብሎ ስልኩን ዘጋው ።

የሰጣትን ማስታወሻ ተመለከተች ። 'የማቲዎስ ወንጌል ምዕራፍ
አምስት ፡ ከሶስት እስከ አስር' ይላል ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፉን ፈልጋ
አወጣች ። 'በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁአን ናቸው ፡ መንግስተ ሰማይ
የነሱ ናትና ። የሚያዝኑ ብፁአን ናቸው ፡ መጽናናት ያገኛሉና ። ዕድኅን
የሚራቡና የሚጠሙ ብፁአን ናቸው ፡ ይጠግባሉና ። የሚማሩ ብፁአን
ናቸው ፡ ይማራሉና ። ልበ ንፅሆች ብፁአን ናቸው ፡ የእግዚአብሔር ልጆች
ይባላሉና ። ስለዕድቅ የሚሰደዱ ብፁአን ናቸው ፡ መንግስተ ሰማያት
የእነርሱ ናትና' በመጠኑ ተረጋጋች ። የሚቀጥለውን ጥቅስ ተመለከተች ፡
የማቲዎስ ወንጌል ምእራፍ ስድስት ከሃያ አምስት እስከ ሰላሳ አራት
አነበበች ። የመጨረሻው ቃል በይበልጥ ደስ አላት 'ነገ ለራሱ
ይጨነቃልና ፡ ለነገ አትጨነቁ ። ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል ።' ደግማ
ደጋግማ አነበበች ።

በተሰጣት ጥቅስና ባነበበቻቸው ቃላት ሁሉ ተደሰተች ። 'እመን
ብቻ እንጂ አትፍራ' የሚለው ቃል በይበልጥ አፅናናት ። 'በእርግጥ...'
አለች የተሰጣትን የመጨረሻ ጥቅስ የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት
ቁጥር ሰላሳ አንድን አንብባ ' በእርግጥ ጌታ ክርስቶስ እንደኛ አይነቱን
ሀጥአን ሊሰበስብ እንጂ ፃድቃንን ሊጠራ አልመጣም' ደስ ተሰኘች ።
ሰባኪው ሲል ሰምታዋለች ፡ 'በጌታ ደስ ይበለን ፡ ሁሌም እንይሰት ።'
መንፃት አሁን የሆነ ያክል ተሰማት ። አንዳች መንፈስ ውስጧን
ሲያለብሰው ተሰማት ። መጽሐፉን አጥፋ ደስ እያላት ከቤተሰቦቿ ጋር
ተቀላቀለች ።

ቡና እየተጠጣ ትዝ ያላት ኤርምያስን አለማግኘቷ ነው ። ድንግጥ
አለችና የቀመሰችውን ቡና ቁጭ አድርጋ ውልቅ አለች ። አባትና እናቷ
ተያዩ ። እህቷ ብቻ ትሰቃያለች ። 'ጨንጨ ሆና ነው' አለች በሁኔታዋ ግራ
የተጋቡትን ወላጆቿን እየተመለከተች ።

"ይህን ነገር ጆሮዬ አይስማም" አሉ እናቷ ፊታቸውን አዙረው ።
እወነት የልቧን የተረዳላት አልነበረም ።
አባቷ ምንም አስተያየት አልሰነዘሩም ።

Scanned with CamScanner

ምእራፍ አሥራ ሦስት

ክንፈ በጅምር የቆመውን ቤቱን በአዘኔታ ይመለከተዋል። እንዲጠግቁ ያስቀመጣቸው ዘበኛ ስሞታ ደግሞ ታክቶታል። "ብርድ— ከ ገደለኝ... ሌባ አስቸገረኝ...ምነው ቤቱን ተዋቸሁት?፣ ገንዘብ ሚዳ ላይ ፈሰ ይቅራል እንዴ?" አሉት።

'የታደሉ ሽማግሌ' አላቸው በሆዱ፣ የደረሰበትን የተመሰቃቀለ ህይወት ባለማጤናቸው ይህንን መናገራቸው ሳያስከፋው። ግቢው ውስጥ በቆርቆሮ በተበጀች የዘበኛ ቤት ሲሚንቶውን፣ ብረቱን አጭቀው፣ ውስጥ ዳር ከዳር፣ ሜዳ ለሜዳ ሲሯሯጥ የሚያድረው መንጋ አይጥ ቆርቆሮውን በጢጠው ቁጥር አጠር ያለችውን ወፍራሟን ፈሮ ጨብጠው "ማነህ" ሲሉና መልስ ሲያጡ የሚያላልፉት የስቃይ አዳር እየታከታቸው ሄዷል። በወር የሚጥልላቸው ገንዘብ ደግሞ በየቀኑ ለብርዱ ብርታት እንድትሰጠኝ እያሉ ከሚጎነጩት ጠጅ አላልፍ እያለቻቸው፣ ሲላት ደግሞ ለውሃውም ቢሆን ወር አላደርስ እያለች ታበሳጫቸዋለች። ለሷ ግን ዘዴ ዘይደዋል። ለቤት መሥሪያና በኋላም ለቤቱ ግልጋሎት እንዲውል ታስቦ አስቀድሞ የገባውን የቧንቧ ውሃ በቅርብ ላሉ ሰዎች በስርቆሽ እንደበና ውሃ መቸብቸብ ጀምረዋል። በቀን ለጠጁ መደጎሚያ የሚሆን ሽርፍራፊ ሳንቲም ያገኛሉ።

"እሺ፡ ግዴለም። ሁሉም ስራ ከሰሞኑ ይጀምራል" አላቸው፣ የቤቱን ሥራ የመቀጠል እቅድ ባይኖረውም ለአፉ እንዳይቀር ያህል፡ የተናገረው ነበር።

ብቻውን እያጉረመረመ የወር ደሞዛቸውን ሰጥቶ ተሰናብቷቸው ወደ ቮልስዋገኑ አመራ።

ኑሮ ሲንሷሷት ናት። እንደልብ ላለማራመድ ቀፍድዳ ትይዛለች። በተለያየ ማኅበራዊ ቀለበት የታበተ ሰው እሱነቱን እንዳሻው ለመግለጽ አጋጣሚዎች ይጠብቃል። እናም በዚሁ ጊዜ በራስ ፍላጎትና ስሜት ሳይሆን፣ እንዲያው በደመነፍስ ይኖራል። የመኖር ትርጉሙ ምን እንደሆነ ማሰብ አያሻም። ይህንን ሁሉ ሰንሰለት በጣጥሶ ባሻው መንገድ መጓዝ የሚችል ሰው አንድም እብድ ነው፣ ያለዛም መንገዱ አጭር፣ ትልሙም

ዘመዱሁ የሚቋጭ ይሆናል። እኛነታችንን ጠብቀን፣ ተሳካም አልተሳካ የዓላማችንን ግብ ከማጎበረሰቡ የኑሮ አዘቅት ውስጥ ለውሰንና በውስጡም ሆነን እኛነታችንን መፈለግ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። ይህንን ኃይል ነው ክንፈ ለመቀበል የሚታገለው። ሕይወት ምርጫ የላትም። በሕይወት ውስጥ ግን ብዙ አማራጭ የኑሮ መስመሮች አሉ። እናም በየደረሰበትና ባጋጠመው የኑሮ እርከን ውስጥ ቅድሚያ መስጠት ያለበት ለራሱና ለህልውናው ዋስትና ነው። አንዳንድ ጊዜ የእፀገነትን ከሱ መለየት መቀበል የሚያቅተው ጊዜ አለ። ግን እውነት ነው። በተለይ ለምን እንደተለየችው ሲያውቅ ጭራሽ ራሱን ጠልቶ ነበር። በራሱ የነበረው ብቃትና እምነት ጥለውት ኮበለሉ። ህይወቱ በርካሽ የኑሮ አዘቅት ውስጥ ልትዘፈቅ ስታጣጥር አዜብ ደርሳ ዋጀቻት። እንደገና ከዕው ጋ የህይወት አፍታ ይቃመስ ጀመር። ወደ ተረጋጋው እሱነቱ ቀስ በቀስ አዘገሙ፡ ቤቱን ንብረቱን ያስታውስ ጀመር። የህይወት ውጥኑ ሁሉ ሳይዘነጋ ሊፈፅም ወሰነ።

የመጀመሪያ እቅዱ ጅምር ቤቱ ነው። ውጥኑን ለሁለት ተረዳድተው ሰርተው ለመጨረስ ነበር። ያ አልሆነም። ስለዚህ ያቅሙን ያህል ብቻውን ሊምክር ወሰነ። መቼ እንደሚጀመር እርግጠኛ አይደለም። ቢሆንም የቤቱን ጅምር መጥቶ መቃኘቱ የመጀመሪያ የመንደርደሪያ እርምጃ አድርጎታል። ቤቱን ቃኝቶ እንደተመለሰ በቀጥታ ያመራው ወደመኖሪያ ቤቱ ነው። ቤቱ እንደገባ ያጋጠመው ያልጠበቀው ሁኔታ ነው።

መኪናውን አቁሞ ሳሎን ወዳለው ፒያኖው አምርቶ የሚወዳትን የድሮ የኤልቪስን ዘፈን እየተጫወተ ሳለ የቤቱ ነባር ሰራተኛ ብርቁ ብቅ አለችና

"ጋሼ!" አለችው። አልሰማትም። በሙዚቃው ተመስጦ ነበር። ደግማ ጠራችው።

ከፒያኖው ላይ ቀና አለ። ጣቶቹም መምታታቸውን አቆሙ። "አቤት!" አላት የምትለውን ብላ እንድትሄድለትና ሙዚቃውን ለመቀጠል ቸኩሎ።

"ሠራተኛ ይፈልጉ።"

'ቋሚው?' አላት ደንግጦ።

"አይ..." አለችና ትንሽ አቅማማች። ቀጥላም "እንዲሁ ነው

Scanned with CamScanner

ሠራተኛ ይፈልጉ።'' ግራ ገባው። ''ምን ሆነሻል ብርቁ ቅር ያለሽ ነገር አለ?''

''ኧረ የለም...'' አለችና አውንም የእጇን ጥፍር እየቁነጣጠሰች ተወዛወዘች። ''ግዴለም ንገሪኝ። ደሞዝ አነሰሽ?''

''በቂዬ ነው ግን...'' ተጨነቀች ''እኔ ሴት የሌለበት ቤት ሰርቼ አላውቅም። ምኑን ከምን እንደማደርግ ግራ ይገባኛል። እና ሰው ይፈልጉ፡ ክንፈ ብልጭ አለበት። 'አንቺ ሴት አይደለሽም?' ሊላት ፈለገና ተወው። ''አስብበታለሁ'' አላት ከወትሮው ቅላፄ ድምፁን ቆጣ አድርጎ። ብርቁ ትንሽ አቅማማችና ተመልሳ ወጣች።

ጊያኖ ጨዋታውን አልቀጠለም። እጆቹን እያወናጨፈ ከበርኩማዋ ላይ ተነሳ። እንኳንስ ሰራተኛው ሄዳ እዐገነት ከሄደች ወዲህም የቤቱ ጭርታ ሊገድለው ደርሷል። ይሽንን ሁሉ ማሰብ አስጠላው። በአእምሮው የመጣው፡ የቦሴ ቤትና የውስኪው ብርጭቆ ነው...ወደዚያው አመራ።

ፍፃሜዎ ማለቁ ላይቀር ይህች አጭር ህይወት ስቃይዋ በዛ። ለወትሮ በትንንሽ የህይወት አሽክላዎች ነፍሳችኝ ተሸራርፋ ታልቃለች፣ ለዛውም አልፋና አሜጋ ለሌለው የኑሮ ብክነት።

ቦሴ ቤት ሲደርስ የመኪናውን መሪ በቡጢ ነረተና ከመኪናው ወረደ።

* * *

አዜብ ከሄኖክ ጋር ከመምጣቷ ጀምሮ ለረጅም ሰአት ተጨቃጨቁ። አሸናፊና ተሸናፊው ሳይለይ ሁለቱም ወደየመኝታ ክፍሎቻቸው አመሩ። ሄኖክ ሲገባ ትንሽ ሞቅ ብሎት ነበር። በዛ ላይ በእዐገነት ነገር ተበሳጭቷል። ለትንሹም ለትልቁም ቁጣው ያይላል። ከአዜብ ጋር ያጣላው ግን መሰረታዊ ነገር ነው። ገና ከመምጣቱ የህይወቱን መስመርና አቅጣጫ በተገቢው መንገድ እንዲቀይስና እንዲመራ የተናገረችው ግልፅ ባይሆንም ሁለቱም በመሃከላቸው ያስቧት የነበረው እዐገነትን ነው። በተጨማሪ እንደዚህ ሰክሮ ልታየው አትፈልግም። ታናሽ ወንድሟ በመሆኑ እንደትንሽ ልጅ ታየዋለች። በዛ ላይ ደግሞ ሞቅ ብሎት ወይ ሰክሮ ካቸው የአባቷ ምስል በሀሊናዋ ድቅን ይልባትና ሰላም ያሳጣታል፡ ያንዣንጫታል።

ሄኖክ ቤቷን ለቅቄላት እሄዳለሁ በሚል እልህ ተወጥሯል። እሷ ደግሞ ወደፊት ሊያጋጥመው በሚችለው ኑሮ ውስጥ በሃሣቧ እየዳከረች

ትጨነቅለታለች። በሁለት ተቃራኒ አቅጣጫ የሚጓዙ ሰዎች ሆነዋል።

የጊዜ ዝግመት፡ ፍጥነት፡ ንጋትና ምሽት በአዜብ ህይወት ውስጥ ቦታ አጥተዋል። ይመሻል። ይነጋል። ወራት ቀናቸውን ይቆጥራሉ። የሳምንቱ ቀናትም እንደዚሁ፡ ሀሳቧ የተበታተነ ሆነ። የረጋ መንፈስ የላትም። ለራሷ የምትሰጠው ጊዜ አነስተኛ ነው። ስለ ክንፈ፡ ስለሄኖክና እዐገነት እንዲሁም እንዲሁ ባልጠበቀችው ሁኔታ ግንኙነታቸው ስለተቋረጠው ስለ ሲራክም ታስባለች። ከዚህ የተረፈቻትን ጊዜ ደግሞ ለፈጠራ ሥራዋ ታውለዋለች። እንደራሷ. ስብዕና ታየውና ታከብረው በነበረው የሥነልቦና ጥናት ትኩረት፡ በሥራ ሰዓት በምታገኘው ጊዜ ከመፅሀፎቹ ጋር የራሷን ግንዛቤ እያሩሩመች ትጦዛለች። አንዳንድ ጊዜ የስነልቦናዊ ጥናት ልምዷ ከፈጠራ ሥራዋ ጋር እየገጠመ ሲሰምርላት መንፈሷ በሃሴት ይወራጫል። ስለህይወት ጥሩ ትቀኛለች። ያኔ ህይወት ለሷ ብርቅ ስጦታ ትሆንባታለች። ታዲያ በመሃሉ እንቅፋት አታጣም። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ክንፈ በሐሳቧ ድቅን ይልባታል። ያኔ ሁሉ ነገር ያስጠላትና ከሱ ጋር መሆን ትመርጣለች። ባትሆንም ስለሱ ማሰላሰል ትወዳለች። 'የሚያገረሽ ፍቅር አደገኛ ነው' አለ፡ ትልና በራሷ ትተርታለች። አውንም መልሶ ህዘን የሚገባት የወደፊት መንገዳቸውን፡ የድርጊት ፍፃሜያቸውን ስታስብ ነው። ያኔ ህይወት በድዷ ትስቅባታለች። ወጣት የሆነችው አሮጊት...ሙቱ ተገዘታባ...ከዚህ መእት የሚያድናት አይኖርም። ብቻዋን ትተባሻር ራለች።

ለምን እንደሆነ አታውቅም። በነዚህ ክፉ ሰአታት ሲራክን አታስታውሰውም። አንዳንዴ ሆን ብላ ስታስበው የመለያየታቸ ምክንያት ክንፈ አይመስላትም። አጋጣሚ ሲጠብት የቆየ ጉዳይ መስሎ ይታያታል። 'በፍፁም ማንኑቱን ሊረዳ ያልቻለ ሰው' ትላለች፡ በሃሳቧ ሲራክን አድርጋ እየቆጠረች። በተለይ በመጽሐፍ 'እንደምታነቢያቸው ቁጀሮች መኪናዬ ጀጉዋር ስላልሆነ...አድኬንቸሪስት ስላልሆንኩ' ያላት የመጨረሻ ታሉ አንጀቷን ቆርጦታል። ብኩን ህይወት ትልሚም አሳቧም ብኩን ነው እያለች። ያም ሆነ ይህ፡ የተፈጠረው አጋጣሚ አለያይቷቸው ቀርቷል።

ሁሉን ትታ ከገፀ ባህሪያቱ ጋር ትንቅንቅ ያዘች። ውጣ አልወጣም፡ ተናገር አልናገርም፡ በተለይ ደግሞ ያስቸገራት ውስጣዊ ማንነታቸውን ፈልፍሎ ማውጣት ነው። በብእሯ የነደፈቻቸው የእያንዳንዱ ገፀባሕሪያት ውጫዊ ማንነት ሳይሆን፡ እነሱነታቸውን በጥቅል የሚመረምረውን

Scanned with CamScanner

ስነልቦናዊ ህይወት መዳሰሱ እርካታ ይሰጣታል። ባህሪይ ከባህሪ እየተሳ
ከረ ከታሪኩ ግጭት ይልቅ በራሳቸው ማንነት ህይወት መጫወት ይበልጥ
ያረካታል። የሚያናድዳት ግን ስታሳድዳቸው ሲሸሿት፣ ልትይዟቸው
ስትል ሲያመልጧት፣ ተሳክቶላት ብትይዛቸውም ውስጣዊ ማንነታቸውን
ለመፈልቀቅ ስትይዝ፣ ሲበረቱባት፣ አቅቷት ስትተው፣ በድንነታቸው
ልፋቷን ሁሉ መና ሲያስቀሩት ደግሞ እልህ ይይዛታል።

'እንኳን በብእር የተፈጠሩ ገፀባሕሪያት ይቅርና በህይወት ያሉ
ለዎችንም ስነልቦናዊ ህይወት መፈልፈል አስቸጋሪ ነው' ይላታል ሀሳቧ፣
ብላ፣ ደከማ አቅቷት በሃሣብ ማዕበል ስትናወጥ።

''እና ምን ይሻላል?'' ትላለች የምታደርገው ግራ ገብቷት። ዝም ብላ
እንዳትፅፋቸው ውስጣቸው ያልታየ ገፀ ባሕሪያት በድን ይሆኑባታል።
ራሳቸውን ችለው አይቆሙም። ይልፈሰፈሱባታል። ግልፀት የሌለው
ብእር የማያውቀውን እንደመፃፍ ሆኖ ይሰማታል። የምታውቀውን
ለመግለፅ ደግሞ ብእሯን ስትጨብጥ ገፀ ባሕሪየቱ ማንነታቸውን ይደብቁ
ባታል።

'ድርሰት የገሃዱ ዓለም ነፀብራቅ አይደለም!'

'እና?'

'አይግረምሽ! በገሃዱ ዓለም ያሉ ሰዎች ስነልቦናዊ ህይወታ
ቸው ግልፅ—ኮ አይደለም። ስውርና ምስጢር አዘል ነው። ያንን
ለማግኘት ታላቅ ልፋትና ጥረት ይጠይቃል።'

'ቢሆንስ' ትላለች እልህ እየያዛት።

'ቢሆንስ ብሎ ነገር! በቀላሉ መግለፅ አትችይማ! ልፋትና
ጥረት ይጠይቃል።

'እንዴት ራሴ የፈጠርኳቸውን ገፀ ባህሪያት ማንነት ማወቅ
ይሳነኛል?'

'ግዴለም እያደር ታውቂያቸዋለሽ። ፈጣሪም ፍጡራንን
ሲፈጥር ማንነታቸውን አስቀድሞ ቢረዳ ኖሮ፣ ተድሞውኑ በገነት
አያኖራቸውም ነበር።'

'እሺ፣ እሱስ ይሁን በድርሰት ውስጥ የምናፍቃቸው ሀቅና ውበት
የታለ? ቃላት እርቃናቸውን እየገጠጡ ከማስጠየፋቸው በቀር…'

'አይዞሽ እሱም ከገፀባህሪያትሽ ውስጣዊ ማንነት ጋር አብሮ
ይገለጣል። የአለማችን እውነትና ውበት የሚገኘው ከያንዳንዱ ሰው

ውስጣዊ ማንነት ነው። ያለዛ የገፀ ባህሪያቱ ውበትም ሆነ እውነት
መሠረቱ ቢስ ነው።'

እንደገና ትግል ትጀምራለች። በመጠኑ ይሳካላታል። ቃላት ከቃላት
እየለመረ ገጠው ማስቀየማቸው ቀርቶ በደምና በስጋ ተሞልተው ሲንቦለ
ቦሉ…ክንፉ ደግሞ ብቅ አለ—በሐሣቧ፣ አልተናደደችም።

አንድ ነገር ጭንቅላቷን መታት። የምትጽፈው ገፀ ባህሪ በተለይ
አንደኛው፣ የክንፉን ባህሪይ በመጠኑ ተጋርቷል። ግራ ተጋባች። እንደገና
ገፀባህሪዋን መረመረች። አመነታች፣ ነው?—አይደለም!

ጣጣ ነው! ገፀባሕሪ ከገሃዱ አለም ሲሳከር መጨነት፣ ደግሞ ከገሃዱ
አለም ያፈነገጠ የመሰለ እንደሆነ አሻንጉሊት እየመሰለ ግጥም!

ጀርባዋን አመማት። ከማጅራቷ ይጀምርና መሃሉን ይዞ እስከመቀ
መጫዋ ድረስ ድንዝዝ ብሎ አንደመርፌ ጠቅ ያደርጋታል። ጡንቻዎቿ
እንደተዳከሙ ታወቃት። ሰአቷን ተመለከተች፣ ሳታውቀው እኩለ ለሊት
አልፏል።

መድረስ ጭንቅ ነው። በአካልም በመንፈስም መሰቃየት። ከመቀመ
ጫዋ ተነስታ ሰውነቷን አንቀሳቀሰች። 'ይሄኔ….' አለች በሃሳቧ፣ ጥሩ ባል
ቢኖራት አልጋው ሞቆ ይጠብቃታል። እናም እንዲህ ሲደክማት አልጋው
ይናፍቃት ይሆናል እንጂ እንዲህ እንደ ሬሳ ሳጥን መንፈሷን አይጫነ
ውም። ተንከባካቢ ባልም ቢገኝ ቡናውን ጥዶ ያጠጣታል።

ሁለተኛው አሳቧ አሳቃት፣ የወንድ ትምክተኝነት በተጠናወተው
ማኅበረሰብ ውስጥ በርግጥ ይህንን ማሰብ ያስቃል። መተሳሰብ ግን ወንድ
ሴት አይልም። እንዳውም ሴት ልጅ ራሷ ተፈጥሮ ለእንክብካቤ አመቺ
እንድትሆን አስተካክሎ የፈጠራት ትመስላለች። የወንድ ትምክህት
ጋረደው እንጂ።

'አበባ ውበት አላት። ያም ውበቷ እንዳይጠፋ ተንከባካቢ ያሻዋል።
ያለዛ የውበቷ እድሜ አጥሮ ጠውልጋና ከስማ ትጠፋለች። ሴት ልጅም
አበባ ናት። ውበቷን የሚያጣጥምና የሚንከባከብ ወንድ ያሻታል። ያለዛ
እሷም የአበባው ዕጣ ይደርሳታል።'

ሃሳቧን ትታ ከገሃዱ ዓለም ጋር ተፋጠጠች። ልታገኛቸው የምትፈል
ጋቸው ግን ያላገኘቻቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ሁሉም የገፀባህሪያቱ
ውስጣዊ ማንነት ያክል አያስጨንቋትም። አንድ ደራሲ ከድርሰቱ ሌላ
የሚፈልገው ቁሣዊ ነገሮች ቢኖሩትም በሁለተኛ ደረጃ ናቸው። ከድርሰቱ

Scanned with CamScanner

ሌላ ህልውና የለውም። ህይወትንም አያጣጥምም። ፈጣሪ ሱስ ነዉ፣ የማያረካ ሱስ…

‘ኤጭ! በቃላት ተቦጥቡጣ ያለቀች ነፍስ’ አለችና ሠፈው አልጋቀ ላይ በቁሟ ወደቀች።

***

ሽፈራው የቦሴን ቤት አርግፍ አድርጎ ትቷል። አልፎ አልፎ ብቅ ቢልም ቶሎ ይወጣል። የሚመጣው ያለምክንያት አይደለም። እዛ የምትሠራው ወዳጁን አስናቀችን ለማግኘት ሲፈልግ ብቻ ነው። በተረፈ እንኳን እሱ እያለ ባይኖርም እንደዛ አይነት ስራ ውስጥ እንዲመለከታትም ሆነ እንዲያስባት አይፈልግም። ስራዋን አስቁሞ ሊያስቀምጣት ገና አልተዘጋጀም። ያለበት አንዲት ጠባብ ክፍል እንኳን ሰው ተጨምሮባት እንዲሁም ጠባዋለች።

የምታደርገው አጥታ ነው እንጂ እሷም ይገባታል። ለመኖር ደግሞ መስራት አለባት። ለጊዜው ከዚህ የተሻለ ስራ አላገኝችም። የምታስቸግረው ዘመድ አዝማድ የላትም። የሚያፈቅራት እንጂ የሚያስቀምጣት ወዳጅ አላገኝችም።

ዛሬ ከምትሰራበት ከወ/ሮ ቦሰና ቤት በቀጥታ ይዟት የሄደው ወደ ጠባቧና ባለአንድ ክፍሏ መኖሪያ ቤቱ ነው። የቤቱን ቁልፍ ከፍቶ እንደገባ ተከትላው ገባች። አስቀድሞ ትንሽነቷንና አንድ ክፍል መሆኗን ቢነግራትም ይሄን ያክል ታንሳለች ብላ በፍፁም አልገመተችም ነበር። በመገረም ዙሪያዋን ቃኘቻት።

“ቁጭ በይ” አላት፣ የቤቱን ዙሪያ የምትቃኘውን ወዳጁን አስናቀችን እየተመለከተ።

“ቤቱ ፈረስ ታስጋልባለች አይደል?” አለ በመቀጠል መገረሟን ገፏ ላይ እያነበበ።

“በደንብ ብትያዝ ቆንጆ ክፍል ነች” አለችው ክስርዓት ውጪ የተለጠፉትን የግድግዳ ስእሎች እየተመለከተች።

ሽፈራው የገዛ ቤቱን እንደ እንግዳ አየው። ራሱን በራሱ ታዘበ። ቦታ አጥተው በየቦታው የተንከረባበቱትን ማንቆርቆሪያ፣ ሲኒ፣ ማንኪያ የመሳሰሉትን እንኳን በወጉ ማስቀመጥ አልቻለም—‘ሴላው ቢቀር ሰው ከማምጣቱ በፊት እንኳን መስተካከል የሚቻሉ ነገሮችን ስናራ ባስይገ’አለ በሃሣቡ ።

ብዙ በመቆጨት ጊዜ መግደል አልፈለገም። የደረሰበትን ነገር ይቀበላል—ሽፈራው። “ሻይ ላፍላልሽ?” አላት በሷ ትይዩ አልጋው ላይ ተቀምጦ። ቤቱ ሴት ይዞበት ሲመጣ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው ነው። ምን ዘምን እንደሚያደርግ ጨንቆታል።

“ምንም አልፈልግም” አለችው።

“ወይ የምትጠጪው ቢራ ላስመጣልሽ?” አላት፣ ይህንንም አስቀድም ማዘጋጀት እንደነበረበት እየታሰበው።

የተነሳውን እንዲቀመጥ እያከላከለችው “የለም አልፈልግም። ለስራዬ ብዬ የምጠጣውም ጤና ነስቶኛል፣ እንኳን ተጨምሮበት” አለች ፡ ምሬታ ፊቷ ላይ እያስታወቀባት።

ቆንጆ ናት። በተለይ የደም ግባት የሚሉት ነገር በሷ ላይ ጎልቶ ይታያል። ለአፍታም ሆነ በእንክሮ ላያት የውበቷ ግልፀት ልብን ያሸብራል። የአቋሟ ምንነት ስሜትን የማነቃቃት፣ የበረደን የማሞቅ ወሲባዊ መስህብ አለው—ታጓጓለች።

ይህ ሁሉ ደግሞ በይበልጥ ጎልቶ የሚታየው አይኗ ላይ ነው። አይኗን አትኩሮ ላየው ሰው አንድ ነገር ሊረዳ ይችላል። ያም ሳትፈልግ ያጋልጣታል። ስለሚያጋልጣትም ሰዎች ይጓጉታል። በሰዎችም ላይ የምታሳድረው ጊዜያዊ የወሲብ ስሜት፣ ሰዎች ከወሲባዊ እርካታ በቀር ከሷ ሌላ ነገር እንዳይሹ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ ልቧ ዘወትር ለፍቅር ይጠማል። አፍቅሮ መፈቀርን ይሻል። አጋጣሚው ግን አልተገኘም። እሷም ለገንዘብ፣ ሰዎችም ለወሲብ ብለው አንዴ ቀሚፏን ከሚገልጡት ለፍቅር ሺ ጊዜ ብትገልጥላቸው አይቆጫትም። ለገንዘብ ብላ ወይንም ደግሞ አልጠግብ የሚል የሴስኝነት ባሕሪ ተቆራኝታት ሴተኛ አዳሪ አልሆነችም። ለዚህ አወያፊና አስከፊ የኑሮ ገፈት ተቋዳሽ ያደረጋት ወሬ ነው፣ ልቧን አነሳስቶ ‘በትንሽ ልፋት ፍላጐትን ሁሉ አርክቶ መኖር ይቻላል’ የሚል ከአዲስ አበባ ዘምቶ ገጠር ተጋኖ የተወራ ወሬ! አብርሮ አመጣት። ማንም ለተሻለ ኑሮ የማይጓጓ የለም። የማይመኝ፣ የማይተልም፣ የማይወጥን አይገኝም። ለሆነለት ይሳካለታል። ካልሆነም ያው ነው። ህይወት የደረሳትን የኑሮ እጣ ክፍል መረረም ጣፈጠም ተቀብላ ትኖራለች። እንኳን ኑሯችንን መፈጠራችንም አጋጣሚ አይደል!

ታዲያ ጥሎባት ለፍቅር የተመኘት አላገኘችም። ሁሉም መአዛዋን

Scanned with CamScanner

ጣእሟን እንደሸንኮራ አገዳ መጦና አጣጥሞ መልሶ ይተፋታል። አቅበጥ ብጦና አንጉቶ ሰላም የነሳቸው ውበታን በቀላሉ በገንዘብ ስለሚያገኙት አንቅሮ ለመትፋት ጊዜ አይወስድባቸውም። ያረክሷታል። ማንም ዲግሞ ፍቅርን ከርካሽ ቦታ ሲሸምት አይሻም፣ ረግጠው ያልፍታል።

ለምን እንደሆን አይገባትም እንጂ ብዙ ወንዶች ከተገናኟት በኋላ ይከፉባታል። ይሰድቧታልም፣ እንደጉድ ያንቋሽሿታል—ግራ ይገባታል። አስቀድመው ሊዘፍኑላት ሊሰግዱላት ዳርዳር ሲከጅላቸው ይውሉና ከእልጋው በኋላ ግስላ ሊሆኑባት በራሷ አንዳች ጉድለት ያገኙባት እየመሰላት ትሰቃያለች፣ ትላቀታለችም። ያንን ለማካካስ ወንዶቹ እንደፈለጉት ትሆንላቸዋለች። በዚህም እጅግ አድርገው ይንቋታል። ያንቋሽሿታልም። ሳይታወቃቸው ለካ ሁሉም ወንዶች የሰገዱለት ያመለኩበትን ውበት በቀላሉ ማግኘታቸው ያበሳጫቸው ኖሯል። እሷ ይህንን አትረዳም። እንኳን እሷ፣ ራሳቸው ወንዶቹ ይህንን መገንዘብ ያዳግታቸዋል።

በዛ ሀይወቷ ላይ የአንድ ቀን የሽፈራው ግንኙነት ወትሮ ከሚያጋጣማት የተለየ ይሆናል ብላ አልጠበቀችም። ቢሆንም ግን አማራጭ አልነበራትም። መኖር አለባት፣ ለመኖር ደግሞ መስራት፣ የስራ እጣዋ ደግሞ አካሏን መሸጥ ሆኖል። ተፈጥሮ ለውበትም ርህራሄ የላትም…አብራው አደረች። እሱ ከሌላው የተለየ ነገር አላደረገም። እንደሌላው በገንዘብ ስጋዋን ገዛ። ግን በአንድ ነገር ይለያል። ርህራሄ ነበረው። በእያንዳንዱ እንቅስቃሴው ይንከባከባት ነበር። ገላዋን እስኪያገኘው ብቻ አልነበረም። ካገኘውም በኋላ አመለከው። ወደደችው።

ፍቅርን ግን አልገመተችም ነበር። መውደድን ደጋግመው ካሰቡት ፍቅር ይሆናልሳ! ደጋግማ አሰበችው። አይኗ እሱን ይራብ ጀመር። ያ የፍቅር ጥንስስ እርሾ በሱም አድሮ ኖሮ እንደማግኔት አቆራኛቸው። እሱን ከቦሴ ቤት ሲያርቀው በፍቅሩ እየተለበለበች ትሄድ ጀመር።

ለሱ ስትል ከወንዶች ጋር መውጣት ትታለች። ግን አፋጠ የያዛት ነገር፣ መኖር አለበት። ለመኖር ደግሞ መስራት፣ ስራዋ…እሱ ደግሞ እስካሁን የኑሮ ዋስትና ሊሆናት አልቻለም። እና ተጨንቃለች።

ቤቱን ለማየት ያጓጓት አንዱ ምክንያትም ይሄ ነው። ለጋብቻው መዘግየት ያቀረበላትን የቤት ችግር አላመነችውም ነበር። ሌላ ሌላውን ጣጣ አስቀድመው ጨርሰውታል። አብሮ መኖር ሁለቱም የጓጉበት ሀይወት ነው።

"እዚህ—ጋ ነይ" አላት ሽፈራው አልጋው ላይ እንድትቀመጥ እየጋበዛት። አላቅማማችም። በቀጥታ ሄዳ ጎኑ ተቀመጠች። እጆቹን ትከሻዋ ላይ አሳረፈና ጉንጯን ሳመው።

"ሽፌ!"

"ወይ" አላት ወደጎን እያያት።"

አይኖቿን በቀስታ አንከባለለቻቸው። ያሳሳሉ "መቼ ነው እንድነት መኖር የምንችለው?"

"እንድ ቀን።"

መልሱ አላረካትም። "እኮ ያ ቀን መቼ ነው ሽፌ?" አይኖቿ እንባ እንዳቀረሩ ተመለከታቸው። "ያለሁበትን ታውቃለህ አይደል በዚህ ሁኔታ እንዴት ልቀጥል እችላለሁ ሽፈራው? ይታይህ! ያለፍላጎት በየጊዜው የምጋታቸው መጠጦች፣ በዛ ላይ ስራውን የምታውቀው ነው። ለስንቱስ እስከመቼ ምክንያት እየሰጠሁ እችላለሁ! ሁሉም በገንዘቡ የሚገዛው ዕቃ አድርጎ ነው የሚቆጥረን…" ንግግሯን ገታችው፤ መናገር እንዳትታት እንዲያውቅባት አልፈለገችም። እንደምንም ራሷን ተቆጣጠረችና "ሴትዬዋስ ቢሆኑ ደስ ይላቸው ይመስልሃል! እስካሁን አንተን ብለው እንጂ ፊት ከነሱኝ ቆይተዋል። እንዲያውም አንዴ 'የማንንም ቅምጥ የማስቀምጥ መሰላት ወይ፣ አንደኛውን ልጃገረድ ነኝ ትበልና ይለይላት' ሲሉ ሰምቻለሁ። እኔን ባይሉኝም ሌላ ማንንም እዛ ቤት ውስጥ እንደማይሉ አውቃለሁ። ይታይህ ሽፈራው ለምግቤና ለአንዳንድ ነገርስ ቢሆን እስከመቼ አንተን ብዬ አንተስ ለኔ ባክነህ ይዘለቃል! እባክህ ሽፌ ከልብህ አብሬህ እንድኖር ከፈለክ ጨክነን አንድ ነገር እናድርግ፣ ተደጋግፈን ጎጇችንን ማቆም እያቅተንም…" ዕንባዋ ከአይኗ ኮለል እያለ ይወርዳል።

ሽፈራው ነገር ሁሉ ተምታታበት። የሚያደርገው ግራ ገባው። በቦጵቃላት ሊደልላት አልፈለገም። ካለ ያለውን ማድረግ አለበት። አሁንም ሁሉን ተወና በቅድሚያ ማድረግ ያለበትን ለቅሶዋን መግታት ጀመረ።

ተረጋጋችለት። አሁንም ለውሳኔ አልቸኮለም። እየቀለደ አዘናጋት። እየደባበሰ አረጋጋት። እየሳመና እያሻሸ የሰውነቷን ሙቀት ጨመረው። የርሱም የውስጥ ሱሪ ሊፈንዳ ደርሷል።

በሁለቱም ውስጥ ውበት መንቀሳቀስ ጀምራለች። በየፊናቸው እየተሻሹ አንዳቸው አንዳቸውን ውጦ ለማስቀረት ይራቆታሉ። በእጆቹ

Scanned with CamScanner

እየተሳበ ቀሚሷን ሲሰበስበው ጭኖቿ የጋለ ብረት መስለው ፈጠጡ። ሲመለከታቸውም መቆጣጠር የሚያስችግር ከአቅም በላይ የሆነ ስሜት ያሳድራሉ። የውስጥ ሱሪዋ ያለ የሌለ ውበቷን ደብቆ ሊያስቀር ቃጥቶ የተነሳ ይመስላል፣ ያናድዳል። ወደታች ገሸለጠው…እሷም ብርቱ ኖሯ የሱሪውን ቁልፍ ከፍታ አዘጋጅታለታለች።

የደስታ ጣራ መለኪያ የለውም…የጥልቅ ሀዘን መለኪያም እልተፈጠረም…ሰዎች የምድርን ምስጢር ጠንቅቀው አላወቁም…ይቀራቸዋል። ገና ብዙ ይቀራቸዋል። በተለይ የውበት ጥልቀትን አካቶ የያዘ የወሲብን ጥልቅ ስሜት መግለጽ የሚችል አንዳች ቋንቋም ሰዎች ከቶ አልፈጠሩም…ምክሩ እንጂ አላገኙም።

* * *

ግልደው ወሮች መንፈላሳት ሲጀምሩ፣ አስቀድሞ የነቃው ሽፈራው ነው። ዞር ብሎ ተመለከታት፣ ጭው ያለ የሰላም እንቅልፍ ውስጥ ያለች ትመስላለች። ለሊቱን ያለእንቅልፍ ሲያስብ ሲያሰላስል ያደረው ሽፈራው ንጋት ላይ አንዳች ተስፋ በልቡ አድሯል። በላቲ መፍትሄ ባይሆንም ለጊዜው ሠኖለታል። ቀስ ብሎ ከአልጋው ተነሳና ልብሶቹን መለባበስ ጀመረ። አስናቀች ከእንቅልፏ ነቃችና? "ወዴት ነው ሳይነጋ" አለችው በሚነፋነፈው የማለዳ ድምጿ።

ሊነግራት ፈለገና መልሶ ተወው። "አንድ ጉዳይ አለኝ፣ ቶሎ ለመድረስ ነው" አላት የሸሚዙን እጅታ ቁልፍ ፈልጎ እየቆለፈ።

ከአልጋዋ ቀና ብላ በአባበጡት አይኖቿ ተመለከተችው። ደብዛዛው የጣሪያ አምፖል በፈታ ላይ ሲያርፍ አንዳች ስሜት ፈጠረባት። የሱ አይኖች ግን ጡቶቿ ላይ ፈጠጡ። አንሶላውን ጎትታ ጡቶቿን ከለለች።

"አንቺ ተኚና ቆዪ፣ እኔ ጉዳዬ ልድረስ" አላት በውስጡ የተፈጠረበትን ስሜት ለመደበቅ እየሞከረ።

አትማማች። ደግሞ የምትሄድበት የላትም። "ተመልሰህ ትመጣለህ?" አለች።

"ይረፍድብኛል፣ በዛው ስራ እገባለሁ። ስትሄጂ በሩን ቆልፈሽ ሂጂና ማታ ቁልፉን መጥቼ እወስዳለሁን እሺ?" አላትና አጠገቧ መጥቶ ጉንጯን ሳመው።

የውጪው ጨለማ ተገፎ ብርሃን ቢጻብሰውም የእለቱ ዳመና ከጸር ጸር ግጥም ብሏል። ከአድማስ አድማስ የተንሰራፋው ዳመና በመንፈስ ላይ

የመጫን ስሜት ያሳድራል። ብርዱ ደግሞ የፊት ቆዳ ሳይቀር ሰርስሮ ይገባል።

ሽፈራው ወደዋናው መንገድ እየተጣደፈ ወጣ። ለማኞች በያሉበት ድሪቷቸውን እያራገፉ ማዛጋት ጀምረዋል። በጠዋት ከየቤቱ ዳቦ ለመግዛት በየሱቁ ደጃፍ የተኮለኮሉት ህፃናት በረባ ባልረባው አይናቻቸውን እያሹ ያንጫንጫቸዋል። ሳንቲሙን የጣለ ያለቅሳል። በዛ ብርድ ጭቃውን እየጠጠ ይፈልጋል። ይሄ ሁሉ የሰፈሩ ትእይንት እንጀቱን በላው።

አንዲት ውይይት ባዶዋን ቆማ ወያላው ሲጣራ ደረሰባት። አላመነታም፣ ተሳፈረ። ታክሲዋ ሞልታ እስክትሄድ የፈጀችው ሰዓት ቢያበሳጨውም ከንፈ ላይ የደረሰው ገና ሳይወጣ የመኪናውን ሞተር ሲያሟሙቅ ነው።

በቀጥታ ወደ አመጣጡ ምክንያት ገለባ ገባ። ያሰበው ተሳካለት። እስከተወሰነ ጊዜ አብረውት መቀመጥ እንደሚችሉ፣ ከዛን በኋላ ካለስት እንደ እቅዱ ቤቱ ተጠናቆ ሲወጣ ለብቻቸው እንደሚሆኑ ነገረው። ተደሰተ። ለሊቱን ሙሉ ሲያስጨንቀው ያደረው ጉዳይ እንዲህ በቀላሉ አልባት ማግኘቱ ገርሞት፣

"የጎጆው ጣጣ እንዴት ታየህ?" አለው ከንፈ፣ በድንገት ላገባ ነው ሊለው በሃሳቡ ተደንቆ።

"ይሄው አይደል የመኖር ትርጉሙ፣ ማንኛችንም በምን መንገድ እስከመቼ እንደምንዘልቅ አናውቅም። የነገ ትልማችን ዛሬ በገጠመን ሁኔታና በተናገርነው ሳይሆን የነገ ሁኔታ ራሱ ወሳኝ ይሆናል።"

"ለመሆኑ ማንን ልታገባ አሰብክ?"

"ማንን ልበልህ፣ አታውቃትም" አለውና በድንገት "እንዴ! እንዴ! ታውቃታለህ። ያኔ ቦሴ ቤተ አይተሃታል። ጭማቂዬን እያልኩ ግራ ሳጋባት የነበረች ልጅ!"

ከንፈ ሊያስታውሳት አልቻለም። ሁኔታው ትዝ ይለዋል። ልጅቷን ግን ለይቶ አላወቃትም። የዛ ቤት ሴቶች ቶሎ ቶሎ ስለሚቀያየሩበት አንዳቸውንም አያውቃቸውም።

መኪናውን ይዘው ከግቢው ከወጡ በኋላ፣ ከንፈ "እስቲ ሠራተኛ ካገኘህ አምጣልኝ" አለው ሽፈራውን እየተመለከተ።

"የምን ሠራተኛ?"

"የቤት ነዋ!"

Scanned with CamScanner

ምንው እቺስ?'' አለ ሽፈራው ቤት ያለችዋን አስታውሶ

''ምን አውቅላታለሁ፣ እሄዳለሁ ትለኛለች። ምክንያቷ ሁሉ ግራ ነው። ሴት የሌለበት ቤት ሰርቼ አላውቅም ነው የምትለኝ'' ሽፈራው ሳቅ አለና ''ያለዛ እመቤት አድርገህ ገረድ ቅጠርልኝ፣ ብላስ አላማረጠችህም?''

''እንተ ትቀልዳለህ'' አለ ክንፈ።

''ቆይ! አሁንማ ሴቷ ልትመጣላት አይደል! እመቤት ካሻት'' አለና በድንገት አንድ ነገር ትዝ ብሎት ''እንዳውም መልካም አጋጣሚ፣ ትሂድ ተዋት፣ የኔዋ ራሷ ምን ስትሰራ ትውላለች? ለኔና ላንተ ማብሰል አያቅታት'' አለ የወደፊት ሚስቱን እያሰባት።

ክንፈ ከበደው ''ሙሽራ ደግሞ ከመቼ ወዲህ ነው ማጀት የምትገባው?''

''የሙሽርና ጊዜው አልፏል—ባክህ።''

* * *

ክንፈ ሽፈራውን አድርሶ ቢሮው ከገባ በኋላ ያሰብ የነበረው ስለትዳሩ ነው። በአጋጣሚ እንደድንገት የተወጠነ ትዳር እውንም እንደአልባሌ ነገር ፈራርሶ ሲቀር አስገረመው። የሽፈራውም ባለትዳር መሆን እሱን ብቻ ሳይሆን ሁለት ነፍሱን ሆኖ ለጊዜው ቤቱ እንዲያርፍ መፍቀድ፣ ሁሉም ሃሳብ ተደባለቀበት። ደግሞ አዜብ ከሃሳቦቹ መሃል ብቅ ‹አለችበት። የምትጨበጥ ፍጥረት አይደለችም። እስካሁን ከሷ ጋር ያሳለፈው ጊዜ የቀድሞውም ቢሆን፣ እሷ እንዳሻትና እንደወጠነችው እንጂ፣ እሱ ፍቃዷን ከመሙላት ሌላ የሚያደርገው አንዳች ነገር የለም።

ክንፈ ለሴት ልጅ ያለው አክብሮት ላቅ ያለ ቢሆንም፣ የአዜብ ግን በተለየ መልኩ ነው። ምክንያት አለው። በመጀመሪያው የወዳጅነት ዘመናቸው የአስተሳሰቧ ልቀት፣ የግንዛቤዋ ጥልቀት፣ እጅግ በጣም ይማርኩትና ያስደንቁት ነበር። እንኳን ከሷ ራሱ እንኳን በፍፁም አስቦባቸው ተገንዝቧቸውም የማያውቃቸው ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የምትሰጠው ጠለቅ ያለ ግንዛቤ፣ የአስተሳሰቧ አድማስና ጥንካሬ፣ እንዲሁም ለአላማዋ ግብ ያላትን ዕናትና ከሚያጋጥሟት ማኅበራዊ እንቅፋቶች እንዣር የምትፈጥራቸውን ዘዬዎችን በቅርብ ሆኖ ይከታተል ስለነበር፣ ሳይወድ በግድ ስብዕናዋን እንዲያከብረው፣ ማንነቷን እንዲገነዘበው አድርጎታል። ሳትናገር ፍላጎቷን ያውቃል። ለማለት የፈለገችውን

በቀላሉ ይረዳላታል። አሁንም ከሷ የተገነዘበው ነገር ቢኖር፣ የወደፊት ግንኙነታቸው ምን መስመር መያዝ እንዳለበት ያለመወሰኗ ነው። ይህ ደግሞ እሱን ግራ አጋብቶታል። ውሳኔ እንዳይሰጥ እንቅፋት ሆኖታል።

ተላላኪው እንዲመጣለት ደውሎን ተጫነው።

''እባክህ ወፍራም ቡና አምጣልኝ'' አለው ተላላኪው በሩን ዘልቆ እንደገባ። አዜብጋ ለመደወል ስልኩን ካነሳ በኋላ መልሶ ተወው። ይህንን ሁለት ቀናት አልተገናኙም። ነገም የሰንበት መጀመሪያ ነው። ከሰዓት አብሯት ቢውል አይጠላም። ሰዓቱ ላይ ያለውን የቀን መቁጠሪያ ተመለከተ። ቀኑ ገስግሷል። የነሐሴ ወር ተገባዶ የአመቱ ምርቃት ቀናት ተቃርበዋል። በስተቀኙ የተቆለሉትን ፋይሎች የመጀመሪያውን አንስቶ መመልከት እንደጀመረ፣ በሩ ተንኳኳ። የመሥሪያ ቤቱ ሴት ተላላኪ ነች። በርካታ ፋይሎች ተሸከማለች። አንዱን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጣለት ሄደች። እናቱ ላይ አስቸኳይ ይላል። አስቸኳይነቱ አልታየውም። አስቸኳይ የሚለው ቃል ፈሊጥ እየሆነ ሄዷል። እንደዛ ካልተባለ አንድም ሥራ ላይሠራ ነው። ሰነዶቹን አገላብጦ ተመለከታቸው። ሁሉም ፊርማ ብቻ የሚያስፈልጋቸው ናቸው። ሁሉም ከጥናት ሪፖርታቸው ጋር ተያይዘው ቀርበዋል። ፋይሉን እጥፎ አስቀመጠ። እሱን የጨነቀው የሃላፊው ፊርማ ከሚለው ግርጌ ፊርማውን ማኖር አይደለም። ያልተስተካከሉ የግሉ ብዙ ጣጣዎች አሉ።

የገዛ ሀሊናው ታዘበው ፡ 'በተቀመጥክበት ሰዓት ያለፈችው እያንዳንዷ ደቂቃ እንደሠራህበት ተቆጥራ የሚከፈልህ ደመወዝ እያለ ቅድሚያ ለራስህ ጉዳይ ታዳላለህ' ከራሱ ጋር መነታረክ አልፈለገም ። ፋይሎቹ ውስጥ ያሉትን ጉዳዮች በጥንቃቄ እየተመለከተ ይፈርም ጀመር።

በመሃሉ የላከው ቡና መጣለት ፡ ላመልታክል ማሰል አድርጉ ቀመሰው ። ቀጭን ቡና ነው ። እንደገና አሳቡ ተበታተነበት ። የእፀገነትን ነገር ውል ማስያዝ አለበት ። ለይቶላቸውም ሽማግሌ መግባት ካለበት እንኳን ፍቺውን ሕጋዊ ማድረግ አለበት ። ጣጣው ደግሞ ታየው ። ፍርድ ቤት ፡ የቤተዘመድ ሽማግሌ ፡ እንደገና ፍርድ ቤት ፡ ውጣ ውረዱ ለሱሰች እንዳላዘነ በራሱ ሊሆን ሆነ ።

ደግሞ ለቤተዘመድ ሽምግልና ማንን ይዞ ሊቀርብ? በውል ጠንቅቆ የሚያውቃቸው ቤተዘመዶቹን ቀርቧቸው አያውቅም ። በትዳር ህይወቱም ጣልቃ ሊገቡለት የሚችሉ ጓደኞች አሰበ ። ደግሞ ተወው ፡ ጊዜው

Scanned with CamScanner

ሲደርስ እንዳሻው ሊወጣው እያሰበ ።

ቡናውን አጣጥሞ እንደጨረሰ እናታ አልቀየም ። ስልኩ አንቃ ጨለ። የውስጥ አጥሬተር ነች ። "አቶ ክንፈ ፡ ከውጭ መስመር ሰው ይፈልጉታል ። አዜብ ነኝ ይሉኛል" አለች በለስላሳና እንደመረዋ በሚያስተጋባ ድምጿ ።

"እገናኝኝ አላት ተጣድፎ ፡ ሊያገኛት መጣደፉ ራሱን አስደነቀው ።

"...ስራ ላይ ነህ ክንፈ?" አለችው አዜብ ።

"ችግር የለም ፡ የት ጠፍተሽ ከረምሽ?..." አላት ስትናፈቅ መክረሟን እየነገራት ። ጣጣ አላበዛችም ፡ ወሬያቸውን ባጭር አድርገው ነገ ከስራ በኋላ የሚገናኙበትን ወስነው ተሰናበቁ ።

ከስልኩ በኋላ ረጋ አለ ። ሳያስበው ያስጨነቀው ነገር ይህ መሆኑ እያስደነቀው ስራውን በትጋት ያከናውን ገባ ።

ከሰአት በኋላ በደረሰው የስልክ ጥሪ ተደናግጦ ከቆየ በኋላ ትንሽ መንፈሱ ሲረጋጋ አዜብ ጋ ደወለና ፡

"አዝናለሁ አዜብ ፡ የነገ ቀጠሮዬን መሰረዜ ነው" አላት ። ንድድ አለች ። አዜብ ቀጠሮ የሚያፈርስ ሰው አትወድም ። ያውም የምትፈልገውና የምትጓጓበት ቀጠሮ ። በዛ ላይ እሷ የወሰነችው ቀጠሮ ከሆነ እንዳች መጥፎ ስሜት ይሰማታል ።

"ምነው?"

"ነቅቃም በላይ ሆኖብኝ ነው ። በአስር ሰዓት ቀብር አለብኝ ።"

"እ... ምነው ማን ሞተ?"

ክንፈ አመነታ "የእፀገነት ወንድም!"

"ምን ነካው?"

"አላውቅም" ስሜቱ በደንብ እንዳልተረጋጋ ያስታውቃል ።

"አዝናለሁ! ቀብሩ የት ነው?"

ስፍራውን ነገራትና ስልኩን ዘግቶት ተነሳ ።

* * *

የዮሴፍ ቤተክርስቲያን መግቢያ በር ተጨናንቋል ። ፀሀዩ ደግሞ እያንዳንዱን ሰው ካልሰለቀጥኩ ይላል ። የቤተክርስቲያኑን በራፍ እንዳለፉ ግራና ቀኝ በሚያጅበው የሙታን መንደር ላይ እያረፈ ከእምነበረዱ ላይ የሚፈናጠረው ጨረር አይን ይወጋል ። ኡኡታውና ለቅሶው ሁካታ የፀሀይ ግለት ከሚያንፀባርቀው ብርሃን ጋር ተዳምሮ የሚፈጥረው

ሁካታ የመሰለ ስሜት ምድርን የቀለጠች ያስመስላታል ።

የሳቀበትና የሳቀችበትን ልብ በእጅጉ ቢፈታተንም ስነስር ቀቷን እንደሀፍረተ ቢስ ሴት ቆጥራ ከመኪናው ስትወርድ ከእግሯ ስር ያለችው ምድር እንደ ሰፊ ባሻገር የሚያውቋቸው የቤተሰቡ አባላት ሁኔታ ስሜቱን ከሰው ትውውቅ ባሻገር ያሳጣው መሆኑን ተገነዘበ ። ይሁንና ከሁሉም በላይ ሊፈፀም ጥቂት ደቂቃ ቀርተውታል ። አስከሬኑ የቤተክርስቲያኑ መራቱ ሊፈፀም ጥቂት ደቂቃ ቀርተውታል ። ሻልሻል ያሉት ሰዎች ደጀኑ ካሳለጡት በኋላ ወደተዘጋጀለት ስፍራ እያመራ ነው ። ከመሬት እጅግ ያዘኑትን በድጋፍ ይረዷቸዋል ። አስከሬኑ ወደተዘጋጀለት ስፍራ ደርሶ ቁልቁል ወደተድንዳድ ሲያዘቀዝቅ እፀገነት ራሷን ስታ መደቀች ። ቀድሞ አጠገቧ የደረሰው የቤተዘመድ ወገን ደግፎ ከያዛት በኋላ ፡ ክንፈ እየተንደረደረ ሄዶ በሁለት እጆቹ እግሯንና ማጅራቷን አንከብክቦ ይዞ ወደ ዛፎቹ ወሰዳት ። ይህን ሰአት ክንፈ አይኑ በእንባው አየራብ ነበር ።

ይህንን ሁሉ አዜብ ፈንጠር ብላ ከሀዘንተኛው ጋር ተቀላቅላ ይህንን አጋጣሚ በምትመለከትበት ጊዜ መንፈሷን አንዳች ኃይል ተጫነው ። የከንፈና የእፀገነት ሁኔታም የታሰባት በቅፅበት ነው ።

ከለቅሶው ሃዘን ሌላ ልቧም ራሱ ለራሱ ሲያዝን ተሰማት! በውስጧ አንድ ነገር እያደገ መሄድ ጀምሯል ። ክንፈ የርሷ አይደለም! ይባስ ብሎም ከፈጠራ ስራዋ ላይ ሳትፈልግ ድቅን እያለ ይፈታተናት ጀምሯል ። አሁንም አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባት ይሰማታል ። ግን ፈርታለች ። ላለማሰብም ትሞክራለች ። ካሬ ግን ሁለቱን ስትመለከት ከምንጊዜውም ይበልጥ ፈጠ ታያት... እናም ልቅሶውም እንደ ሰርጉ ። ተሽሎከልካ ወጣች ፡ መቋረጥ ልቧን እየቆረጠው ።

* * *

እፀገነት ከሟንጎት ሰመመኗ የነቃችው በመኪና ወደ መኖሪያ ቤት ስትመለስ ነው ። አይኗን ገልጣ አካባቢዋን ቃኘች ። ምን አይነት መኪና ውስጥ እንዳለች ባታውቅም ቤተዘመዷ ግራና ቀኝ ደግፈው ወደ ኋላዋ መቀመጫውን አስደግፈው አስተኝተዋታል ። በመጀመሪያ የታያት ምስል ኤርምያስ የተንጠለጠለበት ገመድ አንገቱን ፈጥርቆ ፡ ሁለት እግሮቹ አንዱ ከአንዱ የረዘመ መስለው ፡ እይኖቹ በአንዳች ነገር የደነገጡ

Scanned with CamScanner

ይመስል ያለእርግብጊቢት ፈጠው የተቆጪት ሲመስሉ ፡ ሰውነቷን አኮማትራ አይኖቿን ጨመቀቻቸው ። ትኩስ እንባ በጉንጮቿ ወረደ ።

እውነት እውነትም አይመስላት ። ከአውን አውን ይህ ክፉው ህልሟ አብቅቶላት ማየት ትመኛለች ። ነገሩ ግን ህልም አይደለም ። እውነት ነው። እውነቱ ደግሞ ቀጠለ ። በቅርብ ሀያው የሚመስለው ገላው ባጥቂር የራሳ ሳጥን ቤተክርስቲያን ሲሳለም ከዛ··· ከዛ አስቀያሚውና ጠባቡ ጉድጓድ···

እንደገና የያዟት እየገላገሏት መኪናው ውስጥም ታስቸግር ጀመር። ደግሞ የወረቀት ብዛት ። ያን ሁሉ ምንጊዜ እንደፃፈው ያስገርማል ። ለምርመራ ያስፈልገናል ብለው ደግሞ ፖሊሶች ወስደውታል ። ምን እንደፃፈ ለማወቅ ጓጉታለች ።

'ጉድ ሠራኸኝ' አለች ለራሷ ፡ ሙቱን መውቀሷ ነበር ። የቱቀመጡት ቤተዘመድ "ኤርምያስ ላንቺ ብቻ አይደለም ወንድምነቱ" ብለዋት አፅናኙ ራሳቸው አቃታቸው ፡ የወጣት ሞት አንጀት ይበላል ።

እፀገነት የምትለው የላትም ። እንደ እስረኛ ግራና ቀኝ ታጅባ አይኗን ብቻ እንደጨመቀች ቤት ደርሳ ፍራሽ ላይ አስቀመጧት ። ለቀስተኛው ለቅሶው የወጣለት ይመስላል ።

ክንፈ ቂጡ አላረፈም ። ይሯሯጣል ። ከእድር ሽማግሌዎች ጋር ፡ ከቤተሰብ አባላት ጋር ስለለቅሶው ጣጣ ይማከራል ፡ ያሠራል ፡ ይሠራል ። የሚያስፈልግ ነገር ካለ ያችን የፈረደባትን ፮ልስዋገኑን ይዞ የእድር ወንበር ፡ ሳህን ፡ ኩባያ ሲያመላልስባት ውሏል ። የድንኳኑን መብራት ፡ ከመብራት ሰሪዎች ጋር ሲቀዋል ሲበጥስ··· ሀሊናውም ፡ ሰውነቱም አላረፈ ። አንድ ደግሞ የጠላው ፍልሚያ አለ ። የእፀገነትን ቤተሰቦች አስተያየት አልወደደውም ። ከሀዘኑ ባሻገር በሱ ላይ አንድ አይነት አመለካከት የሚያንፀባርቁው መሰለው ። ተሳቀቀ ።

እፀገነት ባሏን የምትከታተለው በልዩ አትኩሮት ነው ። ሀዘን አወይቦት በገረጣውና ፍም በመሰለው ፉቷ ላይ ፡ በርበሬ መስለው በተጨናበሱ አይኖቿ ፡ ትርጉም ያለው መልእክት ታስተላልፍለታለች ። ክንፈ አተኩሮ ሊያያት አይፈልግም ። ሆን ብሎ ይሸሻታል ። ከሁሉም የደነቀው ነገር ቢኖር የአዜብ ለቅሶ ላይ ያለመኖሯ ጉዳይ ነው ። የት እግኝቶ እንደሚጠይቃት ጨንቆታል ። ያለአንዳች ምክንያት ይህንን እንደማታደርግ ያውቃል ።

የጥንት ወዳጆቹ ሆኑ ያውኖቹ በአብዛኛው በለቅሶው ላይ ተገኙተ ፃል ። የአዜብ አለመኖር አውንም አሳስቦታል ። የእራት ሰአት ገደማ ቤቱ ደመቅመቅ እያለ ሄደ ። ደጃፉ በመኪና ተጨናንቋል ። በአብዛኛው ሀዘተኛው ለቅሶ ለመድረስ የሚመርጡበት ጊዜ ጀምበር ካዘቀዘቀች በኋላ ነው ። በውብ ካፖርት የተጀቦኑ ወንዶች ፡ እንዲሁም ግሩም በሆነ ሰሌት የተሰፉ ጥቋቁር የሃዘን ልብሶች የለበሱ ወይዛዝርት ፡ ድንኳኑ እየጠበበ በየቢቱ ጥግ አግዳሚ ወንበር እየተቀመጡ ሽር ጉዱም እየበዛ መሄድ ጀመረ ። አውንም በዚህ ሰአት አንዲት ከላይ እስከታች ጥቁር የለበሰች ዘለግ ያለ ቁመና ያላት ሴት ከድንኳኑ ወጣች ። ያቺ ሴት አዜብ ነበረች ። ምን ሰአት መጥታ ለምን ያህል ሰአት እንደተቀመጠች የሚያውቅ ሰው አልነበረም ።

* * *

እፀገነት ህይወት ከዘፈቀቻት የሃዘን አዘቅት ውስጥ የምትወጣበት ምንም መንገድ አልታያት እያለ የባሰ ተስፋ መቁረጥ ጀምራለች ። ሳትወድ በግድ በሙቱ ወንድሟ እንድትቀና አድርጓታል ። አንድ ነገር ስታስብ እጅግ አድርጐ ይዘገንናታል ። የተሰቀለበትን ሁኔታ የመጀመሪያው ተመልካች እሷ መሆኗ ።

ለወትሮው ጠዋት ጠዋት እሱን ሳታገኘው መስሪያ ቤት አትሄድም። እና እንደከዚህ ቀደሙ ወደመኝታ ቤት አመራች ። ያለልማዱ በሩን ክፍት ሆኖ አገኘችው ። ምንም ክፉ ነገር አልጠረጠረችም ። ውስጥ ገብታ ለእፍታ ጠበቀችው ። አልመጣም ። የስራ ሰአት ደግሞ ሊረፍድባት ሆነ ። ተመልሳ ወጣችና ወደ ዋናው ቤት ልትሄድ ስትል የሆነ ነገር ከነከናት ። ሳታገኘው ልትሄድ አልፈለገችም ። የሰርቪስ ቤቱ መፀዳጃ ቤት ውስጥ ይሆናል ብላ ነው የገመተችው ። ለተወሰነ ደቂቃ ጠበቀችና ጭራሽ ሊረፍድባት ሲሆን ፡ እየተጣራች ወደ ሽንት ቤቱ ሄደች ። መልስ ስታጣ ፡ ባይኖር ነው ብላ ልትመለስ ካለች በኋላ አውንም ልቧ አልችል ብሎ የሽንት ቤቱን በር ከፍታ ወደ ውስጥ ተመለከተች ። ያየችውን ማመን አልቻለችም ። አፍን በእጆቿ ይዛ ወደ ኋላ ተፈናጠረች ፡ ማረጋገጥ ፈለገች። እውነት ነው! በጎይል እየፎገች ወደ ላይ ቤት ሮጠች ። መንገድ ላይ ምን እንዳደናቀፋት አላወቀችም ። መሬት ወድቃ እሪታዋን ታቀልጠው ጀመር ። የሆነችውን በትክክል መግለፅ አልቻለችም ። ደንግጠው አጠገቧ የደረሱትን ሁሉ በእጆቿ ሽንት ቤቱን ታመለክታቸው

Scanned with CamScanner

ጅመር... ከዛ ቤቱ ተደበላለቀ ።

ነገሮች ሁሉ ተደበላልቀውባት የመኖር ፍላጐቷ ትርጉሙን አጥቶ ሀዘን በላይ በላዩ ሲጨመርባት ራሷን ጠላች ። አዲሱ ወዳጇ ደግሞ የሚነግራት ግራ ይገባታል ። 'የደረሰብሽን ሀዘን በዐጋ መቀበል ይኖርብሻል' ይሏታል ። ባይሏትም አማራጭ የላትም ። ግራ የገባት ግን ሀይወትን ከአሁን በኋላ እንዴት እንደምትቀበለው ነው ። ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ ተቀበልኩት ያለችው አምላኳም የረዳት አንዳች ነገር አልታይ አላት ግራና ቀኝ በቃላት ናዳ ጆሮዋ ከመደንቆራቸው በቀር ።

'ሰይጣን ወደ እግዚአብሄር የሚጠጡትን ሰዎች በተለያየ መንገድ ይፈታተናቸዋል ። ይሽው አንቺም እንድታዝኚ ፡ በእግዚአብሄር እንድታማርሪ ሊያደርግሽ ይሞክራል ። አንቺ ግን መፅናናት በሚሰጥ በእግዚአብሄር ልትበረታቺ ይገባል' ሲላት የመስሪያ ቤቷ ሰባኪ

'ምን?' አለችው ደንግጣ ።

ግራ ገብቷታል ። 'እንዴት ተደርጐ! የኔ ማመን ወንድሜን ሊገለው ቻለ?' ብላ ተሳቀቀች ።

የሷ ማመን የወንድሟ ሞት ጠንቅ የሆነ ያክል ለሁለት ቀናት ስትሰቃይ ቆየች ። ሳይታወቀው አማኙ ያዕናናት መስሎት እሷህ ዘርቶባት መሄዱን አላስተዋለውም ።

እሷም 'እንዴት ይሆናል'ን ብቻ አርግባ አልተወችም ። ዋንትም ከቤተሰቧ ጋር ሆና የምታውቀው አምላክ ይህንን አይሰራም ። አዲስ የምትቀበለው አምላክም የላትም ። ሁሉ ነገር ውሸትና ከንቱ ነው ። የመፅሀፍ ቅዱስ ቃል ትዝ አላት 'ሁሉም ነገር ከንቱ የከንቱ ከንቱ' ይላል ።

ሚቺ ወንድሟ አንዴ የተናገራት ሀሊናዋ ላይ ደመለባት ። አዲስ እምነት ተቀብላ ማመኗን እንዳወቀና እንደተረዳ

"እወነት"

"አቤት"

"ምን ይሉሻል አዲሶቹ ሰዎችሽ?"

"የቶቹ?"

"የምትሄጅባቸው ናቸዋ! የሚያስመልኩሽ ።"

መልስ አልሰጠችውም ። ዝም አለች ።

"ለመሆኑ መፅሀፉን ያስጠኑሻል?"

"የቱን መፅሀፍ?"

"መፅሀፍ ቅዱሱን ነዋ!"

"አም ። ምነው?"

ኤርምያስ ባሽሙር ሳቅ ብሎ 'በኋለኛው ዘመን ብዙ አሳሳቾች ይመጣሉ' የሚለውን ቃል ምን ብለው ያስረዱሻል?"

እወነት ያንጊዜ ጥያቄው አልገባትም ነበር ፡ ሰሞኑን ነው የተከሰተላት ።

ይህንን ሁሉ ስትገነዘብ ይበልጥ ተንገበገበች ። ሌላው ቢቀር የዘንፈን መለየት እንኳን እግዚአብሄር ቢፈቅድ ነው ይህንን ያደረገው እያሉ ሲያሰናኟት ሲያዘናጓት ቆይተዋል ። ያለማንም ባዶዋን አስቀሯት ። የወንድሟ ሞት ያንቺ እምነት ነው አሏት ።

"እመቤቴ ማሪያም ጌታዬንም አንቺንም አስቀይሜያለሁ ። ይቅር በዪኝ" አለች አንገቷን ወደላይ አቅንታ ወደጣራው እየተመለከተች ።

ጣራውን አይታ ወደ እውኑ አለም ስትመለስ ከጐኗ እናቷና የእናቷ እህት አክስቷ ፍራሽ ላይ ተቀምጠዋል ። ለአዘንተኞች ቡና ይዞራል ። በየተራ እንግዶቹን መመልከት ጀመረች ። ከነፈ ከአባቷ ጋር ያወራል ። የእፎይታ ስሜት ተሰማት ። በድንገት ትዝ ያላት ሄኖክ ነው ። ትናንት ቀብር ላይ ይምጣ አይምጣ እርግጠኛ አይደለችም ። ዛሬ ግን በፍፁም አላየችውም ።

ተገረመች ።

መገረሟ ባለመምጣቱ አይደለም ። ከክንፈ ጋር እያነባወረች እንጂ ፡ ፍፁም የሚወዳደሩ አልሆኑባትም – የትናየት ። የሚይንቃት ግን ያንያህል ጊዜ አይኗን በጥቁር ጨርቅ ሸፍኖ ያሰራት ነገር ነው ። ምንጊዜም በእጇችን ካለው ነገር ይልቅ የሌለን የመሰለንን ነገር እንናፍቃለን ። ስናገኘውም ደግሞ እንዳልባሌ ተቆጥሮ ወደ ሌላው እንሮጣለን ። ሆኖም ሌላውን ለማግኘት ስንል እንደምንጥለው የራስ-ፅቃ አይከብድም። ማንኛውንም ነገር እየኖሩበት ከሚመለከቱት ይልቅ ፡ ራቅ ብለው ቢታዘቡት የሚባኑን ክብደት ማጤን ይቻላል ።

በድንገት ታናሽ እህቷ መጥታ ወደ'ሷ ጠጋ ብላ ስልክ እንደሚፈል ጋት በጆሮዋ ነገረቻት ። ይህን ሁሉ ሀዘንተኛ አቋርጦ መሄዱ ቢከብዳትም አማራጭ አልነበራትም ። ቀስ ብላ ልትነሳ ስትል እናቷ በደፈረሰ አይናቸው እየተመለከቷት ፡

"የት ልትሄጂ ነው፤ወ አሏት ፡ ከኤርምያስ ሞት ወዲህ እያንዳንዱን

Scanned with CamScanner

የቤተሰብ አባል ማመን ትተዋል ። ድንገት ሄደው ሙትት የሚሉ ነው የሚመስላቸው ።

“ሠጣሁ ስልክ ፈልጐኝ ነው ።”

ከዛ ሁሉ ለቅሶ ደራሽ ውስጥ እንቅስቃሴዋን በእጅጉ ይከታተል የነበረው ክንፈ ነው ። አባቷ ጊዜውና ሁኔታው አላመች እያላቸው ተቸገሩ እንጂ ፡ ያሰሰባቸውን የሁለቱን ጉዳይ ቢያነሱት በወደዱ ነበር ።

“እወገነት እጅግ በጣም አዝናለሁ” አላት ከስልኩ የወጣው ድምፅ፡ ማንነቱን ለማወቅ አላዳገታትም ፡ “ምንም አይደል” ብላ መለሰችለት።

“በረታሽ?” አላት ሄኖክ ።

መልስ መስጠት አቅቷት ዕንባ ብቻ ይተናነቃት ጀምሯል “ምን_ ም–ን እሆናለሁ ብለህ ነው!”

ነገረ ስራው ሁሉ አናዷታል ። ከጠበቀችው በላይ ባለጌ ሆነባት ። እስቲ ማን አላት ፡ ለማን ስትል ይህንን ሁሉ ፈተና ታያለች ። በእርግጥ ለሞኑን እንዳስከፋችው ይታወቃታል ። ያስከፋችው ወዳ አይደለም ። ከቁጥጥር ውጭ ሆኖባት እንጂ ።

“መጥቼ ለቅሶ እንዳልደርስ…” አለና አቅማምቶ “… ባለቤትሽ እንዳለ ስለገመትኩ ነው” አላት ።

ምክንያቱ አስገረማት ፡ አናደዳትም ። “አምን! ልታየው አይገባም።” ድምጿ ተንቀጠቀጠ ።

አልገባውም ። “ለምን? ለምንድነው ማየት የማይገባኝ?”

“እንጃ ፡ አላውትም ፡ አንተውነህ ያልከው ።” አሁንም እልህ ተናነቃት።

“አዎ ፡ ባላየው ይሻላል ።”

“ጥሩ” ስልኩን ልትዘጋው ፈለገች ። ከመዝጋቷ በፊት ግን የልቧን እንድትነግረው ልቧ ከውስጥ ይጮኽባታል ። ልትገላገለው ቆረጠች ።

“…አዎ! ጥሩ! ባታየው ይሻላል ። ሰይጣን አምላክ ፊት እንደምን ደፍሮ ሊቆም ይችላል? ገባህ? አትችልም!” አለችና ስልኩን ጆሮው ላይ ጠርቅማው በረጅሙ ተነፈሰች ። በመጠኑ ቀለል አላት ። ክንፈን የካሰችው መሰላት ። ከአንድም ሁለት ጊዜ እጅግ አድርጋ በድላዋለች ። ለዚህ ሁሉ ታዲያ ይህ በቂ ካሳ አልመሰላትም ። ‘እድሜ ልኳን ንፍሰ ይቅርታውን ስትለምን ትኖራለች’ አለችና ወደ ሳሎኑ ፍራሽ አመራች…

እወገነት የተቀበለችውን ወረቀት ይዛ ወደ መኝታ ቤት ስትገባ እጇ ይንቀጠቀጥ ነበር። ፖሊሶች አስፈላጊ ይሆናል ብለው ለመረጃነት አቆይተውት የነበረው ኤርምያስ የፃፈው ወረቀት ነው። ቀኑ ከነአመተ ምህረቱ በሚገባ ሰፍሯል። በጣም ረጅም ዕሁፍ ነው። በዛ ላይ በጥሩ የእጅ ዕሁፍ በሰማያዊ ስስ ወረቀት ተጽፏል። ማንበብ ከመጀመሯ በፊት በሩን ቆለፈችና ወደ አልጋው አመራች።

‘ሕይወት እንዲህ ከሆነች ምኗ እንደሚያጓጓ አይገባኝም። እያንዳንዷን የሌላውን ‘ማስክ’ እየለበስን እስከመቼ አስመስለን እንኖራለን? እኔስ ሰልችቶኛል። ራሴን መሆን አልቻልኩም። ነገሮች መስዬ እንድኖር ያስገድዱኛል። የራሴ የሆነ ህሊናዊ መስመር እንድከተል ማንም ፈቃደኛ አይሆንም። እንደማይሆንም ከተረዳሁ ቆይቻለሁ። መቀበል ያቃተኝ ውሳኔዬን ነበር። መታረቁ በውስጤ ይታወቀኛል። ድሮ እንዲህ አይነት ስሜት ሲሰማኝ፡ መፃህፍት በማንበብ፡ ተፈጥሮን በእንክሮ በማጥናትና በመመርመር ውስጤን እየረሳሁ ውጪው ላይ በማተኮር ጊዜውን አሳልፍ ነበር። አሁን ግን አልቻልኩም። እስከመቼ ውስጤን እየሸሸሁ መኖር ይቻለኛል?

‘ተፈጥሮ ራሷ ኮሚክ ናት። እንደሸርሙጣ ውበቷ እንዲታይላት እንጂ፡ ውስጠ ምስጢሯን አትገልፅም። ፍቅር ትጥላለች እንጂ ፍቅር አይዛትም። ለመጣውም ለሄደውም ደንታ የላትም። ታዲያ እኛ እንጋጠን በውበቷ ስንፅናና፡ ውስጣችንን ረስተን እኛነታችንን ዘንግተን መስለን በመኖር እድሜያችንን እንገፋለን። ትውልድ ያልፋል፡ ትውልድ ይተካል፡ እሷ ግን እድሜ ልኳን….

‘ሕይወትም ያው ነች። ምኗ እንደሚያጓጓ ሳትገልጥልን በጉጉት ብቻ አድሚያችንን እንድንገፋ ታደርገናለች። ሲያሻት ለማንም ለምንም ርህራሄ የላትም። ውለታ፡ አንጃ ግራንጃ አታውቅም። ሁላችንም ህይወት ያለን የተፈጥሮ ተቀፅላዎች ነን። ስለዚህም እንደሷው እንሸረሙጣለን። ውበታችንን እንጂ ውስጣዊ ማንነታችንን ማንም እንዲያውቅብን አንፈልግም። አጋጣሚ ሰምሮለት ማንነታችን ያገኘ ሰው ካገኘን ወዮለት፡ የገዳያችን ያክል እንፈታተነዋለን። ሁሉ ነገር በውሸት ላይ በተመሠረተ አለም ላይ መኖር ራሱ እንዴት ያስጠላል! እኔስ አስመስሎ መኖር አልቻልኩም፡ ይብላኝ ለቀሪው!።

Scanned with CamScanner

‘በምንም ይሁን በምን ራሱን የማጥፋት እርምጃ የሚወስድ ሰው ደካማ ይመስለኝ ነበር። አሁን በዚህ ሙሉ እምነት የለኝም። ሌላውን ከማጥፋት ደግሞ ይህ የተሻለ እርምጃ ነው። ሌላው በገዛ እጁ እንዲጠፋ ማድረግ ደግሞ ከሁሉም በላይ የከፋ ስራ ነው። እያንዳንዳችን የምንሰራው ግን ይህን ነው። ኑሮ ያታተን እናልፋለን። የበረቱ ይኖራሉ። ለዚህ ግን የደደረ ሀሊና ያስፈልጋል። በእሁኑ ስአት በማንም ቂም የለኝም። ሊኖረኝም አይችልም። ይህች አለም በጥቂቶች ክፋት የታጠረች ቢሆንም፣ ያንን ለመፋለም፣ የበረታም ባይሆን፣ በአቅሜ ለመጋፈጥ ከመሞከር ወደኋላ አልልም ነበር። ነገር ግን ይህች አለም አሰሯ ብቻ ሳይሆን፣ ጥንስሷም ክፋት ነው። ክፋቷ በዝቶ ቆይቶ ኮምጥጧል። ያን ኮምጣጤ እንደከርስቶስ በግድ ያግቱናል። የስንቱ ደም በየሚዳው በክንቱ ፈሶ ቀርቷል። ስንቱስ በዓላማ ስሜት ገመድ እየታበተ በጥቂቶች አሽከርካሪ ነት በብዙሃን ደም ያለገደብ ዋጅቷል?። ስንቱስ በሌላው ደም ተጠቃሚ ሆነ? በደም ላይ ተቀምጠን የምንጎርሰውስ ዳቦ እንደምን ይዋጥልናል አቤት ይህች አለም! ስንት ግፍ አለባት!

‘ብቻ ደም ክፉ ነው። እንኳን ደም የሰው ጉልበትና ላብ ራሱ መቅኖ ያሳጣል። የሚገርመው ግን በአለማችን ጥቂቶች የደለቡት በዚህ ተግባር ነው። እየፋፋና እየወፈሩ ይሄዳሉ። ለጥቂቶች ሀልውና ብዙሃን መስዋዕት ይሆናሉ። ለጥቂቶች የማይጨበጭ ተስፋ የብዙሃኑ ደም ይዋጣል።

‘እኔ ይህንን ፍልሚያ ሀሊናዬ አልቻለውም። የብዙ አጋሮቼ ደም በየደቂቃው በሀሊናዬ ይደውላል። ሀልፈታቸው ከንቱ የሆነ ያክል ይሰማኛል። ልፋታቸው መና ቀርቶ እነሱም ከጊዜው ጋር አልፈው መቅረታቸው ያስጨንቀኛል። በዚህ አለም በከንቱ እንደፈሰሰ ደም የሚያሳዝነኝ ነገር የለም። እያንዳንዳችን ለማን ሀይወት ሰጥተን እናውቅና ነው ሀይወት የማሳለፉ ስልጣን የተሰጠን? እንዴት ሰው ለሰው ሀይወት ፈራጅ ይሆናል? እንኳን በሰው ሀይወት በራስ ሀይወትም መፍረድ ያስቸግራል። የምንኖረው ግን በሰው ሀይወት መፍረድ በሚቃጣቸውና በሚችሉበት አለም ውስጥ ነው። የራሳችን ሀይወት ለማላችን እንኳን ዋስትና የላትም። ዋስትና እንዲኖራት ካሻት ሌላውን መስላ መኖር አለባት። ይህ ደግሞ ለኔ እጅግ አስቸጋሪ ተግባር ነው። አሁን ያደረኩት፣ ለማጥፋት ሌሎች ይሽቀዳደሙባት የነበረችውን ሀይወት እኔ ቀደምኳ ቸው። ማንም ለሀልፈቱ ተጠያቂ እይሆንም። ልጠይት የሚልም ሰው ካለ

ማስመሰያ ማስኩን በቅድሚያ ያውልቅና ራሱን ሆኖ ይቅረብ። ያኔ የኔም አስረጅነት አያስፈልግም። ሁሉን ራሱ ይገነዘበዋል። ይህንን ስጽፍ የአንድ ይሁዳዊ ታሪክ ትዝ አለኝ። በሀይወት ዘመኑ የተፈፀመበት ግፍና በወገኖቹ የተፈፀሙትን ግፎች ሁሉ አይቶ አንድ ቀን ይህ ሁሉ ግፍ ፍርድ ያገኛል እያለ ሲጠባበቅ፣ በመጨረሻ ተስፋ ቆርጦ ራሱን አጠፋ። ከመሞቱ በፊት፣ ‘ይቅርታ ሊደረግላቸው የማይገባ ወንጀለኞች በመሃከላቸው እያሉ፣ እነርሱው እንደልባቸው ኖረው እንደፍላጎታቸው ሲንፈላሰሱ እየተመለከትኩ መኖር አልችልም’ ብሎ ነበር። የኔም ከዚህ የተለየ አይደለም።

‘ጠዋት ማታ መንፈሴ በቁሞት እየተሰቃየ ያንን ባሰታመምኩ ቁጥር፣ የብዙሃን ደም ሲፈሰሀብኝ፣ ከንቱነታቸው ጎልቶ ሲሰማኝ ራሴንም ከንቱ አድርጌ እቆጥራለሁ። እና በታኝ! ሌላው ላይ ላለመቃጣት ስል በራሴ ለፈፀምኩት ወንጀል ከኔ ከባለቤቱ በቀር ማንም ተጠያቂ አይሆንም። ቢኖርም ነፍስህን የሰጠሁህ እኔ ነኝ የሚል አምላክ ብቻ ይሆናል’ ካለ በኋላ ትንሽ መስመሮች ወረድ ብሎ።

‘እወነት ፡ የዘንጋሁት ነገር! በጊዜው ቢያስደነግጠኝም አሁን ግን እድለኛነቱ ይሰማኛል። የኔ መጥደል አለም ቁጥሯን አይቀንስባትም። ሀዘን ሀላፊ ነው። አስቀድሜ ቤተሰቦቼን ማፅናናት አያሻኝም። እትዘኑ ብልም አይሆንም። ይህን ሁሉ አስቀድሜ አውቃለሁ። አሁን የሚከነክነኝ ግን አንድ ነገር አለ። በተለይ እወገነት ከዚያች ከምታውቂያት ከቀድሞዋ ፍቅረኛዬ ከወይንሽት ልጅ መውለዴን ታውቂ ኖሯል? ለቤተሰባችን ምስጢር ነው። ከቻልሽ ልጁን አምጥተሽ ከቤተሰቦቼ አስተዋውቂው። አቅርቡት። የዘመድ፡ የቤተሰብ አይን እንዳይናፍቅ፣ እኔ አባቱ በከንቱ አለም ተፈጥሬ ከንቱ ሆኛለሁ። ድንገት በሱ ጊዜ አለም ብሩህ ትሆን ይሆን? ያም ሆነ ይህ ቢቻል፡ እናቱ ፈቃደኛ ከሆነች ከእናንተ ጋ አኑሩት። ከእንጀራ አባት አያት ሳይሻለው አይቀርም። ድንቡሽ ያለ ብሩክ ልጅ ነው፡ አለም ከፋቷን እስከታስተምረው ድረስ፡ ሌላው ደግሞ አደራ የምልሽ ለቤተሰባችን ያለሽው እንግዲህ አንቺ ነሽ። ጠንካራም ትመስይ ኛለሽ....’ እዚህ ላይ ማንበቢን ገታ አድርጋ እያለቀሰች የምሬት ሳቅ ሳቅ አለች፣ ‘ስለዚህ አደራ የፈረሰ ቤትሽን ለማቅናት ሞክሪ። እፅሽ እንግዲህ ልጅ መሆን የለም። ከማንም ጋር ሳይጋጩ መኖር አይቻልም። ግጭቱን ደግሞ አለዝቦ ማለፍ የኛ ድርሻ ነው። ዛሬ ብዙው ሰው ደስታ ርቆታል።

Scanned with CamScanner

ምክንያቱ ብዙ ነው። እና ታጋሽ ሁኚ፡ አምላክም እንደሰው ቃላቧ ካልሆነ በመጨረሻ ዘመን እንሰባሰብ ይሆናል። ያችን ትንሽ 'ፈንጣጣ' ሀዘን እንዳታበዛ አድርጊያት። በልጅነቷ ሀዘን ላስተምራት እንኳን አልፈልግም ነበር፣ ምን ታደርጊዋለሽ! ባክኖ ከኖረ ወንድም ምንም ይጠበቃል። ባይሆን እነአበባን ወንድ ውለዱልን ብላችሁ ጨቅጭቋቸው፡ አያ....ለካ የኔ ጎረምሳ አለ! ሞት ይርሳኝ። ረሳሁትኮ ፤ እፅሽ ስሙን አልነገርኩሽም። ምስጢረ ነው ስሙ። ምስጢረ ኤርምያስ! ምስጢሬ መሆኑ ልክ አይደል?

'እፅሽ ሞትን ፈራሁ መሰለኝ፡ አላማዬን ዘንግቼ ዝም ብዬ እፅፋለሁ። በቆየሁ መጠን የመኖር ፍላጎቱ ገደቡን እንዳያልፍ እፈራለሁ። በተለይ አሁን ስለልጇ ሳስብ የመኖር ፍላጎቱ ሲንቀሳቀስ ይሰማኛል። እና በዚሁ ልቋጭ 'ነገር ቢበዛ በአሀያ አይጫንም' ይላል የሀገሬ ሰው፡ ቻው!

ከወረቀቱ ላይ ቀና አለችና ወደ ግድግዳው አፈጠጠች። አንደኛውን አጠናቆ ሁለተኛውን ሳምንት የያዘው የወንድሟ ነገር እንዲሁ መቅረት አንጀቷን በላው።

ቤት ውስጥም የለቅሶ ደራሹ ቁጥር ከአለት ወደ አለት እየቀነሰ ሄደ። ከቅርብ ቤተዘመድ በቀር፡ አልፎ አልፎ ካልሆነ ቤቱ ጭር እያለ መሄድ ጀምሯል። ሳምንቱ እንዳለቀ ደግሞ እርሷም ስራ ትገባለች። ይህን ሁሉ ስታስብ አንጀቷ መባባት ጀመረ። ክንፈን ካየችው አራት ቀን ሊሆናት ነው። ነገ ለአስራ ሁለቱ ይመጣ ይሆናል ብላ ተስፋ አድርጋለች።

ግን እንደጠበቀችው በማግስቱ አልተገኘም።

ምእራፍ አሥራ አራት

በውስጡ የሚተራመሰው ሃሳብ እየተንፈራገጠ ሰላሟን ገፍቷል። ለወትሮ ያስጨንቃት የነበረው የፈጠራ ሱሷ አኩርፏት ይሁን በሌላ ባላወቀችው ምክንያት እርግፍ አድርጎ ትቷታል። ጠዋት ማታ ሃሳቧ ከክንፈ ሁሪያ አያልፍም።

ባሯ ቤቷ ገብታ ጀርባዋን ደህና አድርጉ የሚደበድባት የሙቅ ውሃ ሻወር ስሜቷን አፍታቶ ሰውነቷን ቢያዝናናውም፡ ሃሳቧ አድማሱን ተሻግሮ ርቆ ነጉዷል። እንደዘወትር ልማዷ ለመታጠብ ከመግባቷ አስቀድማ ያወጣችው የአስቱር አወቀ 'አደራ እላለሁ' የሚለው ዜማዋ አንጀቷን እየበላው አሁንም ክንፈን ታስባለች—አዜብ።

....''አንተ የኔ ከሆንክ፡
የኔ ቆንጆ
የግል የብቻዬ...
የግል የብቻዬ
በሄድክበት ልሂድ
የኔ ቆንጆ
አንተን ተከትዬ''.....

ድምጿን ከፍ አድርጋ በተመስጦ ብታንጎራጉረውም ግጥሙ ከሁኔታዋ ጋር አልሄድ አላት። ክንፈ የግሏ የብቻዋ እንዳልሆነና ሊሆን እንደማይችል መገመት ከጀመረች ቆየት ብላለች።

ሳታስበው ዕንባዋ ከአይኗ ይወርድ ጀመር። ልታቆመው አልፈለገችም። ስቅስቅ ብላ እስኪወጣላት ድረስ አለቀሰች። አልቅሳ እንደጨረሰች፡ ከክንፈ ጋር ያላትን ግንኙነት ልትቋጭ ቆረጠች። ከለቅሶዋ በኋላ ሰውነቷ ከየት መጣ ባልተባለ ብርታት ሲጠነክር ታወቃት። ተደነቀች። 'ሴት ልጅ ለቅሶዋ መድሃኒቷ ነው' የሚል የት እንዳነበበች ትዝ አልልሽ አላት። ብቻ ተበራታች።

ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ይማርካትና ያዝናናት የነበረው የሙቅ ውሃ አስጠላት። ሙቁን ዘግታ ቀዝቃዛውን ብቻ ተወችው። የውሃው ቅዝቃዜ ሰውነቷን ሲያርበተብተው ፊቷ ላይ ግሩም ፈገግታ ፈነጠቀ።

Scanned with CamScanner

መፃፍ አለባት። ካልፃፈች፣ የሕልውናዋ ደብዛ ሚሽቶ ይጠፋል። የመኖሯ ተልእኮ ባንፃሩ ሚዛን ይደፋል። የወሰነችው የሚመስላት የክንፈ ጉዳይ ደግሞ፣ ከባኖው ወጥታ ሰውነቷን በፎጣ እያደራረቀች፣ እንዴ አዲስ ድቅን ይልባት ጀመር። ሜራሽ ውሳኔዋን ዘንግታ ገላዋን መናፈቅ ጀመረች። ሳይታወቃት ህይወትን ሰለቸቻት። የመኖሯ ተልእኮ እንደብ ዙሃኑ በተራና በክንቱ አለማዊ ስሜት ተውጦ እድሜን መግፋት! ቀፈፋት።

'የለም! ፍቅር ተራና ርካሽ ተግባር ሳይሆን፣ የአለማችን ታላቁና ሀያሉ መሳሪያ ነው። ህይወትሽ በፍቅር በመጠመዷ ራስሽን ልትወየፊው አይገባም።'

'አሃ! በፍቅር አሳቦ ታላቁን የህይወት ተልእኮ ደብዛ ማጥፋት ነዋ ታላቁ ተግባር!'

የሕሊናዋ ሽሙጥ እርሷኑ ይተገትጋት ጀመር። የደራሲ ህይወት በጡዙ ነገር የተወጠረች ነች። በተሰጥኦ የፈጣሪን ሚና ለመጫወት ስትለፋ፣ ያም አንዴ ሲሆንላት ደግሞ ሲፈርስባት፣ ስብእናዋ ደግሞ እንደማንም በማንኛቸውም ማህበራዊ ጉዳይ ስትጠመድ፣ የማህበረሰቡ አካል በመሆኗ ህመማቸው ህመሟ፣ ደስታቸው ደስታዋ፣ ሌላውም ሌላ፣ እየሆነባት ከፈጠራ ስራዋ ጋር ሲሳከርባት፣ ከፈጣሪንት ሚናዋ ወርዳ ከፍጡራን ጋር ስትዋዋት፣ ደግሞ ተገንጥላ ወደፈጣሪንት ዙሩኗ ስትወጣ. ..ማንኛቸውንም አይነት ማህበራዊ ጉዳይ እርግፍ አድርጋ መተው ሲቻላት ፍቅር ግን ከፉኛ ተፈታተነቻት። በተለይ የሴት ልጅን ህይወት ከፍቅር ጋር ስለምታሰላ የህይወትን ተልእኮ ከፍቅር ነጥላ ብቻውን ለማየቱ እጅግ ይከብድባታል። ህይወቷን ባልተጨበጠ ነገር ላይ እንሳፋ በክንቱ ትቃትታለች።

እዚህ የቃተተች ነፍሷን ይዛ በሃሳብ ሞገድ አንድ ጊዜ ወደላይ ደግሞ ወደታች ስትናውዝ፣ የፈጠራ ዙፋኗን ረሳችው። ሳይታወቃት መንፈሷ ከተልእኮው በመፈናገጡ ይወራጫል። ለጊዜው እንደማንም ሰብአዊ ፍጡር አይኗን ሸብቦ የያዘው ግን ፍቅር ነው። የተቀያየጠ ፍቅር!

የሰው ሰውን መውደድ በህልሟም በውኗም አስባው የማታውቀው ነገር… በጣቃ ስታሰላስለው እጅግ አድርጎ ይደንቃታል። እሷኑን፣ ግንኙቷን እስክትጠራጠር ድረስ ይፈታተናታል። አስባ አታበቃም፣ ራሷን በመጠየፍ ትደመድመዋለች። እንዳንዴ ስለክንፈ ያላትን አመለካ

ከት በግድ ትለውጠዋለች። 'ክንፈ'ኮ ከተራው ማህበረሰብ የወጣ፣ ተራ የህይወት ተልእኮ ያለው ተራ ግለሰብ ነው' እያለች ትቆይና የመለየት ብርታቷን ለማጠንከርና ሃሳቧን ለማፅናት ትሞክራለች፣ እይቻላትም።

'እንዳንቺ ጠዋት ማታ ታላትን እያጣመሩ በመንደፍ ካልተኖረ በቀር ህይወት ተራና ተልእኮ አልባ መሆኗ ነው?'

'ባፋንኩሎ!' ተናደደች።

ይሄ ሁሉ የሃሳብ ሙግት መለየትን ለመሸሽ ነው። ይህን እውቆ ነው መሰል፣ መለየት እያነፈነፈ በየሄደችበት ይከታተላታል። ስትሸሸው ስትርቀው እያሳደደ ያድናታል። ስትታገለው ይረታታል። መርታት ብቻ አይደለም፣ ስሜቷን። መንፈሷን፣ ሁለንተናዋን ከምድር ቢታች ወደ ጥልቁ ሲአል ይወረውረዋል።

አዚህ ክንፈንና እወገኑትን በለቅሶው ስሞን ተከታትላቸዋለች። በተለይ እወገኑትን፣ ባሏን በጥላቻ አይን እትመለከተውም። እንዳውም በይቅርታና በርህራሄ አይን ነው የምታየው በተለይ ከአላቷ ጋር ተቀምጠ ሲያወራ፣ የልጅነት እንጂ የአማችነት ምልክት እይታይበትም። በምንም አይነት ደግሞ የመለያየታቸው ምክንያት እሷ እንድትሆን አትፈልግም። ወንድሟ ለዚህ የተጫወተው ሚና ጮች አነሰና! እንዳንድ ጊዜ የግንኙነታቸው ምስጢር፣ የመለያየታቸው፣ እንደነና የመገናኘታቸው ባጠቃላይ በመሃከላቸው የተፈጠረው ውስብስብ ውኔታ የሚታያት እንደ ተዓምር እንጂ፣ አጋጣሚነቱን መገንዘብ ያዳግታታል። እህትና ወንድም ለአንድ ትዳር ጠንቅ የሆኑበትን ሁኔታ ማሰቡ ራሱ ሀሊናዋ ከሚችለው በላይ ሆኗል። ይሄን ስታስብ እንዳዲስ ትደነግጣለች። ያም ሆነ ይህ በመጨረሻ እንደምንም ብላ ህይወቷን ከክንፈ ህይወት ውስጥ መንጭታ ማውጣት እንዳለባት እየተሰማት ሄደ።

* * *

እንደወትሮው የአመት በአል ዋዜማ ቤቱ ደመቅመቅ ብሏል። የሰሞነኛ ብቸኝነቱ በተለየ መልኩ እንጂ በቤቱ ሞሪታ አልታወከም። የመዳበሉን ህይወት ለምዶታል። ሽፈራው ከነሚስቱ ጠቅልለው ቤቱ ከገቡ ወዲህ እሱም በጊዜ ቤቱ ማለት ጀምሯል። በጊዜ ይገባሉ፣ አብረው ሲጫወቱ ያመሻሉ። የተለየ ነገር የሚመስለው የሱ ብቸኝነት የሽፈራው ባለትዳርነት ነው፣ ''ሽፈ'' የጥንት አመሉን አልተወውም። ቤቱን ያበጃጀል። ዕቃዎች ቦታ ይለዋውጣል። በዚህ በኩል ሚስቱም ጉልህ

Scanned with CamScanner

ድርሻ አላት። ያሳለፈችው ዘመን በአሁኑ ህይወቷ ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርግ ባት ሽፈራውና ክንፈ የተቻላቸውን ያህል ይጥራሉ። የቀድሞ ህይወቷን የሚያስታውስ በመሃከላቸው የሚነሳ አጋጣሚ ካለ፣ ወዲያው ተረባርበው ያዳፍኑታል።

በረንዳው ብረት ላይ የታሰረው በግ ምን አምሮት እንደሆን እንጃ፣ ዝምብሎ ይጮሃል። ሽፈራው አጭዶ ያስቀመጠለትን ሳር ንክች አላደረገም። ሽፈራው የገዛት ዶሮ ተሸላ ተገኝታለች። ያገኘችውን ጥርግ አድርጋ መልቀም ነው። ሰፈሯ ገና ጀምበር ከማዘቅዘቋ በጭስ መታጠን ጀምራለች። ደመናውም ዋዜማውን ብሎ ነው መሰል ገለል ብሏል።

ክንፈ በጉን እየጎተተ ቤት ሲደርስ ዘንግቶት የነበረውን ችቦ ተመልሶ ሂዶ ገዝቷል። በቁጥራቸው ልክ ።

ለሁለት አዋጥተው የገዙትን 'ብላክ ሌብል' ውስኪ ከፈት ለፈት ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው የጥንት ወግ መጠረቅ ጀምረዋል። የሽፈራው ሚስት አስናቀች ትንደፋደፋለች። ሠራተኛዋ ብርቁ ቤቱን ጥላ ከሄደች ለነባብታለች። ክንፈም እሄዳለሁ ካለችው ወዲህ ሊያስቀምጣት አልፈለገም። ላይታወቀው ጥላው ልሂድ ማለቷ ባያት ቁጥር ያናድደው ስለነበር ጠላት።

አስናቀች ከጓዳ አይኗን እየጠራረገች ብቅ ስትል፡

"ምን እንርዳሽ አስኑ?" አላት ክንፈ ፈገግ ብሎ።

አስናቀች ያን ዘወትር የሚፈታተነውን የሚያባብል አይኗን ወዲያና ወዲህ እያንከራተተች "አመሰግናለሁ፡ ይልቅ ማዕድ ልስራ ወይንስ ችቦውን ታበሩት?" አለቻቸው ምርጫውን ለነሱ ትታ። የማድቤቱ ሙቀት ፊቷን በርበሬ አስመስሎታል።

ሽፈራው ከመቀመጫው እየተነሳ "እንዴ ይብራ እንጂ" አለ ክንፈን እንዲነሳ እያደረገ።

ችቦውን አቀጣጠሉ። ሽፈራው አዲስ ህይወት የያዘበትን ዘመን፣ ክንፈም በተደበላለቀ ሁኔታ ያሳለፈበትን፣ ከፋም ለማም ያለፈውን አመት በችቧቸው ዘከሩት። አስናቀች ግን የሚታያት ብሩህ ተስፋ ነው።

ክንፈ ደግሞ ወደቤት ሲገባ የታሰበው፣ የነገው የአዘብ ቀጠሮ ነው።

* * *

ጠዋት ለአንድ አፍታ አዲስ አመት መሆኑን የምታበስር ጮርቃ ፀሐይ ብልጭ አለች። አውደአመት በመንፈስ ላይ የሚያሳድረው ልዩ

የሆነ ኃይል አለው ።

አዘብ በሃገር ባህል ልብሷ ተጀቡና ሳሎኑ ውስጥ ትንሳዳሳዳለች። ሄኖክ የት እንደሄደ አታውቅም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባመጡት አዲስ አመል ኑሯቸው መናቆር ብቻ ሆኗል። ንግግራቸው ሁሉ ካንገት በላይ ነው። ለዛች ለሚገናኙባት አጭር ጊዜ በመሃከላቸውም ሰላም አትሰፍንም። ሁለቱንም ታነጫንጫቸዋለች።

የቤቷ ሁኔታ እንዲህ በአንድ ጊዜ ውጥንቅጡ መውጣቱ እየታሰባት፡ ደግሞ ሁሉንም ስፍራ ስፍራ ለማስያዝ የተቃረበች እየመሰላት ስትዕናና ፡ ልቧ ደግሞ ስታዩን ይጀምራል ። የክንፈ ፆልስዋገን ጡሩምባ ከሃሳቧ ገላገላት ።

ወደቤት እንዲገባ አግዶረደረቸው ። የሚሞክር አይነት አልሆነላትም ። ሳልናገር ከሚቀር ያለችው እንጂ ፡ እሷም አስባበት አይደለም ። ቀድሞም በፍፁም ቤቷ ገብቶ ተስተናግዶ አያውቅም ። አንዳንድ ጊዜ አብረው ሊያመሹ አጥር ግቢ ውስጥ ያስገባትና ይመለሳል እንጂ አይገባም ።

መኪናዋ እንደወትሮዋ ከከተማ ውጪ መንገዱን ትሸነሽነው ጀመር ። ተስማሚ ወደሆነ የፀጥታ ስፍራ ወሰዳት ። እውደ ዓመት በመሆኑ ሆቴሏ እንግዶች አልበዛባትም ። ሰላሟ በጭርታ ተከብሯል ። ተረታሁ ስትል የነበረችው ፀሀይ ያለየሌለ ጉልበቷን አስተባብራ 'አለሁ' እያለች ነው ። አስተናጋጁ የበሩን ቁልፍ ይዞ ቀድሞ እየመራቸው ፡ ክፍላቸውን አሳያቸው ። ጥቂት አረፉ ።

አዘብ ስትፈራና ስትጨነቅ ሃሳቧን ለሁለት ከፍሎ ሞግቶ ይዞ የነበረው ሰአት ደረሰ ። ቃላት ጠፉ ። ልቧም ያመነታ ጀመር ። 'ህይወት የባለቤቷን ቆራጥነት ትፈታተናለች' ያለው ማን ነበር ? አሁን እሱን ለማሰብ ጊዜ የላትም ።

ክንፈ ደግሞ ንጉቷል ። ስሜት ወጥሮ ይዞታል ። አዘብ ግን ሁሉን ነገር ከነገረችው በኋላ እንዲሆን ፈልጋለች ።

እየደባበሰ ሊስማት ሞከረ ። በእንቅስቃሴዋ ገታችው ። አተኩሮ ተመለከታት ። አስተያየቷ እንደወትሮ በራስ የመተማመንና የቆራጥነት መንፈስ የለውም ። እንቅስቃሴውን ቀጠለ ።

"ቆይ ክንፈ !"

Scanned with CamScanner

"ምነው?"

"እስቀድመን የምንነጋገረው ጉዳይ ስላለን ነው"

ፈራ ። ነገሩ የቀለለ አልመሰለውም ። "ምንድነው?"

"ስለኔና ስላንተ ጉዳይ..."

ይህ ጉዳይ አንድ ቀን እንደሚነሳ ገምቷል ። ግን በእንደዚህ ሰአት እንዲሆን አይፈልግም ነበር ፡ ስንት ጊዜ ሞልቶ !

"ሊቆየን አይችልም ?" ደባበሳት ።

"ካልክ ! ..."

እሷም መረታት ጀምራ ነበር ።

ተራክቧቸው ከወትሮ ለየት ያለ ነበር ። እሱነቱን ለመጨረሻ ጊዜ እንዳገኛች ቆጥራ እሷ ራሷም በደንብ ናኝችበት ። ፈጣን እንቅስቃሴዋ እፀግነትን አስታወሰው ። ወዲያው ፈዕሞ ረሳት ።

ትንሽ ቆይታ ታለቅስ ጀመር ። ሁኔታዋ አሁንም የእፀግነትን ሁኔታ አስታውሰው ። አጋጣሚው ያለፈ ትውስታ ከአሁኑ ጋር እየተሰበጣጠረ ግራ አጋባው ።

በአንድ በኩል ሴቶች ለቅሶን ለምን እንደመፍትሄ እንደሚቆጥሩት እያሰላሰለ በዘዴ ወጥ አሰኛት ። ድጋሚ መቃበጥ አላማራቸውም ። ልብሶቿን ለባብሳ በስርአት ተቀመጠች ።

"ለምን አንወጣም ?" አለችው ድምጿን አለስልሳ ።

መልስ አልሰጣትም ። አውልቆ የነበረውን ጀኬት አንግቦ ተነሳ ። ቦርሳዋን ይዛ ተከተለችው ። ሆቴሉ ውስጥ እንዲቀመጡ ያቀረበላትን ጥያቄ አልተቀበለችውም ። ጠባቧን ቮልስ መረጠች ።

ነገሩን ማንሳት ትጀምርና ሰውነቷ መንዘፍዘፍ ሲከጅለው ፡ አምቃ ታግላ ታሸንፈዋለች ።

"እስከመቼ ?..." አለችና ሰፈውን የፊቱን ገጽታ እያስተዋለች "... እኔም ባለትዳር እንዳማገጥኩ ፡ አንተም ጠቅሜ ላልጠቅምህ በኔ መከራህን ታያለህ?"

ንግግሯ ለውይይት የሚጋብዝ አይነት አይደለም ። ውሳኔ ይሁን ምክር መለየት አዳግቶታል ። "እንዴት እናድርግ ትያለሽ?" አላት ፊቱ ተባ እያለ ።

አቅማማች "መቼም በዚህ ሁኔታ መቀጠል እንደማንችል ይገባሃል፡ አይደል ?... አይኗ ውሃ እያረገዘ አስቸገራት ። "...እንዳመጣብኝ

ልለያይህ ነዋ !" አለችና ስቅታዋ የእንባቷን ደምስሮች ሁሉ እየተናነቀ ዕንባዋ ይወርድ ጀመር ። ክንፈ መሪውን በቡጢ ነረተ ።

"አዜብ ለቅሶኽ መፍትሄ አይደለም ።"

"ለሴት ልጅ ግን መፅናኛዋ ነው ።"

የሚያደርገው ግራ ገባው ። ትከሻዋን ፡ ማጅራቷን ይደባብሳት ጀመር ።

ቀልቱው በደፈረሱት አይኖቿ አየቸውና ፡-

"ክንፈ እወድሃለሁ ፡ ልለይህ አልፈልግም ፡ ግን እለይሃለሁ ! ይገባሃል ? ካንተ ጋር ብሆን ደስታዬ ወሰን የለውም ። ታውቃለህ ? ለኔ የተፈጠርክ ብቸኛ ሰው ትመስለኛለህ ፡ ነህም ፡ ግን የኔ አይደለህም ... ተቀደምኩ ።" እንባዋን መግታት አቃታት ። ዝም እንድትል አባበላት ። መናገሯን ግን አላቆመችም ። የሚያደርገው ቢያጣ የራሰውን መሃረቧን በመሃረቡ ቀየረላት ። "ገባህ ክንፈ ? ጣውንትነቴ እንዲሰማኝ አልፈለ ግም። ግን ሆንኩ አይደል ?" አንዳች ምላሽ እንዲሰጣት አይኖቿን በፊቱ ላይ አንከባለለቻቸው ፡ እሱም የሚመልስላት አጥቶ ግራ ተጋባ ። ቢጨንቀው "ከዚህ ቦታ እንሂድ !" አላት ። ጥያቄው አልገባትም "ምን ለመሆን ?"

አመንትቶ ዝም አላት ። እሷም በተስፋ መቁረጥ አይን ተመለከተ ችው ። እይታዋን ከሱ ላይ አነሳችና በመኪናው መስኮት ወደ ውጭ አትኩራ እየተመለከተች ፡

"ክንፈ ያጠፋህ ያክል ሆኖ አይሰማህ ። መተዛዘን ፡ ማዘን ፡ መከፋት በአንባራዊነት የምንቀበላቸው የሰውነት ድርሻዎቻችን ናቸው ። ምን ታደርገዋለህ ?... የኔ ግን በአንባራዊ መልኩ አይደለም ። ሁሉ ሐዘንተኛ ፡ ሁሉ ተከፊ ነኝ ። ሁሉም ብቸኛ..." አሁንም ሲቃዋ ያስቸግራት ጀመር ፡ "... በተፅዕኖ የኔ የምላቸው ሰዎች አጋጣሚና ምክንያት እየፈለጉ ይለዩኛል ። እነሱም ባይፈልጉ ፡ ተፈጥሮ ምክንያት ፈልጋ ከኔ ትለያቸዋ ለች ። የአጋጣሚ ነው እንዳልል መለየቱ በኔ በዛ ። በሰፈው አለም ውስጥ እኔነቱን የሚያስተውል ጠፋ ። ባልጠፋ ሰው ብቻዬን የተፈጠርኩ ያህል ፡ አለም በብቸኝነት ስታስጨንቀኝ ፡ ስትፈታተነኝ ግማሽ ዕድሜዬን ገፋችው ክንፈ..." በእንክሮ ተመለከተችው ። "...ፍፁም ብቸኝነቱን የምረላው ካንተ ያለነም ከፈጠርኳቸው ገፀባህሪያት ጋር ስሆን ብቻ ነው። ሁለታችሁም ህልውናዬ እየሆናችሁ ተፈታተናችሁኝ ፡ ማንኛችሁን

Scanned with CamScanner

ልተው? ይህ ለኔ ከባድ ፈተና ነው ። ካንተ ጋር መሆን ከጀመርኩ የፈጠረ
አድባሪ ቀንታ ይውን አኩርፋ አላውቅም መዛፍ አልችልም ። ለመዛፍ
ስነሳ ሁለት ፈተና ከፊቴ ይጋረጣል ። አንተና ብዕራ! አሳቢ ወዳንተ
ያደላና ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጌ እተዋለሁ ። ሁሉን ትቼ ስላንተ ላስብ
ደግሞ ፡ የሌላንትሀና ጣውንትነቴ ከፊቴ እየተጋረጠ ሰላም ይነሳኛል ።
በአመታት የኖርኩባቸው የብቸኝነት ጓደኞቼ እንኳን ከዚህ አላስጣሉ
ኝም። ዘልቀህ ውስጤ ድረስ ገብተሃል ፡ ይገባሃል ? አዎ ማንም እንዳንተ
የሚረዳኝ አላገኝም ። ይህን እያወኩ ደግሞ መለየትን ማሰብ ሕይወቴ
በብቸኝነት ከሲኦል ሲኦል እንጦርጦስ ስትወረወር ይታየኛል ። ይኸው
ልህ ከባድ ፈተና !" አለችና ወደቦርሳዋ ተመልከታ ዚፑን ተረተረችና
ከውስጥ የታሸገ ፖስታ አውጥታ ሰጠችው ። ግራ ተጋብቶ ተቀበላት ።

"ምንድነው?"

"እቤትህ ስትደርስ ለብቻህ አንብበው ።"

"ተይ አዜብ !" አላት እየፈራና በነገሩ እየተጠራጠረ ።

"በኔ ይውንብህ ።"

አመናት ።

አብረው ዋሉ ። ምሳቸውን በአ[illegible] ላይ ተቋደሱ ። ረፋዱን
እስከማምሻው ከከተማው ውጪ ሲንሸራሸሩ ቆዩ ። የአ ፡ባቢው ባና ፡
ሜዳው ፡ እርሻው በልምላሜ ተውበው በመ ፡ረስ ላይ ታላቅ የመግነጢስ
ኃይል ያሳድራሉ ።

ጀንበሯ ስታዘቀዝቅ ወደከተማ ማቅናት ጀመሩ ። በድንገት
"እቁምልኝ" ብላ አስቆመችው ። ግራ ተጋብቶ ተመለከታት ። በጣቷ
ወደጀንበሯ ጠቆመችው ።

"እየሃት ጀንበሯን ?"

"አዎ"

"ደስ አትልም ?"

"በጣም !"

ውስጧ በሃሴት እየፈነደቀ "ተፈጥሮ ትማርከኛለች ። ቅጣቷ
ቢያስከፋኝም ውበቷ ያፅናናኛል ። ስለተፈጥሮ አውርቼልህ አውታለሁ?"
አለችው ።

"አይ!" አላት አንገቱን እየነቀነቀ ።

"ጀንበር ስትጠልቅ ማየት እንደምወዳ ታውቃለህ ?"

"አዎ!"

ፈገግ አለች "ይሄንንስ መጠየቅ አልነበረብኝም ። የልብ አውቃኔት
ህን መች አጣሁት ... ጀንበር ሳይ የወደይ ብርሃን ተግባሯን አከናውና
ስትገባ የምትሰጠን ልዩ ውበት በወጣትነት እድሜ እመስለዋለሁ ።
ውብና አጭር ጊዜ ። ዘመኑ በቅዕበት መንገዱ ሲታሰበኝ ፡ በጀንበሯ
እየተደሰትኩ በሌላ ወገን አዝናለሁ ። እንግዲህ ይታይህ ! ጀንበሯ
ልትጠልቅ ስትል ፡ ሁለት ተታራኒ ስሜት በውስጤ ታላድራለች ። ሀዘንና
ደስታ ! ታዲያ ይህ የተፈጥሮ ምስጢር አይደንቅህም ? የባህር ሞገድና
ግዝፈት ከየዋህነትና ርህራሄ ጋር እየተዛመደ ፡ ከጀንበር መግቢያ
ጣፋጭና አጭር ዘመን ጋር ፡ በተለይ ደግሞ ሁለቱን በአንድ ላይ
ካስተዋልኩ ራሴን እስክስት በስሜት እዋጣለሁ ። አይገርምም ?"
አለችውና እንዲሄዱ ነግራው መኪናውን አንቀሳቀሰ ።

ክንፈ ስለሷ የተሰማውን ጠንቅቆ ማወቅ አልቻለም ። እሷን ቤቷ
አደረሰና ወረቀቱን ለማንበብ ወደቤቱ እየተጣደፈ አመራ ።

* * *

ክንፈ የተዳባዮቹን ስሜት አላጤነም ። በእመት በአሉ ምድር ቤቱን
ጭሎ ብቻቸውን ስላዋላቸው የተሰማቸውን ስሜት በገያቾቸው ሊያሳዩት
ቢሞክሩም አላስተዋላቸውም ። የቸኮለው መኝታ ቤቱ ገብቶ ደብዳቤውን
እስከሚያነብ ድረስ ብቻ ነው ።

እጁ እየተንቀጠቀጠ ፖስታውን ቡትርፍርፉን አወጣው ። በልቡ
የመኝታ ቤቱን በር መቆለፉን አረጋገጠ ። ለምን ይህን እንዳደረገ ማወቅ
አላስፈለገውም ። ብቻ የሚገጥመው ነገር ደግ እንዲሆን ፈጣሪውን በልቡ
ተማፀነ ። ወረቀቶቹ ራሳቸው ይንቀጠቀጡ ነበር ። ራሱን እየታዘበ ፡
ደብዳቤውን ይነብ ጀመር ።

'ክንፈ ፡ እጅግ ለሚያፈቅሩትና ለሚወዱት ሰው ደብዳቤ መጫር
ደስታን የሚሰጥ ፡ እርካታ የሚያጐናጽፍና ቀላል መስሎ ይታየኝ ነበር ።
ተሳስቻለሁ ። የምጥ ያክል ተጨንቄያለሁ ። ስሜቴና ታላቁ አልሰምር
አልገሰጥ እያሉኝ ተወናብጀለሁ ። ከዚህ ወረቀት በፊት ሶስት ወረቀት
አበላሽቻለሁ ። ይህ የመጨረሻዬ አይሆን ይሆናል ። የኔ ወለላ ! ከየት
ልጀምርልህ ? ገና ከተድሞው የዩኒቨርሲቲ ግንኙነታችን ፡ ወይንስ

Scanned with CamScanner

ግንኙነታችን ዳብሮ ከጐለመሰ በኋላ ? ወይስ ህይወት ጅረት መልሶ ካቆረጠን ወዲህ መጥፎ ሁን ጥሩ ፍጹም ከማልገነዘባት ከቅርቧ ቀን ልጀምር ?።

'ተምታቶብኛል ። ብቻ ወስኛለሁ ። ውሳኔውም ለኔ እንጂ ላንተ ህይወት ትክክለኛ መስሎ ይታየኛል ። አብራህ ብኖር መደሰቴን አውቃለሁ ። አንተ ለኔ ደስታ መስጠትህን አልጠራጠርም ። እኔ ላንተ ደስታ መስጠቴን ግን እርግጠኛ አይደለሁም ። ነፍሴ እንዴት አድርጋ ለሁለት ጌታዋ ልትሆን እንደምትችል አላውቅም ። አጉል ሙከራ ሞክሬ ነበር ፡ አልተሳካልኝም ። በልቤ ውስጥ ሁለት ፍቅሮች ሲበሉኝ ይታወቀኛል ። ያንተና የኪነጥበብ ፍቅር ። በሁለቱ ፍጭት ነፍሴ ተጨንቃ መሞቷ ነው ። ከወዲሁ አንድ ነገር መወሰን አለብኝ ።

'የኔ ጌታ ! አፈቅርሃለሁ ። ፍቅሬ ግን ያለቦታው መሆኑ እየተሰማኝ ሄዷል ። ባለትዳር ነህ ። በህይወትህ ላይ በተፈጠረብህ ስንክሳር ተጨማሪ መሆን አልነበረብኝም ። ግን ምን ታደርገዋለህ ! 'ፍቅር የራስ ወዳድነት ምልክት ነው' የሚለውን ጥልቅ የሳይኮሎጂስቶች አባባል ስታጤነው በወንዳዊነት ትቀበለዋለህ ። ይህ ደግሞ እርባና ቢስ ያደርገኛል ። ራስ ወዳድነቱን ማወቅ አልፈልግም ። ደግሞ ብቸኝነቴን እጠላዋለሁ ። ለብቸኝነቴ መድሀኒት ያገኘሁ ሲመስለኝ ራስ ወዳድነቴ ደግሞ ጐልቶ ይታወቀኛል ። ብቻ ምናለፋህ አንዳቸው በአንዳቸው ጀርባ እየተከለሉ ያባዝኑኛል ።

'የህይወት ዕድሏ እንዴ ነው ። በውስጧ የሚገኙ አጋጣሚዎችም እንዲሁ ከእንዴ አይዘሉም ። ከዚህ ቀደም በህይወቴ ስመጥኝ ። እንደምንም እውጥቼ ጣልኩህ ። እንለያያለን ብዬ አልነበረም ። ሴት ልጅ ብዙውን ጊዜ ውሳኔዋ ድንገተኛና በተለይ ደግሞ አይሆንም እያለች ነው ። ይገርምሃል ። እንለያይ ስልህ እውነት የምንለያይ አልመሰለኝም ነበር ። ግንኙነታችን ሲቋረጥ ግን ደነገጥኩ ። መለየት ብፈራም ፡ በተለይ ካንተ በቀላሉ እለያለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም ። እድሜ ልኬን አንተን ደግሜ ላገኝ የምችልበትን ዘዴ ሳውጠነጥን ከረምኩ ። መንገዱ ጠፋኝ ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን ፡ በልቤ እንዳች ክፋት አላሰብኩም ። ብቻ በደፈናው ላገኝህ እዋትት ነበር ። ጊዜ አጋጣሚውን አመቻቸልኝ ። አላመናታሁም፡ በእድሉ ተጠቀምኩበት ፡ አገኘሁህ ። ግን የድሮው ከንፈ አይደለህም ። ያንተ መለወጥ ሳይሆን የኔ ።

'እንደቀድሞው የግሌ የብቻዬ አድርጌ ላስብህ አልቻልኩም ። ሌላው ደግሞ ያ ጥንት ዘወትር የሚፈታተነኝ መለየት ዛሬ ወይም ነገ ደግሞ እንደሚመጣ ስለማውቅ መንፈሴ ሰላም አጣ ። ልትለየኝ እንደምትችል ማወቁ ፡ አንድ ቀን መሆኑ እንደማይቀር ከመጠራጠር አልፎ እርግጠኛ እያደረገኝ መጣው ፡ መንፈሴ ሰላም አጣ ።

'ሙስጠ ሊረጋጋ ባለመቻሉ ወደፊት ራሴን መስሞአት ላደርግ የተዘጋጀሁለት ድርሰት በመዘንጋቱ ሰላሜ ደፈረሰ። ሁሌታትሁ በውስጤ ትራቅቱ ጀመር ። እኔነቴ ለውሳኔ ተዳረገች ። ክንፈ ምን ታደርገዋለህ ! ሕይወቴ መለየት እጣ ክፍሏ ነው ። የአሁኑ ምርጫዬ ግን መኖርን እስክጠላ ተፈታትኖኛል ! ሕይወት መራራ ነች ። በተለይ እኔን በእጅጉ ተፈታትኖኛለች ። ይህማ ጉዴን ተረድታ ወቅራኛለች ። እንባዬ አልገታ ትም ፡ ብሶቴ አልተሰማትም ። ለሰቆቃዬ ልቦና ቢኖራት ተደናቂራ ትቀር ነበር ። እርሱም አልሆነም ። ሕይወት ፍቅር ነው ። ፍቅር ሕይወት ነው ። በተለይ ለሴት ልጅ ፡ ካንተ ስለይ ሕይወት አልባነት ይሰማኛል ። አብራህ ልኖርም አልቻልኩም ።

'ክንፈ ለመሆኑ የልቤ ሰቆቃ ይሰማሃል ? ዝንተ አለም አንተን እንዳከበረህ ይኖራል ። አካል ባዳ ነው ፡ ከሌላም ይለምዳል ። ክንፈ ፡ ቢሆንም ሰው ሁሉ እንዳንተ አይደለም ። አካሌ እንጂ መንፈሴ ከማንም አይቆራኝም ። ከሰው ብኖር እንጂ ተጣጥሞልኝ አይደለም ። ተፈጥሮን ታገልን እንጂ መቼ ተረታችልን ? እም ሕይወት እጣ ፈንታዋ አንድ ነው ።

' ህይወትህ በኔ እንዲሰቃይ አልሻም ። አንዴ የበደልኩህ ይበቃል ። የእድሜ ልክ በዳቴ ! ጊዜ ያለፈበት ዕዳ ደግሞ ዋጋ የለውም ። ልብን ያዳክማል ። ሁሉ ሚታ አምሽቼ ወደ አልጋዬ ስሄድ ምን አልማለሁ መሰለህ ? በአልጋዬ ውስጥ አንተን ። ለራስህ ባታጤነውም ድንቅ ሰው ነህ። ብዙ ጊዜ ጥሩ ሰዎች ለራሳቸው የሚኖራቸው ግምት አናሳ ነው ። በራሳቸው እይመኩም ። ስለዚህ ሙገሳዬ የዘፃ ይመስልህ ይሆናል ። ግን ትክክል ነው ።

'እስካሁን በትዳር ያለመኖሬ መንስኤ ምን መሰለህ ? አንድ ቀን አንተን አገኛለሁ የሚል ተስፋ ! እድሜዬ መግፋቱ ይሰማኛል ። ሆኖም በመጨረሻ አገኘሁህ ። ግን አንዳች ነገር እንደቀድሞው አይገኝም ። የራስ አስተሳሰብና እምነት እንኳን ካላሰቡት ቦታ ይገኛል ። ስለራሴ ከስነ ፅሁፍ ስራዬ በቀር የምተነብይልህ አንዳች ነገርም ሆነ ተስፋ የለኝም ። ህይወት

Scanned with CamScanner

ለኔ እጅግ በጣም ቀዝቃዛ ነች ። በብእሬ ዘወትር ተስፋን ፡ ደስታንና እርካታን ለመግለፅ እሞክራለሁ ። ድንገት በልቤ ያጣሁትን ከወረቀቱ አገኘው እንደሆነ ብዬ !

'የኔ ውድ ! የመጀመሪያ የስነፅሁፍ ስራዬ የተሳካ ከሆነ መታሰቢያነቱን ላንተ ባደርገውስ ? ላደርጋቸው ከምፈልጋቸው ዋነኛ ነገሮች አንዱ ተሳካ ማለት ነው ። ፍቃድህን መጠየቅም አያስፈልገኝም ።

'ከንፈ የባለቤትህን ነገር አደራ ። ይትር፟ታ አድርግላት ። ከአሁን በኋላ የአንተና የኔ የግንኙነት መስመር ሁለታችሁን በተመለከተ ጉዳይ ብቻ ይሆናል ። ልትታረቃት ይገባል ። ለኔም የበደሉ ካሳ ይሆንልኛል ። ላንተም የተረጋጋ የወደፊት ህይወት ቀና መንገድ ይሆንልሃል። ስለዚህ ለሁለታችን ስትል ይህን አድርግልኝ ። ያለሳ የህሊና እረፍትና ሰላም አይኖረኝም ። አደራ ከንፈ! ቻው ።

እህትህ አዜብ

እንብበህ እንደጨረስክ አቃጥለው ።'

ከንፈ ደብዳቤውን እንብቦ እንደጨረሰ አምርሮ አለቀሰ ። ትንሽ እንደቆየ ሽፈራው የመኝታ ቤቱን በር ይደበድበው ጀመር ።

"ከፈት እንጂ ምን ሆነሃል ?" አለው ሽፈራው እየተቆጣው ፡ ሰአቱን ሲመለከት ሁለት ሰአት ሆኗል-ከምሽቱ ፡ ጥፋቱ ሁሉ ተደራርቦ ተሰማውና የሁለቱን አይን ማየት ተሳቀቀ...

ምእራፍ አሥራ አምስት

ከላይ እስከታች ያጠለቀችው ጥቁር ቀሚስ ከአቋሟ ጋር መሄዱን መስታወት ውስጥ ታስተውላለች ። ጥቁሩ ልብስ ፡ በቀይ ሰውነት ላይ ጉልህ የመሆን ዐባይ አለው። እወንነት በመስታወት ውስጥ በተመለከተችው ገፅታ ፈራች ። ለፋሺን ስትል ያጠለቀችው እንጂ በፍፁም እዘንተኛ አልመሰላት አለ ።

ረዘም ያለ ጥቁር ጉርድ ቀሚስና ከላይ ወፈር ያለ ፡ እንገተ ክብ ፡ እጅጌ ሙሉ ፡ ድፍን ጥቁር ሹራብ ሞከረች ። በምርጫዋ ተስማምታ ከመስተዋቱ ፊት አንድ ሁለቴ ዞረች ። 'የዘዘን ልብሱ እምርባታል... እንኳን ዘመድ ውሻ የሞተባት አትመስልም...ዘዘኑ ተስማማት አይደል?' የመሳሰሉትን አባባሎች እጅግ አድርጋ ትጠላለች ። ጽሲን ከዚህ አይነቱ አሉባልታ ለመሰወር ትጥራለች ። ለሰሞኑም ቢሆን ለቢሮ የወፈ ምላስ ግሚሻ መሆን አልመረጠችም ። ልማድ ደግሞ እግር ከወርች አሥሯታል ።

ሐዘን ያጋጠማት ሴት ፡ ማት ለብሳ ፡ እንባት ደፍታ ፡ ተጉሳቁላ ካልታየች አረመኔ ነች ያስብላታል ያውም ወንድምን ያህል ነገር ! በዚያ ላይ ለተወሰነ ጊዜ ከሳቅና ጨዋታ አካባቢ ገለል ማለት አለባት ። ስትገባ ኮስምና ስትወጣ ተክካ ካልሆነ ልበድንጋይ ያሰኛታል ።

እወንነት እንደድሮው ወጉሯን ዘንፈል አድርጋ ትከሻዋ ላይ መተው አልፈለገችም ። ወደ ላይ ጠቅልላ ከሩ ባለ ወንር መያዣ ማጥም አድርጋ ካስያዘችው በኋላ ፡ በባለወንፈት ጥቁር ሻሽ ጥብት አድርጋ አሰረችው ። ፊቷን በእንዴ ሜርታ ወረሰው ።

የተፈለገውም እንደሳ ለመሆን ነው ።

እንደሌላው ጊዜ ኩልና የከንፈር ቀለም አላስፈለጋትም ። ቦርሳዋን አንስታ ከቤት ወጣች ። ግቢ ውስጥ ሽራ ለብሳ የቆመችውን መኪና አየች። በዚህን ሰዓት ኤርሚ የመኪናውን ሞተር ያሚሙት ነበር ፅንባ በእይኗ አቀረረ ።

የመናርን ትርጉም እያሰላች ወደታክሲ መጠበቂያው አመራች ። የሰኞ ማለዳ የትራስፖርት ችግር ደግሞ ከዘወትር ቀናት ይለያል ።

ትዳሯን በወጉ ሳትይዝ የዘመድ አዝማድ መዘባበቻ ሆና ትቅር?

Scanned with CamScanner

አልተናደደችም ። በልቧ ግን መጥፎ ስሜት እያንሳፈፈ ወሰዶ አጉል ቦታ ጣላት ። የዋህነቷና ግልፅነቷ ፣ ለሰዎች ያላት ቀና አመለካከቷ ዛሬ ጥቁር መነጽር ደንቅሮባት አለምን አክፍቶ አሳያት ። የለመደችውን ሕይወት የመኖር ፍላጐቷን ደብዛውን እያጠፋው ፣ ሰላምና እርካታ እያጣች ትኖራለች ።

የከንፈ ሁኔታ ቢያቀርባትም የራሷ ሐጥያት ዳግሞ ያሸሻታል ። በሷ ፊት ሄኖክ ሰው አይደለም ። አዳምንና ሄዋን አስቶ ከገነት እንዳባረራቸው እባብ ትፈራዋለች ። በትዳሯ እያለች እሱ እንዴት ቀልቧን እንደገፈፋት ከዛን በኋላ ለምን እንደፈራችው...ሕይወት እንቆቅልሽ ሆነችባት – ሴላ መልስ የላትም ። ብቻ ይቅርታውን በምን ታግኘው ?

በስንት ግፊያና ትርምስ ታክሲዋን አግኝታ ቢሮዋ ደረሰች ፣ ለቅሶዋን የደረሰ እየቀረበ የትህትና ሰላምታ ሲያቀርብላት ፣ ያልደረሰም ሲሸኛት ።

"እፀገነት ፣ ከእንግዲህ አይዞሽ ፣ በርቺ" ብለው አፅናንተዋት ገቡ አለቃዋ ።

ቢሮዋ ተቀምጣ በመስኮቱ ወደውጪ ተመለከተች ። ሁሉም ነገር ያስገርማል ። ሰዎች ከዘወትር እንቅስቃሴያቸው አንዳች ለውጥ አያሳዩም። ለአፍታ ከአካባቢው የተገለለች ያክል እየተሰማት አንዳች ለውጥ ይኖር ? በማለት ውስጧ ያሰላ ነበር ። ግን ምንም የለም ። ሁላችንም አለማችን እንደልባችን ፅልመትና ፍካት የምትለዋወጥ ይመስለናል ። ግን አንዳች ቅፅበታዊ ለውጥ አናስተውልም ።

ለብዙ ቀናት የተለየቻቸውን የጠረጴዛ መሳቢያዎቿን እየከፈተች ፣ ቃኘቻቸው ። ከዘወትር አቀማመጣቸው ለውጥ አላሳዩም ። አዛጋች ። አይኖቿ አሁንም ዕንባ አረገዙ ። ሆድ ባሳት ። አለም ሁሉ የጠላት መሰላት። አሁንም በራሷ እጅግ አድርጋ አዘነች ። እየተጣደፈች ከቦርሳዋ መሐረቧን አወጣች ።

* * *

ሄኖክ በተደጋጋሚ የመሥሪያ ቤቷን ስልክ ቢሞክርም ሥራ አልገባችም ይሉታል ። ደውሎ ካገኛት ወዲህ ልቡ አላረፈም ። 'ገና ይቀራል' ሲል ለራሱ ተናገረ ።

ደግሞ እንደዚያ ተናግራው ስልኩን ከዘጋችበት ወዲህ ፣ በደሏ

ተደራርቦ ተሰምቶታል ። 'ትንሿ ሰይጣን' አላት በልቡ ፣ እሷነቷን እየረገመ ። ዛሬም በቅድሚያ ቢሮው እንደደረሰ ስልኩን የሞከረው እሷው ጋ ነው ፣ ተሳካለት ፣ አገኛት ።

ስልኩን ከዘጋ በኋላ 'ምን አባቷ ያንጠባርራታል' አለ ለራሱ ። ሳይታወቀው ድምፁን አጉልቶ ኖሮ "ምነው ምን አረገችህ?" አለው የቢሮው ጓደኛው ማንነቷን ባያውቅም እንዲሁ በደፈናው ።

"ምን እነሱ የማያደርጉት አለ ብለህ ነው?"

"ወዳጅ ማብዛት ትርፉ ይኼው አይደል?" አለ ሀሰን ተንጠራርቶ"

"እሽ...." ብሎ ወገቡን ወደኋላ እንደላስቲክ ለጠጠው ።

"የኔ ወዳጆች ካንተ አይበዙ ። ይልቅ ቢሮ ከመግባቴ አንዷ ደውላልህ ነበር ። አንተ እስክትገባም ትእዕግስት አልሰጣት ። ለመሆኑ ምን እያቀመስካቸው ነው?" አለው ሄኖክ ።

"የወንደላጤ ደንቡ ነው ። እንዳልከው ግን የማቀምሳቸው መድሀኒት የለኝም ። መድሃኒቱ የምሰጣቸው ንፁህ ፍቅር ነው ።"

ሄኖክን አሳቀው "ፍቅርህን ለስንቱ አከፋፍለህ ብትዘልቀው ነው?" "ለሰው ዘሮች ሁሉ"

"ሀሰን!..." አለው ሄኖክ ጨዋታውን በአስተያየቱ ወደቁም ነገርነት ለመለወጥ እየፈለገ።"...ሴቶች ለመሆኑ ከሁሉ አስበልጠ ሊማር ካቸው የሚችለው ነገር ምንድነው?"

ሀሰን ለምን ይህን ጥያቄ ሊጠይቀው እንደፈለገ እያስገረመው "ምንልበልህ ፣ ሴትን ልጅ የማይማርካት ምን ነገር አለ? ፣ ቀይ ወንድ ያለዛም ጥቁር ፣ ጡንቻው የፈረጠመ ያለዛም ቀጫጫ ፣ ረጂም ፣ አጭር ምን ልበልህ እንደ ሴቱ አይነት ይለያያል" አለው አይኖቹን አጨንቁሮ ጢሙን ወደታች እየሞገተ ።

"እንደሱ ማለቴ አይደለም ። እንዳው ባጠቃላይ ሴቶች በአብዛኛው ሊማርካቸውና ሊያሸንፋቸው የሚችል ነገር ።"

ሀሰን ጣቱን ወደላይ አውጥቶ እያንጠባጠበ "ዝና...ዝና...ዝና... ነው ሴቶችን ተፈታትኖ የሚፈጠርቃቸው ገመድ ። የትኛዋም ሴት ዝና ላለው ወንድ ትግረከለታለች ። መሆን ባትችልም የሱ የመሆን ፍላጎቷ ግን ከውስጧ ይኖራል ። ታዋቂ የሆነ ወንድ ነፍሳቸው ነው ። ቢሳካላቸው በዚህም በዛም ብለው የራሳቸው ሊያደርጉት ይሞክራሉ ። በተለይ ይህ

Scanned with CamScanner

የለለጠኑ ሀገሮች ሴቶች በሽታ ነው ። እንኳን በውን ላውቁት በየቴሌቪዢኑ እና በየመፅሄቱ ላዩት ታዋቂና ዝነኛ ወንድ በእጅጉ ይወድቁለታል ። ለዚህ ነው በሙዚቀኞች ፡ በፊልም ተዋናዮች እና በመሳሰሉት የሚበዛ ። በስፖርት ፡ በስነ ጥበብ በመሳሰሉት የሙያመስኩች ያሉ ግለሰቦች ከሕብረተሰቡ ጋር ባላቸው ቀጥተኛ ተዛምዶ ለእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ይጋለጣሉ ። ይህ ደግሞ ከሴቱም አልፎ በአንዳራዊ ሁኔታ በወንዶች ላይ ከፍተኛ የመንፈስ ተዕእኖ ያሳድራል ። በቅርቡ የሆነውን አልሰማህም?›› አለውና ወደ ጠረጴዛው መሰቢያ እጁን ሰዶ መዕደት እያወጣ “...ይሽውልህ በቅርቡ በአለማችን ከማንኛውም በላይ ስሙ እየገነነ የሄደው የሚዳ ቴኒስ ተጫዋች ይህ ነው ። እንዳውም በጀርመን አገር ውስጥ ‘ከጀልስዋገን መኪና ቀጥሎ ስሙ የሚጠራ ጀርመናዊ’ እያሉ ጋዜጠኞች ይናገሩለታል ። ታዲያ መቼም በዳበሩትና ሰለጠን በሚሉት አገሮች የማይሠራ ነገር የለም ግለሰቡን የሚፃረር ክበብ ተቋቋመ ።

“ማን መሰለህ የክበቡ ስያሚ ‘ቢከር ምናባቱ’ የሚል ነው ። ታዲያ አንዱ ለምን የክበቡ አባል እንደሆነ ሲጠየቅ ያለውን ልነግርህ ። ‘ከሴት ወዳጄ ጋር ሆነን ጨዋታውን በቴሌቪዢርን በምንመለከትበት ጊዜ እሷ በሱ በመመሰጧ ሙራሽ ከነመኖሬም ትረሳኛለች ። እና እናደድበታለሁ› ሲል እማኝነቱን ገልጿል ። ይህ ሁኔታ በኛም ሀገር እየተለመደ መሄዱ ጀምሯል ። ለዚህ ነው ወጣት የፈጠራና የስፖርት ሰዎቻችን በአጭሩ በሴቶቻችን እየተጠለፉ የሚቀሩት ፡ ጠንካሮች ብቻ ናቸው ይህንን ፈተና የሚወጡት ፡ እና ሴቶች ልጆች ከማንኛቸውም ይበልጥ ዝነኛን ያሳድጻሉ። ግባቸው ግን አደገኛ ነው ። ምክንያቱም እሱነቱን ሳይሆን ዝናውን ስለሚሹ ነው ። ዝና ደግሞ በአብዛኛው የእለት ተእለት ክንዋኔ ውጤት ነው። ያለፃ ዛሬ የተጨበጠች ዝና ነገ የሌላ ትሆናለች ። እነሱም ትኩረታቸው ያኔ ወደሌላው ይሆናል ። ”

ሄኖክ በመጠኑ ፈገግ ብሎ ትንሽ አሰላሰለና “የሚጠሉትስ?” አለው።

“ምን ልበልህ ፡ ሴት ልጅ መጥፎ የሆነውን ነገር ሁሉ እንደማንም ሰው ትጠላለች ። ከተቃራኒ ፆታዋ ጋር ባላት ግንኙነት ግን ሴት ልጅ ከሁሉ አብልጣ መበለጥን ትጠላለች ። መበለጥ ሞቷ ነው ። ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ ሴቶች ልባዊ የሆነ የሴት ጓደኛ የማይኖራቸው ። በራሷ እጅግ አድርጋ በማንኛውም ነገር የምትመካ ሴት ትተሃት ከአስቀያሚ ሴት ጋር

እንኳን መወዳጀትህን ካየች ውስጧ ይበግናል ። ይህ ሳያስታውቅባቸው የሚያሳልፉ አሉ ። ቢሆንም መናደዳቸው ግን የማይቀር ነው ። በተረፈ ሴትነታቸውን የማያከብር ወንድ ያናድዳቸዋል ። በተለይ ደግሞ በአብዛኛው የራስ በራስ እምነትና ጥንካሬ የሌላቸው ስለሆኑ ትንሽ ነገር ይበቃቸዋል ። ሴት ልጅ አካባቢዋን ከመጥላቷ በፊት ራሷን አስቀድማ ትጠላለች ። ይህ ራሷን ዝቅ አድርጋ ከመገመት የመጣ በሽታ ነው ። በተረፈ ሴት ልጅ በምንም አይነት መበለጥንአትቀበልም ። አጥብቃም ትጠላዋለች ።

“ፈረንጆች ምን ይላሉ መሰለህ ፡ ‘ሴት ልጅን መግደል በጥይት ሳይሆን በቤተ ነው’ ይላሉ” አለውና “ግን ይህን ሁሉ ለምን ጠየከኝ?” አለ የቢኩን ጫፍ በጥርሱ እየነከሰ ።

“አይ እንዲያው ነው” አለ ሄኖክ ጥያቄውን ጠልቶት ።

ሀሰን ሁኔታውን አይቶ “ለዕውቀት እንጂ ለክፋት እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ።”

ሄኖክ መልስ አልሰጠውም እያፋሸከ ቢሮውን ከፍቶ ወጣ ።

* * *

እፀገነት ከስንት ጭቅጭቅ በኋላ ቀጠሮውን መቀበሏ አናዷታል ። ሙራሽ ባታገኘው በወደደች ፡ ግን ደግሞ መንቻካ ሆነባት ። አሁን አሁን ሄኖክ ምኑም አያጓጓትም ። ስሜቷ በጭንቀት ባክኖ ፍፁም ሊፍታታላት አልቻለም ። ስለዚህ ሄኖክን ማግኘት አትሻም ።

‘ብሽቅ!’ አለች ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የስድብ ማጎደር ሆናለች ። ቤት ውስጥ መሳደብ፣ መነጫነጭ ፡ ራሷ ሰላም አጥታ ሌላውንም ሰላም መንሳት ።

* * *

“ተው ሄኖክ እንደሱ አትበል ፤ ለምን ያለፈ ጉዳይ እንደአዲስ ታነሳለህ? ለምን አትተውውም ።”

“በደልሽ ነዋ! ማሞኘትሽ ነዋ የሚያንገበግብኝ ፡ ሀጢያትሽ በዝቶብኝ ያንገሸገሸኝ ፡ ባዳፍነው ልተወው ብለው እንቢ እያለ ሰላም የነሳኝ ፡ ያ ሁሉ አንሶሽ አሁን ደግሞ ...”

“በቃ ተወኝ ብዬሃለሁ....” ሳይታወቃት በቁጣ ጮክ አለች ።

Scanned with CamScanner

መልሳ አፈረችና አካባቢዋን ቃኘች ። ምግብ ቤቷን በሞሏት ሰዎች ጫጫታ መሃል ድምጿ ተውጣ ቀርታለች ። ያስተዋላት የለም ። በአስር ሰአት ከስራ እንደወጣች በቀጠሯቸው መሰረት ካገኘችው ሰአት ጀምሮ ይነተርካታል ።

"ደግሞ ባንቺ ብሶ ያስጮሀሻል!" አላት አይኑን አጉረጥርጦ ።

"ወይኔ አምላኬ!" አለችና ራሷን ጠረጴዛው ላይ ደፋች ። አለቀቃትም ።

"እንውጣ" አላት ። አላቅማማችም ። ተያይዘው ወጡ ።

ወዴት እንደሚወስዳት ስፍራ እየመረጠ ሳለ " እዚህ ጋ ታክሲ ልያዝና ወደ ቤት ልሂድ" አለችው ቀና ብላ እየተመለከተችው ።

"አይሆንም!"

"ለምን?" አለችው ቆም ብላ አይታው ።

"ከኔ ጋር ትሄጃለሽ።"

"የት ነው የምሄደው?"

ቆጣ አለና "የትም ይሁን ፣ ከኔ ጋር አምሽተሽ ትመለሻለሽ ።"

"አልችልም" አለች ንግግሯን አክርራ ።

"እንዴት?"

ዝም ብላው መሄድ ጀመረች ። ትከሻዋን ስቦ አቆማት ።

"ምነው?"

"ምንም!"

አናደዳት ። "ባክህ ሄናክ ልሂድበት" ሁሉም ነገር የታክታት ትመስላለች ።

"አላበሳሽውም?"

ለአፍታ አትኩራ እያስተዋለችው "ትንሽ አይሰማህም ሄናክ? ሐዘን ላይ መክረሜን ረስተኸው ነው? ወይንስ ትእዛዝህን አክብሬ መምጣቴ ነው እንዲህ ያደረገህ" አለችው በጥልቅ እያዘነች ።

"እንደፈለግሽ ተርጉሚው ።"

በሸቀች ። ጥላው ልትሄድ ስትል በድጋሚ ጎተቻት ። ይሄኔ ትከሻዋን ምንጭቅ አደረገችና " ልቀቀኝ! አበሳኸው! ከመንገድ እንደም ትጎትታት ሸርሙጣ አልምሰልህ!" አጉረጠረጠችበት ።

"ትጠራጠሪያለሽ?" አላት እሱም አፍጥጦ።

"እንዴት?"

"ሸርሙጣ መሆንሽን ነዋ!"

ፊቷ ሲለዋወጥ ቢያስተውልም ጊዜ አልሰጠችውም ። ሁለት ጊዜ ደርሶ መልስ በጥፊ አጮለችውና ተንደርድራ ቆማ ያገኘቻት ታክሲ ውስጥ ገባች ። በአካባቢው የነበሩ በርካታ ሰዎች ተገርመው ቃኟቸው ።

ሄናክ በአሽሙር ፈገግ አለና ጉንጩን በመዳፉ እያሸ መንገዱን አቀና ። ድርጊቱ ብዙዎችን አሳቃቸው ።

ታክሲው ውስጥ እንባዋ እንደምንም አምቃ ቤቷ ደረሰች ። 'ኤርምያስ ይህን አለም ለመገላገል እንዴት ተሳካልህ?' አለች ታላቅ ወንድሟን እያሰበች ፣ አልጋዋ ላይ ተደፍታ ተንሰቀሰቀች ።

የአርባው ዝግጅት ቤቱን አተራምሶታል ። እፀገነት መምጣት አለመምጣቷን ያስተዋለ የለም ።

በድንገት 'ሁሉም ነገር ከንቱ ፡ የከንቱ ፡ ከንቱ ፣' የሚለው የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል ትዝ አላት ።

* * *

ሄናክ ቀጠሮ እንዳለበት ሰው እየተጣደፈ ወደ ፒያሳ አቀና ። ፒያሳ ሲደርስ አይን ያዘ አድርጓል ። ሞቅና ደመቅ ወዳለ የታወቀ መጠጥ ቤት ገባ ። ከትኩስ ነገርና አልኮል ሽያጭ በቀር እሱ የሚፈልገው ድራፍት ገና አልተጀመረም ። መቀመጡን ያየች የቤቱ አስተናጋጅ ወደሱ ቀረበ አለች። ሽቶዋ ክፍት ይጣራል ። በዛ ጫጫታ መሀል የምትለው ባይሰማም 'ከምን ልታዘዝ' እንደማያልፍ በመገመት "ድራፍት!" አላት ። አንገቷን ወደ ላይ እየመዘዘች ወደ ግድግዳው ሰአት ጠቆመችው ። ተመለከተው ፣ ለአንድ ሩብ ጉዳይ ።

"በስንት ሰአት ይጀምራል?" አላት ፣ ከፊቱ ለመሄድ ያኮበኮበች ውን አስተናጋጅ እየቃኘ ።

"በአንድ ሰአት!"

"እስከዛው አፕሬቲቭ " አላት ያልፈለገውን መጠጥ በማዘዙ ቅር እየተሰኘ ። የመጠጥ ቤቱ ሙዚቃ ከጣራ በላይ ይጮኻል ። የድራፍት መጠጥ መጀመሪያ ሰአት በቀረበ መጠን ደንበኞች ቤቷን እያጨናነቁት ሄዱ ። በአብዛኛው ወጣቶች ናቸው ። ወንበር ያላገኘው በየባንኮኒው ላይ ተደራርቦ ተኮልኩሏል ።

Scanned with CamScanner

መጠጡም ሙዚቃውም እየደራ ሲሄድ ፣ ለመደነስ የሚቃጣቸው ቤቱን ከሞሉት ሴት አስተናጋጆች ጋር የሚያውቁትን ከማያውቁት ሳይለዩ መዳራት መቃለድ ፣ ስካራቸው እስኪያስታውቅባቸው መለፋደድ ...ሆነ ። ሄኖክ ቅድም ጀምሮ በአይኑ ሲከታተላት የነበረችው ወጣት አይኑ ገብታለት እንድትመጣ ጠቀሳት ። አዲስ አልመሰለባትም ። እንደምታውቀው ጨብጣው አጠገቡ ተቀመጠች ።

ስትጫወት ቀልጣፋ ነች ። አሳሳቋም ውብና ማራኪ ነው ። ስታወራ ትቸኩላለች ። 'እቦ ተወና' የምትለው ፈሊጥ አላት ። ጉረኛም ነች ። አታፍርም ። በሴትነቷ ትኩራራለች ። ቢገጥማት እንደምትረታው በእጅ አዙር ትነግረዋለች ። ሄኖክ ባትለውም በልቡ ሊገጥማት ዝቷል ።

የአልጋውን ፎርማሊቲ አብራ አስጨርሳው ክፍሉ ካደረሰችው በኋላ ፣ እሷ ቤቱ እስኪዘጋ ስራዋን መሥራት እንዳለባት አስረድታው ተመለሰች ። መጠጡ ቢያደክመውም ፣ ጨርሶ አልተሸነፈም ። አልጋው ላይ ተቀምጦ ያውጠነጥናል ። 'ገና ይቀራታል' አለ በስካር መንፈስ እፀገነትን እያስታወሰ ።

ወጣቷ በሩን በቀስታ ከፍታ ስትገባ ፣ ሄኖክ እንቅልፉን ይለጥጣል ። በሩን ቆለፈችና ከጀኬት ኪሷ ውስጥ ሲጋራ አውጥታ እያያዘች ። ቅላቱ ከቅጥነቱ ጋር ማርኳታል ። ደስ የሚላት ወንድ ቢጤ ነው ። የጠጣችው መጠጥ ከስራዋ ጋር ቢያደክማትም የምትስበው ሲጋራ ሄኖክ ካሳደረባት ስሜት ጋር ብርታትን አጎናፅፏታል ። ልብሶቿን በየተራ አወላለቀቻቸውና በውስጥ ሱሪዋና በጡት መያዣዋ እንዳለች ሄኖክን ቀሰቀሰችው ። ሲነቃ አይኑ ቁመናዋ ላይ ፈጠ ቀረ ። አላፈረችም ፤ ደስ አላት ።

"እንቅልፋም! ጠጋ በል ልተኛ" እያለች የቀኝ እግሯን አስቀድማ በጉልበቷ አልጋው ላይ ወጣች ።

እስኪበቃው ሰውነቷን አፍተለተላት ። እንደፈለገው አድርጎ አስተካከላት ። እንደፈለገው ሆነችለት ። ባልጠበቀችው ሁኔታ ከስርአት ውጭ ተገናኙት ።

ብትታገለውም አልሆነም ። መፈናፈኛ አሳጥቶ ፈጥርቆ ይዟታል ። ሀመም እየጠናባት ተሰቃየች ። አቃሰተች ። እንዲተዋትም ተማፀነችው ። ይህ ሁሉ ሲሆን ደንታ አልሰጠውም ። በአሳቡ ወጣቷን በእፀገነት መስሎ እንዳሻው ተጫወተባት ። ተንፈስ አለ!

"ብስብስ ቅሌታም ነህ! እንዲህ አይነት ሰው ትሆናለህ ብዬ

ለልጠበኩም ነበር" አለች ፣ ወጣቷ አይኗ በርበሬ መስሎ እያጉረጠረጠች በት ።

ፈገግ ብሎ "እኔም እንደዚህ አይነት ሰዎች አትመስሉኝም ነበር" አላት እያሾፈ ፤ ምን ማለት እንደፈለገ አልገባትም ።

"የማነህ ባክህ!" ተነስታ ልብሷን መለባበስ ጀመረች ።

"ያንቺው ነኛ" ብሏት ፣ ይህንን ነገር ዶግሞ እንደማይሞክረው ምሎ ተገዝቶ አስተኛት ።

* * *

ክንፈ ፒያኖውን በጣቶቹ እየዳበሰ በሃዘን ያንጎራጉራል ። ህይወት በትካዜ ታሰምጣለች ። ኑሮ በብክነት ታስባዝናለች ። የውስጥ እሮሮና ብሶት ሰሚ አጥቶ በዋል ፈሰስ ይቀጣጠብራል ። ትናንትን እያስታወሰ ፣ ትውስታው ዛሬም እያስተከዘ ነገን ለፈተና ይዳርጋል ። ፍቅር ከንቱና አላማ ቢስም ሲኮን መኖርን መኮነን ይጀምራል ። ህይወት ድንቅነቷ አያከትምም ።

በመስኮት አሻግሮ ልትጠልቅ ያለችዋን ጀንበር አስተዋላት "ድንቅ ፀጋ" አለ ለራሱ ፣ ጀምበሯም መማረኩን አይታ ነው መሰል በቶሎ ተከተተች ።

"...ተፈጥሮ ትማርከኛለች ፤ ብታስከፋኝም ውበቷ ያፅናናኛል..." የአዜብ ንግግር በሕሊናው አስተጋባ ፣ ከመቅጽበት ጎልታ ታየችው ። በእውን አጠገቡ ያለች እስኪመስለው ድረስ ።

ሳያውቃቸው ከሷው ጋር ያሳለፋቸው ውብ ስእታት እለፉ ። ህይወት ስትበድልም ማካካሻዋን ሰጥታ ነው ። እፀገነት ብታስከፋው አዜብን ጣለለት ። በቁንፅል ህይወቱ እንደቀስተዳመና ደምቃ በተስፋ መቁረጥ ታብታ የነበረችው ነፍሱ በተስፋዋ ዋገቸች ። በውበቷ እደመቀ ቻት ። ብቸኝነቱን አጥባ ፀዳል አላበሰችው ። ሴት ልጅ በውሳኔዋ ጨካኝ ነች ።የመሰላትን ከማድረግ አትመለስም ። ያለመችውን ካልፈፀመች እረፍት አታገኝም ። ተልእኮዋም ፣ ግቧም ፍፃሜውን ሳያገኝ ልቧ አያርፍም ። አሳቅሎ ይይዛታል ።

ወንድ ልጅ ሞተር ሲሆን ሴት ደግሞ ነዳጅ ነች ። ተፈጥሮዋ የህይል ምንጭ ነው ። በአግባቡ ካልተያዘ ግን አደገኛ የሚሆንበት ጊዜም አይጠፋም ። ክንፈ ወደፊት እቅዱ ላይ ጠዋት ማታ በሃሳብ ሲጨነቅና

Scanned with CamScanner

ሊዋትት ከርሞ ፣ እርባና ያለው የሃሳቡ መቋጫ ላይ ሳይደርስ ታክቶ ይተወዋል ። አዜብ ግን እንደ ክንፈ አልሆነችም ። ለውሳኔ ብትቸገርም በመታከት አልተወችውም ። ፍቅሯን ከሀይወቷና ከኑሮዋ ብክነት ለይታ መመልከት አልተቻላትም ። አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ እንዳለባት የግድ ነው ። ደረሰች ።

ፒያኖው ታና ለውጠ ያጫውተው ጀመር ። የውስጡን ሰላም ሰፈው ፒያኖ ሊያነናፅፈው አልቻለም ። ጣቶቹን ከመጫወቻው ላይ አንስቶ ቤቱን በጭርታ አስዋጠው ። ማምሻውን ደግሞ እንሽፈራው ቤት ጠባቂ አድርገውት ሄደዋል ። ቤቱ ውስጥ ከሱ በቀር ማንኛቸውም የሉም ። ቀስ ብሎ ከመቀመጫው ተነሳና ጨለማ እየዋጠው በመሄድ ላይ ያለውን ቤት በመብራቱ አደመቀው ። በሳሎኑ ግድግዳ የተሰቀሉት ፎቶግራፎችና ስእሎች ድምቀት ጨመሩ ።

ጥቁር ካባና ኮፍያ ደፍቶ በዩኒቨርሲቲው ምረቃ ሰሞን ተነስቶ ያሳደገውን ፎቶግራፉን አስተዋለው ። የልጅነት ገጽታ በፊቱ ይነበባል ። ያለፈ የተማሪነት ዘመኑን በቅናት አስታወሰው ። የሰላም ጊዜ ፣ የደስታና የቡረቃ ህይወት ፣ በማንኛነት በምንድነኛነት ህይወት ፈጥረቃ የማታንገላ ታበት ወቅት ። ደግ ዘመን ፣ ዛሬን በተድላ ፣ በፍስሃና በሰላም ከመኖር በቀር ፣ ነገን በጥሩ ተስፋ ከማለም በቀር ፣ የኑሮ ስኬት ሳይታለም የሕልውና ፅናት ሳያሳስብ ፣ ከራስ በቀር ሀላፊነት የማይታለምበት ። የቤተሰብ ፣ የመስሪያ ቤት ፣ ያካባቢ ባለእደራነት በእጅጉ ያልተጫነበት ። ያ ጊዜ! ተስፋው ሁሉ የማር ቂጣ ። እሾህና አሜከላ ባስጨነቃት አለም ውስጥ ፣ በወጣትነት ልብ ውስጥ በሚንቀለቀለው እሳት ስንከሳሯ ጠፍቶ ጠርታ የምትታይበት ያች ውብ አለም ። ድንቅ ጊዜ አሰፈ ።

የበሩ ኳኳታ ከአሳቡ እባና አወጣው ። የውጪው የቆርቆሮ ..ር በእጅጉ ይደበደባል ። የሽፈራው ድብደባ እንደሆነ አልተጠራጠረም ።

* * *

ሃሳቧን በአንደበቷም ሆነ በደብዳቤ ለክንፈ ከነገረችው ወዲህ አዜብ በመጠኑ የመረጋጋት መንፈስ ይታይባታል ። ነገር ግን የጓንችለት ንና ዘወትር የምታልመው የድርሰት ስራዋን ገና አልጀመረችም ። ያልተጠናቀቀ ትልቅ ስራ ከፊቷ ተጋርጠ ይጠብቃታል ።

ክንፈን ብቻውን ባዶ ሚዳ ጥላዋለች ። አሁንም ሀላፊነት እንዲሰማት ታደርጋለች ። ማድረጓም ያስደስታታል ። በዚህ አለም ለሚወዱት ሰው የሚጠቅመውን ከማድረግ የበለጠ ምን እርካታ ይገኛል? የጨነቃት

ግን የክንፈ አይደለም ፣ ዋነኛውም ስራዋ በእፀገነት በኩል ያለው ነው ፣ እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ የሚታያት ። ፈርታለች ።

በሄኖክ በኩል ጉዳዩን መጨረስ አመቺ መንገድ ነበር ። ግን እንዳሁኑ ይሆታው በጭራሽ የሚሞክር አይነት አይደለም ። ማደራቸው አልቀረም እንጅ ፣ አይጥና ድመት መሆን ከጀመሩ ቆይተዋል። በተለይ በቅርብ ቀን ውጭ በማደሩ ልትቆጣው ብትሞክር ልክልኳን ነግሯት ሄዷል ። 'ልቆጣጠር የምትይበት ዘመን አልኸል' አይነት ንግግሩ ወሽመጧን ቆርጦታል ።

ስለዚህ በሱ በኩል የሚደረግ ሙከራ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ተረድታለች ። በጣም ማወቅ የምትፈልገው ነገር ቢኖር ሁለቱ በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንዳሉ ነው ። የምታውቅበት ምንም አጋጣሚ አላገኘችም ።

የቀራት አማራጭ እሷን በቀጥታ ለማግኘት መሞከር ነው ። ብታገኛታስ ምን ልትጠይቃት? ታረቁ ማለቱ አልዋጥልሽ አላት ። 'እንቺ ደግሞ ምንድነሽ?' የሚል ጥያቄ ብታነሳባትስ? ነገሩን የባሰ ማበላሸት መሰላት ። ሌላ ዘዴ ማሰብ ጀመረች ። በቀጥታ ሁኔታውን ሁሉ ግልጥልጥ አድርጋ ደብዳቤ ልትፅፍላት አሰበች ። አሱ ደግሞ የማይሆን ነው ። ብዙ የተድበሰበሱና ልትገልጣቸው የማትፈልጋቸው ነገሮች ሊኖሩ ነው ። ታዲያ እንዴት ቢሆን ይሻላል?

በታ ብቸኛውና አማራጭ የሌለው ዘዴ ክንፈ ሆኖ ታያት ። ክንፈ እንዲያደርግላት የምትፈልገውን ሁሉ ለመፈፀም እንደማያመነታ እርግጠኛ ነች ። ብቸኛው ቁልፍ ሆኖላታል ። ምን ማድረግ እንዳለባት ታውጠነጥን ጀመር ።

* * *

ክንፈን ማታ በስልክ አግኝታው በማግስቱ ከስራ ሰአት በኋላ ሊገናኙ ቀጠሮ ያዙ ። እሱም እግረ መንገዱን በመካሄድ ላይ ያለውን የቤቱን ስራ ሊመለከትና እሷንም ሊያሳያት እሷም ሃሳቧን ልታጫው ተው።

በቀጠሯቸው ሁለቱም በሰአቷ ተገናኙ ። ተያይዘው በቮልስዋገን ወደ ከተማ ዳር ።

"ለመኖሪያ በጣም ጥሩ ቦታ ነው" አለች አዜብ ተመርቶ በተሰጠው ቦታ ላይ የጀመረውን ቤት እያየች ።

Scanned with CamScanner

ስራውን በደንብ ታኙ ። ቢሆንም ፣ ክንፈ እንዲሰራ የጠበቀውን ያክል አልሰሩለትም ። ሰራተኞች ደግሞ ከሰር ከሰር እየኩተኩቱ ካላሰሯቸው በደንብ አይሰሩም ። ለዚህ ደግሞ ተከታትሎ የሚያሰራለት ሁነኛ ሰው አላገኘም ።

ተቆጣጣሪ የሆነውን ልጅ እግር ቢጤ አስጠራውና ስለስራው አንዳንድ ሁኔታ ያነጋግረው ጀመር ። አዜብ ፈንጠር ብላ በራፏ ሃሳብ ባህር ተንሳፋ ቤቱን ትዞራለች ።

ክንፈ አነጋግሮት ከጨረሰ በኋላ ሊሄድ ሲል ልጁ ራሱን እያከከ ቀረብ አለው ። የሆነ ነገር ሊናገረው እንደፈለገ ጠርጥሮ ክንፈ ቆም አለ ።

"እ… የኛህ ዘበኛ ነገር ግራግብት ብሎኛል ። አንድ ነገር ቢያደርጉት ይሻላል" አለ መሬት መሬት እየታኘ ።

"ምነው ምን አደረጉ?"

አውንም ፀጉሩን እያከከ "ተጪ ብላቸው ፣ በፍፁ ሊሰሙኝ አልቻሉም ።"

ክንፈ ግራ ገባው ። እንደመብሸቅም አደረገው ። በዛ ጊዜ ፀጉሩን እያከከ የሚያወራለት ሰው አይወድም ። "እኮ ምን ሆኖ ው?"

"ዘወትር እየጠጡ ነው የሚመጡት ። እንኳንስ ሊ ሰብቱ እንጂላ ቸው! ከነሳቸውም ይዘዋቸው ሳይሄዱ አይቀሩም ። በዛላይ ፣…" አውንም ራሱን ያካል ።

"…የቧንቧውን ውሃ ለመንደርተኛው ያስቀዳሉ ። ተው ብላቸው እንተን ምን ቸግሮህ ምናገባህ ይሉኛል ። ቀኑን ሙሉ ሲጋዝ የሚውለው ውሃ እንዲህ ቀላል አይምሰልህ ።"

"የት ናቸው አውን?"

"ያው ጠጅ ቤታቸው ይሆናሉ ።"

"ሰርታችሁ ስትጨርሱ ዕቃውን ለማን አስረክባችሁ ነው የምት ሄዱ?"

"ተጠርተው ይመጣሉ ።"

ክንፈ አውን ሊያስጠራቸው ፈለገና እስካውን ሰክረው ሊሆን ስለሚችል ተወው ።

"ነገ በዚህ ሰአት እንዲጠብቁኝ ንገራቸው!"

አዜብን ጠራትና ወደ መኪናው አመራ ።

"እንዴት ነው ወደድሺው ቦታውን?"

"በጣም! በጣም እንጂ!"

"ቢቃ! ወደፊት 'ሚኪንድ' እዚህ ግሳለፍሽ ነው ።"

"ሳስብ የነበረው እሱን ነበር ። በዕረፍት ቀኔ መስኩ ላይ ተጋድሜ ስፅፍ ይታየኛል ።" ቀዝቃዛ ፈገግታ ፈገግ አለች ።

ክንፈም አስተዋላትና መኪና ውስጥ ገባ ።

• • •

ክንፈ ወደቤቱ ሲገባ በሽርሽሩ ወቅት የቀላል ክባድ አድርጋ አዜብ ታል ያስገባቸውን ነገር እያሰላሰለ ነበር ። ሽፈራው ከእስናቀች ጋር ሳሎን ቁሙ ብሏል ። እነሱን ሲመለከት አንድ ጥያቄ አዕምሮው ውስጥ ተፈጠረ። እሱን እያሰበ ተጨነቀ ። እወነኑ ከመጣች ሽፈራው አብሮት ሊቆይ አይችልም ። ይህንን መነጋገርም አላስፈለገውም ። ሽፈራው እርፎ እንደማይቆመጥለት ያውቃል ።

ይህንን ሲያወጣ ሲያወርድ "ምን ነው ትቆዝማለህ!" አለው ሽፈራው ።

ክንፈ ደንብር "አይ ፣ እንደው ዝም ብዬ አንዴን ሳወጣ እንዴን ሳወርድ" አለው ፣ ስለምን ያስብ እንደነበር ያስታውቅበት ይመስል ፈቴን በሠፍረት ፈገግታ እያጠበ ።

"ይህን ሰሞን አዲስ አመል አምጥተሃል!" አለ ሽፈራው ።

እስናቀች ሁኔታውን በጥሞና ትከታተላለች ። በጣም ስሱ ነች ። ትንሽ ነገር ያስጨንቃታል ። የክንፈ ሁኔታ ወትሮም ከምታውቀው የተቀየረ እየመሰላት የራቧን ምክንያት እየፈጠረች 'ከበድነው ይሆን!' በማለት ራቧን ሰላም ትነሳለች ። አውንም መልሱን ለመስማት ጓጉታ ለች።

ክንፈ ጨዋታው መጣለት ። ስለጅምር ቤቱ ፣ ዘበኛው ስለሰሩት ስራ ሁሉ አወራለቻው ። ጨዋታቸው ደራ ። ቴሌቪዢኑም ይሞሃል ። የሚያናውጠው የለም ። እስናቀች መሃከላቸው ልትቀመጥ አሰበችና እመናታች ። ተመልሳ ወደ ጓዳዋ ሄደች ።

ደክሟታል ። ለመተኛት ደግሞ ሳሎን ማንጠፍ አለባት ። ብቻዋን ተቀምጣ ስለኑርዋ ስታውጠነጥን አውንን ትታ ወደ ጓላዋ ነጮደች ። ቤተሰቦቿ በተለይ እናቷን ፣ ግቷ ከብቱ ከግመሽ ሲመለስ ፣ ሲነጋ ውሃ ለመቅዳት እንስራና ገንቦ ተሸክሙው የሚጠራሩት የመንደር ኮረዶች ፣ ወንዝ ገንቦና እንስራ አሻካሚው ጉብል ፣ እንዲያ ሲል የክንፈር

Scanned with CamScanner

ወዳጇን፣ የሚያስቸግረው ጐረምሳ ፣ ሁሉም አይረሳም ።

ደግሞ ጠና አለች ሲባል በየሰርጉ ፣ በየዓመት በዓሉ ፣ ቤተክርስቲያ ንም ለመሰላም ሲወጣ ክንብንቡ ፣ የጐረምሳው ፣ የጉብሉ አይን፣ ሽኩርምሚያው ፣ ተራው ሲደርስ መዳሩ ፣ የጫጉላው ቤት አዲስ ሕይወት ....ቀድሞ ያላወቁት ነገር ፣ ፍርሃቱ ፣ መጨነቁ የወንድ ፉከራ ሁሉም ነገር... የሚረሳ የለም ።

የትዝታ ሃሳቧን ሳትቋጭ እንቅልፍ ያዳፋት ጀመር ። ግልጅጅ ፣ ደግሞ ቀና...በመጨረሻ ተነስታ ሳሎን ገባች ። ክንፈ መኝታ ቤቱ ገብቷል ። ሽፈራው ብቻውን ሶፋው ላይ ተቀምጦ ይተክዛል ። ቴሌቪገርኑ እንደቀድሞው ብቻውን ይጮሃል ። አጠፋችው ። ፍራሻቸውን ዘርግታ መኝታቸውን ታስተካክል ጀመር ።

ተኝተው መብራቱን ካጠፉ በኋላ ፣ በላይዋ የነገሰውን ትካዜ ለማባረር በሰውነቱ ውስጥ ሽጉጥ አለች ። የማይመጣባት የሃሳብ ጓዝ የለም ። ኑሮ ፈተና ነው ። ትንሹም ትልቁም ከሕልውና ጋር እየተቆራኘ ያስጨንቃል ። እኔንትን ይፈታተናል ። ይህን አይነቱን የሞራል ደዌ ሳይቀምሳት የሚያልፍ የለም ።

“ሽፌ አሰቃየሁህ አይደል?” አለችው ሊወርድ የሚተናነቃትን እንባዋን ለመግታት እየታገለች ።

“ደግሞ ምን እደረግሽኝና!” አላት አዝማሚያዋን ፈርቶ ።

ልትናገር አለችና እስኪያልፍላት ደረቱን ጡቱን በክንፈሯ ፣ በምላሷ ትነካካው ጀመር ። ሩህሩህና ልባዊው ፍቅሯ በያንዳንዱ የሰውነት ክፍሉ ሲሰራጭ እየተሰማው ጥብቅ አድርጐ አቀፋት ። ደስ አላት ። የመጀመሪያ እለትም አጥብቃ የወደደችው በእቅፉ ነው ። አጥብቆ የሚያቅፋት ወንድ ከአባቷ በቀር አላጋጠማትም ። ሽፈራው ሲያቅፋት ፣ ሁለንትናዋ በውስጡ የቀለጠ ያክል ይሰማታል ። ወደሰውነቱ አጣብቆ የለሰለሱ እጆቹን ያከናንባታል ። በውስጡ የሰመጠች ያክል መላው ሰውነቷ በፍስሃ ይወራጫል ።

“ሳትወድ በግድህ...” አለችው አንገቷን ቀና አድርጋ ፊቷን ስሩ እያስገባች “ሳትወድ በግድህ የጓደኛህን ፊት እንድታይ እደረኩህ አይደለም? ሽፌ ለኔ እኮ ያቺ ጠባቧ ጓዳችን ትበቃን ነበር ። እምቢ አልከኝ...” አቋረጠችው ንግግሯን ።

ሽፈራው ግራ እንደመጋባት አለና “ምን ሆነሽ እስኑ?” ክንፈኽ ጓደኛዬ ብቻ አይደለም ። ወንድሜም አብሮ አደጌም ነው ። ይህን ስንቴ ልንገርሽ? ቤቱ ቤቴ ነበር ። አብረን ብዙ አመት ኖረናል ። ለምን ትጨነቂያለሽ?” አላትና በንግግሯ እየተበሳጨ “ሁለተኛ ስለዚህ ነገር አታንሽብኝ ። አንቺም በከንቱ ራስሺን ስታስጨንቂ አትዋይ ። በነዚህ አጭር ጊዜያት ካንቺ ጋር የመሰረታችሁትን ፍቅር እንኳን አትመልከቺም። ለምን ቤቱን እንደቤትሽ አትመለከችውም? እኛን በማኖሩ መሳቀቅ ሽን እሱ ቢያውቅ ምን ያክል ቅር እንደሚሰኝ አታውቂም? ለምን መጥፎ አሳብ በጭንቅላትሽ ታመጪያለሽ? ሙች! ልክ አይደለሽም” አላት ቅር እየተሰኘ ።

አስናቀች ልትናገር የፈለገችውን አልተረዳላትም ። መውደዷን ለመግለፅ ቃላት ያንሷታል ። ሽፈራው ለሷ ሲል የማያደርገው ነገር እንደሌለ ትገምታለች ። ስቃዩ ፣ ድካሙ ፣ መንገላታቱ ሁሉ ለሷ ሲል ፣ ከዛም አልፎ ወደፊት ለሚወጥናቸው ለሚተልማቸው ሃሳቦች ሁሉ ምክንያት እሷ እንደሆነች ይሰማታል ‘አትሰቃይብኝ ፣ በቃህ ፣ ሁሉም ነገር ካንተ ጋር ከሆነ ይበቃኛል’ ማለቷ ነበር ። ታስታውሳለች – ሁሉን ነገር፣ ወ/ሮ ሶስና ቤት እያለች ባህሪውን አብረዋት ይሰሩ ከነበሩት ሴቶች፣ ከባለቤቷ ጭምር ሰምታለች ። ያን ሁሉ አመሉን እንዳልነበር እርግፍ አድርጐ ትቶታል ። ለኑሮው አይጨነቅም ነበር ። አሁን ግን አብዝቶ ያስባል... ይሄ ሁሉ ለሷ ሲል የተሸከመው ቀንበር መሆኑን ታስባለች ። አንድ ያላስተዋለችው ነጥብ አለ ። ይህንን ሁሉ የሚያካክስ የመንፈስም ሆነ የአካል እርካታ ከሷ እንደሚያገኝ አለመገንዘቧ ነው ። ቢቻላት ሁለንተናዋን ጨምራ ብትሰጠው ዋጋውን የከፈለች አይመስላትም ። እሱ ግን በቅንጣት ነገሯ ሳይቀር ይደሰታል ። ደስታውን ለመከፈል ዘወትር ለሷ ይታትራል ። ጥረቱ ደግሞ ለሷ የመንፈስ ጫና እየሆነ ያስጨንቃታል።

ፍቅር ኑሮን ትለውጣለች ። ከእሬት የመረረን ሁኔታ አጣፍጣ ጣት ታስቆረጥማለች ። ፍቅርን በማፍቀር ይወጡታል እንጂ ፣ ለሚወዱት ሰው የሚፈልጉትን በመስጠት መወጣት ቢፈልግ አለም እንዳለች ለስሙታ ብትሰጥ አታጠግብም ።

አስናቀች በኑሮ ውጣ ውረድ ለጥቅም ከአንዱ መደፍ ወደሌላ ፣ ለህልውና ከአንድ ሰውነት ወደሌላው እንደ እላቂ ሳሙና ስትሙለጨ

Scanned with CamScanner

ለጭ፣ ሽፈራውም ከኑሮ ተኳርፎ አለምን በጥቁር መነጽር እየቃኘ ሲሰላች፣ ህይወትን ባሰበ ቁጥር ሲያዛጋ ፣ የሁለቱንም ህይወት ፍቅር ዋጋችላቸው ። ሁለቱም ዋጋዋን ሊከፍሉ ይዋትታሉ ። ይቃትታሉ ።

ክንፈ ማታ ከእራት በኋላ ስለአዜብ ያጫወተው ጨዋታ በሽፈራው ላይ መንፈሳዊ ቅናት አሳድሮበታል ። ሽፈራው ጣልቃ ያልገባበትን ህይወት አዜብ ተነከራበታለች ። ሁለቱን ለማገናኘት የምታደርገውን ጥረት በማድነቅ አሰበው ። ያም ሆነ ይህ በጥረቷ ብተገፋበት እሱም ቢረዳት ወደደ ። በአዜብ ማሳሰቢያ መሰረት ደብዳቤ እንዲፅፍላት ቃል እንዳስገባቸው ሲነግረው እሱም አበረታቶታል ። አሁን ያሳሰበው ግን ቤት የማግኘቱ ነገር ነው ። በዛፊው ጊዜ ደህና ቤት በደህና ዋጋ ማግኘት ራሱ ግመልን በመርፌ ቀዳዳ የማሾለክ ያክል ሆኗል ። ለዛውስ በየትኛው ገንዘብ! እስከዚያው መጠነኛ ቤት የሚከራይበትን ዘዴ ያውጠነጥን ጀመር ። መልሱን ሳያገኝ አጠገቡ የተኛችው አስናቀች ወደ ሄደችበት የፅልቅልፍ አለም ነጎደ ...

* * *

ክንፈ ለሊቱን ሙሉ ለእፀገነት እንዴት አድርጐ እንደሚፅፍላት ሲያወጣ ሲያወርድ ሃሳብ አልመጣ እያለውም አንድ ቃል ለመግፍ ተራራን የመግፋት ያክል ሲሆንበት ተስፋ ቆርጦ ተወው ።

ጠዋት በቃሉ መሰረት ለአዜብ ደወለላት ።

"ጨረስከ?" አለችው መልሱን ለመስማት እየቸኮለች ።

"እባክሽ እቃተኝ!" አላት አፈር ብሎ ።

"እንዴት?"

"አልመጣልህ አለኝ ።"

"ድርሰት ነው እንዴ ለመፃፍ የፈለከው?" ብላ ሳቀችበት ።

"እሱንማ ተይው! እንዳውም ማታ ትገ ብለሽኝ አገኘልሻለሁ ። እኔ ደብዳቤ መፃፍ ያቃተኝ እንቺማ እንዴት ትሆኚ?" አላት አባባሏ ከልቡ ተሰምቶት።

"ቀሽም!... እኔ ፅፌ ባዘጋጅልህ ወስደህ ትሰጣታለህ?"

እንደገና ለመፃፍ ሞክር ትለኛለች ብሎ ፈርቶ ስለነበር "በማን እድሌ!" አላት ፡

አዜብ ቀናች ፡ 'ከኔ አብልጦ ይወዳት ይሆን?' ስትል አሰበች ። ለጊዜው አሳቡን ተወችውና "ከሰአት ከቢሮ ስትወጣ በኔ በኩል አለፍና

ደብዳቤውን ውሰድው" አለችው እንደማዘን እያደረጋት ።

ጥቂት አውርተው ስልኩን ከዘጉ በኋላ ፡ ደስ ሳይላት ዋለች ። ቀኑን ሙሉ ሳትፈልግ 'ከኔ አብልጦ ይወዳት ይሆን?' የሚለው ሃሳብ ሲፈታተ ናት ቆየ ።

ምእራፍ አሥራ ስድስት

ጠዋት ሀውልት ምርቃት ደርሶ በመኖሪያ ቤት የተዘጋጀውን ፀበል ፀዲቅ ለመቅመስ ወደ ቤት ገሰገሰ ። ድንኳን ተጥሎ ወንበር ተደርድሮ መጠነኛ ገቢ ያለው ቤተሰብ የደገሰው የሰርግ ድግስ ይመስላል ። አላስፈላጊው ወጪ እየታሰበው ድንኳን ውስጥ ተቀመጠ – ክንፈ ።

አስቴር ከሰዎች መሃል እየተሹለከለኩች ሄዳ የእህቷን ባል ሰላም ካለች በኋላ ወደ ላይ ቤት እንዲመጣ ሹክ አለችው ። ፈራ ተባ እያለ አካባቢውን ቃኝና ተከትሏት ሄደ ። ዋናው ቤት በራፍ ላይ እንደደረሰ እፀገነት ተቀብላው ወደ ውስጥ ይዛው ገባች ። ወደ መኝታ ቤቷ ።

ገና አዲስ እንደሚያውቃት ልጅ ፈራ ተባ እያለ አልጋው ጫፍ ተቀመጠ ።

"እዚህ ይሻልሃል ብዬ ነው ያስጠራሁህ" አለችው ፡ ለየት ባለ አስተያየት እየተመለከተችው ።

"አመሰግናለሁ" አላት ግራ ተጋብቶ ።

የሚበላ ምግብ በልዩ ሳህን ይዛለት መጣች ። ከመምጣቷ በፊት ግን፡ ፖስታውን በኪሱ መያዙን አረጋግጦ ነበር ።

"የሚጠጣ ምን ላምጣልህ?" አለችው እፀገነት ገፅታውን በጥሞት እያቃኘች ።

"ስራ ገቢ ነኝ ። መሄድ አለብኝ" አላት ማርፈዱን እያስታወሰ ።

ልታስቀረው ፈለገች ። ደግሞ ፈራችው ፡ ለአቷን ተመለከተችና "ለስላሳ መጠጥ ይምጣልሃ? " አለችው ።

"እሺ!" አላት ልቡ እየተጨነቀ ።

ቶሎ ይዛ ተመለሰች ። ለስላሳ መጠጡን ከፍታ ከሰጠችው በኋላ "ብላ እንጂ አልነካኸውም'ኮ" አለች ። ለብቻ የተቀመጠውን እንጀራ

Scanned with CamScanner

ወደፊቱ እያቀረበች ።

"ብቻዬን ሆንኩ'ኮ!" አላት ቀና ብሎ እየተመለከታት ።

ሰውነቷን እንዳች ነገር ነዘረው ። "አብሬሀ እበላ ...ለሁ" አለች ፊቷን እንዳያይባት እያዘረች ። አጠገቡ መዋታ ስትቀመጥ መብላቱን አቁሞ ፣ ይመለከታት ጀመር ። ቀና ማለት አቃታት ። ልታየው ስትሞክር ቀልቶ እንባ ያጠበውን አይኗን ሲያይ አንገቷን ሰበር አደረገችው ።

አንገቷን ሁለት እጆቹ መሃል አስገብቶ አንገቱ ሥር ስትሸጐጥ ሁለቱን ጎይለኛ ማእበል አናወጣቸው ።

"አልጠላሽኝም ክንፈ?" አለችው እያለቀሰች ።

"እንዴት አድርጌ ውዴ!"

"አሁንም ውዴ ትለኛለህ?" ንግግሯን ሲቃ ቆራረጠው ።

"ሁሌም እልሻለሁ!"

ለረጅም ደቂቃ ተቃቅፈው ተሳሳሙ....

"ምንድነው ይኼ?" አለችው እፀገነት ከቤት ሲወጣ ሲል የሰጣትን ፖስታ እየተመለከተች ።

"ስጦታዬ ነው" አላት ፈገግ ብሎ ። ያንን ገራገር ፊቱን እያስተዋለች መኪናው ድረስ ሸኘችው ።

* * *

ወዲያውኑ ደብዳቤውን ከፍታ ማንበቧን ቀጠለች ።

'እፃ!

'ወደኋላ ተመልሰን የእያንዳንዳችንን በደልና ክፋት ከተመለከትን ወደፊት የምናልመው ህይወት የኋለኛው ክፋት ጥንስስ ይሆናል ። ከትናንት መማር ያለብን ለወደፊቱ የሚበጀንን መልካም ነገር ለማድረግ መሆን ይኖርበታል ። የትናንቱ በደል ዛሬም እየታወሰ የዛሬውን መልካም ቀንም ሆነ መጪውን ብሩህ ቀን እያጠቆረ ማበላሸት የለበትም ።

'ባለፈው ወንጬ ፡ ዛሬ ያረገዝኩትም ሆነ የወለድኩት የበደል ቂም የለኝም ። ዛሬ ከማንኛውም ቀን የጠራች ንፁህ ቀን ነች ። ልቤ ያለፈ በደሏን በይቅርታ አፅድታለች ። የበደለችውም ካለ ይቅርታ ጠይቃ አልፋለች ። ለዛሬ ሽክሟ ከትናንት የወረሰችው አንዳች በደልም ሆነ ቂም የላትም ።

'እፀገነት ሁላችንም መስሎ በታየን የኑሮ መንገድ ዘልቀናል ። ደግነቱንም ክፋቱንም አይተናል ። ከኑሮ ልምድ የበለጠ አስተማሪ አይገኝም ። ይቅርታ መደራረግ ደግሞ የስብእናችን ውጤት ነው ። ዛሬ ፣ እኔም አንቺም የሚያስፈልገንን ለማግኘት ፣ በትናንት በደል ቅሬታ ታስረን ፣ ዛሬን በይሉኝታ ተጋርደን ፡ ነገ የማናልመው ሕይወት ለመኖር የምንገደድብት ሁኔታ አይታየኝም ። ያለፈው አልኾል ። በቃ! ።

'እዚ ምን ለማለት እንደፈለኩ ሳይገባሽ እይቀርም ። ዛሬም ቤቴ ቤትሽ ነው ። ዘግተሽው እንደ ወጣሽ ከፍተሽው መግባት ትችያለሽ ። እኔ ያው የምታውቂኝ ክንፈ ነኝ ። እንቺም እንደዛው ። የበደልሽኝ ቢመስለኝም ፡ ዛሬ ሙሉ ይቅርታ በልቤ ስላደረ ሁሉን መርሳት ያንችም ፈንታ ይሆናል ። ታላቁ ነገር ካለፈው መማር ነው ። ዛሬም እንደ ትናንቱ ሁለት አጆቼን ዘርግቼ ውዲን ባለቤቴን እጠብቃለሁ ። ትዳር ትምህርት ቤት ነው ። ትዳር መቻቻል ነው ። ትዳር መግባባትና መረዳዳት ነው ። ከዚህ ሁሉ መሃል ታዲያ ጥፋትም ይኖራል ፡ ይቅር ይባላል ። በደልም ይኖራል ። ይካሳል ። እና ተፋቅረን ያዋቀርናትን ጎጆ ደጋግፈን እናቅናት ። መቼም ከዛሬ የበለጠ ቀን የለም ። ትናንት አልኾል ። የነገም ባለቤት አይደለንም ። ቤትሽ የምትገቢበትን ቀን እናፍቃለሁ ።

አፍቃሪሽ ክንፈ'

* * *

እፀገነት ደብዳቤውን አንብባ እንደጨረሰች ወረቀቱን አጣጥፋ ከልቧ ጋር አጣበቀችው ። ለዘመናት ጨለማ ቤት ታስራ እንደተፈታች ነፍስ ደስታዋን መግለፅ አቅቷት ፣ የተሰማት ስሜት ወዋሮ እየቀሰፋት በደስታ ታቃስት ጀመር ። ትንሽ ስትረጋጋ ፣ እንባዋ ዝርግፍግፍ አለባት። የህይወት ጣዕሟ ዘልቆ ተሰማት ።

* * *

ወዲያ ወዲህ ተራሩጦ የተገኘለትን ባለሶስት ክፍል ቤት ወረቀት ገዝቶ መለጠፍ ጀምሯል ። አስናቀች ከሥር ከሥሩ የስንዴ ዱቄት ፡ ውሃና ትንሽ ስኳር እያደረገች ሙቅ ታሞቃለች — ለወረቀቱ መለጠፊያ ።

Scanned with CamScanner

ያዝልኝ ሲላት ፣ ስትቀልድ ወረቀቱ ሲቀደድ — ስትስቅ ከውጭ የመኪና ጡሩምባ ተነፋ ። ሽፈራው የሚለጥፈውን ወረቀት ትቶ ወደ ውጭ ወጣ ። ክንፈና ሽፈራው ተያይዘው ሲገቡ ፣ አስናቀች ከተቀመጠች በት ተነስታ ፣ "ጥቁር እንግዳ!" አለችው ክንፈ የያዘውን ዕቃ እየተቀበ ለች።

አስናቀች የምትወደውን ጣፋጭ ለስላሳ ኬክ በብዛት ይዞላት መጥቷል ። "ከአዲስ አበባ ፣ ከምኑም ከምኑም አትውጪ አትውጪ የሚለኝ ለዚህ ለሱካር ዳቦዋ ነው" ትላለች አዘውትራ ።

ክንፈ በጅምር የቀረውን ግድግዳ ተመልክቶ "አይ ሽፈራው! ልፋ ሲልህ ነው እንጂ እኛ ከሰሞኑ መልቀቃችን አይቀር። ምን አለፋህ" አለው እያሾፈበት ።

"እስከዛው" ብሎት መቀመጫ አቀረበለት ።

እወገነት ቤቷ ከገባች ሳምንት ሊያልፋት ነው ። ከዛ ወዲህ ክንፈ የነሽፈራው አዲሱ ቤት ብቅ ሲበል የመጀመሪያው ነው ። መራራቃቸው ለራሱም ታውቆታል ።

"እንዴት ነው ሙሽራህ ለመደች?" አለ ሽፈራው ክንፈ ጐን እየተቀመጠ ።

"ላላምድ ብዬ አይደል የጠፉሁት" አለው ።

አስናቀች የተጣደውን ሙቅ አውጥታ ትንሽ ብረት ምጣድ ካደረገች በት በኋላ ታጥቦ ተለቅሞ ከተመቀመጠው ቡና ዘግና መቁላት ጀመረች ።

"ቡናሽ እንዳይቀጥን! ያን ወፍራም ቡና ካስለመድሽኝ ወዲህ ፡ ሌላው ቡና አልጠጣልህ ብሎኛል ። ከሚስቱም ሳታኳርፈኝ አትቀሪም" አላት ።

አስናቀች ሶስት ጊዜ አማተበችና "እረ በሰማም በል 'ቱ! ለምን ትኳረፋለህ!' አለችው ፊቷን አጨፍግጋ ።

ሁለቱም ሳቁባት ።

ክንፈ አቦሉን ቡና ጠጥቶ እየተጣደፈ ወደ ቤቱ ገሰገሰ ። እወገነት ቀድማው ገብታለች ። አዲስ የገባችውም ሰራተኛ ቡና ለማፍላት ምግብ ቤት ውስጥ አጐዛ አንጥፋ ሳር ጐዝጉዛ ደፋ ቀና ትላለች ። ቡና ጠጥቻለሁ ብሎ ቅር ሊያሰኛቸው አልፈለገም ።

* * *

ማታ አልጋው ውስጥ ከገቡ በኋላ ቀን ሲያውጠነጥን የዋለውን ነገራት ።

"እሺ!"

"ወዴ!"

"መድሀኒት መውሰድሽን እቁሚ! እሺ?" አላት በማግባባት ።

"ለምን ክንፈ?" አለችው የሃሳቡ ለውጥ ምን እንደሆነ ለማወቅ ፈልጋ ።

"እስካሁን ብቻችንን ኖርን አይበቃንም!" አላት ደረቷን ጡቷን እየደባበሰ ። ትንሽ አሰብ አደረገችና "በመጀመሪያ ቤት ሰርተን እንጨርስ ያልነውስ?" አለችው አሳቢ ወደ እናቷ እየወሰዳት ።

'ወይ እንደኛችሁን ልጆች ወልዳችሁ ከነሱ አልሆናችሁ ፣ ወይ ደግሞ...'

'እማማ ቤት እየሰራን'ኮ ነው...'

'ኤዲያ! አሁን ያላችሁበት አንቧችሁ ነው?'

'እሱ—ኮ ኪራይ ቤት ነው'

'ቢሆንስ ለሁለት ነፍስ! ደግሞ ቤት ቤት የምትሉን ማን ሊኖርበት፣ ማን ሊቦርቅበት ነው? አግብቶ ልጅ ሳይወልዱ ደግሞ ሌላ ጣጣ'

'መጀመሪያ ቤቱን ሰርተን እንጨርስ ብለን'ኮ ነው'

'ኤዲያ! ለአንድ ነፍስ መሆን አቅቷችሁ ነው ። እስቲ አንድስ ልጅ ቢሆን ምን አለበት ፣ አሁንማ ይኸው ሶስተኛ አልፋችሁ አራተኛችሁን ልትይዙ አይደል ። ይሄኔ የአራት ልጆች እናት ትሆኚ ነበር ።'

እንዳለፈው አሁን የአራት ልጆች እናት መሆን መቻሏ አልዘገነና ትም ። እንዳውም በይበልጥ ደስ የሚላት መስላት ።

"አሁንማ—እንግዲህ ቤቱንም ማጠናቀቃችን'ኮ ነው ። ትንሽ ነው የቀረን" አላት ፡ ቀኝ እጁ የሚያፍተለትለውን ጡቷን እየተጫነ...እየተጠ ጋት ።

"እ—ሺ" አለችው ወደሱው እየተሳበች ።

ወትሮም የሚማርከው ቅልጥፍናዋ አሁንም አለ ። የቀድሞው ደስታዋ የበፊት እርካታዋ አሁንም ያንሠራራል ። በምትኩ የምታልመው አንዳች ሌላ ሰውነት የለም ። ሁሉን ክንፈ ይዞታል ። እንዳውም ከሱ ሌላ ህይወት ቆሽሾና አስጠይፎ ይሰማታል ። ከቆሻሻው አለም ለማምለጥ

Scanned with CamScanner

ራሷን በሰውነቱ ውስጥ ደበቀች ። በውስጡ አንዳች ክፉ ነገር የለም ።
...ክፋት ተወግዶ ደግነት የሞላው አለም ፣ ተንኮልና ምቀኝነት ጠፍተው ፍቅርና ቅንነት ያጥለቀለቃት አለም ፣ ጨለማው ተውግዶ ብርሃን ከአጥናፍ አጥናፍ ያንፀባርቀባት ብሩህ አለም ፤ እነሶቅራጥስ ከመቃብር በላይ ነግሰው ይፈላሰፉሉ...ቻርለስ ዳርዊን አባቱን መስሎ መቃብሩ ላይ ቆሟል ። የፊቱ ክፋት ያስቀይማል...ካርል ማርክስ ካፒታልን ተሸክሞ ቆሟል ። የመፅሀፉ ክብደት ሊጥለው ደርሷል ። አልበርት አንስታይን ብቻውን ይጨነቃል ። ከያኔው ይከይናል፡ ሰአሊው ይስላል ፣ ደራሲው ይደርሳል ፣ የአለም ጠበብት ይጠበባሉ ፣ ፈላስፎች ይፈላሰፋሉ...

ሁሉም ተጨንቀው ተጠበው ያልደረሱበትን ፣ ምንነቱን ያላወቁትን ጥልቅ ውበት ፤ ሁለቱ ብቻ ናኝተው ተመለሱበት ።

* * *

በጥዋቱ ተነስተው እፀገነትን መስሪያ ቤቷ ካደረሰ በኋላ ወደ ቢሮው ገሰገሰ ። ቢሮው ሲደርስ ጥቂት ዘግይቷል ። በፀሀፊዋ በኩል የቆየው መልዕክት ነበረው ። አዜብ ደውላ እንደገባ እንዲደውልላት መልዕክት ትታለች ።

ወዲያውኑ ደወለላት ።

"አጋጣሚ ሆኖ ስንፈልግሽ ነበር" አላት ክንፈ አዜብን እንዳገኘ ።

አዜብ ግራ ተጋባችና "ከማን ጋር?" አለችው ።

"እኔና እፀገነት!"

ደነገጠች ። "ምነው ለምን?"

"ቅዳሜ እቤት ምሳ ጋብዘንሻል ።"

"እውነትክን ነው?"

"ሙች እውነቴን ነው ።"

አሁንም ይበልጥ ግራገባትና "እሺ ነገሩስ ይሁን ፣ እሷ በምን መንገድ ነው ልትጋብዘኝ የተሰናዳችው? ደግሞ አስቀድሚ እንዳጫወት ኩህ በወንድሜ በኩል ታውቀኛለች ። እና እንዴት ይሆናል?" አለችው እየተጠራጠረች ።

ክንፈ ፈገግ እያለ "ለመታረቃችን ምክንያት አንቺ መሆንሽን ሁሉ ነግሬያታለሁ ። አስፈላጊ ካልሆነው በቀር ዩንቨርሲቲም አስቀድመን እንደምንተዋወቅ ገልጨላታለሁ ።"

"ደብዳቤውንስ እኔ እንደፃፍኩልህ ታውቃለች?" አለችው ።

"በጭራሽ" አላት ብዙ እስኪነጋገሩ ድረስ ለምን ፈልጋው እንደደወለችለት ሳይጠይቃት በመቅረቱ እየተፀፀተ ።

"ዛሬ ከመግባቴ በፊት እንዴት ደወልሽ?"

"ባክህ በጣም አዝኛለሁ ።"

"ምነው ምን ነካሽ?" አላት ደንግጦ ።

"ትናት ማታ ወንድሜ ብጣሽ ወረቀት ጥሎልኝ ሄደ ።"

ክንፈ ተጣደፈ "ምን ሆነ? የምን ወረቀት!"

አዜብ በረጅሙ ተነፈሰችና "አብረን መኖር አልቻልንም ። ስለዚህ ራሴን መቻል አለብኝ ፣ ለእስካሁኑ አመስግናለሁ የሚል ።"

ክንፈ ሊያረጋጋት ፈልጐ "ታዲያ ምናለበት ዛሬ እሱ ትንሽ ልጅ አይደለም ። የሚሰራውን ያውቃል" አላት ሌላ የሚላት እየጠፋው ።

"አ—ዎ..." አለች በረጅሙ እየተነፈሰች "ምን ታደርገዋለህ! ችግሩ እኮ የሱ አይደለም ። ቢያስቀይመኝም ባስቀይመውም ልለየው አልሻም ። እንኳን የገዛ ወንድሜን ፣ የከረመች ሰራተኛ እንኳን ከቤት ማባረር አልችልም ። ባባርራትም የተወሰነ ጊዜ ይጨንቀኛል ። ክፋቱ እኮ መለየቱ ነው ። ምን ታደርገዋለህ! ተው ብለውም መንፈሴ አላረፈ ፣ ያዝናል ። ብቻዬን መፈጠሬን እያወቅሁ ምን እንደዚህ እንደሚያደርገኝ አላውቅም ። እድሜ ልኬን መለየት የተጐዳውን መንፈሴን ሳስታምም መኖሬ ነው የሚያሳዝነኝ ።"

"የለም እንደዛ መሆን የለብሽም ፤ የሄደው ወዶና ለጥቅሙ ብሎ ከሆነ መጨነቅ የለብሽም ።"

"እስቲ እንዳልክ ይሁን..." አለችው የታከተች መስላ ። "... ለማንኛውም ቢሻለው ነው የሄደው ፣ እኔን የሚያውቅልኝ አጣሁ! እንግዲህ ከማን መልመድ ይቻላል? ። ሁሉም ይቅር ። ለማንኛውም ለአንተ የደወልኩት መፅናናት እችላለሁ ብዬ ነው ። ደግሞም ነው ። ሌላው ቢቀር ምን ለማለት እንደምፈልግ እንኳን ትረዳልኛለህ ። በል ስራ አላስፈታህ ፣ ቻዎ! ሰሞኑን እድውልልሃለሁ" አለችው እሱም "ቻዎ"

Scanned with CamScanner

ብሏቸ ስልኩን ዘጋ ። ለተወሰነ ጊዜ ተረጋግቶ ስራውን መስራት አልቻለም ። ትዝ አያለችው አዘነላት ።

'ምንም ክፋት ሳይኖራት በመለየት እሳት ተለብልባ ማለቋ ነው ሲል አሰባት ። ዘወትር ሲያስባት መንፈሱ እዝን ይልበታል ።

* * *

በሳምንቱ መጨረሻ ቅዳሜ ጠዋት እፀገነት ገብታ የአለቃዋን ቢሮ ካስተካከለች በኋላ ፣ ራሷ ቢሮ ሆና ጥፍሯን በጥፍር ሞረድ ትስላለች ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ አለቃዋ ቢሮዋን ከፍተው ገቡ ።

"እንደምን አደርሽ?" አሏት ጐርናና ድምፃቸው ፣ ፈገግ ብላ የሰላምታውን አፀፋ መለሰችላቸው ።

ለአንድ አፍታ ቢሮዋ ቆም ብለው "ሰሞኑን ባህሪሽ ተለውጧል ። እንቀድሞሽ የድሮዋ እፀገነት ልትሆኚ ነው ። ስራሽም እየተስተካከለ መጥቷል ። ገፅታሽ እንደዚሁ" አሏትና ወደቢሮዋቸው ዘለቁ ።

እፀገነት ለውጧ ለራሷም ታውቂታል ። ለአካባቢዋ የነበራት አመለካከትም ተለውጧል ። ማንኛውንም ነገር በክፋት መመልከት ትታለች ። ሰላሟም ህይወቷም እየተረጋጋ መጥቷል ።

አለቃዋ ከገቡ በኋላ ስራዋን ስትሰራ ቆይታ የሻይ ሰአት ሲቃረብ ፣ የቢሮዋ በር ተንኳኳ ።

"ይግቡ" አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ ።

ከመጣው እንግዳ ጋር አይኗ ሲጋጭ ሰውነቷን እንደኤሌክትሪክ ነዘራት ። ሄኖክ ነው ። ከጨበጣት በኋላ ከእንግዳ መቀበያ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ ። ሁኔታው ያኔ ከውጭ ሀገር ሲመጣ የነበረው አይነት ነው ። አሁን ግን በልቧ ያለው ስሜት ከበፊቱ ፍፁም ተለውጧል ። እንደማንኛውም ሰው ልታነጋግረው ወስና አናገረችው ። ንዴቱ ከደቂቃ ደቂቃ እየጨመረ መሄድ ጀምሯል ። ብዙ ጊዜ ስልክ እያነሳች ዘግታበታለች ። ይህንን ሁኔታ ሁለቱም አላነሱትም ። በመጨረሻ ለምን ስልክ ልትዘጋበት እንደቻለች ጠየቃት ። መመለስ አልፈለገችም ። ወጥሮ ያዛት ። መልስ አንድትሰጠው አስጨነቃት — ተናደደች ።

"እንተ ሽርሙጣ ጋ ምንልትሰራ ትደውላለህ!"

አይኗን አጉረጠረጠችበት ።

"ደስ ሲለኝ" አላት እንደመዝናናት እየቃጣው ።

"ድንቄም" አለችው ቱግ እንዳለባት ።

"እመጣጤ እንኳን" አላት መቀመጫውን ወደኋላ እየተደገፈ እግሩን አጣምሮ ፣ "እንኳን ደስ አለሽ ልልሽ ነበር" አለ ጀነን ብሎ ። እሷም ኮስተር እንደላች ።

"ለምኑ?" አለችው ።

"ከባልሽ ጋር በመታረቅሽ ነዋ!"

ሆን ብሎ ሊያበሳጨት እንደ መጣ ገባት ። ትክ ብላ እየችው ። በግንባሩ ቀንድ አውጥቶ ማጅራቱ ስር ፀጉሩ የሸፈነው አይን ያለው ፣ ድሮ ልጅ ሆኖ የምትሰማው አይነት ጭራቅ መሰላት ። ተጠየፈችው ። "አመሰግናለሁ ፣ ውጣልኝ !" አለችው ጮክ ብላ ።

ከት ብሎ ሳቀ ። "ያኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ስመጣ ውጣልኝ ብለሺኝ ነበር ። እንደ ውሻ አነፍንፈሽ ተከተልሺኝ እንጂ፡ ወድጀሽ አብራሽ የከረምኩ እንደይመስለሽ ፡ ፍላጐቴ ልበቀለሽ ነበር ። ፍቅሬን አመድ አድርገሽ ስለቆየሺኝ ። ለድርጊትሽ በቂ ቅጣትሽ ነው ። እስካሁን ያየሽው መከራ ይበቃሻል ፤ ውሻ!" አላትና ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ በሩ እየሄደ፡ "እንቺም እህቴም አህዮችና እብዶች ናችሁ ። እኔ ስሄድ ፍቅሯ አላልቅላት ላለ ወዳጄ አገናኝታ መልሳ አቆራኝችሽ ። ላጤ ወዳጅ አትወድም መሰለኝ ። ሚስት ያለው ወንድ እንደሚማርካት አውቃለሁ ፣ አጋብታሽ ልትሰርቀው ስለምትሻ ፡ መልሳ አቆራኝችሽ ። ለመሆኑ ከንፈ ለአዜብ ምኗ እንደሆነ ነግሮሻል ወይንስ...?" አለና ንግግሩን ሊቀጥል ሲል እሳት ሆና እሳት ጐርሳ ከመቀመጫዋ ብድግ ስትል ፣ በሩን ከፍቶ ጥሏት ሄደ ።

ቁጭ ብላ ጠረጴዛው ላይ ትንሰቀሰቅ ጀመር ። ትንሽ ስትረጋጋ የከሰአቱን የምሳ ግብዣ ከአዜብ ጋር እንዴት እንደምታሳልፈው ጨነቃት ። የስልኩን እጀታ አነሳችና ክንፈ ጋ ደውላ በአስቸኳይ መጥቶ እንዲወስዳትና ልታነጋግረውም እንደምትፈልግ ገልፃለት መልሳ ዘጋችው ።

'ምን ዕዳ ነው የገባሁት' ስትል ዕድሏን ክፉኛ አማረረች ።

"ታዲያ ይህን ሁሉ ታሪክ ለምን ደበከኝ?" አለችው እፀገነት ታሪኩን ሁሉ ተንትኖ ካስረዳት በኋላ ።

"መንገሩ አስፈላጊ መስሎ ስላልታየኝ" አላት መኪናውን አስነስቶ

Scanned with CamScanner

ወደ ቤታቸው አቅጣጫ መስመር እያመራ ።

ቤት ደርሰው አዜብ ከመምጣቷ በፊት የሚዘጋጀውን ነገር እፀገነት እያዘጋጀች ነበር ። የምትሰራውን አቋርጣ ክንፈን እየተመለከተች ።

"ክንፈ" አለችው ፣ ቀና ብሎ አያት ።

"የነገርከኝ የአዜብና ያንተ ታሪክ በጣም አሳዝኖኛል ። ሀይወት ምን አይነት ነች፣ አዜብ እጅግ አድርጋ አንጀቴን በልታዋለች ፣ ደብዳቤዋን አሳይሻለሁ አላልከኝም?" አለች ።

ክንፈ ተስፈንጥሮ ተነስቶ ደብዳቤውን ካስቀመጠበት ቦታ አምጥቶ ሰጣት ። ስራዋን ለእንድ አፍታ አቁማ ደብዳቤውን ማንበብ ጀመረች ። አንጀቷን እየበላው ሄዶ መጨረሻ እንባዋ ተፈታተናት — አንብባ እንደጨረሰች ።

"ለምን እንዳለችህ ደብዳቤውን አላታጠልከውም?" አለችው ቀና ብላ ተመልከታው ። "እንጃ አላሰኘኝም" አላት ።

"እንተ ባታደርገው እኔ ትእዛዟን እፈፅማለሁ" ብላ ክብሪት አምጥታ ወረቀቱን ለኮሰችው ፣ የደብዳቤው መንፈስ አንጀቷን እየበላው።

"ክንፈ" አለችው ።

"አቤት"

"ሀይወት የሚሏት ምን አይነት ነገር ነች?" ስትለው ፣ ትክዝ አለና አይኖቹን በምታቃጥለው ወረቀት ላይ ተክሎ "እንደዚህ እንደምታቃጥ ይው የወረቀት እላት" ብሏት አዜብን ሊያመጣ ተነሳ ።

* * *

ሁለት ወሮች አለፉ ።

ክንፈ አዲስ የገቡበት ቤታቸውን የአሸንዳ ውሃ መውረጃ ያስገጥ ግል ። ቅዳሜ ከሰአት የእረፍት ቀኑ ነው ። እፀገነት የሀኪም ቀጠሮ አለኝ ብላ ከወጣች ቆይታለች ። መመለሻ ሰአቷ ደርሷል ። በመኪና እንዳያደርሳት መኪናዋ የተፈቀደላትን የነዳጅ ተመን ልትጨርስ የቀራት ትንሽ ቤንዚን ነው ። ነዳጅ ለመሙላት ሰኞን መጠበቅ አለበት ።

አሸንዳው ሲገጠም የፈጠረው ኳኳታ መንፈሱን ተጭኖታል ። አማራጭ አልነበረውም ። ጀሮውን በጥጥ ለመድፈን እስኪያስብ ድረስ ተጨንቆ ይንቆራጠጣል ።

እፀገነት ከሄደችበት ተመልሳ ክንፈን እንዳየችው ተንደርድራ አቀፈችው ።

"የምሥራች" አለች ፣ አፉን ጉንጩን እየላሰች ።

"ምስር ብይ ፣ ምንድነው?"

"ዶክተሩ ወንሰሻል አለኝ" ፍንድቅድቅ አለች ። እሱም ደጋግሞ እየሳማት አቅፎ መኝታ ቤት ወሰዳት ።

* * *

ሽፈራው እነክንፈ ከወጡ በኋላ ተመልሶ የገባበትን የክንፈን ቤት አጥር ሲያስተካክል ውሎ ወደ ቤት ገባ ።

"ደከመህ የኔ ጌታ?" አለችው አስናቀች ደክሞት ፊቱን ኮሶ አስመስሎ የገባውን ባሏን እየተመለከተች ።

መልስ አልሰጣትም ፣ መኝታ ቤቱ ሄዶ አልጋው ላይ በጀርባው ወደቀ ። ተከትላው ስትገባ ተኝቶ ይመለከታታል ።

"ሻይ ላፍላልህ ቡና?" አለችው ሆድ ሆዷን ሲያያት አፍራ ።

"ምንም አልፈልግም ። ይልቅ ማሙሽን ቶሎ ቶሎ አድርሽልኝ እንዲረዳኝ" አላት የሆዷን መግፋት እያጤነ ።

"እይ! ማሚቴ ነች ። እኔን ነው የምትረዳው" ብትለው ከአልጋው ተስፈንጥሮ ተነስቶ ሆዷን ፣ ጡቷን እየነካካ ሲያቃልዳት ቆይቶ ፣ ጀርባዋን ከግድግዳው አስደግፎ ይስማት ጀመር...

ጀንበሯ እያዘቀዘቀች መሄድ ጀመረች ።

* * *

በዛው ሰዓት አዜብ ቤታ በረንዳ ላይ ቆማ ፣ በጀንበሯ መጥለቅ የጨረቃዋ ድምቀት እየጉላ መሄድ አስደንቋት ለረጅም ሰአት ስትመለከታት ቀየች ።

ጨረቃዋ ብትጉላም ደብዛዛ የነበረው ብርሃኗ ጨለማ ሲከበው እሷ እየደመቀች እየጠራች ስትሄድ ታየቻት ።

"ብቸኛ ነች" አለቻት ጨረቃዋን እያስተዋለች "ዘወትር ብቻዋን ፣

Scanned with CamScanner

ስትገባ ስትወጣ ሁሌ ብቸኛ! በስራ ብዙ ነገር ያልፋል ። ብታዝን ሁሌ እንደፈካች ሁሌ እንዳማረባት ። ዘወትር ብቻዋን እንደዘለቀች ። የጨረቃዋን ድምቀት ከተፈጥሮ ጋር ፣ ብቸኝነቷን ደግሞ ከራሷ ህይወት ጋር እያዛመደች በውብቷ የተቀሰቀሰባትን የፈጠራ ዳንኪራዋን ልትረግጥ ቀለም እየሸተታት ወደ ቤት ዘለቀች ።

የተወሰነ ሰአት ሳታቋርጥ ከፃፈች በኋላ ተመልሳ ወደ በረንዳዋ ወጣች ። ጨረቃዋ ከምንጊዜም በላይ ደምቃ በአናቷ ትከከል ሆናለች ።

"ተፈጥሮ የበደሏ ካሳ በእጥፍ ነው" አለች ለራሷ ፤ ነገ ከጨረቃዋ የደመቀ ቀን ሲሆን እየታያት ።

ተፈፀመ

በዚች አለም ለዩ ገፀባሕሪ ያወጣሁባቸውን ሰዎች
ይህንዴያለቻ ምክንያት፡ የንባብ ልምዳቸው
ሙንቃሴ በዙሪያቸው ለተሰሙት፡ ሲኖንአለም።

- ማህበኛንትና መላዴማ ሃገንታና ነገሥር ለእኔ ይሚል ሬሥን ሩዋቸው
- ጠንሪ ሰትጠነቀለው የሚዲገባሀን በነንጂ-ሪ እዩዮማሀ፡ነው.
- ፍሬሀት፡ ሁሉን ማመሳሰል ስለሚቀርንፅፅ፡ የሚዲያስኳሪ ነገር፡ የለም· የሱሀፊ ች፡ ናዝዘጂንት· ፍራንክሊን ሩዝቬልት
- ችሎታ-- ጠለት፡ ማጠንከር ሙያና ለሠራ ሳንቆመመ እንዲሚረመጣሱበጣነው·
- መጠን የሚዴያበሉ ሚዲያ ትነው፡ ይንገሠ ታንሸፉ ነው· እሠራንተ ሪነት ይሰጉ ዋል፡ 1000
- ነንቱንት፡ የነቂጣን! መሰጉታ·ቀት ነው·

* የሚዩ ውን ሳቲሜ መሠራት ለመሣመቅ የሚያስቱን ሠን ማመልከት መጥሪያት እዩሩሪጣዘሀሪ

- የሕንተ ጋሳርለ የአሳቂ ዘመ ፍ.ሙሜ ሂሪቪ ሥርሰ ሲለመሂዳ ማህነው
- ሊሠ ቀጠሮ ምን ሩለሀ መለሰን ነገንተታን ሻ ፃመያን የሚጠ ሥ·ት፡ ትሩቅ ሚያሠ·

- ለተሳሳሪ ጠቻ· ስመሳንሳመን ጽሠራሳ ነመሠራ ቀቃደን ነንተና ቆሠንንት· ስመሳዩሪመ ንሪት መግነለ ታ·ለቅ ለዩ ነት· ሲለ·
- ሽዩለ፡ ነለሠ ሠ·ገት ሽለሪ·

Scanned with CamScanner

"ሰላዩ ቀጥቅጠኝ ነፍሰ" መጽሐፍ
የተሰጠው አስተያየቶች

ድርሳኑ ጥበቅ ቤት ያለው ፣ ገፀ ባህሪያቱ ባወጣ የተሳሉና አሳው-
ውነው የተፈጠሙተ ነው ። እያንዳንዱ ገፀ ባህሪይ ከውስጣና ከውጭ
ይታያል - ሥነልቦናዊ አሰሳቸው [illegible] ። ፍቅር ፣ ቀለጅ ፣
ታማኝነት ፣ ማጽናት ውሸብ ፣ ፍ[illegible]ብነት እየታ ገዙና ቁሥነ
- ልቦና መነፅር እየታዩ ተርከዋል - በደራሲው ማዕዘን ። እንደውም
ድርሰቱ Psychological Novel ነው ፣ በርሱ ልጅት ፍላጎትና
እንዲሁም ሳይ የማይተዋር ጥሌቅ ድርሰት ።

ደራሲ ተበየሠ ዳየሮ

* *

[illegible] መንፈስን ሲያሳትት የቻሪው የብ[illegible]
[illegible] ምንም በር ነገር እሆን ።"

ጸር መነኩ ከ[illegible]

[illegible] ንኝሳስቃ ። አለ፡ "ከሱ ነው [illegible] ሥራ ላይ የተኩራት
እይቻታሁት አንቡ" ብሎት ነበር ። ደህንነ "የሰ
"ሰላዩ ተቀጥቅጠኝ ነፍስን" መጥ ሥራ ነው ብሎ ሲናገር እነዚህን ነው
መጥፀፍ ጀመሪያት ግምት ሳደረው ደርጋለም ከሁ ደ[illegible]

ንጉሤ ዓ/ም/ር

ዋጋው ብር 6.50

Scanned with CamScanner